የአቶ ተፈራም ማሣ ከመንገድ ዳር ስለነበረ፤አለፈ አግዳሚው ጤንነታቸውን እየጠየቀ ሲያልፍ፤ ሥራቸው ያስደሰታቸው ወደበቆሎው ማሣ በመግባት አረሞን በመንቀል እርዳታዎችን ያደርጋሉ። አቶ ተፈራም ለእውነቱ የግብርናን አስደሳችነትና በተለይ ሠራተኛ መሆን በሰዎች ዘንድ አክብሮትን የሚያሰጥ ከመሆኑ ሌላ ለሚሰራውም ትልቅ ደስታ ነው ይላሉ።«ሰው ሆኖ ራሱን ችሎ ቤተሰብን ከችግር ለመጠበቅ ካልተፍጨረጨረ ቢናገር አድማጭ የለውም፤ ለምሳሌ ከሦስት ዓመት በፊት ከገበሬ ማሕበር እንዳንገባ ተከልክለን የነበርነው ሰዎች ዛሬ እኛው ተሸለን ተገኘን፤በግፊት ከተቋቋመው ማሕበር ይልቅ እኛ በተናጠል ሠርተን የሥራችንን ውጤት ያሰየነው ገበሬዎች በፍላጎታችን ማሕበር ብናቋቅም ወጤት ይኖረናል።ቀድሞ እንደተነገረብን አደሃሪ አይደለንም።እኔ በበኩሌ ወገንን ለመጉዳት በፍጹም ዕቅድ የለኝም።በራሱ የሚተማመንና ሠርቶ ራሱን አሻሽሎ ለወገን ምሳሌ ለመሆን ዕቅድ ያለው ሰው መሰል ወገኑን ለመጉዳት ሕሊናው አይፈቅድለትም።በእርግጥ ሕብረተሰቡ በአጠቃለይ አንድ አይነት እምነትና አስተሳሰብ አለው ለማለት አይቻልም።ብዙ ልዩነቶች አሉ፤ሕዝባችን መሻሻሎችን አላደረገም፤ምክንያቶቹን ግን በዝርዝር አላውቃቸውም፤ብዙ ስህተቶች ሲፈጸሙ አያለሁኝ፤ግን እንደዘንድሮ ያሉ ስህተቶች ሲፈጸሙ አይቼም አላውቅም፤ጠላት ሃገራችንን በወረረበት ዘመን በሕዝባችን ላይ ብዙ ግፎች ተፈጽመውበታል።የዘንድሮ ግፍ ወገን በወገን ላይ ስለሆነ ይበልጥ ያሣዝናል። ወደ መንገደኛው እየተመለከቱ የምታየው ሕዝብ አንግቶት የሚጓዘው መሣሪያ አንድ አይነት ነው።ሰዎቹም ኢትዮጵያውያን ናቸው።ከአንድ ዓመት በፊት ጥቂቶቹ ያለውን መንግሥት ግድያና እስራት በመፍራት ከዱር መሽገው ይኖሩ የነበሩ ሲሆኑ፤ የቀሩት ደግሞ አብዮቱን እንዲያስከብሩና ወንበዴን ለመከላከያ ተብሎ ያስታጠቋቸው ሲሆን ሁለቱም ወገኖች የያዙት መሣሪያ በአንድ መንግሥት የተሠራ ሲሆን የዱሮቹ ከሶማሊያ ሲያገኙት የቀሩት ደግሞ ከመንግሥት በኩል የተሰጣቸው ናቸው። ይህ ሁኔታ ኢጣሊያ ሃገራችንን የወረረችበትን ዘመን ያስታውሰኛል።በዚህን ክፍለሃገር ጠርሰ የመሰሎኒ ጦር አልተዋጋም። ሦስት የጦር መኰንኖች ብቻ መላውን ክፍለሃገር በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል ችለዋል።ይህም ሊሆንበት የቻለው አስቀድመው ሕዝቡን አጠኑት። ጉሣ በጉሣ ከፋፈሉት ከዚያንም መሣሪያ አድለውት ፤ እርስ በእርሱ ሲጫረስ እነርሱ ግን የሚፈልጉትን ሲያደርጉ፤ ችለው የማይዋጉትን ለጥይት መጫኛ ያመቻ ዘንድ ጥርጊያ መንገድ አሰሯቸው። ይሄውልህ ከዚያ ምንም ሣንማር አሁንም ያረጀና ያፈጀውን የመለያየት በሐሪ ይዘን እርስ በእርሳችን እንጫረሳለን። ሶማሌም ከቅኝ ገዢዎች የተማረችውን በሐሪ በመጠቀም «አማራ» «ሶማሌ አቦ» «ምዕራብ ሶማሊያ» እያለች መሣሪያ እያስታጠቀች ስታዋጋን ቆየች። የዘንድሮው መንግሥትም ልክ



እንደምትወደው ሆኖ ስለተገኘለት ይህው እንደምታየው ነው። አሁንም በትክክለኛው መንገድ ቁጭ ብሎ ለመነጋገር እውቀትና አስተማማኝ መሪዎች በመጥፋታቸው፤ ወረኛው ጉሮሮው እንዳይዘጋበት በመሐል ጣልቃ በመግባት ሕዝብን በማቃቃር ያ ሁሉ እልቂትና የንብረት መጥፋት ሊደርስ ቻለ። የአንድ ሃገር ሕዝቦች የራሳችንን ችግር በራሳችን መፍታት እቅቶን እርስ በእርሳችን እንጫረሳለን።እውነቱ ቢነገር ለዚህ አካካቢ ፈጽሞ የመንግሥት ወታደር አያስፈልገውም።ብልህና አስታዋይ የሕዝቡን ችግር ዕለት በዕለት የሚከታተል መሪ ቢኖረው ይህ ሁሉ ችግር ባልተፈጠረ ነበር።ልማትን ለማሳደግ ሆነ አንዳንድ ድክመቶችን ምክንያት በማድረግ ልዩነቶች እንዳይፈጠሩ በማስረጃ የተደገፈ ስለአካባቢው ሕዝብ የተደረገ ጥናት ቢኖር ይህ ሁሉ ነገር ባልመጣ ነበር። ጸጥታ ደፍርሷል ተብሎ በጦር ክፍል የሚደረግ የመረጃ ስብሰባ ማቃቃር እንጂ ውጤታዊ አይደለም። ለማንኛው ጥቃቅን ነገሮች መሣሪያ አስታጥቶ ወታደር መላኩ ሕዝብንና ሐብትን ወደጎረቤት ሃገሮች እንዲወጡ ከማድረግ ሌላ ውጤት የለውም»

ባልቻም ከአቶ ተፈራ በተሰጣጡት ቀጠሮ መሠረት ከማሣቸው ስለመጣ፤ እሳቸውም የጀመሩትን አመም አጠናቀው አብረውት እንደሚሄዱ ነግረውት እስከዚያው ድረስ ከበቆሎ ማሣ ውስጥ ከሚገኘው ትልቅ ዛፍ ሥር እንዲቀመጥ ቢነግሩት፤ እርሱም እስከምንሄድ በማለት ለእረሙ አብሮአቸው ሲሰለፍ፤አቶ ተፈራም አቅም እንደሌለው ጠቅሰው በተጨማሪ «የመንግሥቱን ወታደር ያሰራል ተብዬ እከሰሳለሁ በለማለት እንዳይሰራ ቢነግሩት፤

ባልቻም «አሁንስ ይበቃል፤ ከራሴ በላይ ስለእኔ ማን ያውቃል?» በማለት በአካባቢው ስለደረሰበት ችግር በሮሮ መልክ ያቀርባል፤ እኔ ይላል ባልቻ «ይህ አካባቢ የተወለድሁበት አይመስለኝም፤ቀድሞ ከጦር ግንባር ሆኜ በሕልሜም በውኔም ይታየኝ የነበረው የመንደሬ አረንጓዴው መስኳ ከዓመት ዓመት የማይጠወልጉት ዛፎቿ መደራችንን ከመሐል ከፍለው የሚወርዱት ጅረቶቿ ከማማችን ሆነን ሁሉም የሌሊት አውሬ ለማስደንበር ድምጻችንን ከፍ አድርገን ማሰማታችን ጀንበር ዘቅዘቅ ስትል የሰንዴ፣ የሽንብራና የአተር እንኩቶ ማንኮታችን የማሽለና የበቆሎ እሸትማ ሲደርስ ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጃገረዶችን ከወንዝ ተከትሎ መሄዱ ትዝ ሲለኝ ከጦር ግባር ሆኜ አይኖቼ እንባን ያቀሩ ነበር። በእከሌ ላይ የደረሰው አደጋ ቢያሣዝነኝም ወደአካባቢዬ በመምጣቴ ሳልደሰት አልቀረሁም ግን ውዬ አድሬ ስመለከተው የተወለድኩበትና ያደኩበት አካባቢ አይመስለኝም።ቀድሞ አውቃቸው የነበሩት የመንደራችን አዛውንቶች አብዛኞቹ የሉም። የቀሩትም ቢሆኑ እንደማንተዋወቅ እንተሳለፋለን።ሃገሬውም ቢሆን እኛ ሚሊሻዎችን ሲያዩ መጠጥ ቤቱን ለቀው ሲወጡ ቆመው የሚያወሩትም የሚነጋገሩበትን እርዕስት ሲለውጡ ያለዚያም መነጋገራቸውን ሲያቆሙ፤ በማየታችን እኛ

ሚሊሻያ የሆነውን በሙሉ የአእምሮ እረፍት ነስቶናል። ባለመጠጥ ቤቶችም በይናገሩት እንጂ በንሄድባቸው ፍቃዳቸው ነው። አቶ ተፈራም ምክንያቱ ምን እንደሆነ ቢጠይቁት፤ «ባውቀውማ ምን ያስጨንቀኝ ነበር?»

«ሕዝቡ እንኳ ሚሊሻዎች ስትመጡበት መጠጥ ቤቶችን ለቀውላችሁ የሚወጡት፤ የሚነጋገሩበትን አርዕስት የሚለውጡት አሁንም ከአለው መንግሥት ለሰላይነት የተላከችሁበት እየመሰላቸው ነው። አንድ ተረት አለ። መብረቅ ዘመዶቹን የጨረሰበትን ሰው የሚጊጊው ምንድነው ተብሎ ቢጠየቅ ሰሙን መጥራት ፈርቶ እጆቹን ወደሰማይ አመለከተ ይባላል። ታዲያስ ሕዝቡ አይፈራችሁ ምን ይሁን ትላለህ? እንኳንስ እናንተን የመንግሥት ቁታ የለበሳችሁትን መሣሪያ የታጠቃችሁትን ይቅርና ለሦስት ለአራት ሳምንት ከዚህን መልምለዋቸው የንቃት ትምህርት ወስደው ሲመለሱ የሚቀርባቸውና የሚሉትን የሚያዳምጣቸው ሰው የለም።ይህም የሆነበት ምክንያት ሕዝቡ ለአካባቢው የሚበጀውን ሐሣብ ሲያቀርብ አወናባጅ እየተባለ በቁሙ አፈር ሲለብስ እየተመለከትን ማን ትንፍሽ ይላል?

ቢቸግር ነው እንጂ ቢጠፋብን ውሉ
ምጥማጥና ዶሮ መች አብረው ያድራሉ።»

ባልቻም አቶ አፈራ ምንም ሳይጠራጠሩት የሚያውቁትን ነገር በሙሉ ሳይሸሽጉት ስለነገሩት በጣም አድርጎ አመስግኖአቸው ባለፉት ጊዜያት ስለሰራባቸው በደሎች መፀጸቱን ይገልፃል። አቶ አፈራም በመሣቅ «አይ ባልቻ አሁንም የተሻለ ነገር ታገኛለህ ብትባል እንደቀድሞህ ከማድረግ አትቆጠብም» በማለት ይወርፉታል። እርሱም መልሰ አሁንስ ይበቃል፤«ከእንግዲህስ ዕለተ ሞቴን መጠበቅ እንጂ እንዲች ብዬ በማያገባኝ ነገር ውስጥ ሥራዬን መሥራት ትቼ ሽቅብ ቁልቁል አልልም። ፊቱንም ባለማወቅ ነበር፣ እዚያ ነገር ውስጥ የገባሁት። »

አቶ ተፈራም «ባልቻ ሆድ ለሆድ ተገናኝቶ አለመነጋገር እንጂ በወታደሩም ሆነ በሲቪሉ ሕዝብ መካከል ጉልቶ የሚታይ ቅራኔ የለም።ሆኖም ግን ከሲቪሉም ሆነ ከወታደሩ ክፍል በሕዝብ ላይ በደል የሚያደርሱ ግለሰቦች የሉም ማለት አንችልም። ማናችንም ብንሆን አንድም ሆኑ ሁለት በወትድርና የተከፈሉ ዘመዶች አሉን።ከዚህን አካባቢ እንደማየው ቤተሰብ በመርዳት የወታደሩን ክፍል የሚደርስባቸው የለም። ለራሳቸው መንግሥት በሰጣቸው ልብስና በሚሰፍርላቸው ራሽን በረሃ እየኖሩ ደመወዛቸውን ለቤተሰባቸው የሚለቁ አሉ። በማንኛውም መንገድ ልጆቻቸውን ለማስተማር ጥረቶችን ሲያደርጉ እናያለን።ግን ፍቅሩ ይኑራቸው እንጅ ከቤተሰባቸው ሆነ ከሚኖሩበት አካባቢ ሕዝብ ጋር ያላቸው ግንኙነት በጣም ውስን ነው።ለተወሰኑ ዓመታት ከአንድ አካባቢ ቢሰሩ በሚቀጥለው ከዚያን ወደሌላ አካባቢዎች ይዛወራሉ።ያም በመሆኑ እንኳንስ የአካባቢውን ሕዝብ የአኗኗር ሁኔታና የልጆቻቸውን ጸባይ



እንኳን ለይቶ ለማወቅ በጣም ያስቸግራቸዋል። የሃገሬው ሕዝብ ቢሆን ስለእነርሱ ያለው እውቀት ውስን ይሆናል። አሁንም እናንተ እንደምታደርጉት ከሕዝብ የሚያገናኛችሁ አንድ ሥፍራ ቢኖር መጠጥ ቤት ብቻ ነው። መጠጥ ቤትም ሁሉም ስሜቱን ገልጾ የሚነጋገርበት ሥፍራ አይደለም።የወታደሩም ክፍል የሕዝቡን ፍቅርና ስሜት ለመሰብ ከሚያገኝት ደመወዝ አውጥተው ከበር መልስ መጋበዛቸው እንደው ከምንም ተነስተው አይደለም። ሕዝቡ በወታደሩ ላይ መጥፎ አመለካከት እንዳይኖረውና በቤተሰባቸውም ላይ ጥላቻዎች እንዳይፈጥሩባቸው ብሎም ግንኙነቶችን ለማጠናከር በማሰብ ነው። ግንኙነቶቹ ጥሩ ቢሆኑም መንገዱ ይህ ብቻ አይደለም። በሁለቱም አቅጣጫዎች ጥረቶች ያስፈልጋሉ።ችግሩ ዛሬ እዚህ ያየናቸው ወታደሮች ነገ አይኖሩም።ይህም ሁኔታ ብዙ እንዳንተዋወቅ አድርጉናል።ከዚህም ተነስተን ነው የወታደሩ መንግሥት የሕዝቡን ችግር በሚገባ አይፈታውም የሚባለው እንጂ የወታደሩ ክፍል ከሲቪሉ ሕዝብ ውጭ የተፈጠሩ ናቸው ለማለት አይደለም።ስለሃገራቸው ችግር በሚገባ ያውቃሉ። ያ ባይሆን ኖሮ ከቤተሰባቸው ተለይተው ከዓመት ዓመት ከሥፍራ ሥፍራ አይዘዋወሩም ነበር።ሕይወትን በሙሉ ከቤተሰብ ተለይቶ በወታደር ካንፕ መኖር ቀላል ነገር አይደለም።ይህንን ሁኔታ ያልተረዳው አይኖርም።ግን አስተዳደር ላይ ሲመጣ ችግር ሊፈጠር ይችላል።ሃገርን ለማስተዳደር ከቤተሰብ ተነስቶ በአካባቢው ሕብረተሰብ ሥር አልፎ ሁሉንም ደረጃ ጠብቆ የሚሄድ እርምጃ ነው። ለምሳሌ የምንጠጣው ሰንበቴ ማሕበር እድር ፣ የምንጥለው እቁብ፣ መውሊዱ፣ ሰደቃው እርስ በእርሳችን ለመተዋወቅና ጥሩ መሪዎችን ለማውጣት ያሉን ትምህርት ቤቶች ናቸው።በቤተሰባችንም ሆነ በአካባቢያችን ያሉትን ችግሮች ለማወቅ ያስችሉናል።ይህንንም ስልህ ወታደር የሆነ ሁሉ ሕዝብ ማስተዳደር አይችልም ከሚለው መደምደሚያ ላይ እንዳትደርስ።ከካንፖቻው ሆነ በእሉበት ሕብረተሰብ እስተዋፅኦ ያበረከቱ ግለሰቦች አካባቢያቸውን ወክለው የማይመረጡበት ምንም ምክንያት አይኖርም። እንደውም ሃገር በተለያዩ ጊዜ በችግር ላይ ስትወድቅ ግንባር ቀደም ሆነው ለወገኖቻቸው በተግባር ተሰልፈው የነበሩትን ወታደሮች ሕዝብ ለመሪነት አጥብቆ ይፈልጋቸዋል። በአንዳንድ ሃገሮች እንደሚነገረው ዓለም አቀፍ ጦርነቶች ላይ ሃገራቸውን ወክለው የተገኙ ወታደሮች በትልቅ ደረጃ በድምፅ አሸንፈው ሃገር ይመራሉ። በሃገራችንም የመጻፍና የመናገር መብቶች ባለመኖራቸው የትኛው ክፍል በቂ ነው አይደለም ለማለት ባለመቻሉ በመካከላችን የሌሉትን ልዩነቶች በመፍጠር በግልጽ እንዳንነጋገር በጥቂቶች በመደረጋችን እንጂ ልዩነት የለንም። ሁኔታው ግልጽ ነው መሠረታዊ የሆኑ የሕዝብ መብቶች በተነፈጉበትና መሣሪያ ወሳኝ በሆነበት ሃገር ሁሌ ተጠቃሚው ወንጀለኛው ይሆናል። ጥፋቱ እንዳይገለጽበት መስሎ ለመገኘት የማያደርሰው ጥፋት አይኖርም። በሃገራችንም የመሪዎቻችንን ማሕደር ቢመረመር ብዙ የሚገለጽ ነገር ይኖራል።

የአንዳንዶች ጥፋተኞች በአስተዳደር ሥራ ላይ መገኘትና መተቸት አለመቻሉ በሃገሪቱ ላይ ጥፋት ሊያስከትል ይችላል። ለዚህም ነው ማንኛውም የሃገሬው ሕዝብ ስለሃገሩ ተሰትፎ ይኑረው ለምን? ከወታደሩ ክፍል ብቻ ይሆናል ሁሉም እኩል አላፊነት አለው ለማለት እንጂ የጥላቻ ጥያቄ አይደለም።»

አቶ ተፈራም ወደባልቻ ዞር ብለው «የገበህውን ቃልኪዳን እንዴት አድርገህው ነው ሁለተኛ እንደዚህን ካለ ነገር ውስጥ አልገባም የምትለኝ? ቀድም እንደምናውቀው እንደ ሰው ወታደርነት ሲቀጠር ለንጉሠ ነገሥቴና ለሃገሬ በታማኝነትና በቆራጥነት አገለግላለሁ የሚል ቃልኪዳን ይገባል።በዛሬውም ቢሆን ወታደርነት ሲገባ ቃልኪዳን እንደሚኖር አልጠራጠርም። ግን አንተ ከምንም ነገር ውስጥ አልገባም ብለህ ስትለኝ የዋሸህ ይመስለኛል፤»

ባልቻም አረም መንቀሉን አቁሞ ትንሽ ከአሰበ በኋላ፣ «በግል የገባሁት ቃል ኪዳን የለኝም፤ ሆኖም ግን እንደማንኛውም የሃገሪቱ ዜጋ ሃገሪቱን ለማገልገል ጠያቂና ተጠያቂ የሌለው ሙሉ ሃላፊነት በግሌ እንዳለኝ አውቃለሁ፤» «ያማ ሁላችንም ሃገራችንን ለማሳደግና ለመጠበቅ ከአባቶች የተረከብነው ሃላፊነት አለብን። ሃገር ወዳድ ለመሆን ግድ ወታደርነት መቀጠር ወይም ታጠቅ ጦር ሠፈር መግባት አይኖርብንም።መለዮ መልበስ ወይም መሣሪያ መታጠቅ ግድ የሚያስፈልግ አይደለም። እንድትነግረኝ የፈለኩት፤በንጉሠ ነገሥቱ ፋንታ ማንን እንዳሥገባችሁ ነው።»

«ማሕላው መፈክሮችን ማሰማት ሲሆን ለምሳሌ አብዮታዊት እናት ሃገር ወይም ሞት፤ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነፃነት»

አቶ ተፈራም መልሰው «እኛ ለሦስት ሺ ዓመታት በነፃነት የኖርን ሕዝቦች ነን። ማነው ባሪያ ናቸው ብሎ የነገራችሁስ የማነው ኀበዝ እንደዚህን ባሪያ እያለ የሚያስፎክራችሁ?»

«ሊቀመንበሩ ናቸው» «እርሱማ እውነቱን ነው» በማለት ተስማምተው ለተፈለጉበት ጉዳይ ከገበሬው ማሕበር ጽሕፈት ቤት ይሄዳሉ።





አቶ ተፈራ ባልቻና እውነቱ ከገበሬው ማሕበር ጽሕፈት ቤት ሲደርሱ ቀለብ ተሰፋሪው ሕዝብ ከውጭ ተሰብስበው ሳሉ ከውስጣቸው ፤ አካባቢውን ለማልማት ተብሎ ከሌላ ክፍለሃገር አምጥተው ያሰፈሯቸውና በጦርነት ላይ ተመተው የልማት ግብር ኃይል ተብለው የተላኩትን ሚሊሻዎች ያጠቃልላል። ከዚያንም እያንዳንዱን ሰው እንደቤተሰቡ ቁጥር እያስፈረሙት የስንዴውን ዱቄትና የታሸጉ ምግቦችን ሲያድሏቸው፤ ቀድሞ የደረሣቸውም አብስለው ለመብላት፤ የተሰጣቸውን ቀለብ በቀኝ፤ ጠብመንጃቸውን በግራ ትከሻቸው ተሸክመው ወደየሰፈራቸው ሲሄዱ፤አቶ ተፈራም ከባልቻ ጋር እግር መንገዳቸውን አብረው ሲጓዙ እርሱም ከተሸከመው ጠብመንጃና የቀለብ እህል ጋር ሲቸገር ተመልክተው «ከስንዴውና ከጠብመንጃው የትኛውን ትመርጣለህ» በማለት ሲጠይቁት፤ ባልቻም የተሸከመውን ሸክም አውርዶ «አሁንስ መረረኝ፤ይህን ደረቅ እንጨት ተሸክሜ ሽቅብ ቁልቁል ከምል ምነው እግዚአብሔር የቀድሞ ጤንነቴን መልሶልኝ በጎልበቴ ሠርቼ በበላሁኝ ይሻለኝ ነበር፤ ቀደም ሲል የመሣሪያን አስፈላጊነት ይናገሩ የነበሩት መሪዎቻች አንዲት ቀን እንኳን የዳቦን አስፈላጊነት አንስተው ሲናገሩ ሰምቼ አላውቅም፤ አሁን በተግባር እንደማየው የሰው ማጥፊያ መሣሪያ ከሚያስታጥቁን ምነው ረሃብን የምንዋጋበት መሣሪያ ካለ ቢሰጡን?» «እርሱንማ ቀድሞ ስቅለህው ሄደህ የለም? የተሸከምከው ልዋጩን ነው» «ይህንማ ምን ረሃብን እዋጋበታለሁ የተራበን እዋጋበታለሁ እንጂ፤» «ባልቻ የተማሪዎችን መጠየቅ አመጣህው ለተራብ ዳቦ»የሚለውን።

አቶ ተፈራም ባልቻ ጨርሶ መሣሪያ አያስፈልግም ከሚለው መደምደሚያ ላይ እንዳይደርስ ነግረውት፤ ግን አስፈላጊነቱ ለውጭ ጠላት መከላከያ እንጂ እንደእነርሱ አካባቢ በሰላም በሚኖር ሕዝብ ውስጥ ተሸክሞ ያለሥራ ሽቅብ ቁልቁል ለማለት አለመሆኑን ሲያረጋግጡለት፤ «መሣሪያን ያለበታው መጠቀም ይህን አሁን እየዋኘንበት ያለነውን ረሃብና በሽታ መንስኤ መሆኑን አንተው እራስህ ከተግባር አይተህዋል። ቀድሞም እንደነበርከበት መሣሪያ ታጥቆ የሚሰራውን ክፍል አቆርቋዥ አዳሃሪ በማለት የመሥራት ፍላጎቱን ስለተዳከመ፤ መጨረሻው አበሳው የሁላችንም ሆነ። ምነው በራሳችን ተወስኖ ቢቀር መልካም አልነበረም? ግን ለሚመጣው ትውልዳችንም የማይጠፋ የረሃብ ምልክት ማህተም አኖርንላቸው።»

ባልቻም ከጦር ሠፈር ሆኖ በየቀኑ የደለበ ሠንጋ ሲጣልላቸው መስለው የሃገሩ ሕዝብ እንደእርሱ ጠግቦ የሚያድር ይመስለው እንደነበር ተናግሮ፤ ውሎ አድሮ ግን «እውነቱን አየሁት» ይላል።

አቶ ተፈራም «የወታደሩ ክፍል ሙሉ በሙሉ ሕዝቡን አይወክልም ችግሩንም አይረዳም ብዬ ያልኩህ ስህተት ነው ወይስ እውነት እስቲ በል ፍረደኝ፤»

እውነቱም የሚታደለውን የምግብ እርዳታውንና የሚቀበለውን ሕዝብ ከአቶ ተፈራ ጋር ሆኖ ሲመለከት ቆይቶ፤ ከሥነስርዓቱ በኋላ «መፍትሔው ምን ይሆን?» በማለት ለአጎት ተፈራ ጥያቄ ሲያቀርብላቸው፤ እሳቸውም «እናንተ ወጣቶቹ የሚበጀውን ፈልጉ እንጂ እኛማ የተቻለንን ሞከርን፤የአካባቢያችን የልማት ጅምር ስመለከተው ግን ለከርሞም ከረሃብ የምንወጣ አይመስለኝም፤የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንደሚለው ነው፤ እንዲያለው ተብሎ ከሌላ ክፍለሃገር አምጥተው ከዚህ ያሰፈሯቸውን ሕዝቦች ያለሙትን ልማት የምናየው ነው፤ የእነርሱንና የሃገሬውን ቡቃያ ልብ ብለህ ተመልከተህው እንደሆን ትልቅ ልዩነት አለው።የዘሩት ስንዴና በቆሎ በእርዳታ ለቀለብ ከተሰጣቸው ላይ በመሆኑ የአካባቢው የአየር ፀባይ የአፈሩ ንጥረ ነገር ይዘታ ወሰኝ ሲሆን፤እህሉም ከልዩ ልዩ አገራት መጋዘን በእርዳታ ስም የተላከ ስለሆነ የእህል በሽታ እንዳለውስ ማን ያውቃል?»

እርሱም «የስጦታን ፈረስ ጥርስ ማን ይመለከታል?» በማለት ሲመልስ፤ «ያ! ሆነና ውጤቱ ይህን መሰለ፤ እኛ የዘር እህላችንን የምንመርጠው ከእውድማችን ሲሆን በተለይ በቆሎን የሚያጠቁት ብዙ ሕዋሰቶች ስለእሉ ዘሩን ከጭስ የምንሰቅለው እንዲያው ያለምክንያት አይደለም።መሬቱም ቢሆን ሜዳ በሆነ አይታረስም፤ይህ እነርሱ ያረሱትን መሬት ሰናርሰው የቆየነው እህል እንደማያበቅል እናውቃለን፤ ስለሆነም ከብት ስናረባበት ኖረናል፤ ጫካውን መመንጠሩም የጥፍ እጥፍ ጥፋት ነው፤ጫካ በለበሰ እህል አያበቅልም።እያንዳንዱ አካባቢ የራሱ የሆነ ፀባይ አለው።የአካባቢውን ሕዝብ የአሰራር ዘዴ ተመልከት፤ጫካውን ጨርሰው ሳያጠፉት፤በውስጡ ቡና ጫት፣ ጌሾ፣ ብርቱካን ፖፖዬ፤ ዘይቱና ማንጎ ትርጎ ወዘተ ተከለውበታል። በቡና ውስጥ ለቀለብ በቆሎ ተዘርቷል።ይህ እንግዲህ ለገበሬው ምርት ለመሬቱም ጌጥ ነው።እንደምታየው ከትልልቆቹ ዛፎች ላይ የንብ ቀፎዎች ተሰቅለዋል፤ይታይህ ተፈጥሮ እንደዚህ ተደጋጋፊ ነው፤አንደኛው ካለአንደኛው መኖር አይችልም።ይህንንም የአካባቢው ሕዝብ ብዙ ከመቆየትና ጠንክሮ ከመሥራት ሁኔታውን ተቀብሎታል።እንግዲህን ከመሬቷ በአንድ በኩል የወሰድክባትን በሌላ አቅጣጫ ካልመለስክላት ለከርሞ የምትሰጥህን ሰብል ትነፍግሃለች።ውጤቱም እንደምታየው ረሃብ ነው።ከዚህ ሌላ እናንተ ተማሪዎች እኛ ያልደረስንበት ካለ ብታከፍሉን ሁሉም ሰው አዲሱን የአሰራር ዘዴ ለመቀበል ፍቃደኛ ነው።እውቀታችሁን ከጠረጴዛ ዙሪያ ወደመስክ ብታወጡት የማንቀበልበት ምንም ምክንያት የለም። እንደዘንድሮው የእርሻ ዘዴ ግን እንደጦጣ ከዛፍ ዛፍ የሚቆናጠር አይነት ከሆነ ውጤቱን ያየነው በመሆኑ መቅረቱ የተሻለ ነው። እንደውም የምፈራው ሊቀመንበሩ ይህንን አካባቢ ከአየር ቁልቁል ተመልክቶ ጫካውን መንጥሩ ሜዳውን እረሱ በማለት ያለ የሌለውን



የእርሻ መኪና አምጥቶ እንዳያስፍርብን ነው። ያ ከሆነ ደግሞ ጥፋቱ ከነበረው እጥፍ ለመሆኑ፤ ሰዎች ከዚህን አካባቢ መጥተው ከሰፈሩ የጠፋውን የተፈጥሮ ሐብት ይህን ያህል ነው ብሎ መገመት ግምት መስጠት ያለመቻሉ ጥሩ ማስረጃ ነው።እንዴ ዛፍ አሁን ከምናየው ደረጃ ለመድረስ ቢያንስ ከመቶ ዓመት በላይ መውሰዱን ማወቅ የሚቻለው፤ ሃገሬው የቤተሰባቸውን ሐረግ ከትውልድ ትውልድ በዛፉ ዕድሜ ስለሚቆጥሩ በግምት ቢናገሩትም ብዙ አይሳሳቱም። አንድ እግር በቆሎ ለመዝራት ሲቆረጥ ግን በጣም አድርጎ ያሣዝናል። ዛፍ በሌለባቸው አካባቢዎች ሕዝቡ ዛፍ እንዲተክል ሲነገር በሌላ በኩል ለማይረባ ነገር ያስቆርጡታል። በሁሉም አቅጣጫዎች መሳ ቀጤ የጠፋ ሁኔታ ነው።በቀላልና በዘዴ ሊሠራ የሚቻለውን ሥራ ሸርበው ሸርበው ውሉን ያጠፉታል። ከነአካቴውም ሕዝብን ያለፍላጐቱ ከአንድ አካባቢ አንስቶ ከሌላ አካባቢዎች ማስፈሩ ትልቅ ስህተት ነው። ራሴን በምሳሌነት ብጠቅስ ከዚህን ከኖርኩበት አካባቢ ዘመድ ለመጠየቅ ከሌላ አውራጃ ስሄድ የሚሰማኝን የአእምሮ መሸበርና መጨነቅ አውቀዋለሁ ። ያም በመሆኑ ሳልውል ሳሳድር በመቻኮል ወደአካባቢዬ እመለሳለሁ ። ምንም እንኳን ሕዝቡ በአካባቢው በተፈጠረው የዝናብ እጦትና የአየር መለወጥ የአስተዳደር ጉድለት ለማምረት ባይችልም ስለ ለምለሞቹ አካባቢዎች በቂ መግለጫ ቢሰጠውና ለመሄድና ለመስራት ፍላጎት ያላቸው ከቀረቡ መንግሥት ማንኛውንም እርዳታዎች እንደሚያደርግላቸው በተግባር ቢያሳይ ሕዝቡ ከመራብ ራሱ ሠርቶ ማደር የማይፈልግበት ምክንያት አይኖርም። ከአካባቢውም ቀለብ ተሰፋሪ ከዚህም ቀለብ ተሰፋሪ ከሆነ ልዩነቱ ከምኑ ላይ ነው? በሃገራችን ትልቁ ችግር የግንኙነቱም ጉዳይ ሌላው ሲሆን፤ ከዚህን በፊተ በዚህ አካባቢ መቶ ኪሎ ጤፍ ሃያ ብር ፣ስንዴ ስምንት ፣ገብስ አምስት እየተሸጠ ወሎ ተራበ ተብሎ ሲነገር ለአካባቢው ሕዝብ እንቆቅልሽ ሲሆን፤ ዘንድሮም የአንዳንድ ክፍለሃገራት መራብ ለጎጃም ገበሬ ታምር ሳይሆንበት አይቀርም።ወሳኙ በሥራ ላይ ብዙ ጊዜያትን ማሣለፍ ብቻ ሳይሆን መሬቱንም በደንብ ማወቁና መከባከቡም ነው። ጎጃም የረዳው ነገር ቢኖር መሬት የተወሰጀ በመሆኑ ሁሉም ለሚመጣው ትውልድ መገልገያ መሆኑን ተረድቶ በክብከቤ ስለያዘው ውጤቱ ሊያምር ችሏል።በተጨማሪ ሃገሬውን የረዳው በሥራቸውና በመሬታቸው ማንም ጣልቃ አልገባባቸውም።ልክ እንደዚህን አካባቢ ትምህርት ቤት ካልተከፈተልን ሐኪም ቤት ካልተሰራልን ግብርም አንከፍልም ከብታችንንም እናስቆጥርም በማለታቸው፤ እንደተዘመተባቸው ሁሉ የጎጃምም ሕዝብ በመሬቱ ጉዳይ ተዘምቶበታል። አሁን ውሎ አድሮ ለተመለከተው ማነው ትክክለኛ?የዛሬው ውጤት ከትናንት በስቲያ ሰዎች የደከሙበት የሥራ ፍሬ ነው ለማለት ነው የጠቀስኩት።የግብርናን ሥራ ከአካባቢው ሕዝብ በላይ የሚያውቁ ቢኖሩ በአካባቢው ተቀምጠው ብዙ ጥናቶችን ያካሄዱና ጥናቶቹንም በተግባር የተሮጎሙ ግለሰቦች ብቻ ሲሆኑ ይህም ብዙ ትዕግሥት

ፍቃደኝነት ሃላፊነት ጠንክራ የሥራ ባህል ገንዘብ ያስፈልገዋል። ሆኖም በመጨረሻ ግን አሻሪ ነው። ያለበለዚያ ግን በሌላ አከባቢ ጤፍ አምራች የሆነውን ገበሬ አምጥቶ የንብ ቀፎ ጥረብ ቡና ትከል ማለት ውጤታማ አይሆንም።ካለፈው አለመማር ነው እንጂ ከዚህን በፊት የወርቃ ልማት በማለት የመንዝን ገበሬዎች መሣሪያ አስታጥቀው ከዚህ ዱር አስፍረዋቸው ጫካውን መንጥረው የተለያዩ የእህል ዘሮችን ዘርተው፤ ለመጀመሪያው ጥሩ ምርትን ቢያስገኙም፤ ከጥቂት ዓመታት በኋላ አከባቢው ምድረ በዳ፤ ሆነ።ሕዝቡም በወባ በሽታ እየተለከፈ እየታመመ ሲያልቅ ለውጡም እንደመጣ ጫካ ገብተው የነበሩት በመጀመሪያ ኢላማቸው ያደረጉት እነዚሁኑ ሕዝቦች ነበር።

በአጠቃላይ ስንመለከተው የሰፈራው ሁኔታ የርሰበርሰ ግጭቶችን ፈጥሮአል።ሌላው ቀርቶ ከአርሲ ከሸዋ አከባቢ መጥተው ከዚህን ሰፍረው የነበሩት ሕዝቦች ከሃገሬው ጋር ቅራኔዎች ነበሯቸው። ቅራኔው ከአሰራርና ከባህል ልዩነት የመጣ ግጭት ሲሆን ፤ የሃገሬውን የአሰራር ሁኔታ ቀድሚ ገልጬዋለሁ።የአዲስ መጪዎቹ አሁን እንደምታየው ነው። ሁሉንም በየአቅጣጫው ተመልክቶ የሚያዋጣውንና የማያዋጣውን ለይቶ ሳይታወቅ ትምህርት ሳይሰጥበት በጅምላ ሕዝብን ማስፈሩ እንዲያው ጥፋት እንጂ ልማት አይደለም።»

አቶ ተፈራም ከቡና አትዕክልታቸው ሥር አረም እየነቀሉ፤አንዳንዴም የቡናው ፍሬ ከብደት ሊገነጠል የደረሰውን ቅርጫፍ በባላ እየሰደገፉ፤ «መልካም ሥራ ይህን ይመስላል» በማለት ለእውነቱ እያሣዩት፤ «ዘንድሮ ባይለፍሩብን ወይም ባይቆነጥሩብን በሁሉም አቅጣጫ ሰብሉ የሚያስደስት ነው። ሆኖም ግን ሰዎች ያስፈራሩኛል፤ለፍተህ ለሰው ነው፤ ምርቱም በአጠቃላይ ከገበሬው ማሕበር ጉተራ ይገባል ይባላል፤ባይገርምህ ይህንን ውዥንብር የሚነዙብን ምንም እርሻ የሌላቸው ክፍሎች ሲሆኑ፣ የእነርሱ ሞያ መሣሪያ ተሸክሞ የእርዳታ ስንዴ መቀበል ሲሆን፤ለእኔም ሆነ ለጠንክራ ገበሬ መሥራት ከሩቅ ጊዜ የመጣ ልምዳችን በመሆኑ፤ቢወስዱትም ቅር አልሰኝም። አንዳንድ ሰዎች የራሳቸውን ሥራ ሠርተው ከማደር ይልቅ ከትንሽ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ መሣሪያ ይዘው ከጠዋት እስከማታ ቅጂ አትቅጂ በማለት ሥልጣናቸውን ለማሳይት የሚሹ ዓይነት ነው፤ የአብዛኛው የሕዝባችን የሥራ ባህል፤ ሁሉም የሚፈልገው ይህንን ነው እኔ ግን ሠርቼ በጉልበቴ ያፈራሁትን መንግሥት ዛሬ ቢወስደው ነገ እንደእኔ የሚሰራለት ስለማይኖር ያው ወደእርዳታው መቀበሉ መሄዱ አጠያያቂ ባይሆንም ተቀምጭ የእርዳታ ቀለብ ከምቀበል ያመረትኩትን ቢወስዱብኝ ያኮራኛል፤ የሥራ ልምዱም ምንጊዜም ከእኔው ቀሪ ነውና።»



## ፴፯

የአከባቢው ሕዝብ ቁጥር ጨምሮአል በሚል ስም የወረዳ የልማት አስተዳደሪ ተሾሞ ከበላይ መሥሪያ ቤት ተላከ። ከላይ የተሾመው ባለሥልጣን ብዙም በአከባቡው ውሎ ሳያድርና ስለአከባቢው ምንም ዓይነት ጥናቶችን ሳያካሂድ ሕዝቡ የሚፈልገውንና የማይፈልገውን ሳይረዳ ከበላይ ባለሥልጣኖች በተነገረው መሠረት «ማንኛውም የአከባቢው ሕዝብ ቢኖረውም ባይኖረውም የመንግሥት ግብር መክፈል ግዴታ ስለሆነ እንድትዘጋጁበት» በሚል፤ ገበያ ለወጣው ገበያተኛ በአዋጅ መልክ መግለጫውን አስተላለፈ።ሕዝቡም ቀደም ሲል በተፈጠረው የአስተዳደር ድክመት የደረሰውን የንብረትና የሰው ሕይወት መጥፋት በማገናዘብ «አሁንም ይህንን የሰብል ወቅት ተጠብቆ ሰው መሳኩ ወደነበርንበት በረሃ እንድንመለስ ሆን ተብሎ የታቀደ በመሆኑ ድርጊቱ ብዙም ሊያስደንቀን አይገባውም በማለት የተሰማቸውን ርስበርሳቸው ተገናኝተው ተነጋገረውበት፤ ይህ ባይሆን ኖሮ እናቶች በወሊድ ምክንያት ሲሞቱብን ታመን የመዳን ተስፋ ማይኖረን ልጆቻችን ትምህርት ቤት ሳይከፈትላቸው እኛም የእርዳታ ቀለብ ተስፋሪ ሆነን፤ ከብታችንም በበሽታ ሲያልቅብን እየተመለከቱ ከዚህን ችግር የምንላቀቅበትን መንገድ በመጠቆም በሥራችን ላይ ሊተባበሩንና የሚያስፈልገንን ሊያሟሉልን ሲገባቸው፣ ግብር ክፈሉ ብሎ በአሁኑ ጊዜ መጠየቁ አግባብ ያለው መንገድ አይደለም። በቅድሚያ ያለንበትን ሁኔታዎች ጠንቅቀው ማወቅ ሲኖርባቸው ይህንንም በተግባር ለመረዳት አከባቢውን የሚወክሉ የሃገር ሽማግሌዎች እንድንመርጥ ተፈቅደልን ከዚያን በኋላ ተወካዬቻችን የተስማሙበትን ነገር እንድንፈጽም ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ቅር ባልተሰኘን፤ ግን የአከባቢው ሕዝብ ተወካዮች በውሳኔው ላይ ሳይገኙ ያለተወካይ ገንዘብ አምጡ ብቻ ከሆነ ለምንስ እንደሚውል ስለማይታወቅ በደፈናው መክፈሉ አግባብ አይሆንም።ለዚያውስ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ሕዝብ የእርዳታ ቀለብ ተስፋሪ ሆኖ ሳለ ከታታሪዎቹ ገበሬዎች ላይ ግብር አምጡ በማለት መጠይቅ ማቅረቡ አትስሩ እጃችሁን አጣምራችሁ ተቀመጡ ማለት አይሆንም? እንደሚታወቀው ከበረሃ ከገባን ይህ የመጀመሪያው ሰብላችን ሲሆን እነርሱም በይበልጥ እንድንቋቋም በሒሣብና በአንዳንድ ቁሳቁሶች ከመርዳት ይልቅ ባላችሁ ንብረት ሁሉ ሌላው ቀርቶ በደሮ ግብር መጠየቁ አትሥሩ የእርዳታ ስንዴ ተቀበሉ ማለታቸው ስለሆነ ምን ማድረግ ይቻላል?» ከአከባቢው ሽማግሌዎች አንደኛው በመናደድ «እውነት ይነገር ከተባለ በዚችን ሃገር በፍጹም እውነተኛ የሕዝብ አስተዳዳሪ የለም።ወደበረሃ ስንሰደድ የተከለነው ቡናችን ዳዋ ለብሶ ሙዙ የዝንጀሮ መፈንጫ ሆኖ የሰቀልነው የማር ቀፎአችን ማር እንደዘለ የወታደሩ የኢላማ መለማመጃ ተደርጎ በጎተራ የነበረው እህል እሣት ተለቆበት እንደጠፋ እያወቅን ሃገራችን ነውና መንግሥት በሠራው ጥፋት ተፀጽቶ ወደሰላማዊ ኑሮ እንድንመለስ የጋበዘን

መሆኑን አምነን ተቀብለን ወደነበርንበት ተመልሰን ያለፈውን እረስተን ደከመን ታከተን ሳንል ለመቋቋም ያደረግነው ጥረት ከቁጥር ሳይገባ ቀርቶ ዛሬ በምላሹ ግብር አምጡ ከሆነ የምንስ ሃገር እውነተኛ አስተዳደር አለ? በረዥም ዘንጋቸው መሬቷን እየመቱ በጠላትም ጊዜ ከዚህን እምባችን ርቀን ወደትም አልሄድንም።ልጆቻችንም በዚችን ሥፍራ እንዲተኩን እንሻለን።ይህ አካባቢ ቢለማና ቢያድግ የሚከፋ የለም።ከእመሬትነውም ለሕክምና ሆነ ለትምህርት ቤት ለመንገድ ማስሪያዎች በአጠቃላይ ለአካባቢውም ሆነ ለሃገር ግብር መክፈሉ የያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ቢሆንም ፤በጊዜው ያስቆጣን ጉዳይ ቢኖር ገና ሳንቋቋምና በውሰኔው ላይ ሳንገኝ ለምን እንከፍላለን የሚለው ሲሆን እስከዛሬ እዚች መሬት ላይ ከኖርን ጀምሮ ስንከፍለው የነበረው ግብረ ተወስዶ ለአካባቢያችን የሚበጅ ምንስ ነገር ተሰራልን? ቀድሞም ለሚያስሩን ለሚፈቱን ደመወዝ ከፋዮች ነበርን፤ ዘንድሮም ደግሞ ተኮሰው ለሚገድሉን እንድንከፍል ተገደናል። የወደፊቱን አርቀው የሚያስቡ እውነተኛ የሃገሪቱን ችግር የሚረዱ፤ አስተዳዳሪዎች ቢኖሩ ከዚህን ለየት ባለመንገድ ሁኔታውን በተመለከቱት። ሆኖም ከግብሩ በፊት በመካከላችን ጥሩ ግንኙነቶች ተፈጥረው የሚወክሉን ግለሰቦች ከአካባቢያችን ተመርጠው፤ችግራችንንም አቅርበውልን ግዴታችንን በየጊዜው ቢያስታውቁን ለራሳችን ጥቅም ነውና የማንቀበልበት ምክንያት አይኖረንም።ለምሳሌ ቀደም ሲል ለአስር ሄክታር መሬት የምንከፍለው አስራ ስድስት ብር ሲሆን ዘንድሮ ደግሞ ሃያ ብር እንድንከፍል ስንጠየቅ ምክንያቱ የተጨመረበት አልተገለጸም። ተወካዮች ቢኖሩን ምክንያቱን በውል መረዳት ይቻል ይሆናል ብለን እንገምት እንጂ ተመካዮችስ የታያቸውን ለመናገር ነፃነት አላቸውን? የሚለውም ሌላው አጠያያቂው ጉዳይ ነው። በዚያን አንፃር ስንመለከተው ደግሞ ሒሣብን በትክክል መግለጽ ያለመቻሉም ለዚህ ሁሉ ወጥቅት ምክንያት መሆኑን ከመደምደም ደረጃ ላይ ያደርሰናል።»

እንግዲህን በየጊዜው ያለ ጥናትና የሕዝብ ተሳትፎ አውቅልሃለሁ በማለት የሚተላለፉት የዋዠቁ መመሪያዎች ሕዝብን ያለእምነት ከማስቀረታቸው ሌላ የመሥራት ፍላጐቱን ገድለው የሃገር ፍቅሩንም ያሳጡታል። ያለውም መንግሥት የሚያደርገውን በግልጽ ብናየው «በአሁኑ ወቅት ሰው ተመርጦ አስተዳዳሪ ይሁናችሁ ተብሎ የተላከብን ምክንያት ይህን የደረሰ ቡናችንን ለመካፈል ሲሆን አሸፈረን ብለን ካልን እንደቀድመው ወንብደዋል ተብለን ተኮሰ ተከፍቶብን ልጆቻችንና ከብቶቻችንን ይዘን ከበረሃ ስንገባ እንደተለመደው የለፋንበትን ዳዋ እንዲለብስ ለማድረግ የታሰበ ስውር ሴራ እንጂ አዙሮ ማያ አንገት ያለው ሰው ይህን ተግባር ይሆናል ብሎ የሚያቀርበው አይደለም። በምንሰፈረው የእርዳታ ስንዴ እየተቆጨንና እነርሱም በዓለም ሕዝብ ፊት እየተሽማቀቁና የሆነ ያልሆነውን እየተናገሩ እንደሚያገኙት እያወቁ ሕዝቡ ራሱን ለመርዳት ሲፍጨረጨር ከመርዳት ይልቅ የልመና ስለቻውን ይዞ እንዲሰለፍ መገፋፋቱ ፍጹም ለአንድ ሃገር ዜጋ የሚዋጥለት ድርጊት አይደለም።



ለሁሉም የልማት አስተዳዳሪው በጠራን ስብሰባ ላይ ስንገኝ በአካባቢው እምጥተው ስለአስፈሯቸው ሕዝቦች መጥፎ ቃል ከመናገር መቆጠብ እንደሚኖርብን ሁላችን አስቀድመን ማወቅ እንዳለብን ነው።ቀርበናቸው ውስጣቸውን መርምረን ባለማወቅ እንጂ እነርሱም ዘንድ ብሶት አለ። መሣሪያ በታጠቁ ብቻ የመንግሥት ደጋፊዎች የሕዝብ ተቃዋሚዎች አድርጎ መውሰድ የለብንም። እንዳንዶቹ ከዚህን ተመርጠው የመጡት የዚህ አካባቢ ሕዝብ በመወንበዱ የደረሰውን ሰብል ሰብስበው እንዲወስዱ ሲሆን፤ ያው ጦር ግንባር ለተላከው ሚሊሻያ እንደተነገረው ለእነርሱም የአካበቢያቸው የገበሬ ማሕበር ቤተሰባቸውን እንደሚከባከብላቸው ተነግሯቸው ከዚህን እንዲሰፍሩ የተደረጉ ሕዝቦች ናቸው።ከዚህን እንደደረሱ እንደምናውቀው ምንም የሚሰበስቡት ሰብል አላገኙም። ከዚያን ሌላ ዱሩን መንጥረው እንዲያለሙ ሲነገራቸው፤ የማረሻ በሬ እስከሚገዛላቸው ድረስ በዶማ እንዲሰሩ ሲደረግ በዶማ ልማቱም ሳይፋጠን በርቹም ሳይገዙ እንዲያውኑ ለሁለት ዓመት የችርታ ቀለብ ሲቀበሉ የኖሩ ሕዝቦች በመሆናቸው፤ ይህንንም ኑሮ አምነው ስላልተቀበሉት በየጊዜው ወደ መጡበት አካባቢዎች እየጠፉ በመሄድ ላይ እንዳሉ እየተያዙ ከክፍለሃገሩ እስር ቤቶች የሚማቀቁ ሲኖሩ እንዳንዶቹንም ሲገሏቸው ያየነው ነገር ነው። ለእንዳንዶቹም ይባስ ብለው ቤተሰባቸውን ያመጡላቸውም አሉ። አንድ ወይም ሁለት ሕፃናት ትተው የወጡ አባቶች የሕግ ሚስቶቻቸው ተደፍረው ከሌላ ሰው አንድ ወይም ሁለት ሕፃናት ጨምረው የመጡ ቢገኙባቸው፤ በማን ይፈረዳል? ባልም ይህቺ ደግሞ ከየት መጣች ወይም መጣ በማለት ቢጠይቅ እናት ምን ትመልሳለች? ከሕጋዊ ባል የተወለዱት አባባ በማለት ከወላጅ አባታቸው የአባትነትንና የልጅነትን ፍቅር ሲቀባበሉ፤ ከውጭ የተወለዱት ግን ጣቶቻቸውን ከጉንጮቻቸው ጨምረው እይኖቻቸው እንባን አቅረው የእናቶቻቸውን እርዳታ ሲጠይቁ እናቶችም እቅፍ አድርገው አለሁላችሁ ለማለት ባለቤታቸውን ሲፈሩ በማየት ከዚህን ደስታ የሚያገኝ ከእኛ ውስጥ አለን? በምንኖርበቲ አካባቢና ክፍለሃገር ወሰን እንለያይ እንጂ የአንድ ሃገር ሕዝቦች ነን በሁሉም አካባቢ የሚሠራው ግፍ አንድ ነው። ከዚህ እንደምናያው የሚሊሻውን ሚስቶች በመከባከብ ስም የገበሬ ማሕበር ተመራጮች የዘማቾቹን ባለቤቶች በመድፈር ሲወልዱ ዡር በማለት ችግር ላይ ሲጥሏቸው ተመልክተናል። የነዚህን ሰዎች ትዳር እንዲበላሽ ያደረጉት እነዚያው መንግሥት ተከባካቢዎች ብሎ የሚጠራቸው ሰዎች መሆናቸውን መጠራጠር የለብንም። ለሁሉም አስተዳዳሪውን ሚዛናዊና አጠቃላይ የሆነ ጥያቄ ማቅረብ አግባብ ያለው መንገድ ሲሆን፤እርሱም ስለአካባቢያችን ጠለቅ ያለ እውቀት እስከሚኖረው ለሚያስተላልፋቸው መመሪያዎች ትዕግስት እንዲኖረው እንነግረዋለን። አልቀበልም ብሎ ከበላይ የተሰጠውን መመሪያ ብቻ ለማስፈጸም ግትርነት ከሣየ በራሱ የማይተማመን መሆኑን ተረድተነው እንደፈለገው ሲያደርግ በትግዕስት መመልከት አለብን።»

## ፴፯

የወረዳው የልማት አስተዳዳሪ በስተሳለፈው የስብሰባ ጥሪ መሠረት አብዛኛው ሕዝብ ከመሰብሰቢያው ዛፍ ሥር ተገኘ። ሥራቸው እኀገቷቸው በማሣቸው ላይ የቀሩትም በጥበቃ ጓዶች ተይዘው እንዲገኙ ተደረገ። ስብሰባው ሳይበተን ማንም ሰው እንዳይሄድ በሚል ስም መሣሪያ የታጠቁ ግለሰቦች ዙሪያውን ከበው ቆሙ።

አስተዳዳሪውም በስብሰባው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቶች በመገኘታቸው የተሰማውን ደስታ ገልጿ፤ስብሰባ ያስጠራበትን ምክንያት በመዘርዘር አቀረበ።ሕዝቡም የዘመኑን ግብር መክፈል ግዴታው ሲሆን፤በተጨማሪም በአካባቢው የሚኖረውን ሕዝብ ቁጥር ለማወቅ ስለተፈለገ የቤተሰባችውን ቁጥር እንዲያሰውቁ ለማድረግ ጭምር እንደሆነ ገለጸ። የግብርናው ሥራም እንደቀድመው እጣምር ማከሄዱ ቀርቶ የከብት እርባታውና የመሬት ማረሱ ሥራ በተለያዩ ባለሞያዎች እንደሚከናወን አስረዳ። በሞያቸውም ለመከፋፈል ንብረታቸውን ማስቆጠር እንደሚኖርባቸው ገልጾ አዋጁንም ለማደናቀፍ አንዳንድ አድሃሪያን ስለማይታጡ እነርሱንም ተጠንቅቆ መጠበቅ እንደሚኖርባቸው በማሳሰቢያ ስም አቀረበው። ሁኔታው ሕዝቡን አስቆጣው። ምንም ማድረግ ስለማይችሉ ለሁሉም ስብሰባው ተፈጽሞላቸው ወደቤታቸው ለመሄድ ተጣደፉ፤ ንግግሩም እየተራዘመና እየተደጋገም ሲመጣ ሕዝቡ ለመስማት ታከተው፤ እናቶች ሕፃናትን በጀርባቸው አዝለውና በጉያቸው አቅፈው በፀሐይ ሲንቃቁ አንዳንድ ሕፃናትም ምግብ አስፈልጓቸውና የፀሐዩ ሙቀት አቃጥሏቸው ሲያለቅሱ ጉዳይ ያላቸው አልነበረም። የአስተዳዳሪውንም ንግግር እንደዚያው።

አቶ ተፈራም ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ልጄ በማለት ንግግራቸውን ለማሰማት ሲነሱ፤በአጠገባቸው የተቀመጡት አዛውንት «ተፈራ የመንግሥት መልከተኛ ነው ጌታዬ በል ሲሏቸው፤»«የልጄቼን ባልጀራ ጌታዬ አልልም» በማለት ንግግራቸውን አቀረቡ፤«እንደምታየው የአካባቢው ሕዝብ መቋቋም ገና መጀመሩ ነው።ከበረሃ ከተመለሰ ይህ የመጀመሪያው ሰብሉ ሲሆን፤ቀደም ሲል ባስተላለፍከው አዋጅ ደሮ እንኳን ያለው ግብር ይከፍላል በማለትህ ስንቆጭ፤ በተጨማሪ ዛሬ ንብረታችንን ልናስቆጥር፤ጎን ለጎን እናከሄደው የነበረውን የግብርና ሥራችንን ልታስለውጠን ማሰብህን ጠቅሰሃል፤ ዕቅዳችሁ የምንሰራውንና የምናመርተውን ልትቆጣጠሩን ነው። እንደምታየው አብዛኛው ሕዝብ የእርዳታ ቀለብ ተሰፋሪ ሲሆን ቀደሞውንም ምንም ሥራ የሌለውን ሰው እንዴትስ የሥራ ምርጫ ይሰጠዋል? ንብረትስ እንዲያስቆጥር ይጠየቃል? ለሁሉም ጊዜ አለው።ቀደም ተከተሉን ጠብቆ የሚመጣ ነው፤ሕዝቡ ጠንክሮ እንደየፍላጎቱ ለሥራ ከተሰለፈ፤የሚዋጣውን የሞያ አይነት መርጦ መያዝ መብቱ ሲሆን፤እንዴትስ የሥራ ፍላጎቱ ተመርምሮ ሳይታወቅና በሥራው ተሰልፎ ሳይፈተን ይህን ሥራ ያንን አትስራ ብሎ ገደብ ማድረጉ ያለውን ችግር አያባብሰውምን? በመጀመሪያ ከአካባቢው ኗሪዎች ስንቱ እጅ ሠርቶ አደር መሆኑን ማወቅ ቀደምትነት ተሰጥቶት ሣይጠናና የሕዝብ ተሣትፎ ሳይጠየቅ በማስፈጸም ስም ብቻ ውሳኔዎችን ማስተላለፉ በመጨረሻ ተፈፃሚነት ሲያጡ ችግር እንደሚያመጡ በቅድሚያ ማወቁ ጥሩ ስይሆን እንደማይቀር ልጠቁምህ እሻለሁ።ለማንኛውም ለአካባቢያችን የሚበጀውን እየተመካከርን ብንሰራው ውጤቱ መልካም ይሆናል ብዬ አስባለሁ» በማለት አቶ ተፈራ ንግግራቸውን ሲፈጽሙ ትልቅ ጭብጨባ ከተሰበሰበው ሕዝብ ተደረገላቸው።

የአካባቢው ሕዝብ ተጠሪ ሽማግሌዎች በየተራ እየተነሱ የአቶ ተፈራ ሐሣብ ሐሣባቸው መሆኑን ለአስተዳዳሪው ገለጹለት።አስተዳዳሪውም ሕዝቡ ከቁጥጥሩ ውጭ መሆኑን ተገንዝቦ የተለመደውን የማስፈራርቾ ቃላቶቹን ሰንዝሮ፤ የተሰጠው ሐሣብም በትክክል የአካባቢውን ሕዝብ ችግር የሚመለከት ሳይሆን ጥቂት ጥቅማቸው የተነካባቸው ግለሰቦችና በአንዳንድ አወናባጆች ቀስቃሽነት እንዲነገር የተደረገ ሐሣብ መሆኑን ገለደላቸው።

አንድ የስልሳ ዓመት አዛውንት ምርኩዛቸውን ደገፍ ብለው፤«ልጄ አንተም ሆንክ መሪዎቻችን መቼ ይሆን ሕዝብ ልክ ነው ብላችሁ የእምነት ቃላችሁን የምትሰጡት? ሠርቶ አደሩ፤ ሕዝብ ሁሌ ስህተት ሰሪ የመንግሥት ቅጥረኛ አዋቂና ለሃገር ሐሣቢ እድርጋችሁ ከወሰዳችሁት ከምታለሙት የምታጠፉት ስለሚበልጥ በመጀመሪያ ሞያውን አስቀድሞ ማወቁ ሣይጠቅም አይቀርም። እኛ ሕፃናት አይደለንም፤ስለአካባቢያችን ብዙ ከመሳሳት ብዙ ተምረናል።አንተ እንዳልከው አንድ አወናባጅ መጥቶ የማናምንበትን እንድናደርግ ነግሮን የምናደርግ አይደለንም።ከአወናባጅ ይልቅስ የእናንተ ኃይል አይበልጥምን? መሣሪያ የታጠቁ ከዙሪያችን ቆመው ሳሉ የሚታየንን ለመናገር ማንንም ሰንፈራ ስንገልጽ እየሰማህን እንዴትስ በሰው በሉ ባይነት ያላመንበትን ነገር እንድንናገር የተደረግን እንደመሰለህ አልገባኝም።ባታውቀው እንጂ የወገንና የሃገር ፍቅር በእኛም ውስጥ አለ።ችግሩ በጊዜያችን የእናንተን የዘመኑን ትምህርት ባለመቅሰማችን የሥራችንን ቀደም ተከተል ከትበን ባለማስቀመጣችን ምንም እንደማናውቅ ሁሌ በሰው የምንመራ የማንመራመር የሚበጀንን የማናውቅ ተደረጎ መወሰድ የለበትም።ሆኖም ግን ያሳለፍናቸውን ውጣ ውረዶች ለልጆቻችን በቃል ሳንነግራቸው አልቀረንም።አንተም ከቤተሰብህ ብዙ እንደተማርክ እንገምታለን።በአጠቃላይ እናንተ የዘመኑ ወጣቶች ልትከሩብን በተገባ ነበር።የዛሬውን የልመና ስልቻችንን ይዘን ከመንግሥት መጋዘን መቆማችንን አትመልከት።መሪዎቻችንም ይህን የምትሰፍሩልንን ቀለብ ከዓለም ፊት

ተስቅጥጣችሁና እፍራችሁ እምጥታችሁ እንደምትሰጡን ተገንዝበናል።የእኛም ምኞት ይህ ችግር በተደጋጋሚ እንዳይመጣብን በግልጽ ተወያይተን መፍትሔውን በጋራ እንፈልግ ነው።የዚህን ዓይነት ችግር በሃገራችን ተደጋግሞ ደርሷል።ግን ገበናችንን ለማንም ገልጸን አሳሰየንም።ከራሳችን ሌላ የውጪ ሰው ሆዳችንን እንዲሞላልን ተስፋ አድርገን እናውቅም። አሁንም ልገልጽ የፈለኩት የዚህን አይነት አስተዳደር ምንጊዜም ሕዝብን ለችግር አጋልጦ መስጠቱን እየተናገርን የሚበጀውን እየጠቆምን ብናልፍ ይበጃል እንጂ ለመኖር ብቻ የሆነ ያልሆነውን ብንዘለብድ ትዝብት ትወስዱብናላችሁ።እኛም በበኩላችን ባልጠበቅናችሁ መንገድ ስናገኛችሁ እናዝንባችኋለን።የሚተካን ትውልድ አላገኘንም በማለት እንፀጸታለን።ያም እንዳይሆን መተራረም አለብን።ጥፋት ሲሰራ እያየን ብናልፈው ውሎ አድሮ ሁላችንንም ይጎዳል።የተወለድንበትና ያደግንበት ሃገር የኪራይ ቤት አይደለም። ሲበላሽ ሲያረጅ ታይቶ ውልቅ ተብሎ አይኬድም።ይህ ይዞታችን ነው።ማሰመር የሚበጀውን ማድረግ ግዴታችን ነው ለዚህኑ ነጋሪ አስተማሪ አይሻም።እንተም እንድታውቅልን የምንሸው፤ይህንኑ ነው።ተልከህ ከዚህን ከመጣህ ቅርብ ጊዜህ ነው። እብረህን ሆነህ ችግራችንን አላየህም ወይም ስለአካባቢው በጥናት መልክ ተጠናቅሮ የተቀመጠ ጹሑፍ አግኝተህ እንዳላነበብክ እናውቃለን። እንተም ሆንክ መርጠው የላኩህ መሪዎቻችን ያለው ችግር በምግብ ብቻ እንደሚወገድ አድርገው ከወሰዱት ተሣስተዋል፤ ባይገርምህ ከዚህን አካባቢ የእርዳታ ቀለብ መሰፈሩ ችግሩን ሲያብሰው እንጂ ሲያቀለው አላየንም።ምግቡ ሳይስማማቸው ቀርቶ የሞቱትን ሕፃናት ቁጥር እቤት ይቁጠረው። የእርዳታ ቅቤ ልጄን መግቢያት ሞተች ብሎ በአደባባይ መናገር ይቻላልን? ይሆናል ብለን የዘራነውን ቡቃያ አላየህውም።ቀደም ሲል የተገለጹት ሐሣቦች በሙሉ ልጄ ሙት የራሳችን ናቸው።በሰው ተነግሮን እንደአቀረብን አድርገህ መገመትህ ስለአካባቢያችን ጠንንቅቀህ ያለመረዳትህ ነው።አሁንም ደጋግመን ልንገልጽልህ የምንሸው በትዕግስት የአካባቢውን ችግር ተረድተህ ያንንም ችግር የሚወገድበትን ርሰበርሳችን በግልጽ ተወያይተን ከፈታነው በኋላ የጠየክቸው በሙሉ በተግባር ተፈፃሚነት ካላቸው የማንቀበልበት ምንም ምክንያት አይኖርም።እንተም በግልህ ልታደርገው የምትችለው ነገር ከሌለ ለበላዮችህ እኛን መስለህ አስረዳቸው። ይህንን ሁኔታ ነው እኛ ከእንተ የምንጠይቀው።» ለሽማግሌው ትልቅ ጭብጨባ ተደረገላቸው።

የልማት አስተዳዳሪውም የእርሱ ተልዕኮ መንግሥት ያስተላለፈውን መመሪያ በተግባር ለማስፈጸም መሆኑን ጠቁሞ የመንግሥቱን ትዕዛዝ የሚሽረው ነገር እንደሌለ ገልጾ፤ አዋጁንም የማይቀበሉት ከሆነ እንቢተኛነታቸውን ለበላይ ባለሥልጣን ማስተላለፍ ብቻ እንዳለበት ተናግሮ ከላምንም ውሳኔ ስብሰባው ተበተነ።



እቶ ተፈራና እውነቱ ወደቤታቸው በመሄድ ላይ ሳሉ እውነቱን ስለስብሰባው ያለውን አስተያየት ሲጠይቁት «ሕዝቡ ከልማት አስተዳዳሪው በእስተሳሰብ ብስለቱና የአካባቢውን ችግር በሚገባ ማወቁን ጠቁሞ አስተዳዳሪው ምንም አይነት ሥራ በራሱ አነሳሽነት ለመስራት እንዳልተዘጋጀ ገልጾ፤ አንድ ነገር ሠርቶ ቢበላሽበት ወይም ውሳኔ ሳያገኝ ቢቀር እጠየቅበታለሁ የሚለው ጥርጣሬ ሲታይበት፤ይህን አይነት ጥርጣሬ በማንኛውም የሥራ መስክ ከተሰለፉት የመንግሥት ቅጥረኞች የሚታይ ነገር ሲሆን፤ያንንም ለማስወገድ ቀድሞ ተሰጥተው እንደነበሩት ውሳኔዎች በአዋጅ ሳይሆን ራሱ ገለሰቡ እንደአንድ ሰው ለሚሠራው ሥራ እምነት ሲኖረው ብቻ ነው። በታየውና በእውቀቱ መሥራት ካልቻለ በሚሠራው ሥራ እምነት ከሌለው የሕዝብ ሃላፊነት በሚጠይቁ የሥራ መስኮች ላይ ካለመሥራ መቆጠቡ ብልህነት ነው።በራስ የመተማመኑ ጉዳይ በገንዘብ ወይም በአማሪ እቤት ከመንግሥት በተሰጠ ካሣ የሚገኝ ነገር ሳይሆን ራስን በጥሩ ሥነምግባር፤በቤተሰብና በሕብረተሰብ ታንጾ ከማደግ የሚመጣ ነው። ሕዝቡንም ለጥቅም ብሎ ባልሆነ መንገድ መርቶ ችግር ላይ ከመጣል በግለሰብ ደረጃ መጎዳቱ አማራጭ የሌለው ተግባር ሲሆን፤ ግን የወር ደመወዝ እንዳይቷደል በማለት ብቻ ይሁን ማለት በመጨረሻም በራስ መተማማንን አሳጥቶ በሕይወትም ላይ ጉዳትን ያስከትላል።ሕዝብም በምሳሌነት የሚከተለው መሪ ከሌለው ከሚያደርገው የመሸሻል እርምጃ እንዲጋታ ያደርገዋል። የዛሬው አስተዳዳሪ ግን እንኳንስ በቀደምትነት ተጠቅሶና ተመርጦ ሕዝብ ሊከተለው ይቅርና እንደውም የጥሩ መሪዎችን አስተያየትና መንገድ የሚከተል አይመስልም። በአጠቃላይ ሕዝቡ በአውራነቱ በወግን ወዳጅነቱ በሥራው ውጤት አስገኝነት፤ የሚቀበለው መሪ በመንግሥት በኩል ተመርጠው ከሚላኩት ውስጥ ባለማግኘቱ ከአካባቢው የሚያውቃቸውንም ለመምረጥ መብት በመነፈጉ ይሄው ውጤቱን ከዕለት ወደዕለት እንደምናየው ነው። በአጠቃላይ አስተዳዳሪ፣ የደርግ አባል፣ የአብዮት ጠባቂ፣ ካድሬ የሚባሉት የሞያ መጠሪያዎች ሕዝቡን ደጋግሞ ራሱን እንዲጠይቅ በማድረጋቸው፤ይህን መጥፎ ትዝታ ከአእምሮአቸው አስወጥቶ በጥሩ የሥራ ፍሰት እንዲሰለፉ ለማድረግ አብረዋቸው እየሰሩ የሚማሩና የሚያስተምሩ ባለሞያዎች ብቻ ያስፈልጉታል። አስተዳዳሩን ግን ለሕዝቡ መተው አማራጭ የሌለው መንገድ ሲሆን፤ ለዘመናት በነፃነቱ በአንድነቱ ተከብሮ የኖረን ሕዝብ መሪውን አውቆ አይመርጥም አልተማረም በሚል ሰም አስተዳዳሪውን መርጦ መላክ «ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረችትን» ስለሚሆን፤ ያም ሆነ ይህ በሞያው ያልሰለጠነውንና በየጊዜው ከበላይ መመሪያን የሚጠብቅን ግለሰብ ወደ ሕዝብ ከማላክ የቀረ ተመርጧል።ከበላይ በባለሞያዎች ላይ ተጽኖዎችን የሚያደርጉ ከሆነ ያም ደግሞ ሌላው ጥፋት ሆኖ፤በመንግሥት በሕዝብም መካከል መቀራረብ ቀርቶ፤ ቅራኔዎች ሠፍተው፤ መራራቅን ያስከትላል።»

## ፴፰

ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ሆኖ የአቶ ተፈራ ቤተሰብ በሙሉ ተኝቶ ሳለ፣ውሾች ከውጭ ጩኸት በማሰማታቸው፣ ለሰው መሆኑን የተረዱት ወይዘሮ ልኬለሽ ከመኝታቸው ተነስተው ኩራዛቸውን እያይዘው ከራስጌ የሚገኘውን የመውዜር ጠብመንጃ አንስተው ከሌላ ሥፍራ ያስቀምጡታል።የቤቱም በር ይኳኳል፣ ማንነቱን ሲጠይቁት የአካባቢው ኗሪ በመሆኑ በሩ ሲከፈት፣ያስከፈተው ግለሰብና የጥበቃ ጓዶች ፖሊሶች ተከታትለው ሲገቡ የተፈሪ ሱሪአቸውን አጥልቀው ጋቢያቸውን አጣፍተው ከኩርሲ ላይ ተቀምጠው የነበሩት አቶ ተፈራ፣ፎክረው መሣሪያቸውን ወደአስቀመጡበት ቢሄዱም ከራስጌው የለም፣ ሁሉም መሣሪያ ታጥቀው ስለነበር፣ እጆቻቸውን በካቴና አስረዋቸው ይዘዋቸው ሄዱ።በሩን ያስከፈታቸው በአካባቢው የተመደበ ነጭ ለባሽ ኖር አብሮአቸው ሄደ።

አቶ ተፈራ ብዙ ጊዜ በሚቀርቧቸው ጓደኞቻቸው በኩል ያለውን መንግሥት ከመቃወም እንዲቆጠቡ ተመክረዋል ተዘክረዋል ግን አልተለወጡም። ሁሉም ሰው ተበዳይ ይመስላቸዋል። የሃገራቸው ነገር ያሳርራቸዋል ያበግናቸዋል። ግን ሠርተው በጉልበታቸው ማደር የማይፈልጉ ሰዎች ያልሆኑ ዜናዎችን እያቀበሉ እንደሚኖሩ ያውቁታል።ግን ስለሰ ለሃገር እንጂ ወገንን በወገን ላይ መሆን እንደሌለበት በማመናቸው የሚታያቸውን ከመናገር የሚሆነውን ከማድረግ ተቆጥበው አያውቁም። ያም ሆነ ይህ የአቶ ተፈራ እጃቸው ተያዘ። ቤተሰባቸው በችግር ላይ ወደቀ።

ወይዘሮ ልኬለሽም እውነቱ ይተኛበት ከነበረው የአውሬ መጠበቂያ ጎጆ ማልደው በመሄድ፣ እኅቱ ሌሊቱን ተይዘው መወሰዳቸውን ነግረውት እርሱም ወደሰፈር ከመምጣት ከዚያው እንዲቆይ አድርገው፣ ማደራቸውን ለመጠየቅ ከፖሊስ ጣቢያው ቢሄዱ ሌሊቱን ወደክፍለሃገሩ እስር ቤት እንደተወሰዱ ተነገራቸው። ሁኔታው የአካባቢውን ሕዝብ ለጊዜው ቢያስደነግጠውም፣ተጀምሮ እስከሚጨረስ ፍትህን አግኝቶ የሚያውቅ ስላልሆነ የአቶ ተፈራን መታሰር ወይም መገደል የሚጠብቀው ነው።ሆኖም የመንግሥቱ አስተዳደር መሸሸሉን በየጊዜው ስለሚገለጽለት እንየው በማለት እንጂ ከመጠራጠርና እውነት ያለመሆኑን ከማመን ተቆጥቦ አያውቅም።

የአቶ ተፈራን መታሰር ሲሰማ ቀድሞም በጥርጣሬ ላይ ያለው ሕዝብ ከብቱንና ልጆቹን እየያዘ ከአካባቢው እየለቀቀ ተሰደደ። የደረሰውን ቡናና የቀለብ እህል ለአውሬ እየተውት ሰሄድ፣ማግስቱም ገበያ ስለነበር ወደገበያ መጭውም አካባቢውን ለቆ የሚሄደውን ሕዝብ በማነጋገር የተፈጠረውን ሁኔታ ሲነገራቸው ወደመጡብት



መመለሳቸውን ቀጠሉ።መጥፎ ነገር መች ይሸሸጋል ሁኔታው በአውራጃው ውስጥ ዳር እስከ ዳር ሲሰማ፣ሲል፣እንኳንስ ሰው ታስሮ ተገደለ የሚለው ዜና ተነግሮ ይቅርና የወታደር የደብ ልብስ የለበሰ ሰው በገበያ ውስጥ ከታየ በሚቀጥለው የገበያ ቀን የገበያተኛው ቁጥር ከመቀነስ አልፎ፣ ጨርሶም ባዶ የሚሆንበት ቀንም ነበር። የሁለት የሦስት ሰዓት መንገድ ተጉዞ መጥቶ ከሚገበያይ ይልቅ የአስራ አምስት ቀናት ጉዞ ተጉዞ ከጎረቤት ሃገራት ጋር መገበያየትን ሲመርጥ፣ ከዚያንም በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጥ ይገደዳል ምክንያቱም አማራጭ የለውማ።

ለምሳሌ አንዱ የደርግ አባል ተነስቶ ከገጠር ሕዝብ ጋር የሚገበያየውን ከወንበዴዎች ግንኙነትን ፈጠረ በማለት ሲገድለው ከመሐል አገር የሚነግደው ሕዝብ ምርቱን እንዳለ በርካሽ ዋጋ ለጎረቤት ሃገር ነጋዴዎች በኮትሮባንድ መንገድ ያቀርባል።

ከአካባቢው ሰዎችን መገደል ወይም ማሰር በሃገሪቱ ምጣኔ ሐብት ላይ ትልቅ ቀውስ ማምጣቱና ሕዝቡንም በደህነት እንዲማቅቅ ለማድረጉ በቅርብ ለተከታተለው ምንም ሰፊ ያለ ማስረጃ አይሻውም። ሌላው ቀርቶ ከመሪዎች የሚሰነዘረው ቃል ጥንቃቄ ካልተደረገበት ያም ለውድቀት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። ለምሳሌ ሲቀመንበሩ ደቡብ ክፍለሃገራትን በጎበኙበት ወቅት ማለትም የካቲት ፸፬ ዓመተ ምህረት የመንግሥት ሠራተኞች የሥጋ ቤት ከፍተው በማስነገዳቸው ሲቃወማቸው ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳት አጢኖት ይሆን? በጊዜው ትልቅ ዜና ሆኖ በመቅረቡ የአካባቢው ከብት አርቢ ተቀባይ በማጣቱ የደለቡ የሥጋ ከብቶቻቸውን ለጎረቤት ሃገር ለማቅረብ ተገደዱ። በሃገራቸው ከራሳቸው አልፎ ለውጭ ለማቅረብ አቅም ያልነበራቸው ጎረቤቶቻችን በእኛ እርሻ ምርት አቅራቢነት በዓለም ገበያ ቢታወቁበት በስፍራው ሆኖ ለተመለከተው ምንም የሚያስደንቅ አይሆንም። ያም የሃገራቸውን ሕዝብ በውል ጠንቅቀው በማያውቁ የደረግ አባሎችና ተመርጠው ይላኩ የነበሩ አስተዳዳሪዎች ውጤት መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም። እንግዲህን በዚህን አኳያ ስንመለከተው አንዳንድ ግለሰቦችን በማስፈራርቾ ስም እየመረጡ መግደል ሕዝብን ብቻ ሳይሆን ሃገሪቱን እየለቀቀ እንዲወጣ ያደረገው ምንጊዜም ሃገሪቱ የማታገኛቸውን የተፈጥሮ ሐብቶችን ጭምር ነው። የሃገር ኅብኻዎች ይሰቡልን የነበሩት የዱር አራዊቶቻችን ዛሬ የት ነው ያሉት? የተሰደደ ሕዝብስ መንግሥት ሲለወጥ ይመለስ ይሆናል ግንየተፈጥሮ ሐብታችን የባዕድ ንብረት ሆነ።

እውነቱም የአቶ ተፈራ ሁኔታ እስከሚረጋገጥ ከአካባቢው እንዲሄድ ስለተፈለገ የአቶ ተፈራ የቅርብ ጓደኛ ከሆኑት በሼህ ሙሐመድ በኩል የሚቀይበት ስፍራ ስለተገኘለት ወይዘሮ ልክየለሽ ይዘት ወደአዲሱ ሥፍራ የሚሄደውን ግለሰብና ትፍሪድን እንድአረጋቸውን አስከትለው፣ እንዲሁም ለጥቂት ቀናት ስንቅ

የሚሆነው ገንዘብ ለመንገዱ የስንዴ ዳቦአቸውን ይዘው ከጎጇዋ ሲመጡ፤ ከፊታቸው፤ ሐዘን ፀጸት ይነበባል። የከቱን በእጅ የተፈተለውን የቤት ሥር ቀሚሳቸውን ለብሰዋል።ቀሚሱም ነጠላውም መቀነቱም ጥቁር ጥለት ተጥሎበታል።ከጎጇዋ እንደደረሱ መቀነታቸውን ጠበቅ አድርገው ትፍረድንና አንዳርጋቸውን አጎታቸውን እንዲሰናበቱት ሲጠይቋቸው፤ትፍረድ የመቀነታቸውን ጫፍ ይዛ ቆማለች፤ አንዳርጋቸው በእግሩ መሬቱን ይጭራል፤እውነቱም በትንንቅ ሊሰማቸው ቢሞክር፤ትፍርድ ታለቅሳለች፤እንዳርጋቸው ሳይቀርበው ፈለገ፤ለሁሉም በግድ ሰሟቸው፤ ወይዘሮ ልኬለሽን ሊሰናበታቸው ቀና ብሎ ፊታቸውን ለማየት ሲሞክር እይኖቹ እንባን አቅረዋል፤እሳቸውም ያንን ተመልክተው «ጠንከር በል፤እኛ ሴቶቹ እናልቅስ እንጂ ወንድ ልጅ አያለቅስም፤ የወንድ ሆደ ቡቡ አትሁን፤ከአሰብከው ዓላማህ ለመድረስ አታመንታ አትታለል፤ እኔም መቀነቴን ጠበቅ አድርጌ የሚመጣውን እጠባበቃለሁ።እግዚአብሔር ካለ አጎትህ ተፈተው መጥተው፤ሃገር ሰላም ሲሆን ተመልሰህ ትመጣለህ።አሁንም ከዚያን ሁሉ መከራ አምልጠህ መጥተህ ከእኛ ዘንድ እንድትያዝብን እንሽም። ለሁሉም የምትሄድበት ሥፍራ ዛሬ ከምታድርበት ቤት ሲነገርህ፤የአጎትህንም ሁኔታ በየጊዜው ለገበያ ለሚመጡ ሰዎች እገልጽልሃለሁ።መልከም ጉዞ ይሁንልህ ደህና ሁን፤» ብለው ጉንጮቹን ስመውት ተለያዩ።

እውነቱም ከአዲሱ ሥፍራ ከሚወስደው ግለሰብ ጋር ጭለማን ተገን በማድረግ የተመደቡትን የጥበቃ ኃዶች እንዳያያቸው ጫካ ጫካውን አሳብረው ከተባለው ሥፍራ ሲደርሱ፤የአቶ ተፈራ ዘመድ ይመጣል ተብሎ ለመደርተኛው ተነግሮት ኖሮ ተዘጋጅተው ጠበቁት። የመንደሩ ሽማግሌዎች በትልቁ ዛፍ ሥር ቁርበት ተነጥፎላቸው ተቀምጠው ሳሉ፤ እውነቱንና ይዘት የሄደውን ግለሰብ ከአካባቢያቸው ሲደርሱ ለመለየት ጊዜ አልወሰደባቸውም።የጨረቃዋ ብረሃን መርፌ ታስከ ነበር እና፤ ይዘት የሄደው ግለሰብ የአቶ ተፈራ ዘመድ መሆኑን እስተዋውቆት ሽማግሌዎቹ እንኳን ደህና መጣህ በማለት እንዲቀመጥ ፈቅደውለት፤የመንደሩም ሴቶች ያዘጋጁትን ምግብ እንዲያቀርቡ ተጠይቆ፤ ሁሳቸውም እቤት ያፈራውን በቆሪ ገንፎውን፤ ቡራቶውን ሚጭሮውን በቁዱ ወተቱን በጀበና ቡናውን እያመጡ ከዛፉ ሥር ከልኩለውት፤ እንዲያሰልፉ የተመደቡት ሴቶች እንዱን ቆሪ ምግብ ከእንጨት ከተጠረቡ ማንኪያዎች ጋር ለተቀመጡት ሽማግሌዎች እንድ ለሁለት እሲዘዋቸው፤ ወተቱና ቡናው ሲታደል፤ ለእውነቱም ለብቻው አንድ ቆሪ ሚጭሮ ከማንኪያና በቅል ተሞልቶ ለማማጊያ ወተት ቀርበለት፤ለእንግድነቱ ተብሎ ባለቤቱ ትኩስ ማር ቆርጦ አመጣለት።

ይህ በዚህ እንዳለ የእውነቱን ጉዳይ በአደራ መልክ ለማጥበቅ ሼህ ሞሐመድ ከሥፍራው መጥተው፤ ከሽማግሌዎቹም ሰላምታ ተለዋውጠው፤፤ ከዛፉ ሥር ከተቀመጠው ምግብ እንዱን ቆሪ እሳሳፈዋ



ከማንኪያ ጋር እሲዛቸው፤ምግባቸውን እየተመገቡ ይነጋገሩ የነበረው በሃገራችን ላይ እግዚአብሔር ፍርጃውን እንስቶ ሰላሙን እንዲያወርድ ነበር።

የተሰበሰቡት ሽማግሌዎችም ምግባቸውን ተመገበው ከበቁ በኋላ በአንድ አዘውንት መሪነት በሃገራችንና በመደራቸው እግዚአብሔር ያወረደውን ቆጣ አንስቶ ሰላም እንዲያወርድ በጸሎታቸው ሲማጠኑት እውነቱም አብሮት ሊኖር የተዘጋጀው ቃሲም ከዚያን ከሽማግሌዎቹ መካከል ኖሮ ከእውነቱ እጅ ለእጅ እጫበጧቸው። ሼህ ሞሐመድም እርጥብ ሣር ነጭተው ለቃሲም ሰጥተውት በመሬት የሰጠሁህን አደራ በሰማይ እቀበልሃለሁ።በአደራም የሰጠሁህ የወንድሜን ዘመድ እውነቱን ነው።በማለት አደራውን እንዲያጠብቅ ደጋግመው ነገሩት።

ሼህ ሞሐመድም እውነቱን ከሰዎች መካከል ፈንጠር ወደአለ ሥፍራ ወስደውት እሳቸውና አቶ ተፈራ ከአንድ አባትና እናት አለመወለዳቸው እንጂ ከወንድምአማቾች የበለጠ ዝምድና እንዳላቸው ጠቅሰው፤«የሃይማኖትና የጎሣ ልዩነቶች በሁለቱ መካከል ምንም ዓይነት ሥፍራ እንደሌላቸው ተናግረው፤«ቃሲምም ቢሆን አብሮ ኗሪያችን ነው፤ እርሱም ልጆቹም አማርኛና እሮሞኛ ስለሚናገሩ በፈለጋችሁት ቋንቋ ልትነጋገሩ ትችላላችሁ። በአካባቢው የሚኖረው ሕዝብ ጉራ የሚባለው ጉሣ ስሆን፤ በማንኛውም ሥፍራ ሲያዩህ «አማራ» በማለት ይጠሩናል፤ ቃሉንም ከሶማሊያ የፕሮፖጋንዳ ዜና ማሰራጫ ሬዲዮ ጣቢያ ስለሚሰሙት እንደሕፃን ማስፈራርቾ ተጠቅመውበታል፤ እናንተስ ልጆች ሆናችሁ ከቤት ስታስቸግሩ ጋላ ጠርቼ ጆሮአችሁን እናስቆርጣችኋለን ትባሉ የለም!ነገሩ አንድ ለአንድ ነው ለሁሉም አንተ ከዚህ በበለጠ ታውቀዋለህ። እደራ የምልህ ሕዝቡ በጣም ደግ ሕዝብ ነው።አንዳንዶቹ ቢያስቀይሙህም እንኳን በራሳቸው እነሳሽነት እንዳልሆነ ትረዳቸው።ከሶማሊያ የሬዲዮ ጣቢያ የሚተላለፈው የውሸት ዜና እንኳንስ ከቤቱ ወዶትም ሄዶ የማያውቀውን ሕዝብ ይቅርና ብዙ ነገር ያዩትን ግለሰቦች ሳይቀር ያታልላል።በአጠቃላይ ሕዝቡ ሐብታም ነው። ተፈጥሮ አድሏዋለች።ተፈጥሮን መከባከብ እንጂ ብዙም በሥራ አይደከሙም። ከዚህ የሚረባው ከብትና ከዱር የሚለቀመው ቡና ከቀፎአቸው የሚቆረጠው ማር ጎረቤቶቻችንን እማራች አድረጓቸዋል።ለማንኛውም በውስጣቸው ስትገባ የማታውቀውን ነገር ስለሕዝቡ ትማራለህ።ለምንም ተዋጊ እንደሆነ ቀደም ሲል ከምትሰማው ይልቅ በውስጡ ሆነህ እውነቱን ለማየት ስለሚረዳህ ደህና ትምህርት ይሁንህ» ብለውት ሽማግሌዎቹንም ተሰናብተው ሄዱ።

## ፴፱

ቃሲም ለበቤተሰቡ እንግዳ ይዞ እንደሚመጣ ነግሮአቸው ኖሮ ከጎጆቹ ጋር ከሚገኘው ዛፍ ሥር ቅርበቶችን እንጥፈው ለበቶሎ መጥበሻ ፍም እንዲወርደው ግደች ተጋፍጠው የበቶሎው እሸት ተዘጋጅቶ ደረሱ። እውነቱና ሌሎች እንግደች ከሥፍራ ሲደርሱ የቃሲም ሦስቱም ሚስቶቹ ያዘጋጁቱን ምግብ እምጥተው ለእግደቹ ለያንዳንዳቸው በቶሪ ከእንጨት ማንኪያ ጋር እሲዘዋቸው፤ ማማጊያ ቡናውንም በቅል መጠጫ ሰጥተዋቸው፤የተዘጋጀውን የበቶሎ እሸት የዝንጅር ቂጥ በመሰለው ፍም ላይ እየጠበሱ ሳለ፤የቃሲምን መምጣት የሰሙ ጎረቤቶች ከየቤታቸው ቡናና የሚበላ ምግብ እየያዙ ከሥፍራው ተገኝተው ጫወታው ደራ።ቃሲምም ከከተማ ወጥቶ የሰማውን ያየውን ሲያወራ፤ እነርሱም በጥሞና ሲያዳምጡ ከቶዩ በኋላ «መች ይሆን እግዚአብሔር በዝህች ሃገር ላይ ሰላም አውርዶልን ያለ ሥጋትና ፍረሃት ሠርተን መኖር የምንችለው?» በማለት እየተከዙ የማታው ሥግደታቸው እንዳያመልጣቸው ሁላቸውም በየአቅጣጫው ሰሄዱ ቃሲምም ከአንደኛዋ ሚስቱ ጋር ከዚያው ከሚነደው እሣት አጠገብ አንድ ለሰላሰ ጀዲ ዘርግተው ፊታቸውን ወደምሥራቅ መልሰው ስግደታቸውን አደረሱ።

ከዚያንም የበሰለውን የበቶሎ እሸት እየተመገቡ በፍሙ ላይ የተደረገው እያገላበጡ ቃሲም ለእውነቱ የቤተሰቡን ሁኔታ በቅድሚያ እንዲያውቀው በማለት በዝርዝር ሲያጫውተው፤ ሦስቱንም ሚስቶቹን ያገባቸው ከለውጡ በኋላ እንደሆነ ሲገልጽ የመጀመሪያ ሚስቱ ሦስት ልጆች ወልዳለት አራተኛውን ለመገላገል በምጥ ላይ እንደሞተችበት ተናገሮ፤ ቀደም ሲል ሦስት ሚስቶችን ለማግባት ሐብታም መሆን እንደሚኖርበት ጠቅሶ፤ «ጥሎሽ ወይም ገበራ ካልተሰጠ ሚስት ማግኘቱ ከባድ ሲሆን ሌላው ቀርቶ አግብታ የፈታችውን ጋለሞታ ለማግባት ከተፈለገ ለመጀመሪያ ባሏ የተወሰነ ገንዘብ መሰጠት አለበት።እኔ ግን ሶማሊያ ሄጄ መሣሪያ ከመጣሁ በኋላ የመጀመሪያው ዕቅዴ ሚስት ማግባት ስለነበር የትልቋ ሚስቴ እሚና ቧላ ሞቶ ስነበርና የሚወርሰው ወንድም ስላልነበረው በቀላሉ አገኘኋት። መሣሪያ ከታጠክ ምን የማታደርገው ነገር አለህ? ሁለተኛዋን ከዲያን ባሏ መሣሪያ ለማምጣት ሶማሊያ ሰንሄድ መጥፎ ውኃ ጠጥቶ መሞቱን እውቅ ስለነበር እምጥቼ ከቤቴ አገባኋት። ትንሿን ዘይቱናን እንደምታያት ገና ልጅ ናት፤ እሷን የቤቶቿን ከብቶች ከምታግድበት ከሜዳ ጠለፍኳት ፤ ሦስቱን ሚስቶቼን ሦስቱን ልጆቼን እናቴን ጭምር የማስተዳድራቸው በአንድ ጥማድ በሬ ነው።» ሦስቱን ልጆቹን ጠርቶ ሴት ልጁን ዛራን ከአጠገቡ እንድትቀመጥ ከደረገ በኋላ፤ ታላቁን አህመድን ተከታዩን ኡመርን በአማርኛ ስማቸውን ለእውነቱ እንዲነግሩት ጠይቋቸው፤ «እነርሱም ከአካባቢው ከመጡ በአማርኛ ቋንቋ እንዳንዴ አባታቸው ከሚስቶቹ ምስጢር ለመሸሸግ ሲፈልግ ከእናገራቸው በስተቀር ተጠቅመውበት እንደማያውቁ አብዛኛውን ጊዜም በአሮመኛ መናገርን እንደሚያዘወትሩ ያጫውቱታል።» እውነቱን ሲያገኙት ግን ሁለቱንም የሚናገርላቸው በመሆኑ ደስታቸው ከፍተኛ ይሆናል።

ቃሲምም ተከዝ ብሎ «ያ ቀን አለፈ፤ ለውጡ እንደተጀመረ፤ በየዕለቱ ግድያ ብቻ ሲሆን የምናውቃቸው የአካባቢያችን እዛውንቶች ከእስላሙም ከክሪስቲያኑም ከፍል ሲሞቱ ስናይ ልባችን ሸፈተ። ከሶማሊያም ጠላታችሁን መከላከያ መሣሪያ ይታደላችኋል የሚለውን ዜና ስንሰማ ስንቃችንን መሰነቅ ጀመርን። እኔም በወቅቱ ምንም ስለአልነበረኝ እነዚህን ሁለት ወንዶች ልጆቼን ለሰው ማስቀጠር ግድ ሆኖብኝ፤ ታላቁን ልጄን አህመድን ለስንቄ መጫኛ አህያ ሳልተወሰነ ጊዜ ለከብት እረኝነት ሣከራየው ትንሹን ኡመርን በሁለት ቁና ስንዴ ለጥጃ እረኝነት ሰጠሁት። ሴቷን ዛራን ከእርጊቷ እናቴ ጋር ትቻት፤ከዚያም ስንቄን በአህያዬ ጭኜ ከአካባቢያችን መሣሪያ ለማምጣት ከሶማሊያ ከሚሄዱት ሕዝቦች ጋር ጉዞዬን አደረኩ። ጉዞውም በጣም አሰልቺና አደጋ የበዛበት ስለነበር፤ ከየአቅጣጫው መጥተው እንጓዝ ከነበርነው ሕዝቦች ውስጥ ብዙዎቹ በረሀብና በውኃ ጥም አለቁብን። የተበላሸ ውኃ በመጠጣት የሞቱትም ቁጥር የዘኑ ያህል ነበር።የሞቱትንም በየመንገዱ ላይ አፈር እያለብስናቸው የእኛም ቀን እስከሚደርስ ተስፍ በመቁረጥ ስንጓዝ፤እኔም ተራዬ መች ይሆን እያልኩ እነዚህንም ለባርነት የሰጠኋቸው ልጆቼ ገጽጣቸው እየመጣብኝ ተስፋ በመቁረጥ ምነው አላህ ቶሎ በገላገለኝ በማለት በጸሎቴ የጠየኩበትም ቀን ነበር። እንደምንም በመጓተት መሣሪያ ከሚታደልበት ስንደርስ የጫናቸው በቅሎችና አህያዎቻችን ሲቀሩ ግመሎቻችንን አርደን በላናቸው።መሣሪያ ይዤ እንደመጣሁም አንዲት ጥይት በማንም ላይ ሣልተኮስ ከደጋው ተሸሽጌ በመውጣት ልጆቼንም እናቴንም አምጥቼ በደህና ላሰባሰብቸው ቻልኩኝ።ሚስት ማግባቱ ተቀዳሚ ዕቅዴ ስለነበር ያንንም አሟላሁ። ቢያንስም ቢበዛም በሃገሬና በቤተሰቤ መካከል ስለአለሁ ደስታ አለኝ።አሁንም የደርግ ቀለብ ተሰፈሪዎች የሚሰጣቸው እንዳይጓደልባቸው አልፎ አልፎ ጥይት ከሚቶኩሱብን ሌላ እኛ በራሳችን እነሣሽነት የምናደርገው ጦርነት የለንም። በእ ርግጥ ቀደም ሲል በሶማሊያ ወታደሮች ገፋፊነት የመንግሥት መልክተኞች ናቸው ብለን በምንገምታቸው ላይ ተኩስ ከፈትንባቸው አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ አደረግን። ከዚያ በኋላ ግን ረሃቡም ስለአጠቃን እኛም መሣሪያ ይዞ ሽቅብ ቁልቁል ማለቱ የሚያዋጣ መንገድ አለመሆኑን ተገንዝበን ወደሥራ ተሰማራን። እንደምታየው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በአሉት አካባቢዎችና የገበሬ ማሕበር በተቋቋመባቸው ሕዝቡ የእርዳታ ቀለብ እንደሚቀበል አይተሃል። እኛ ግን እስከአሁን ቀለብ ተሰፋሪ አልሆንም። ሰላም ኖሮን ጠንክረን ብንሰራ ፍቃዳች ነው።

የጦርነቱ ነገር በቅቶናል። ምክንያቶቹን በየአቅጣጫው ተመልክተናቸዋል። በሁሉም አቅጣጫዎች ጥቅም አለበት። ሁኔታው ሸቃባ ነው። የሶማሊያም መንግሥት እኛን የአንድ ሃገር ሕዝቦች ከጆቢር(አልቤን በለሳንጃ ጠመንጃ መጠሪያ)ጊዜ እስከ አሁኑ የአቶማቲክ መሣሪያ ድረስ እያስታጠቀን ለሃያ ዓመታት ሲያዋጋን የሃገራችንም መንግሥት በማንኛው አቅጣጫ ጉዳት በሕዝቡ ላይ እንደሚደርስ ከለማጤን ሁኔታውን በጥይት ለመፍታት ሲከር፤ ጦርነቱ እነሆ እስከአሁን ቀጠለ። የሚያሣዝነው ይህን በሃገር ላይ የሚደረገውን ለዘመናት የቆየውን ሴራ በግልም ሆነ በቡድን ራስን ጊዜንና የግል ፍላጎትን መስዋዕት አድርጎ እውነቱን ፈልፍሎ የጦርነቱን መንስኤ አውቆ ለሌላው የሚያሳውቅ ማጣታችን ነው። የጦርነት ዘመኖችን የትውልድ ዕድሜ መቁጠሪያ አድርገናቸዋል ይህም የአንድ ሃገር ሕዝቦች የቂም መያያዣ እንዲሆን የጠነሰሱት ጠላቶቻችን ያሰቡት ዓላማ ግቡን እንደመታላቸው ጥሩ ማስረጃ ነው። የሃገራችን ሁኔታ እየባሰ እንጅ እየተሻሻለ ባለመምጣቱ ለእኛም ለዚህ አካባቢ ሕዝቦች ከፍሙ ወደረመጡ እየሆነብን በወለፈኑ እንገረፋለን። የሚገርመው የሃገራችን መንግሥት ወንበዴዎች ሲለን መሣሪያ ያስታጠቁንም ወገኖች የነፃነት ተዋጊዎች በማለት ትውልዳችን ሊገለገልበት የሚገባውን የሃገር ሐብት እኛን በማሣሪያቸውና በሰጡን መጠሪያ ስም ዘብ አቁመውን የልጆቻችን ማሰደጊያ የሆነውን ጥሬ ሐብት ሲያግዙት ማየቱ ነው። ጐርበታችንም ቀኝ ገዥዎች የተውላትን የከፋፍለህ ግዛው መመሪያ በመጠቀም፤ከጥቅም ተከፋይ ከሆኑት ሃገሮች መሣሪያ በመቀበልና ለእኛ በማስተላለፍ ርስበርስ ስታዋጋን የሃገራችንም መሪዎች መንስኤውን መርምረው መፍትሔውን ከመፈለግ ይልቅ ሃገሬውን እንደጥፋተኛ ቆጥረው በጦርነት ለመፍታት መሞከሩ ሁኔታውን ለጀመሩት ከፍሎችና በሃገርም ውስጥ ለጸጥታ ተብሎ እበል ከሚከፈላቸው ግለሰቦች ሌላ ለሃገራችንም ሆነ ለዚህን አካባቢ ሕዝቦች የሰጠው ጥቅም አልነበረም አሁንም የለም።»



## ፵

የቃሲም ቤተሰቡ ቁጥር ሰምንት ሲሆን፤ የሚኖሩት ጣሪያቸው በሣር በተሸፈኑ ግርግዳቸው በጭቃ በተመረጉ ሁለት ጎጆዎች ውስጥ ሲሆን በመካከላቸው ያለው ርቀት ቢበዛ አምስት ሜትር አይበልጥም። በአንደኛው ውስጥ ሁለቱ ሚስቶችና ሴት ልጁ ሲኖሩበት፤ በሁለተኛው ውስጥ እናቱ፣ የመጀመሪያ ሚስቱና የሁለቱ ወንዶች ልጆቹ መኖሪያ ነበር። እርሱ ግን ተራ በተራ ከሁለቱም ሲያድር፤ እውነቱ ግን የራሱን መኖሪያ ጎጆዎን እስከቀልስ፤ከማማው ከእውሬ መጠበቂያው ማማ ላይ መኝታውን ያደርጋል።ምግቡ በየተራ ከእናቱና ፤ ከሦስቱ ሚስቶቹ ዘንድ እንዲመገብ ሆኖ በእርሻውና በእውሬው ጥበቃ ሥራ ቃሲምን ለመርዳት አብሮት ይሰማራል። ያም ሆኖም በአካባቢው አብዛኛው ሥራ የሚሠራው በሴቶቹ ስለሆነ የወንዱ ክፍል የሚሠራው ሥራ እስከዚህም አድካሚና ከባድ አልነበረም፤ ቢበዛ ዱሩን መንጥሮ በቆሎ መዝራት ሰብል እስከሚደርስ የማር ቀፎች መጥረብ ያንንም ቢሆን የሚሰሩት በእድሜያቸው ገፋ ያሉት አዛውንቶች ሲሆኑ የወጣቱ ክፍል ከሰማሊያ ያመጣውን መሣሪያ ተሸክሞ ሽቅብ ቁልቁል ማለት ምግብ የበሰለበት ወይም ጭስ የጪሰበትን ቤት ተመልክቶ ምግብ መጠየቅ፤ያንን ድርጊት አንዳንዴ ቃሲምም ቢሆን የትዳሩን ነገር ለሴቶቹ ተወት አድርጎት እንደአካባቢው ወጣቶች መሣሪያ ተሸክሞ ሽቅብ ቁልቁል ማለቱ አልቀረም።

ሴቶቹ ግን ትዳራቸው እንዳይፈርስ ከጠዋት እስከ ማታ ለቤት ውስጥ ሥራ ጎበስ ቀና ከማለታቸው ሌላ አንዲስ ጎጆ ተሠርቶ ግርግዳው ከተማገረና ጣሪያ ከተዋቀረ በኋላ ሣሩን አጭደው ጣሪያውን ሸፍነው ጭቃ አብኩተው ግርግዳውን መርገው እቤት የሚያስኙት እነርሱ ሲሆኑ፤ በዚያኑም ላይ ቡቃያው ማደግ ሲጀምር ለአረሙም ሥራ ተሰላፊዎች ናቸው። ወደቤት መለስ ያሉ እንደሆን ሕፃናትን በጀርባቸው እዝለው የምግብ እህልን በደጋይ ፈጭቶ የመመገቡም ተግባር የእነርሱ ነው። ሕፃን ማሣደጉ ሲታመሙባቸው የሃገር መድኃኒት አዋቂዎች ዘንድ መሯሯጡም ያው የሴቶቹ ሃላፊነት ሲሆን፤ በተለይ ሁለት ሕፃናት ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ አንደኛው አይኖቹ የምጪመጪና ሊጠፉ የደረሱ ሲመስሉ የሌለኛው ሆዱ የተወጠረ እግሮቹ ያበጡ ሲሆኑ፤ የቃሲምም ልጆች ቢሆኑ ከበሽታው ነፃ አልነበሩም።

ባል ከአባወራነት ሌላ ለቤተሰቡ እንድገትና እንክብካቤ የሚያደርገው አስተዋፆኦ በጣም ውስን ሆኖ፤የሚስቶቹ የቀን ልብሳቸው ሲያልቅ ተመልክቶ አስር ሜትር አቡጀዲ ለግልድምና ከላይ የሚጠለቅ ጥብቆ ለፀጉር መሸፈኛ ሻሽ(ጉፋታ) ሲገዛላቸው፤ የቀን ልብሳቸውን ሌሊት ልብስነት ስለሚገለገሉበት፤ ከባላቸው ጋር በቆጣቸው ላይ የሚጋፈፉት ያንኑ ነው።

አካባቢው ተፈጥሮ ያደለው ቢሆንም ሕዝቡ ግን በምን ዓይነት እንደሚጠቀሙበት ባለማወቅ ብቻ ለችግራቸው በአግባቡ ሊያውሉት አልቻሉም። ከቆረጡት ማር ካደለቡት ሠንጋ ፤ ከዱር ከሚለቅሙት ቡና ሸጠው ለችግራቸውን መዋያ ማድረግ ሲችሉ፤ ግን የመገናኛ መንገድ ባለመኖሩና አማካኝ የገበያ ሥፍራ ባለመከፈቱ፤ በወንበዴነት የስም ማጥፋት ዘመቻ ከአስተዳደሩ ክፍሎች በየጊዜ ስለተነዛበቻው፤፤ወደ ትልልቅ ከተማ የእርሻቸውን ውጤት አውጥተው ለመሸጥ በመፍራት፤ ከብቶቻቸውን የሚያደርጓቸው እየጠፋቸው እየረጁ ያልቁባቸዋል። በዚያውም ላይ የከብቱ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የግጦሹ ሥፍራ በመጥፋቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየቀነሰ በመምጣቱ በኑሮአቸው ወደታች ሲያቆለቁሉ እንጂ መሸሻላቸው አይታይም።የልጆቻቸውም ተወልደው ያለማደግ የሴቶችን አሰቃቂ ሁኔታ ያጤነው በለመኖሩ፤ መነሻውና መድረሻው የጠፋበትን ብሔረሰብ በመሆኑ የውሸት ፐሮፖጋንዳ በመንዛት አንድ የባዕድ ሃገር መሣሪያ እሲዘ ቢያዋጋውና ሐብቱን አግዞ በችግር ላይ ቢጥለው ጥፋቱ የማን ሊሆን ነው።?

እውነቱም የቃሲምን ቤተሰብ እንደመሞከሪያ በመውሰድ፤ ከሕዝቡም በይበልጥ ለመማርና የችግሩን መንስኤ ለማወቅ ጥረቶችን ሲያደርግ፤ የቃሲምን ልጆች ከሥራ መልስ ፊደል በማስቆጠሩን ንጽህናቸውን እንዲጠብቁ በማድረጉ፤እንደድና አንቧይ ባሉ ዕጽዋቶች ልብሳቸውን እንዲያጸዱ ሰውነታቸውን እንዲታጠቡ በመንገሩ ከዕለት ወደዕለት የጤንነታቸው ሁኔታ እየተሻሻለና ደስተኛ እየሆኑ መምጣታቸውን የተመለከቱት የአካባቢው ኗሪዎች ልጆቻቸው ሲታመሙባቸው ቃሲም ዘንድ ያለው ተማሪ መድኃኒት አዋቂ ነው በማለት ለሕመምተኞቹ እርዳታን እንዲያደርግላቸው ከቀየው እየመጡ ሲሰበሰቡ፤ እርሱም ቢሆን ምንም አይነት የሕክምና እውቀት ባይኖረውም፤ ካለው የወበ ከኒንና የራስ ምታት አስፒሪን ከመስጠትና ልብሶቻቸውን እንዲያነጹ ቢያንስ በሳምንት አንዴ ወንዝ ወርደው እንዲታጠቡ ከመንገር ሌላ ምንም ሊያደርግላቸው የሚችለው ነገር እንደሌለው ሲገልጽላቸው ፤ታመው የዳኑላቸው ቤተሰቦችም ትልቅ አክብሮትና ፍቅርን ያሳዩትል። በአካባቢው መሣሪያ ተሸክመው ሽቀብ ቁልቁል ከሚሉት ይልቅ ለእውነቱ ትልቅ አድናቆትንና አክብሮትን ቢሰጡት፤ የእርሱም ችግር ብዙ ያለማወቁ ሲሆን ሆኖም ግን በየዕለቱ በሚያደርገው ሁሉ ትልቅ ደስታ ተሰምቶታል፤

ይህ በዚህ እንዳለ የአጎት ተፈራን ሁኔታ እንድታጣራ የተላከችው የቃሲም ሚስት አሚና መርዶ ይዛ ወደአካባቢው በመምጣቷ የክሪስትያኖችን ሥነሥርዓት የሚያውቀው ቃሲም፤ ማታውን እንዳይነገረው ሸሸጎት ፤ በነጋታው ሊነገረው ወስኖ፤ ከማሣው እንዳለ ለአካባቢው ሕዝብ የአቶ ተፈራን መገደል ተገገሮአቸው በነጋታው ያለቸውን የሚበላና የሚጠጣ ነገር ይዘው ከቃሲም ቤት በራፍ ካለው ትልት ዛፍ ሥር ማልደው የሐዘኑ ተካፋይ ለመሆን ተሰበሰቡ።



ቃሲምም በማለዳ ተነስቶ ከአውሬ መጠበቂያው ጎጆ በመሄድ እውነቱን ቁርስ ተዘጋጅቷል በሚል ሰም ከመኝታው ቀሰቀሰት፤ወደቀዬ እየሄዱ ሳሉ ቃሲም ስለ አቶ ተፈራ እውነተኛ ክሪስትያነት ጠቅሶ፤«እውነተኛ ክሪስትያኖችና እውነተኛ እስላሞች ልዩነት የላቸውም። ግን የዘንድሮዎቹን ክሪስትያኖች አምኖ መቀበሉ ያስቸግራል። የእምነት ጥንካሬ የላቸውም። ቀደም ሲል እስላም ያረደውን ክሪስትያን አይበላም። እስላሙም ክሪስትያን ያረደውን አይነካም። ሆኖም ግን ያ ሁኔታ ያለንን ፍቅርና በአንድነት የመኖር ፍላጎታችንን አላናጋውም። ዘንድሮ ግን እግዚአብሔር የለም እስላሞችም ክሪስትያን ያረደውን ክሪስትያኖችም እስላም ያረደውን ብሉ የሚሉ መሪዎች ስለመጡብን የቀድሞቹ አበቶች ከእስላሙም ከክሪስትያኑም ወገን ያለውን መንግሥት በአንድነት ለመቃወም፤ አቶ ተፈራም ከብዙዎቹ ክሪስትያኖች ተነጥለው ይህ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ከሆነ ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው ቅኖሚአቸውን አደረጉ፤ በሰላምም በጦርነት ጊዜም አብረውን ኖሩ ። ለእስላሙም ሆነ ለክሪስትያኑ በአጠቃላይ ለአካባቢው ሕዝብ ትልቅ አስተዋፀኦን አበርክተዋል። ለምሳሌ የሶማሌ ወታደሮች ከሃገሬው ውስጥ ሠርገው በመግባት ርስ በርሳችን ከፋፍለውን የክርስትና እምነት ተከታይ በሆኑት ወገኖቻችን ላይ ቶክስ እንድንከፍት ሲቀሰቅሱን የቀድሞ ሽማግሌዎችን በመሰብሰብ የሶማሌዎች ተግባር የአንድ ሃገር ሕዝቦችን ደም ለማቃባት ስለሆነ በአንድነት መቃወም እንደሚኖርበት ሕዝቡን አሣምነው ሰላም በአካባቢያችን እንዲሰፍን ያደረጉ የሃገር ሽማግሌ ነበሩ። ሕዝቡ የደርግን አገዛዝ በአንድነት ተቃውሞ በመውጣቱ ሁኔታውን የባዕድ ሃገር ተጠቅሞበት እኛን እያዋጉ የሃገራችንን ንብረት ለአረብ ነጋዴዎች አሸገሮ ለመሸጥ ስለሆነ ለዘለቄታው የሚበጀንን ብናደርግ የተሻለ፤ነው። በማለት ሕዝቡ ነገሩን በጥሞና እንዲያስተውለው የግል ሐሣባቸውን ሲያቀርቡ የደርግም መንግሥት ቢሆን ነግ ተለዋጭ ሲሆን ቀሪዎቹ እኛው ነን በማለት ሕዝቡን አሳምነው ሠርጎ ገቦቹን እንዲያባርራቸው ያደረጉ ግለሰብ ነበሩ። ከዚህም እንደምታየው አንድም የደርግ ወታደር መጥቶ አልተዋጋም። በመንግሥትም በኩል ከሚያውቋቸው የጥንት ሽማግሌዎች ጋር በመገናኘት ብዙ ሰዎችን በወንበዴ ሰም ከመመታት ያዳኑ የአካባቢውም ሕዝብ ወደሰላማዊ ኖሮ እንዲመለስ ከሼህ ሞሐመድ ጋር ጥረት በማድረግ የደከሙ ሰው ሲሆኑ፤እንደማየውና ከቀድሞ ሁኔታ እንደምገመግመው በአቶ ተፈራ ላይ የሞት ፍርድ ያስፈጸሙት ክፍሎች በአካባቢው ሰላም እንዳይኖርና ከጦርነቱም ጥቅም ለማግኘት ጉጉት ያላቸው ጥቂት ስግብግብ ግለሰቦች መሆናቸውን አያጠራጥርም።» ቃሲምም እግር መንገዱን የአቶ ተፈራን ሞት ለእውነቱ አረዳው።

እነርሱም ከቀዬው ሲደርሱ የአካባቢው ሕዝብ በዛፉ ሥር በተነጠፉት ቁረበቶች ላይ ተቀምጠው፤ እውነቱም በተመደበለት መቀመጫ ሥፍራ ላይ ሲቀመጥ፤ ቃሲም እንደአረዳው ለተቀመጡት ሐዘን ደራሾች ገልጾ፤ ከሐዘንተኛዎችም ውስጥ በቅድሚያ እንዲናገሩ

የተጠየቁት የአካበቢው ሽማግሌ የተሰማቸውን መሪር ሐዘን ሲገልጹ፤ ወደፊትም ወደቀድሞው የሰላም ኑሮአቸው ተመልሰው ሰላማዊ ኑሮ የመኖር ተስፋቸው አጠራጣሪ እየሆነባቸው መምጣቱን በዚያን አጋጣሚ ሣይገልጡት አልቀሩም።

በአካባቢውም ሕዝብ ተመርጠው በሽምግልና የሚዳኙትና የሚያስተዳድሩት ሃጂ አህመድም ምርር ብለው «ከእንግዲህ እንደቀድሞው ኑሯችን ተመልሰን ቤተሰብ እንመሰርታልን የሚለው ተስፋችን ተቀጨ። አቶ ተፈራ ጥሩ አገናኝ ድልድያችን ነበሩ። የእኛንም ችግር በቅርብ አብረውን ኖረው ከፉውንም ደጉንም ያዩ ስለሆኑ እንደአንዳንድ አሰዋቂዎች በአፋቸው ሞልተው ወንበዴዎች ብለውን አያውቁም። የዚህን አካባቢ ሕዝብ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ከዚህ እስከሚደርስ በሚገባ ያውቁታል። ሁላችንም እንደምናውቀው ከአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው። እንደዚሁ እንደዘንድሮው በአካባቢው ተመድበው የሚመጡት አስተዳዳሪዎች ያልሆነውንና ያልተፈጸመውን ሁኔታ ለበላዩቻቸው በማስተላለፍ ሕዝቡን በወንበዴ ስም ሲያዘምቱበት ኖረዋል። እነርሱም በጸጥታ ስም የተመደበላቸውን ወጪ ለራሳቸው በመጠቀም ራሳቸውን ሲያወፍሩበት ከመቀየታቸውም ሌላ ሕዝቡ ያመረተውን ወደገበያ አውጥቶ እንዳይሸጥና ኑሮን እንዳያሸሽል መንገዱን በወንበዴ ስም ሲዘጉበት ቆይተዋል። ሕዝቡም ይህንን በደሉን ከዚህ አዲስ አበባ ድረስ በመሄድ አቤቱታውን ለማሰማት ቢሞክር ሳይሰካለት ቀርቶ የመከራ ኑሮው ሲመራ ከኖረ በኋላ፤ ውሎ አድሮ እውነት መውጣቱ አይቀርምና የአካባቢው እንቅስቃሴ መሪና ዋቆ ጉቶና አጼ ኃይለሥላሴ ፊት ለፊት ተገናኝተው፤ ጥያቄዎቹ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱላቸው፣ ክሊኒኮች እንዲቋቋሙላቸው መንገድ እዲዘረጋላቸው፣ የመንግሥት ግብር እንኳን ለመክፈል ገንዘቡን ተቀበሉን የሚሉትን ሃገሬዎች እጅ መሸ የሚጠይቁትን ባለሥልጣኖች እንዲያስወግዱላቸው ነበር። ንጉሡም ለዚህን ቀላል ነገር የሰው ሕይወትና ንብረት መጥፋቱ አስደንቋቸው መጠይቆቹን በተግባር በመተርጎም ሳሉ ሕዝቡም ወደሰላማዊው ኑረው ተመልሶ ኑሮውን በመምራት ላይ እንዳለ ንጉሡ ከዙፋናቸው ወረዱ ተባለ። የሕዝብ መንግሥት ሊቋቋም ነው ከእንግዲህን ጭቆና የለም ሲባል እኛም በደስታ ተቀብለነው ውጤቱን ስንከታተለው፤ መጨረሻው ይሄው እንደምናየው ነው። ንብረታችንን በግልጽ መውሰዳቸው ሲያስደንቀን በሕይወታችን መጡብን መሥራታችንም እንደወንጀል ተቆጠረ። ሕይወታችንን ለማዳን ፍትሕ ተጓድሎብናል በማለት ስም ያነሣነው ጦርነት እስከመቼ ይቀጥላል? በአስተዳደሩ መጥፎነት የተነሣው ጦርነት ተከሮ ለልጅ ልጆቻችን ተሳልፎ ርስበርሳቸው የአንድ ሃገር ልጆች እንዲዋጉ ፍላጎታችን አልነበረም።በኦሮመኛ አንድ አባባል አለ፤«ሞረድን ሞረደ ሙራ ጀናኒ፤ ሞረድኒ ሞረደ ኢሙሩ ሞረድኒ ኢፍ ወል ሙራ»።ሞረድን ሞረድ ይቆርጠዋል ተብሎ ቢጠየቅ ሞረድን ሞረድ አይቆርጠውም ግን እርስ በእርሱ ይቆራረጣል። ለዚህም ነበር ከአቶ ተፈራ ከሼህ ሞሐመድና ከሌሎች የሃገር ሽማግሌዎች ጭምር በየጊዜው



እየተሰበሰብን የሕዝቡንም አስተያየት በቅርብ እየጠየቅን ይህ ጦርነት እንዲቆም የጣርነው። ሆኖም በመንግሥት በኩል የተሾሙት ባለሥልጣኖች ከጥቅማቸው ሌላ የጠቅላላው ሕዝብ ችግር አልታያቸውም። ሁኔታውን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ያዩት ሲሆን፤ ያው ቀደም እንደነበሩት ባለሥልጣኖች የጸጥታ እየተባለ የሚሰጣቸውን አበል እንዳይታገድባቸው ለሰላም የሚጥሩትን ግለሰቦች እየወሰዱ መግደል የዕለት ተግባራቸው ሆነ። ይባስ ብለው ክሊኒኮች ከማቋቋም ይልቅ በአውራጃችን የወታደር ማሠልጠኛ ማቋቋማቸው በእርግጥስ ይህ ሕዝብ ሃገሩን አይወድም ለማለትና ከቀረው ሕዝብ ጋር ለማቃቃር ወይስ ሌላ ምክንያት አለው? አጭር ማስረጃ ለመስጠት የደርጉ አባል አሊ ሙሣ ለግድያ ካቀረባቸው አስራ ስድስት ሰዎች ውስጥ ሊቀበሩበት ከተዘጋጀው ጉድጓድ ላይ ሁለቱ ሰዎች አምልጠው ወደዚህን ከመጡ በኋላ እንደ ማንኛችንም ወደ ጎረቤት ሃገር መሄድ ሲችሉ ከሃገራችን ወዴትም በማለት ምህረት ጠይቀው ወደሰላማዊ ኑሮ መመለሳቸው ለሁላችንም ሰላም ለመፈለጋችን ጥሩ ማስረጃ በሆናቸው ነበር። ሕዝቡ የዚህን ያህል በሰላም መኖርን ሲፈልግ፤ ምን ያደርጋል እንዱን ሰላም ፈላጊውን ጓደኛችንን አጥተናል። እግዚአብሔር ነብሱን ይማረው በማለት ነገግራቸውን ያቆማሉ።»

ሃጂ አህመድ ባለብዙ ንብረት ስለነበሩ፤ በአቆርቃዥ ስም ተወርሰባቸው አንድ የእህል ወፍጮ ሲቀራቸው ያንንም ወስደውት በአቆርቋዥ ስም ሊያስሯቸው ሲፈልጓቸው ከበረሃ የገቡ ሲሆን፤ እውነቱም የልጆቻቸው አስተማሪ ስለነበረ በሚገባ ያውቁታል። ቁምጣውንና እጅጠባቡን ለብሶ ከአጎቱ ሐዘን ተቀምጦ በመጀመሪያ ሲያዩት የተናገሩት ነገር ቢኖር «ይበላችሁ እናንተ ያመጣችሁብን መከራ ነው ለእኛም የተረፈን።»

እውነቱም ለእሳቸው ትልቅ አክብሮት ሲኖረው፤ያም ይኖርበት በነበረው ክፍለሃገር በአጠቃላይ ከሚገኙት አስራ አምስት ሺ ተማሪዎች ውስጥ አንድም የእስልምና ተከታይ የሆነች ልጃገረድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አልጨረሰችም።ይህም እስከ ፲፱፻፷፯ ዓመተ ምህርት ድረስ ያለው ዝርዝር ሲሆን፤ግን ሃጂ አህመድ እውነቱ በሚያስተምርበት የገጠር ትምህርት ቤት የእሳቸው ልጅ በመማሯ የሃይማኖቱ ተከታዮች ተጽኖ ቢያደርጉባቸውም ተቋቁመው በማስተማራቸው ከትምህርት ቤቱ ተልቅ ሽልማትን የተቀበሉ ግለሰብ ከመሆናቸው ሌላ የሕብረተሰቡን ችግር ዘወትር ለመፍታት ቀደምትነትን የሚሰጡ ስለነበሩ በአካባቢው ትልቅ ተደማጭነት ነበራቸው። በጊዜውም በሚያስተዳድሩት አካባቢ ምንም አይነት ተቃውሞም ሆነ ቅሬታ ከሕዝቡ አይሰነዘርባቸውም። በአካባቢው ምንም ዓይነት ወንጀል አይፈጸምም ማለት ይቻላል። ቢፍጸምም እንኳን ከሽማግሌዎች ዳኝነት አያልፍም።

የአካባቢው ሕዝብ በየምክንያቱ ሲገናኝ ከልማት ሥራ ይልቅ እንስተው የሚወያዩት የሰላሙን ጉዳይ ሲሆን፤ ተረጋግተው እንደይቀመጡ በየቀኑ የሚደረገውን በውል ስለማያውቁት፤ ኑሮአቸው

በአጠቃላይ በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተ ነበር ለማለት ብዙም ማስረጃ አይሻውም። ቆርጠውም እጃቸውን ሰጥተው ወደሰላማዊ ኑሮ የተመለሱትንም ቢሆን በየምክንያቱ እየከበቡ እየተከሱ ሲገሏቸው፤ እነርሱም ከያዙት መሣሪያ ጋር እንዲገቡ ተደርጎ ስለነበረ ሲተኩሱባቸው ምላሹን ላለመስጠት መሣሪያቸው ጥይት ጎርሶ ሳለ ሳይተኩሱ እየተገደሉ ሬሣቸው ሲቃጠል፤ በሌላ አኳያዎች እጃቸውን ሰጥተው የሰላማዊ ኑሮ ለመኖር ከክፍለሃገሩ ጽሕፈት ቤት ሲሄዱ «ቀደም ምን አይታችሁ ወጣችሁ አሁንስ ምን አግኝታችሁ ተመለሳችሁ» በማለት የሚያቄሙባቸውን ባለሥልጣኖችን በመፍራት በሌላ ወንጀል ተጠምጥሞባቸው ከመታሰርና ከመገደል ተመልሰው ከበረሃ ሲገቡ፤ እነዘው ባለሥልጣኖች ወንበዴዎች ናቸው በማለት ጦር እንዲዘምትባቸው ያደርጋሉ። ከልማት ይልቅ የወታደር ማሠልጠኛዎች እንዲቋቋሙ ለበላይ የሁኔታውን አሳሳቢነት ያቀርባሉ። ትክክለኛ አስተሳሰብ ያላቸው መሪዎች ቢኖሩ ኖሮ ሁኔታው ቀላል ነበር። ለጦርነትና በስግብግብነት ለግል የሚወሰደውንና ለቅጦት የሚውለውን የግብር ገንዘብ ወደልማት ቢለወጥ የሕዝቡ ኑሮው ቢመቻችና ቢሻሻል ከደሀናው ኑሮው ላይ ተነስቶ ጦርነት የሚያነሣ እብዘም አይኖርም። አማራጭ ሆኖ የተወሰደው ግን በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የነበራቸውን ክፍሎች እየፈለጉ መግደል ሲሆን ያም የጠቀመው መሣሪያ እያቀበሉ የሃገሪቱን ሐብት ለሚያግዙት ብቻ ነበር። ምን ያደርጋል «ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል» ተብሎ የል?



## ፺፩

ለቅስ ደራሹ ሕዝብ ከተበተን በኋላ አሚና እውነቱን ከጎጆው ውስጥ ጠርታ የተሰከለትን ደብዳቤና ገንዘብ ስትሰጠው፤ ደብዳቤውም የተላከው ከወይዘሮ ልክየለሽ ሲሆን፤ይህን ይመስላል፤ ውድ ልጃችን እውነቱ መለያየት ክልል ውስጥ ከተወሰንበት ዕለት እንስቶ ለጤናህ እንደምን ከርመሀል? አዲሱ አካባቢ ተስማማህን? አሚና እንደነገረችን ሰውንም አከባቢውን በጣም እንደወደድከው ነው።

ልጄ በእኛ ቤተሰብ ላይ የደረሰውን አደጋ ልገልጽልህ እወዳለሁ። እንደምታውቀው አጎትህን በዚያን ውድቅ ሌሊት ከቤት አስረው እንደወሰዷቸው ከክፍለሃገሩ እስርቤት ጨመረዋቸው፤ከዚያንም የማሰድጋቸውን ልጆች ትፍረድንና እንዳርጋቸውን ለጎረቤት ትቻቸው የአጎትህን መጨረሻ ለማየትና ስንቅ ለማቀበል ከእህትህ ከጦቢያ ዘንድ ሄድኩኝ። ከዚያንም ለሁለት ሰምንታት እየተመላለስኩ ስጠይቃቸው ቆይቼ በኋላ ግን አዲስ አበባ ሄደዋል ተባልኩኝ። እውነቱ ግን አጎትህንና ሌሎች ስድስት ሰዎችን ጨምረው ከወታደሮቹ ካንፕ ዝቅ ብሎ ጥንት ገና ከምትጫወቱበት መስክ ላይ ጉድጓድ ተምሶ በጥይት ተደብድበው እንደቀበሯቸው ዘግይቶ ተነገረን። የአጎትህ ነገር በዚህ አከተመ። የሚገርመው የእቶ ተፈራ አባት ሃገሬ ብለው በአርበኝነት በሞቱበት አከባቢ ልጃቸው ባልባሌ ሰዎች ያውም በወገን እጆቻቸው የፍጥኝ ታስሮ መገደል የዘላለም ፀጸቴ ነው። የተያዙ ዕለት የሰላማዊ ሰው ነፍስ ያጠፋሉ ብዬ በመፍራት መሣሪያቸውን ከአስቀመጡበት መሸሽጌ ሌላው ሐዘኔ ሲሆን፤ ምነው እንደአባቶቻቸው በቀያቸው ተታኩሰው በሞቱ ኖሮ? ምን ያደርጋል ይህ የወገንና የሃገር ፍቅራችን ለአንዳንድ አላዋቂዎች ፍረሃት አስመሰለብን። ከጦቢያ ዘንድ ሐዘን መቀመጡ አስፈርቶን ዘመዳሞችና አብሮ ኗሪዎቻችን በግልጽ ለማዘን ከቤታችን ከቆላው ወረድን፤ በእዝን ላይ ተቀምጠን ሳለ ንብረታችን በሙሉ በመንግሥት እንደተወረሰ ተነገረን፤ የሚያዝበትም የወረዳው የገበሬ ማሕበር ስለሆነ ከማሣው ዝር እንዳንል ማስጠንቀቂያ ተሰጠን።የእርሻ በሮቻችንና የጥገት ላሞቻችንን ከተሰማሩበት ነዷቸው። ግታቸው የወጠራቸው ላሞቻችን እምልጠው ወደቀያችን ቢመጡም ጥጆቻቸውን እንድንለቅላቸው ተጠይቀን ይዘዋቸው ሄዱ።

ልጄ የደረሰብንን መከራ ምኑን ጠቅሼ ምኑን እተወዋለሁ? በጣም የሚቆጨኝ ነገር ቢኖር ምነው ያን ዕለት የአጎትህን ጠብመንጃ ይዘህው በሄድህ ኖሮ? ምን ያደርጋል ከነሙሉ ትጥቃቸው ወሰዱት። እኔም በሴት አቅሜ ያለአንዳች አጋር ቀረሁኝ።አልሰጥም ለማለትስ ምን አቅም አለኝ? የደረሱት ልጆቻችን የጨው ዘር ሆኑ። በየሃገሩ ተበተኑ። እኔን ሴቷን ልጅ በግላጭ አገኙኝ። የዚያን ጅግና ብረት በመወሰዳቸው ልባቸውን ተራራ አሰከሉት። ጎበዝ ከግድያ ሌላ ብዙ የሚሰራው ሥራ እንዳለ ባውቅም። በጊዜው ሁኔታቸው እናደደኝ። እውነቱ ልጄ ደጋግመን ብናወራው ብንጽፈው ሁሌ ያው ነው። ይህንን ተወት ላድርገውና ለዘለቄታዬ ምን ማድረግ እንዳቀድሁ

ልገልጽልህ እወዳለሁ። በመጀመሪያ ያሳደግናቸውን ልጆች ለየወለጆቻቸ ሰጥቼ ከጦቢያ ዘንድ ለጥቂት ወራቶች እከርማለሁ። ከዚያንም ከወንድሟ ደብዳቤ ጽፌለት እንዲወስደኝ አደርጋለሁ። አባቶቻችን ከአቋቋሙት ደብር ገብቼ በመሎክሴነት ለመኖር ወስኛለሁ። ከእንግዲህስ ምን ዓለም አለኝ? ይገርምሃል የተፍረድ ፀጉር ከአሁኑ ቅጫም አፍርቷል።እንድአርጋቸው ከጎረቤት ልጆች መጫወቱን አቁሟል፤ ከቤት ጥቅልል ብሎ መተኛት ሆኗል፤ለጊዜው ጎረቤቶቻችን የሚጠጡትን ወተት እያመጡለቸው ቢቃመሱም፤የምግብ ፍላጎታቸው ቀንሷል፤ ሌት ላይ ከፉኛ ይበንኑብኛል፤ የጤንነታቸው ሁኔታ በጣም አስገቶኛል፤ምን ማድረግ እችላለሁ? አንተም ብትሆን ከእንግዲህን ሌላ ዘመድ የለህም። ዘመዶችህ አብረሃቸው የምትኖረው ሰዎች ስለሆኑ አክብሮትና ፍቅር ይኑርህ። ከእንግዲህን እኔና አንተ የምንገናኝ አይመስለኝም።ያው እንደሞቱት አጎትህ ቶጥሬህ አዲሱን ኑሮዑን እጀምራለሁ።የተሻለ ቀን ሲመጣ የአጎታችሁን አስከሬን ጅብ ካልበላው ከቀሩት ሰዎች ጋር በመተባበር ጦቢያ ከአቋቋሙት ቤተክረስትያ ከቅዱስሚኬኤል ደብር እንድታስቀብረው እነግራታለሁ። ምን ያደርጋል በአቋቋሙት ቤተክረስትያን ሳይቀበሩበት ቀሩ።አንተም ያሰብከው እንዲሳካልህ በጸሎቴ እሰበሃለሁ። አንተም ሞራልህን ጠብቅ እኛንም እርሰን በየጊዜው ስለእኛ የምታሰላሰል ከሆነ ምንም ነገር ማድረግ አትችልም። ለሁሉም ለጥቂት ቀን ቀለብ ትሆንህ ዘንድ ገንዘብ በአሚና በኩል ልኬአለሁ። አብረሃቸው ተከፈላት።ዘመዶችህ በሙሉ ሰላምታ ያቀርባሉ። ይህንንም ደብዳቤ የከተበችው እህትህ ጦቢያ ናት። ሰላም ትልሃለች። ደህና ሁን ልክየለሽ።

በወቅቱ ሰዎችን በየምክንያቱ መምታት የቀኑ ትዕዛዝ ነበር። ለእውነቱም ቢሆን አዲስ ነገር አልነበረም። ዘመዶቹንና ጓደኞቹን ከኋላው ትቶ ሽቅብ ቁልቁል ይል የነበረው እነዚህን ሁኔታዎች ዝም ብሎ ለማለፍ ሒሊናው ስላልፈቀደለት ብቻ ነበር። በወቅቱ በማንኛውም አከባቢ የተለየ ነገር የለም። ከቦታ ቦታ በሰላም ሠርቶ መኖር አይቻልም። በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ችግሩ አብዛኛውን የሕብረተሰቡን ክፍል ነክቶታል። ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ የማንኛውን ቤተሰብ ሆነ በአጠቃላይ የሃገሪቱን ሕዝብ ከትልቅ ችግር ውስጥ መውደቅ ምንም የሚያጠራጥር አልነበረም።በረሃብም ሆነ በጥይት ተመቶ መሞት ምንም ልዩነት የለውም። የሚመጣውን ገምግሞው በግንባር ቀደምትነት ሐቁን በመናገራቸውና በተግባር በማሣየታቸው የሞት ጽዋ ቢቀምሱም ፈፃሚዎቹ ግፋን በጥፍ ከትውልድ ይቀበሉታል። ያንንም ከአለፈው መማር ይቻል ነበር። ከፉ ሥራ በሰሪው ላይ ብቻ ተወስኖ ቢቀር መልከም አልነበረም? ግን ውሎ አድሮ የራሱንም ቤተሰብ ያጠቃልላል።ረሺያኖች ጥሩ አባባል አላቸው«ሰው ምራቁን ከሚጠጣ ውኃ ውስጥ አይተፋም ይላሉ።»በተለይ የደርግ አባሎች እየተባሉ በየክፍለሃገሩ የሚላኩት ግለሰቦችን ያየ እውነትስ ቀደም ሲል ይተረከላት የነበረችው ኢትዮጵያችን እነዚህን መሰል ሰዎች አቅፋ ይዘ ኖሯልን? የሚያሰኝ ነበር።አንዳንዶቹም አስተዳደጋቸውንና የቤተሰባቸውን ሁኔታ



ነጸብራቅ ነው በማለት አስተያየታቸውን ሲሰጡ የቀሩትም አስከዘሬ ሲለፋበት የነበረው የሥራ ውጤት ነው በማለት ሥርዓቱ ላይ ትችታቸውን ያቀርባሉ። ቀደም ሲል ሕዝቡ የመናገርና የመፃፍ ዕድል ኖሮት አጥፊዎችን በግልጽ ቢወቅስና መልከም ሰሪዎች የማመስገን መብቱ ተጠብቆ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ አበሳ በሕዝባችን ላይ ባልደረሰ ነበር በማለት የሚቆጩም ነበሩ። አሁንም ችግሩ ሃገር አቀፍ ስለሆነ በአንድነት መፍትሔዎችን መፈለግ የሃገሬው ሕዝብና ነገሩን በሚገባ የሚያውቁት የሃገሪቱ እውነተኛ ዜጋዎች ተግባር ነው።

የበላዮችን ለማስደሰት ገራ እጅን አንስቶ መፈክር ማሰማት ወይም በየጊዜው የሚነሱትን መሪዎች ፎቶ በትልቁ ሰቅሎ መሰለሙ የደርግ አባል ከሆነ ማጎብደዱ የጠየቁትን ሁሉ እንዲወስዱ መፍቀዱና ነፍሴን አትኩ በማለት መኖሩ አሁን ሃገራችን ከአለችበት ችግር ለመውጣት ፍጹም መፍትሔ አይሆንም።ለደርግ አባል ለጠጅ ማሩን ለፉሲካ ሙኩቱን ከአዲስ አበባ መጫኑ ዛሬን እንድንውልበት እንጂ ሃገር ለመገንባት ቤተሰብ ለመመስረት የሚመጣውን ችግር ለመቋቋም ፍጽሞ አስተዋፅኦ የለውም።መሪዎቻችን ግን የወገን መሸሸል የሚለው ንግግር ጆሮአቸውን እንዲነካው ፍላጎታቸው አይለደም። ይህ ባይሆን ኖሮ እንደአቶ ተፈራ ያሉትን ሃገርና ወገን ወዳድ ከየአከባቢው ተነስተው ለሃገር የሚበጀውን ሐሳብ ሲያቀርቡ መግደሉ እድሚአቸውን ማሣጠር እንደሆነ አይረዱትም።

በአጠቃላይ መሪዎቹ ማንኛውም ጉዳይ የሚመለከቱት ከግላቸው ጥቅም አንፃር ስልሆነ ጥሩ ሐሣብ ወይም መልከም ሥራ መጥፎ ተግባራቸውን የሚያስለውጣቸው አይመስልም።የዚያኑ ያህል ከሥራቸው ሆነው ልክ ናችሁ የሚሉ አልታጡም። ግን ሁኔታዎች ሲመቻቹላቸው የሉም። እንደማንኛውም ሰው መኩነናቸውን ያደርጋሉ፤ ይህም በቀንድ ሲወጉ ቶይቶ በጭራ የመደሰሱ ሁኔታ መታሰብ ያለበት ነው። ግለሰቦች ለራሳቸው ሊዋሹ ሊያጠፉ ይችላሉ ግን ለቤተሰባቸውና ለሃገራቸው ሰው ምን ተናግረው ያሳምናሉ? የራሳቸው ልጆችስ በምሳሌነት ሊከተሏቸው ወይስ ሊኮንኗቸው እንግዲህን በየአቅጣጫው ተመልክቶ ዘላቂነት ያለውን መንገድ ለመከተል የግለሰቦች የግል ውሳኔ ነው። ማንኛው ሰው ከማያምንበት ነገር በላይ ሊሰራ አይችልም። ከከበደው በራሱ ውሳኔዎችን መውሰድ ሲችል፤ አልፎም የሌላው ሕብረተሰብ መብት ሳይነካ ራስንም ቤተሰብን ማዳን ሲቻል፤ ግን ልክ ኖት ሲሉ ቶይቶ ልክ አይደሉም ማለቱ ሒሊናዊ ወቀሳን ያስከትላል።ለዚህም ነበር አባት ሽማግሌዎች በየቦታው ምንም የተሸሸገ የኋላ ጥቅም ሳያታልላቸው በባዶ እግራቸው እየሄዱ የመሬት ግብራቸውን እየገበሩ በአፃፉው በጥይት እየተደበደቡ እንዲሞቱ የተደረገው። «ጭራ ራስን ይከተላል።» ከላይ እውነተኛ መሪዎች ቢኖሩን ኖሮ ከታች ያሉት እንደአቶ ተፈራ ባሉ ግለሰቦች ላይ የዚያን አይነት ግፍ ባልፈጸሙ ነበር።

## ፵፪

እውነቱም ወይዘሮ ልክየለሽ እንዳሉት ያለፈውን ሁኔታ ማስለሰሉን ትቶ አዲሱን ኑሮውን ከሕዝቡ ተቀላቅሎ ሲመለከተው፤ ቀድሞ ሲል እንደተነገረው በእርግጥም በጣም ደግ ሕዝብ ነው። በእርግጥ ቀደም ሲል እርሱን መሰል ሰው ባለማየታቸው መጠራጠራቸው አልቀረም። ሆኖም ግን የአቶ ተፈራ ዘመድ በመሆኑና ሃጂ አህመድ ያውቁት ስለነበር ብዙ ችግር አልገጠመውም። ሕዝቡ ግን ከጥንት ጀምሮ በጦርነት ላይ የኖረ ስለነበር ከከተማ የሚመጣን ሰው በሙሉ እንደሰላይ ስለሚቆጥሩት ብዙም ከአዲስ መጥ ጋር ገበናቸውን ገልጠው አይወያዩም። ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ ሕዝቡ ተደላድሎ ተቀምጦ አያውቅም። ከአስተዳደር ጋር ግንኙነት የነበራቸው የቀድሞው ባላባቶች ምንም እንኳ ከእነርሱ ውስጥ የወጡ ቢሆንም ባራበራስና ግራዝማችነታቸውን ከአገኙ የቡና መሬታቸውን በቅርብ ለሚገኙት ባለሥልጣኖች ሲሰጡባቸው የደለቡ ሠንጋቸውንም በግብር ስም ሲያሸግቻቸው፤ከእነርሱ ጋር በሥራ ሞያቸው የማይመሳሰሉትን ሕዝቦች ከሌላ አካባቢ አምጥተው በማስፈር ቅራኔዎች በመፈጠራቸው ሲዋጉ የኖሩ ስለሆነ እንብዛም ከከተማ የሚመጣን ሰው በልብ ሙሉነት አይቀበሉትም። ከለውጡ በኋላም ቢሆን እነዚያው የቀድሞ ባላባቶች የደርግን መጥፎነትና ሃይማኖታቸውን የሚያስጥል መንግሥት መሆኑን ሲነግሯቸው ጀሃድ ብለው ጦርነት ሲያነሱ፤ መሪዎቹ ግን ከጎረቤት ሃገር ተቀምጠው መሣሪያ እየላኩ የሚያዋጓቸው ሲሆን ጠላትና ወዳጃቸውን ጠንቅቀው አያውቁም። በመንግሥት በኩልም አካባቢውን እንዲያስተዳድሩ የሚላኩትም ቢሆኑ ከባላባቶቹ ያነሰ እንጂ የላቀ የአመራር ችሎታ የላቸውም። የባላባቶቹ አሸጥርና የጎረቤት ሃገርን የውሸት ፕሮፖጋንዳ ለምን እንደሆነ ጠንቅቀው አያውቁትም። በወቅቱ ችግሩን እንዲያዩ ይላኩ የነበሩትም የደርግ አባሎች ሕዝቡን በየቦታው እየሰበሰቡ ፉከራና ያላቸውን መሣሪያ ጥራት ማውራት እንደጦጣ ዛፍ የሚወጣ መሣሪያ እንዳላቸው መፎከሩ፤ በሚነድ እሣት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር እንጂ መፍትሔ እንደሚያመጣ በምን ዓይነት እንደገመቱት አይታወቅም። ትልቁ ስህተት ጦርነትን ያህል ነገር ያውም በራስ ሕዝብ ላይ ሲታወጅ የሚያዋጣውንና የማያዋጠውን መርምሮ ማየት ሲኖርበት በአንዳንድ የፖሊስ ጣቢያ አዛዦችና የወረዳ አስተዳደሪዎች በተሰበሰበ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ መሣሪያ በሃገር ሕዝብ ላይ ማንሳቱ ከድንቁርና ሌላ ምንም የሚሰጥ ቃል አይኖርም።

እውነቱ ከሕዝቡ ውስጥ ሆኑ እንደተረዳው «ከቀድሞ ጀምሮ በዚያ ሕዝብ ላይ ይካሄድ የነበረው ጦርነት የራሱን ድክመት ለመሸሸግ የተደረገ እንጂ ሕግ ወጥ ድረጊት ወይም የሃገሪቱ ልዕልና ተደፍሮ አልነበረም። አንድ ስለብሔረሰቡ ትክክለኛ ጥናት ሊያደርግ የሚችል ግለሰብ በአካባቢ ለጥቂት ዓመታት ተቀምጦ የሕዝቡን ፍላጎት መርምሮ ጥናት አቅርበበት በዚያን መስመር እየተመረመረ ቢሰራ ኖሮ አንድ ጥይትም የሚያስተክስ ምክንያት አይሮርም የሚያሰኝ ነበር።



ከከጎረቤት ሃገር አስራ አምስት ቀን ገዘ ላይ የሚገኝና ከክፍለሃገሩ ዋና ከተማ የአንድ ቀን ጉዞ በሆነበት አካባቢ እንደአያል ጦር አደርጎ መሣሪያ ለማሣት መሞከሩ ከፍረሃትና ድርቁርና ሌላ ምንም የሚሰጥ ማስረጃ የለም። እንግዲህን አንዴ ጦር በሕዝብ ከዘመተበት በኋላ ለሚደርሰው ጥፋት ከሃገሪቱ መሪዎች ሌላ ማንንም አያስጠይቅም።»

የሃገራችን መሪዎችም በሕዝብ ለሚነሱት ቅዋሜዎች መልስ መስጥት ያለመቻልና ሥልጣን ላይ ለመቆየት ካላቸው ፍላጎት አንፃር በተፈጠረው የርስበርስ ጦርነት የጎረቤት ሃገሮቻችን አገጣሚውን ቢጠቀሙበት በራስ ከማዘን ሌላ አልፎ ተርፎ ሌላውን ባዕድ ሃገር መውቀስ አይቻልም። ለምሳሌ የሶማሌ መንግሥት ከጥንት ጀምሮ ለዚህን አካበቢ ሕዝብ መሣሪያ ሲያስታጥቀው ቆይቷዋል። የጣሊያን መንግሥት ኢትዮጵያችንን ለመውረር በሶማሊያ አከማችቶት ከነበረው አልቤኔ ባለሣንጃ እስከዘመናዊው አቶማቲኩን የሬሺያኖችን መሣሪያዎች መታጠቅ ደረጃ ደርሰዋል። የሶማሊያም መንግሥት ያለምክንያት እነዚህን ሕዝቦች ሲያስታጥቅ አልኖረም። በአካባቢው የሚገኘውን የደለበ ሐብት በየጊዜው ከሚመላለሱት ነጋዴዎች ተረድተው ከፍተኛ ጥናት አድርገውበት እንደሚያዋጣቸው ከተገዘቡ በኃላ ወዳጅ ከሆኗቸው የአረብ ሃገሮች ጋር በመተባበር ያልሆነ የነፃነት ስም በመስጠት የሃገሪቱን ሰላም ከማወክ አልፈው ንብረቱን ሲያግዙለት፤ የሃገራችን መንግሥት ያልደረሰበትን የሐብት ክምችት ያለበትን ሥፍራ ደርሰውበት፤ ቀስ በቀስ የራሱን ቋንቋ አስጥለውት የሶማሊኛና የአረበኛ ቋንቋዎችን እንዲናገር ተጽኖ ሲያደርጉበት፤ ከቅኝ ገዥዎች በተማሩት የከፋፍለህ ግዛው ዘዴያቸው ተመርተው በውስጥ ሃገር ሽብር ሲያስነሱ፤ የሃገራችን መሪዎችም በሕዝቡ ላይ ተከስ ሲከፍቱ የሶማሊያ ነጋዴዎች ገንዘባቸውን በግመል ጭነው ከሥፍራው ከተፍ ነዋ! ሕዝቡ ንብረቱን ሸጦ መሣሪያ ለማምጣት ከሃገራቸው እንደሚሄድ ስለሚያውቁ በርካሽ ከብቶቹንና የእርሻ ምርቱን ለመግዛት ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብር የሶማሊውን ሽልግ በዓለም አቀፍ ምንዛሬ ስድስት ጊዜ የሚበልጠው በዚያን አካባቢ መሣ ለመሣ ሆኖ፤በኢትዮጵያ አራት መቶ በር የሚሸጠው ግመል በሶማሊያ ሽልግ አራት መቶ ያወጣል። ከሶማሊያ ጠረፍ ሲደርስ ግን እስከ አራት ሺ የሶማሊያ ሽልግ ተሸጧል። የሶማሊያ ነጋዴ ለተቀባዮቹ ለአረብ ነጋዴዎች ከዚያን በላይ ይሸጡታል። በወቅቱ የደቡበ፣ የደቡብ ምዕራብና የምሥራቅ ክፍለሃገራት የቀንድ ከብቶቻችን ከአዳማ ገበያ ከመዋል ይልቅ ከሐመር ሆኖል። በልዋጩ ግን ጠብመንጃና ጥይት ሲገበ፤ በአንድ ብር እስከ ሃያ ጥይት መግዛት ሲቻል፤ ከቀበሌ እንደምንም እምልጦ አንድ ኩንታል ስኳር ከአካባቢው ከደረሰ ከሁለት ሣጥኖች በላይ ጥይት ሲለውጥ፤ ዋናውን ጠብመንጃ ግን ከሶማሊያ ሄደ ማምጣት ግዴታ ነው።

እውነቱም ለዚህን ሁሉ ድርጊቶች ምክንያቶቹ ምን እንደሆኑ ቃሲምም ሲጠይቅ፤ እርሱም ፈገግ ብሎ «በእርግጥስ አንተ ምክንያቱን አጥተህው አይደለም፤ ሆኖም የአስተዳደሩ ደካማነትና የግለሰቦችም

ጥሪት ያለመደረግም ነው፤ እለለሁ። እናንተም መማራቸሁ ሃገራችሁን በሚገባ እንድትገለጿት ሲሆን ከከተማ መውጣትን እትሹም እንገዲህን ሰማሊዎች ጠረፍ ጥሰው እስከእልመጡና ሕዝቡም እስከ እልተቀሰቀሰ ደረሰ ውስጡ ገብቶ ከለማጥናትና ከለመመርመር የመጣ ውጤት ነው። ፈደል ቆጠርኩ የሚል ሰው ወደዚህን አከባቢ ሲመጣ እንተ ሁለተኛው መሆንህ ነው። ቀደም ሲል ግለሰቦችም በመንግሥት ተረድተውም ሆነ በራሳቸው እነሳሺነት አከባቢውን አጥንተው ሕዝቡ ምን እንደሚፈልግና ምድሪቱ ምን እንደምትሰጥ ጥናቶችን ያከናወኑ ክፍሎች አልነበሩም። የአከባቢው ሕዝብና የአስተዳደሩ ክፍል የሚተዋወቁት መሣሪያዎችን በመለዋወጥ ብቻ ነበር። እንግዲህን የተማረውም ክፍል ጠሪት ከማድረግ ተቆጥቦና የተሽሞነሞነ ነገር ፈልጎ መንግሥትም ቅዋሜዎችን በመሣሪያ ለመፍታት በመሞከር ውጤቱ ይህው እንደምታየው ሊሆን ችሏል። በሌላ አቅጣጫ ሕዝቡ ንብረቱን የሚነካበት አይወድም፤ይህ የማንኛችንም ፍላጎት ነው።ይህንንም እውጥተው እንዳይናገሩት አስቀድሞ ወንበዴነታቸው ተገልጾ ያለ ስለሆነ በግልጽ ለመወያየት መንገዱ አስቀድሞ በመዘጋቱ፤እንዴትስ ችግሮች ሊፈቱ ይችላሉ? እንደምታየው ሕዝቡ ከዚህን አከባቢ ውጭ ለሆነ ሰው እምሮ ችግሩን መግለጽ አይፈልግም። ሌላው ቀርቶ ከደጋው ክፍል ከመጣነው ክፍሎችና በቆለኛው መከከል ያለመተማመን አለ። ሆኖም በትግዕስት ለተከታተለው ልዩነቶቹ ብዙ የሚያራርቁ አይደሉም። እንተም ስለሕዝቡ ዝንባሌ በውል ለማወቅ ከፈለክ ጥያቄ አታብዛባቸው።እውነተኛ መልስ በቀላሉ አትጠብቅ።ማድረግ ያለብህ የሚያደርጉትን የሚናገሩትን በትዕግስት አዳምጥ፤ ተመልከት።ትግዕስት ያስፈልጋል። በአጠቃላይ በግልም ሆነ በድርጅት ሕዝብን አጥንቶ ፍላጎቱን ለማወቅ ብዙ ውጣ ውረድን የሚጠይቅ ሲሆን፤ ፍላጉቱ ከታወቀ ግን ይህ የምናየው ከገራ ከቀኝ ወደሕዝቡ የሚዘምተው ወታደር ቆሞ፤ ሕዝቡም በራሱ ተሰትፎ በወጣው መመሪያ ራሱን መርቶ፤የጐረቤት ሃገራችን የውሸት ፕሮፖጋናዳ ሥፍራ ያጣል። ሕዝቡ ወስጥ ውለህ ስታድር ብዙ ፍላጉቱን ማወቅ ትችላለህ። የሰማሌን ሠርጎ ገቦችንም ቢሆን እምኖና ወደ የተቀበላቸው እንዳይመስልህ። ሠርጉ ገቦቹንም ቢሆን ከከተማ ከድሬዎች ነጥለህ የምታያቸው እይደሉም። ዘራፊዎች ናቸው፤ በእጅህ ላይ ጥሩ ነገር ከአዩ ወደህ መስጠት ያለበለዚያ ትነጠቃለህ።የእኛም ልጆች ከነዚህ ሠርጎ ገቦች ብዙ መጥፎ ተግባሮችን ተምረውብናል። ቀደም ከጠዋት እስከማታ በስራቸው የሙጥኝ ይሉ የነበሩት እንኳንስ እዲስ መሬት መንጥረው እዳሪ ማውጣት ይቅርና የደረሰውን ቡና መልቀም ተስኗቸዋል። የተያዘላቸው ነገር ቢኖር ተሰብስቦ ከጠዋት እስከማታ ወሬ ማውራት የበሰለበት ሄዶ መብላት ሆኗል። ሠርጎ ገቦቹም ቢሆኑ ያለፉበትን የጫት አትክዕልታችንን ከዛፉ ሥር ተኝተው፤ ቀጠሉን ቀንጥሰው ከመቃም ይልቅ ልጡን እየላጡ በመብላት ዛፉን እስከማድረቅ ደርሰዋል።

በአጠቃላይ ሕዝባችን በሃገር ውስጥ ብስለት ያለው መሪ



በማጣቱ እየተጸጸተ፤ የልጆቹን ማስደጊያ ንብረቱን ከደጃፉ ድረስ በመምጣት መሣሪያ እያሣዩት እንዲዘርፉት ፍላጎቱ አልነበረም። ለዚህን ሁሉ ምክንያቱ የአስተዳደር ደካማነት እንደሆነ ለመግለጽ ያህል ነው። እንደምታየው በአሁኑ ወቅት የመእከላዊው መንግሥት መልክተኛ የሆኑ ዳኞችም ሆኑ ፖሊሶች በአከባቢው አይገኙም። ሕዝቡ ግን ራሱን በሚገባ ያስተዳድራል።ከበድ ያለ ችግር እንኳን ቢፈጠር የአከባቢው ሽማግሌዎች ተሰብስበው መፍትሔ ያገኙለታል። በዚህ አከባቢ ከመጣህ ጀምሮ እንድም ሰው ርስበርሱ ተቷኮሶ ሲጋደል አላየህም። ሁሉም የራሱን ሥራ አክብሮ ስለሚሠራ፤ ሌላው ቀርቶ በውፍ ዘራሹ ቡና ለቀማ ላይ እንኳን ጸብ የለም።እንደዚህ በሰላም የሚኖርን ሕዝብ ቀስ በቀስ አመራራቸውን ከሃገሪቱ ሳዕላዊ መዋቅር ጋር እንዲያያዝ መጣር እንጂ ዘራፍ ብሎ ሕዝብ በተሰበሰበበት መፎከር ሕዝብ ጥርጥር ውስጥ ፍራቻ ላይ ከመጣል ሌላ ምንም የሚያስገኘው ውጤት አይኖርም። ሕዝብ ከተጠራጠረና በአስተዳደሩ ላይ እምነት ከእጣ ምን ቢሆን ሊሻሻል አይችልም።ከአከባቢው ሕዝብ ጋር ለመሥራት አስተዋይነትና አመዛዛኝነት ሲጠይቅ፤እንደዘንድሮው የደርግ አባሎች አንድ የአረብ ብር በቁራን መጽሐፍ ውስጥ ተገኘ በማለት ሰውን ገለው የሦስት ክፍለ ሃገራት የተፈጥሮ ሐብት በጊሮ በር እንዲወጣ የሚያደርጉ ዓይነቶች የሚጉዱት ሃገራቸውን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም ቤተሰብ ጭምር ነው።ለዚህም ነው አስተዋይና አመዛዛኝ መሪ ያስፈልጋል ያልኩት።ሕዝቡም ቢሆን በጣም አስተዋይ ነው። ችግሩ በዝቶበትና ተደጋግሞበት እንጂ ማንም የውጭ ሰው ከቀየው እንዲመጣበት አይሸም።መሣሪያውንም የሚሰጡት ሃገሮች ለራሳቸው ጥቅም መሆኑን ጠንቅቀው ያውቁታል።የተሰጣቸው የነፃ እውጭም ስም ቢሆን ማታለያና የንግድ ምልክት እንደሆነ ጠንቅቀው ተረድተውታል፤አሁንም ሕዝቡ ያለፈው አልፏል ለወደፊቱ ጠንክረን እንሥራ የሚለው መሪ ያስፈልገዋል። ያም ከሕዝቡ ውስጥ ይገኛል።»

በአከባቢው እንደታየው ሕዝቡ ወንበዴ አልነበረም። ግን የአስተዳደሩ መጥፎነት በፈጠረው ቅራኔ የጎረቤት ሃገር በነፃነት ተዋጊ ስም በማሞከሸት ከመሐል ሃገር ጋር እያዋጋቸው የአከባቢያቸው ሐብት እንደሚያግዝባቸው ያውቁታል። ሆኖም የሃገራቸው መሪዎች የውጭ ሃገሩን ፕሮፖጋናዳ እንደሐቅ ተቀብለውት ጦር ማዝመታቸው በመቃወም በየጊዜ መሣሪያ እስከማንሳት ደረጃ አድርሷቸዋል።

በአጠቃላይ ሕዝቡ በሥራውና በራሱ በጣም ያምናል።ለዚያም ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉት አከባቢዎች የእርዳታ ቀለብ ሲሰፈሩ እነርሱ ግን እንድች ብለው የምጽዋት እህል ከቤታቸው አልገባም። እያደር እንቅስቃሴያቸው በአከባቢያቸው የገበሬ ማሕበር እንዳይቋቋምባቸው ለመከላከል እንደሆነ በግልጽ ሲናገሩ፤በእርግጥ የሃገር ሽማግሌዎች በየስብሰባው ወጣቱ ትውልዳቸው ሰማሊያ ሄዶ መሣሪያ ከታጠቀ በኋላ የመስራት ፍጋቶች እየቀነሱ መምጣታቸውን ሣይገነዘቡት አልቀሩም። ራሱን ከረሃብና ከችግር

እውጥቶ በሥራው ያላስመሰከረ ግለሰብም ሆነ ግለሰቦች የሌላው ብሔረሰብ ነፃ እውጪ ብለው ራሣቸውን ሊሰይሙ አይችሉም። መሣሪያ ሥራቸውን የሚያደናቅፉቸውን ክፍል ለመከላከል ከልሆነ እንዲያው ተሸከሞ ሽቅብ ቁልቁል በማለት የሥራ ጊዜን አባክኖ የልመና ቀለብ መቀበሉ ቃል የማይገኝለት ማወናበድ ሲያመለክቱ፤ መሣሪያ ከነገቱ በኋላ ወደ ሥራ መስክ መመለሱና እንደየፍላጎቱ አምራች መሆኑ ለወጣቶቹ እንደሚያስፍራቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች ሣይጠቁሙት አያልፉም። ያም ሁኔታ በደበልጥ በገበሬ ማሕበራት ከተደረጁ አካባቢዎች ስለሚያዩአቸው ከገበሬ ማሕበር ገብተን ልጆቻችንን እናስርብም የሚሉም አሉ። የአስተዳደሩን ጣልቃ ገብነት አይፈልጉትም። የአካባቢው ሽማግሌዎች እንደሚናገሩት «አካባቢያችንን መሣሪያ ይዘን ባንከላከል ኖሮ እስከ አሁን ይህ አካባቢ ወደበረሃ ተለውጦ ነበር። የገበሬ ማሕበር ይቋቋም ይላሉ ደኑ ይመነጠራል አንድ ሰብል ሰብስበውለት፤ ከአንድ መሕር በኋላ እንቢይ ይበቅልበታል ሌላውን አካባቢ ምጠራ በማድረግ ድርጊቱ ሲቀጥል፤ደኑ ዉርሶ ከጠፋ በኋላ ባለሞያዎች ተልከው መጥተው ያጠናሉ፤ ይህ ነው እስከዛሬ ከሸዋ እስከዚህ ሲደረግ ያየነው ሞያ። ከዚህ ደግሞ ወዴት እንደምንሄድ እናውቅም። ጊዜ ጠብቀን ሃገሪቱ ምድረበዳ ስትሆንና ስንራብ ሃገራችንን ጥለን ዘር ቆጥረን ወደ ባዕድ ሃገር መሄድ አንፈልግም። ሃገራችን ከዚህን ስለሆነ እንዳትጠፋብን መከባከብ እንፈልጋለን። መሬትና የወተት ላም አንድ ናቸው። ላምም ወተት ለጥጃዋና ለልጆቻችን ማሳደጊያ እንድትሰጥ መከባከብና ጥሩ መኖ እንደሚያስፈልግ ሁሉ መሬታችንም ይህ ደኗ በውስጧ የሚገኙት እንሰሳዎቿ ምግቦቿ ናቸው። እንገድህን የመሬቲቱን ምግብ አጥፍተን መሬት ሊኖረን አይችልም። ለዚህም ነበር እንደወራሪ ጦር የሃገሪቱን የተፈጥሩ ሐብት ደዝባውን ለማጥፋትና ትውልዳችንን በችግር ላይ ጥለው ለማለፍ የሚጥሩትን ለራስ ኗሪዎች ስንከላከል የኖርነው። ይህንንም ቅን እስተሳሰባችን እንደወንጀል ተቆጥሮ የወንበዴ ስም ተሰጥቶን ሲዘመትብን ኖረ። »

እውነቱም የአካባቢውን ገበሬዎች የአሰራራ ዘዴአቸውን ሲመለከተው ትምህርት ቤት ገብተው ከሰለጠኑትና በሞያው እስተዋፅኦ ካበረከቱት ግለሰቦች አሰራር አሰበልጦ እንጂ አሣንሶ የሚመለከተው አይደለም። በተግባር የሚስተካከላቸው በጊዜው አልነበረም። እያንዳንዱ ሰው ስለአካባቢው አላፊነት አለበት። እያገባኝም ተብሎ የታለፍ ነገር የለም። አንድ ግለሰብ እንደፈለገው የሌለኛውን ይዞታ ሆነ ንብረት ባለንብረቱ ባአካባቢው ባይኖር እንኳን እንዲች ብሎ መንካት አይችልም። ሕብረተሰቡ ለሌኛው ግለሰብ መብት መደፈር በተቀዳሚነት የመቆም የወዴታ ግዴታ አለበት። ዛሬ በሌላው ላይ መጥፎ ተግባሮች ሲፈጸሙ ዝም በማለት ብናልፋቸው ነግ በእኛ ብለው በማሰብ ማንኛውም በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚከናወኑትና ሰዎችን የሚያገናኙ ተግባሮች በጥንቃቄ ሽማግሌዎች እንዲያዩቸው ይደረጋሉ። እንደዚያውም የአካባቢው ሕዝብ ብሔረሰቡ ላይ ለሚደርሰው ችግር የጋር



መፍትሔዎች የመፈለግ ግዴታ አለበት። ግለሰቦችን ሆነ ግለሰብን ከመርዳታቸው በፊት በግል የሚያደረጉትን መፍጨርጨሮች በቅርብ ያጠናሉ። አዲስ ሰዎች ወደአካባቢውም ከመጡ እስከሚቋቋሙ ድረስ ግለሰቦች ተመድበውላቸው ከዚያን እንዲሰሩ ተደርጎ፤ ሰብልም በሚሰበሰብበት ውቅት ከማንኛውም አውድማ በመሄድና በሥራ በመርዳት ለቀለብና ለመጪው መሕር ለዘር የሚበቃቸውን ያህል ቢወስዱ ከልካይ የላቸውም። በሕብረተሰቡ ውስጥ የማይሰራ ጥሩ ስም የለውም።

እውነቱም እንደሄደ ከቃሲም ጉን ተሰልፎ አምራች ገበሬ ለመሆን ጊዜ አልወሰደበትም። በሬ ጠምዶ ካረሰ ብዙ ዓመታት ቢሆኑትም ልምዱን መልሶ ለማግኘት ጊዜ ቢወስድበትም ቃሲም ጥሩ መምህር ነበርና የሥራው ፍላጎት እንዲያድርበት አድርጎታል። በትምህርት ደረጃ እየጨመረ ሲሄድ ሥራውንም እየፈራው እንደመጣ ተናግሮ፤ ያም ሆኖ በጊዜው በፍላጎቱ ይሥራ ስለነበር አልተሰማውም። ቃሲምም እውነቱ ፈሩን እንዳይስት እያስተካከለለት በሮቹን በረጅም ጅራፍ እየነዳ «እውነተኛው የግብርና ሥራ ይህን ይመስለል። »በማለት ቃሲም ቢናገርም፤ ንግግሩ ምኑም ወደጆሮው ሳይደርስ፤ በሮቹ ሽቅብ ቁልቁል ሲሰቡት ጓሉ እንደእንቅፋት ሲያላጋው በእእምሮው ውስጥ ይጉላላ የነበረው ተግባርና ቃል አንድ ያለመሆናቸው ነበር። ቀደም ሲል የግብርና ሥር ቀላል የእርሱን ሥር ከባድ አድርጎ ይገምትው እንጂ በተግባር ሲያየው ይህ ቀላል ያ ከባድ ተብሎ ለሥራ ገደብ እንደማይበጅለት መሆኑን ራሱን በራሱ ያሰምናል።

## ፵፫

ቃሲምም አብሮት በእርሱ ላይ ያመጣበትን በደል ተወት አድርጎ በእውነቱና እርሱን መሰል ግለሰቦች ላይ ያደረሰውን ችግር እያጋነነ ሲናገር፤«ለውጡ ባይመጣ ኖሮ ከእኛ ከደሀዎቹ ገበሬዎች አትሰለፍም ነበር።ምቾትን የለመደው ሰውነትህ እንደተቀጠፈ ቅጠል ሲጠወልግ፤ ጫማ የለመዱት እግሮችህ ንቃቃት ያጠቃው መሬት ሲመስሉ፤ከዚህን ሁኔታ አንተም ሆንክ እኔ አንድ የምንግረው ነገር አለ።ይህውም ብዙው ሕዝብ በጣም ወደኋላ በቀረ ዓይነት ኑሮ ውስጥ እየኖረ፤ ጥቂቱ ክፍል ብቻ ከከፍተኛ ኑሮ ከሚኖሩት ሕብረተሰቦች አይነት ኑሮ ለመኖር ያውም በሰው ሃገር ውጤት መሽቀዳደሙ ለሃገሪቱ እድገትና መሻሻል ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ እንደሌለውና ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ እንደኛው ክፍል መሆኑን መገንዘብ አስችሎኛል።እኛ ወገኖቻችሁ በአለበት ስንረግጥ እንደእናንተ ያሉ ልጆቻችንና ወንድሞቻችን የእኛን ችግር ረስታችሁ ከላይ ከቁንጮ ወጥታችሁ ለራሳችሁ ጥቅም ስትሯሯጡ እኛ በድህነት ስንዋኝ የአንድ ሃገር ሕዝብ በሁለት በተለያዩ መንገዶች ስንጓዙ መታየቱና ከታች ያለውም የላይኛውን ሣያውቀው የላይኛውም የታችኛውን ተመልሶ ለመመልከት ፍላጎት ሲያጣ በምን ዓይነትስ የተለያዩ ሞያዎች በተሻሻለ ሁኔታዎች ሊስፋፉና ሊያድጉ ይችላሉ? ልጆቻችን የአሰራራችንን እድከሚነት ኋላ ቀርነት ተመልከታችሁ፤ ጥናት አድርጋችሁ አንዲት ትንሽ ዘዴን ብታስዩን እኛም አከለንበት መጨውም በአዲስ ዘዴ አዳብሮት ከትውልድ ትውልድ እያሻሻልነውና እያደበርነው በአዲስ የአሰራር መንገድ በለወጥነው ነበር። ግን አልሆነም። ሆኖም ተስፋ አንቆርጥም። ያም ባለመሆኑ ይሄው እንደምታየው ስትወለድ እንጠቀምበት የነበረውን የአሰራር ዘዴአችንን ሣንለውጥ ከሃያ ዓመት በኋላም ተመልሰህ ስትመጣ ያው እንደነበረ ነው። ሃገሪቱን ለቀን የሰው ሃገር ጥገኛና ሁለተኛ ዜጋ እስከአልሆን ድረስ የሕብረተሰቡ ችግር የሁላችንም እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ። አንተም ከዚሁ ለግሩ ጫማ ከሌለው ጤናው ካልተጠበቀ የተመጣጠነ ምግብ ከማይመገብ ንጽህና ከሌለው የዘመኑ ትምህርት ካልተማረ፤ ዝቅተኛ ኑሮ ከሚኖረው ሕዝብ ያመለጥህ መሰሎህ ነበር ግን አልሆነም። እድገቱ ተደጋጋፊ ባለመሆኑ ሚዛኑ ወደእኛ አድልቶ ሊስብህ ቻለ።በእውነቱ ሁሉም ነገር መሠረት ይዞ እንዲያድግ ከተፈለገ መሻሻሉ የሚጀምረው ከዚህ ከታች ካለው ነው።ያለበለዚያ ግን እንዲያውን ውስጡን ሸፍነን ከላይ እንዲያሸበርቅ ብናደርገው ዘር ዘር የምንቀረደው እኛው የሃገሪቱ ሰዎች እንሆናለን።ለእኔም ስለሃገሬ ችግር ከሃገሬ ሰው ሌላ እንዲነግረኝ አልሻም። አንተም ለኔ መንገርና ማስተማር ሲኖርብህ፤እኔም የታየኝን መንገር ሲኖርብኝ ነው።ያለበለዚያ ግን መሻሻል እንደማይኖር አንተ ከእኔ በላይ ታውቀዋለህ። ስለሆነም በስጠሁት አስተያየቴ ቅሬታ እንደማይኖርህ እገምታለሁ። ተምሬአለሁ በወንበር ተቀምጭ ጥሩ ደመወዝ ለማግኘት በቻል ለምን ኋላ ቀር ከሆነው የሕብረትሰብ ክፍል ጋር እገላታለሁ ብለህ እንደማታመነታ ፍላጎትህን አብረን በቆየንበት ጊዜ ለመረዳት ችያለሁ። ሰዎች ለሕብረተሰባቸው ትልቅና ዘለቄታዊ የሆነ ተግባር በኖሩበት ዘመን



ለመፈጸም ዕቅድ ካላቸው ይህም እንደኛው ሥፍራ ነው። ያለበለዚያ ግን ያለ ጠንካራ ሠራተኛ ሕዝብ ያማረችና የበለጸገች ሃገር ማየት አይቻልም። እያንዳንዳችን ራሳችንን ለማሸነፍ የሌላውን ጥቅም ስንጋፋ ጥረት በተሰለፍንበት መስክ ብናደርግ ለዚያ ድጋፍ የሚሰጥ የሕዝብ ክፍል የሆነ አዲስ ዘዴዎችን በማፍለቅ በተግባር ከሕዝብ በመቅደም ዕቅደችን የሚነድፍ በሕዝብ የተመረጠ የአስተዳደር አካል ቢኖር ለመሻሻላችን አሁን ከአለንበት የመከራ ማቅ ለመውጣት ምንም አጠራጣሪ አይሆንም።»ቃሲምም ለእውነቱ እየአስተማረው ባለ ተረኛዋ ሚስቱ ምግብ ይዛ ማሣው ውስጥ ከሚገኘው ዛፍ ሥር ተቀምጣ ስለነበር ምግባቸውን ለመመገብ ከዛፉ ጥላ ሥር ተቀምጠው፤ ምሳቸውም የበቆሎ ገንፎ በቆሪ የፍየል ወተት እስከ እናቱ ተሞልቶበት ከእንጨት ከተጠረቡ ማንኪያዎች ጋር ከማማጊያው ቡና በቅል መጠጫ ጭምር ቀርቦላቸው፤ እየተመገቡ ቃሲም ስለግብርና ስራ ያለውን አስተያየት ከእውነቱ ጠይቆ፤እርሱም የግብርናን ሥራ እንደሚወደው ገልፆለት ግን በሥራው ለመሻሻል ወይም የአሰራሩን ዘዴ ለመለወጥ ምንም አይነተ አስተዋፅኦ እንዳላደረገና ለማድረግም እንዳልሞከረ ገልጾለት፤ከአስራ አምስት ዓምት በኋላ እርፍ እንደጨበጠ ያጫውተዋል።ይህም የሆነበት ብዕር ከጨበጠበት ዕለት አንስቶ የግብርናውን ሥራ እንደሚፈራውና ከፍራቱም የተነሣ ሥራውን ጠልቶት ፍላጎቱም እየቀዘቀዘ መምጣቱን ጠቁሞ፤በክፍል የሚሰጠውን በተግባር ለመተርጎም ስለሚያስፈራውና ሥራውም ከገጠር ስለሆነ በዚያም እንኳር ከከተማ መውጣቱን ስለማይፈልገው ሲጠላው፤ ሌላው ቀርቶ ለዕረፍት ከወላጆቹ ዘንድ ትምህርት ቤት ተዘግቶ ሲሄድ እሸት ከጓሮ መቁረጡ እንኳን እንደሚከብደው ገልጾ፤ሰው ቆርጦ እንዲሰጠው ይሻል። ቃሲም በጥሞና ከዳመጠ በኋላ«ትምህርት ቤት የምትሄዱት ተቀምጣችሁ የሕዝብ ገንዘብ በደመወዝ ስም ለመቀበል ነውን» በማለት ሲጠይቀው፤«ያማ ባሆን ኖሮ እጆቼ እንደዚህን ተለሳልሰው መቻታያቸው ነበር» አለው። እርሱም «ልጆቻችን እንደዚህን ተሸሞንምናችሁ ለመኖር ፍላጎታችሁ ከሆነ ጠንካራውንና ሃገር ገቢውን ሥራ ማን እንዲሰራላችሁ እንደፈለጋችሁ አልገባኝም።ለሥራ የማያዘጋጅ ትምህርት ቤት ከመሄድ የቀረ በተሻለ፤ምክንያቱም ለዚያን የሚውለውን ወጭ ያድናል።እንግዲህ እኛም በትምህርት ቤቶች ላይ እምነት ጥለን፤ለልጆቻችን የነበረንን ሞያ ለማስጠናት ባለሞመከራችን የታሪክ ተወቃሽ ልንሆን ነው።የሃገሪቱ አስተዳዳሪዎችም ለሃገር በማይበጅ መንገድ ልጆቻችንን በማዘጋጀታቸው ለፍርድ ሊቀርቡ ነው።በአጠቃላይ የሥራ ፍላጎት ሊፈጠር የሚችለው ራስን በራስ ለመርዳት ከሚደረግ መፍጨርጨር የሚመጣ ቢሆንም፤ በመንግሥት ደመወዝ ላይ ተማምኖ ለመኖር የሚደረገው ጥረት እንብዛም የሚያስመካ አይደለም። ከአሁኑ ከአንተ ሁኔታ መረዳት ያስችላል። ትኩሱ የሃገሪቱ ወጣት በራሱ ተማምኖ ሃገሩም በአፈራቸውና በሠራችው ከርቶ እርሱም ባለበት ግዴታ አስተዋፆ አበርክቶ የሌላው ዓለም ወጣት ክፍል በሥራ እኩል ለመቆም ባለመጣሩ የተተኪው ትውልድ ተወቃሽ ሊሆን ነው።በአጠቃላይ በዚች ዘመን ከጥቂቶች በስተቀር ሁላችንም ተወቃሾች ልንሆን ነው።»

## ፵፬

እውነቱም ትምህርት ቤት ገብቶ ሣይሆን ከኑሮው ከተማረው ገበሬ የዚያን አይነት አስተያየት ሲሰማ የራሱን ተምሬአለሁ በማለት የውጭ ሃገር ቋንቋ በመናገሩ ብቻ ይሰማው የነበረውን ትዕቢትና ትምህክት በመጠኑም ቢሆን ትክክል አለመሆኑን ሣይረዳው አልቀረም። ከዚያን ወደኋላ መለስ ብሎ ቃሲም የተናገራቸውን ነጥቦች በአእምሮው ሲያውጠነጥናቸው በሙሉ የነበሩና የሚታዩ ሐቆች ነበሩ። እርሱም በገበሬው ቃሲም አስተያየት ላይ በመሞርከዝ የታየውን ሐሣብ ያቀርበል፤«የተማሩት የሃገሪቱ ልጆች ተመልሰው አካባቢያቸውን ሆነ በጠቃለይ ሃገሪቱን ለማሣደግ ጥረት አለደረጉም በማለት ፍጹም የሆነ አስተያየትን ለመስጠት መመከሩ ትክክል ነው፤ባይበልም፣ጥቂቶችም ቢሆኑ የሉም ከሚለው መደምደሚያ ሐሣብ ላይ እንዳንደርስ መጠንቀቅ አለብን።የጥቂቶቹ አስተዋፅኦ በብዙሃኑ ተውጦ ወይም የወገን ሙሉ ድጋፍ ተነፍጎት ሥራቸው ፍሬ እንዳይሰጥ ተደርጎባቸው ተስፋ ቆርጠው የተቀመጡ አይገኙም ለማለትም እንደፍርም። ለዚህ ሁሉ ውጥቅጥና ኋላ ቀርነት የምንከተለው የአመራር ሥርዓትና በውስጡ ያሉ አንዳንድ ራስ ወዳዶች ውጤት ነው ብል ስህተት አይሆንም። ራሴም ብሆን በትምህርት ቤት አካባቢ ሆኜ እንደአየሁት እጥር የነበረው ጥሩ ደመወዝ አገኛቼ በሥልጣንም ከፍ ለማለት መሆኑንም ልክድህ አልችልም። ከተፈለገው ሥልጣንና ደመወዝ ለመድረስም ብዙ ችግር የሚፈጥር አልነበረም፤ አሁንም አይደለም። ለደረጃ መታጪቱ በግለሰቦች ስለሆነ ብዙም ውጣ ውረድ የለውም።የራስን እውነተኛነትና ሐሰተኛነት ለማረጋገጥ ለሕዝብ ለድምጽ አይቀርብም። ስለዚህ አገልግሎቴ ለሥልጣን ለአጪኝ ግለሰብ ይሆናል ማለት ነው። በአካባቢዬ የሚደረጉት ውድድሮች የሃገር ማስደግና የራስ አብሮ ማደግ ሳይሆን፤ ውድድሩ አንድ ወጥ ሲሆን ይሄውም ለውጭ ሃገር አሳቂ ዕቃዎች በመሆኑ፣ የዚህን ውድድር ለማሸነፍና ወፍራም ደመወዝ ለማግኘት ለወገን በትክክለኛው መንገድ መሥራት ይቀርና ለሽመኝ ክፍል ጎበስ ቀና በማለት ፤ የአስተማረኝን ሕዝብ ረስቼው፤ ሕዝብ የሚለው አስተሳሰብ ቀስ በቀስ ከአእምሮዬ ጠፍቶ በአከባቢዬ በኑሮ ደረጃ ከሚመሳሰሉኝ ጋር ብቻ ወድድሬን ሳደርግ፤ የሚከፈለኝ ደመወዝ ከሕዝብ መሰብሰቡን ረስቸው የቀጠረኝ ግለሰብ ከኪሱ አውጥቶ እንደሚከፍለኝ ዓይነት በአእምሮዬ ይቀረፃል።ለሥራው በሕዝብ ስለአልተመረኩ የመረጠኝም ግለሰብ በሕዝብ ባለመመረጡ ከደረጃችን ያወርደናል ብለንም ስለማንሰጋ፤ ተዝናንተን የጡረታ ጊዜያችንን ስንጠብቅ አዲስ ዘዴዎችን ለማፍለቅ ተፈታተኝ ሁኔታዎችም ስለማይገጥሙን እድገቱ በአለበት ሂድ ሆኖአል።ወደኋላ መለስ ብለን ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በፊት ሃገራችን የነበረችበትንና ዛሬ ያለችበትን ሁኔታ ብንመልከት፤ እኔም አንተም በዚያን ዘመን ባንኖርም የአባቶቻችንን የአሁኑን ኑሮአቸውን ተመልክተን አስተያየት ብንሰጥ፤ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም መገልገያ ዕቃዎች በእጃቸው ሠርተው ሲጠቀሙባቸው የምናየው ሲሆን፤ ለማንም ሃገር ምርት



አልተበረከኩም። የበሬ ዕቃዎች በሙሉ በአካባቢው ብረት አጣሪዎች የተሠሩ ሲሆን፤ ከውጭ አገር የተሠራውን ማጭድና በሃገር ውስጥ የተሠራውን ማጭድ ብናወዳድረው በሃገራችን ብረት ቀጥቃጮች የተሠራው የረጅም ጊዜ አገልግሎት እንደሚሰጥ ነው።

ከዚህ ላይ ላነሳው የፈለኩት ነጥብ ቢኖር በሥልጣኔ ስም የእኛ የወጣቶቹ አእምሮ እንደተበወዘና ስለወገኖቻችን የሥራ ወጤቶች ከማድነቅና ከማሸሻል ይልቅ ስለውጭ ሃገር ሕዝብ የሥራ ውጤት እንድናስብ ስንደረግ፤ ጥበባቸውን አደንቀን ከመቅሰም ይልቅ እንደአሽከታብ አጥልቅነው መሽሞንመናችን በአቋራጭ ሰልጥኛለሁ ለማለትና ዘመናዊ ሆኖ ለመታየት የተመረጠ ዘዴ ስለሆነ ዛሬ ይህን አድርግ ያንን አታድርግ በማለት የሚለወጥ ነገር አይደለም። በአባቶች የአኗኗር ዜቤ ላይ ተመርኩዞ የተመሠረት ባለመሆኑ ይህው ሲፈረካከስ የምታየው ነው። እኔንም እንደጥሩ ምሳሌ፤ውሰደኝ ብዙውን ዘመን በትምህርት ቤት አካባቢ አሳልፌ ዛሬ በራሴ ሠርቼ መኖር እንደሚያስፈራኝ በቅርብ አይተህኝ ልትፈርድ ትችላለህ። እንግዲህን በራስ ለመተማመንና በራስ ሠርቶ በራስ ምርት ላይ ተማምኖ ለመኖር በሃገር ወጤት ላይ ለመኩራትና ለማድነቅ የአእምሮ ለውጥ ሲያስፈልገው፤ የብዙ ምሁራንን ድክምና ዘመን ስለሚጠይቅ፤ ዛሬ አንድ ነገር ለራስ የሚበጅ ቢጀመር የተመኘነውን ዘመን ያቀርበዋል። ለምሳሌ ያህል፤ በየሱቁ ተደርድረው የምታያቸው ሸቀጦችን ከሚያመርቱ ሃገሮች ጋር የነበረን የዕድገት ደረጃ ብዙም የሚራራቅ አልነበረም። የምንበልጣቸውም ነበሩ። ግን ቆመን ጠበቅናቸው ጥለውን አለፉ። ዛሬ ነበር ብለን እናውራው እንጂ ከዓለም መጨረሻ ሃገራችን እንድትሆን ያደረግናት እኛው ልጆቿ ነን።አሁንም ቢሆን በጠንከራ ክንድ እውነተኛ ልጆቿ ከተነሣን ከታሰበበት ደረጃ ለመድረስ የሚያግደን ነገር አይኖርም። ከባዱ ነገር ራስን ማሰመኑ ቢሆን በዚያን በኩል ከራሳችን ጋር ትግል ከአደረግን፤ ብዙ ዘመን ይውሰድብን እንጂ ዝቃጭ ሆነን አንቀርም። ማንኛው ሃገር የተሻሻለውና ሕዝቡ በአኗኗሩ ተደስቶ እንዲኖር የተደረገው እንዱ የሌላውን ጥበብ በመዝረፍና በመስረቅ ሲሆን፤ እኛም ያንን የማናደርግበት ምን ምክንያት አለ? ከዘንድሮው የሃገራቸን ሁኔታ ተነስቶ በአሸንጉሊት ነገሮች መሽቀርቀሩን ዋጋ እንደሌለው ያልተረዳ የለንም። አሁንም እኔም ሆንኩ አንተ የምናምንበት አንድ ነገር እንዳለ ሲሆን ይሄው ተግባር ከቃል መብለጡን፤ ቃልም ከተግባር ካልተተረጎመ ፋይዳ ቢስ መሆኑን፤ ተግባሩ ግን የሚታይ ነገር ስለሆነ ማንም ሰው እንዳለ ያሰምናል።

ለምሳሌ ወታደራዊ መንግሥት በመጀመሪያ ሲያቀርባቸው የነበሩት ሐሣቦችና፤ ዛሬ እኔና አንተ ያቀረብናቸው፤ ልዩነት ሳይኖራቸው፤ግን ዛሬ የሚያደርጉትን ስንመለከት ፍጹም እነዚህ ሰዎች ቀደም የምናውቃቸው አይደሉም ለማለት እንደፍራለን።ከዚህ ልንረዳው የምንችለው ነገር ቢኖር የኖርንበት ሥርዓት ልምዶች እንዳሸነፏቸው ሲሆን፤ ያ ቃልን ያለመጠበቅና ሐቀኝነት የጎደለው

ልምድ አሸንፏቸው፤ ቀደም የተናገሩትን ሕዝቡ የራሱን አስተዳዳሪዎች ከአካባቢው እስከ ጠቅላላ የሃገሪቱ አስተዳደር እንዲመርጥ አድርገን እኛም ወደጦር ሰፈራችን እንመለሰለን ሲሉን ከርመው ይህው ከሥልጣን የሙጥኝ ብለው ሕዝቡን ርስበርሱ ሲያጫርሱት እናያለን። እነርሱም በበኩላቸው የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች አሏቸው፤ ለሕዝብ ብናስረክም ያው እንደቀድሞው አንዳንድ አፈሙሊዎች ከሥልጣን ወጥተው ቤተሰባቸውንና የቅርብ ጓደኞቻቸውን ሲረዱ ሕዝቡን ስለሚረሱት የቀድሞው እንዳይደገም ነው በማለት ሊያሳምኑን ቢሞክሩም፤ የወታደራዊው መንግሥት ብዙ ዘመን ወደኋላ እንድንመለስ አድረጎናል። በእርግጥ ከውስጣቸው የሃገር ፍቅርና የወገን ብሶት የማይሰማቸው የሉም ማለት አንችልም። «ወርቅ የተጫነች አህያ የማትከፍተው በር የለትም» የኑዋይ ፍቅር ለጊዜ አሸነፏቸዋል ለማለት ነው። ይህ ሐኪም የማይገኝለት በሽታ ሲሆን እኔንም ከለው ሥርዓት ገንጥለህ አትየኝ፤ እኔም የሥርዓቱ ውጤት ነኝ፤ምናልባት የአንተና የአካባቢው ሕዝብ የቆየ መጥፎ አመለካከቴን ያስለውጠኝ ይሆናል፣ ብዬ እገምታለሁ።»





የእውነቱም ከነበረው ሥርዓት ራሱ ሳያገል በግልጽ ራሱን በመከነኑ ቃሲም ለሒሣቡቹ ክብደት ከመስጠቱ ሌላ አክብሮትና እምነቱን ያሰያዋል።

ቃሲምም የአካባቢውን ለምለምነት እያደነቀ ስለአካባቢው ታሪክ እያጫወተው፤ «ተመልከት» ይልና የቀለውን ቡና በጥቦ «ይህ ሰው የተከለው ሳይሆን የተፈጥሮ ነው፤» ወደ ጫካው እጁን ጎተት አድርጎት ግራ ቀኙን እየተመለከተ «ምን ይሸትሃል?» በማለት ጠይቶት፤እርሱም የአካባቢውን ቀዝቃዛ አየር ወደሣንባው እየሣበ፤ ይህ ነው በማለት ለመናገር በማሰላሰል ላይ ሳለ ቃሲም ከእጁቹ ተጠራርቶ፤ የባሕር ሎሚውንና ሎሚውን በእጅ ጠባብ ሺሚዙ ይዘለት መጥቶ ጎንበስ ብሎ አፈሩን ዘግኖ ይህ አፈር ዳቦ ነው፤ተመልከት ካለጨው በስተቀር የፈለከውን ነገር ብትዘራበት ያበቅላል ብሎት ከሚወርደው ጅረት ወርደው፤ከድንጋይ ላይ ተቀምጠው፤ ቃሲም በሁለት እጆቹ ከትልቁ ወንዝ ከዱማል ውኃውን እየጨለፈ ከተጎነጨ በኋላ «ይህ የአላህ ስጦታ ነው። ይህ ውኃ ለእኔ ልዩ ጣዕም አለው። ከሌሎች ጅረቶች የምጠጣው ውኃ እንደዚህኛው ጣዕም አይሰጠኝም» በማለት እያደነቀ ወንዙን ተሻግረው አፋፉ ላይ ካለው ትልቅ ዛፍ ሥር ተቀምጠው፤ቃሲም በያዘው ከለሸከብ ጠብመንጃ በሠደፉ መሬቱን እየመታ «እኔ ለዚህን በታ ትልቅ ትዝታ ሲኖረኝ ትዝታዬም ሐዘን ፀጸት ቁጭት ሆኖ፤እስከ ዛሬ አብረን ስንከርም ያላጫወትኩህ ምስጢር ሲሆን፤ ለሌሎቻችን ግን ምስጢር አይደለም። ሆኖም ለአንተ ተሸሽጎ ማንም በአንተ ፊት ነገሩን አንስቶት አውርቶት አያውቅም፤» በጠብንጃው አፈሙዝ ወደትልቁ ጅረት ዱማል እያመለከት «አንተን የመሰሉ ተማሪዎች ሞተውበታል ያልነገርኩህ ምስጢር ቢኖር ይህ ነው።»

እውነቱም በመቻኩል «በምን ምክንያት»

እንገቱን አቀርቅሮ በጠብንጃው ሠደፍ መሬቷን እየመታ መናገር ሲጀምር እውነቱም የፊቱ ገጽታ በውል እዲታየው ከፊቱ በመቀመጥ ታሪኩን እንዲያጫውተው በጉጉት ሲጠብቅ፤

ቃሲምም ምራቁን ዋጥ አድርጎ በረጋ እንደበቱ «እንናት ወጣቶች ችኩሎች ከመሆናችሁ የተነሰ፤ ሁሉንም ነገር በአንድ ቀን አከናውናችሁ ማደርን ስለምትፈልጉ ሒደትን አትጠብቁም። በኦሮመኛ አንድ አባባል አለ። ሁኔታዎች በዕለቱ መፈታት ሣይቻል ሲቀር «ዱቢን ሃቡልቱ ይባላል»

ይህ ነገር ጊዜ ይሰጠው ማለት ሲሆን፤ ይህንንም የተረትኩበት ዋናው ምክንያት የወጣቶቹ ችኩልነት ውጤት እሣዘኝ መሆኑን በመገመት ነው።»

እውነቱም ምክንያቱን ለማወቅ በመቻኩል ወደ ዋና ርዕስ እንዲመለሰለት አጥብቶ ጠየቀው።

ቃሲምም እንደቀድሞው መሬት መሬቱን እየተመለከተ በመጀመሪያ «ግን ሁኔታዎች አለሣዘኑንም ነበር፤ ግን ውሎ አድሮ ታሪካቸውን ስንሰማ በዚሁ አካባቢ የሚሠሩ ወለጆቻቸውንም በቅርብ የምናውቃቸው ሆነው ስናገኛቸው በጣሙን ፀጸተን። አውጥተንም ለመናገር አሣፈረን። ዕቅዳቸውም የአካባቢውን ሕዝብ እንርዳ በሚል ስም እንደኛውም የመሬት ይዞታውን ሥራ ትቶ ከእኛ ጋር በነፃ ለማገልገል ተማሪውም ስለአካባቢው ለመማር በአለው ፍላጎት በአንድነት ከእኛ ለመሥራት ወስነው መምጣታቸው ውሎ አድሮ ሲነገር በጣም አዘንን እንዲትስ የወላጆቻቸውን ፊት ደፍረን እንይ ሁኔታው ሲታወስን ሆዳችንን ውስጥ ውስጡን ይበላናል። ባጠቃላይ ሲታይ ግን ጥፋቱ የሃገሬው ሕዝብ ባይሆን፤ በወቅቱ አካባቢውን ያዙበት የነበሩት የሶማሌ ሠርጎ ገቦች ስለነበሩ አስቀድመው ደጆኔና ጌታቸው የሚለውን መጠሪያ ስማቸውን ሲሰሙ ሳላይ ናቸው በማለት የሚከታተሏቸው ሰዎች ስመድቡባቸው፤ እነርሱም ሠርጎ ገቦቹ የታጠቁት መሣሪያ የት እንደተሠራ መመዝገብ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ማብዛት በማንኛውም ነገር ከእኛ ለመመሣሠል መሞከራቸውና እንደውም አልፈው ተርፈው አስላም ያረደውን ሥጋ ሲበሉ ሲታዩ እነዚህ እውነተኛ ክሪስቲያኖች አይደሉም በማለት እኛ ሃገሬው ሳንቀር ተጠራጠርናቸው፤ ሠርጎ ገቦቹም በጊዜው ሃይማኖት የሌለው የደርግ መንግሥት ስለሆነ የደርግ መልከተኞች ናቸው በማለት ለእስራት ሶማሊያ ሊወስዷቸው ወሰኑ። ከዚህ ላይ ነው እናንተ ተማሪዎች ችኩል ናችሁ ያልኩት። ባይገርምህ እቶ ተፈራ የዚያን ያህል ጊዜ ከዚህ ሕዝብ ሲኖሩ በሃይማኖታቸው ላይ ተጽኖ ያደረገ ሳይኖር ሌላው ቀርቶ ሠርጎ ገቦቹም ቢሆኑ የሚወላውለው ክፍል ላይ ከዳቸውን አጠናከሩ እንጂ ጠክራና ስነምግባራቸውን የጠበቁ ሕዝቦች ላይ ሙከራቸውን አላደረጉም። በእርግጥ ወጣቶቹ ለከፋት ሣይሆን ከሕዝብ ለመኖር ካላቸው ፍላጎት እንፃር ጥቃቅን ነገሮች የልዩነት መፍጠሪያ መንገድ አይሁኑ በማለት አስበውት ቢሆንም ግን መሠረቱን ጥሎ አዲሱን እንጠልጥሎ የት ያደርሳል? የጊዜው አዘኙም በሶማሊያ መንግሥት የተመለመለ ግለሰብ ስለነበር እነዚያን ወጣቶች በሰላይነታቸው እምኖ ለእስራት ከሃገራቸው ውጪ ሶማሊያ እንደሚወሰዱ ቢነገራቸውም ከማዘን ሌላ ምንም ነገር አለወጣቸውም።እነርሱም ያደርጉት የነበረው ነገረ በሙሉ በየዋህነት እንጂ በርግጥስ የተነገረባቸው ሁኔታ እውነት ሆኖ አልነበረም። እኛም የሃገሬው ሕዝቦች ሰላዮች እንዳልነበሩ ብናውቅም፤ ግን በጊዜው ይቆጣጠሩን የነበሩት መሣሪያውን የሠጠን መንግሥት መልከተኞች ስለነበሩ የታየንን ለመግለጽ ከእነርሱ ፍላጎት ውጭ መብት አልነበረንም። ማነው የሌላውን ሕይወት ለማዳን የራሱን ሕይወት የሚሰጠው? ለምሳሌ የደርግ ወታደር ጥፋት የሌለበት ጓደኛህን ለግድያ ሲያቀርበው አይደለም በማለት ራስህን አሣልፈህ ትሰጣለህ? ባይሆን የምታጋልጥበትን መንገድ ትፈልጋለህ እንጂ የእኛም እንደዚያው ነው።



ከዚያንም ወጣቶቹ በአካባቢው እንዳልተፈለጉ ሲረዱት፤ ቀደም ሲልም እንደእነርሱ ከሕዝብ ጋር ለመስራት መጥተው የተገደሉ መኖራቸውን ሰምተው ስለነበር ሶማሊያ መወሰዳቸው ውሸት መሆኑን ተገንዝበው እንደሚገደሉም አውቀውት፤ የመሪውም መኖሪያ ከወንዙ ማደ በመሆኑ እርሱ ዘንድ ትወሰዳላችሁ ተብለው በዚች መንገድ በጠብንጃው እያመለከተው ጊዜው መስከረም ነበር ዱማል ጢም ብሎ ሞልቷል፤ ዘለው የሞላው ውኃ ውስጥ ለመግባት ምንም አልተጠራጠሩም። በዕለቱ እጅበዋቸው የነበሩት ግለሰቦች ጅግንነታቸውን ሲያወሱት፤ ሁለት ሆነው በዚህን መልክ ዱማልን የተሻገሩ ሁሉ ስለነዚያ ወጣት ኢትዮጵያውያን ሣያነሱ አያውቁም።ሶማሊዎች ካለ ነገራቸው ጅግና ይወዳሉ። በተለይ ስለ ጥንታዊያን ኢትዮጵያውያን እያነሱ ሲያወሩ እንደው የመሪዎቻቸው ትዕዛዝ እየሆነባቸው እንጂ በጠላትነት ደም መቃባቱን አይሹትም።

መንግሥታቸውም ቢሆን ይህንን አውቆ፤ የራሱን ሠራዊት ከመላክ ይልቅ ሃገሬውን እያስታጠቀ ርስበርሳችን ማጫረሱን መርጦታል። ለዚህም ነው አንዳንድ አዋቂዎችና አለማቸውን የሚያጋልጡ ግለሰቦች ሲመጡ በጥይት ደብድበው የሚገሏቸው። ባለማወቅ እንጂ ርስበርሳችን ተዋግተን የት እንደርሳለን ከመጠፋፋት ሌላ፤ የአንድ ሃገርም ሕዝብ የርስበርሱ ጦርነት ውጤቱ እንደምናየው ረሃብ ደህነት ወደ ባርነት ነው።»

## ፵፯

የእውነቱ በውል ከቃሲም ቤተሰብና ከአካባቢው ኗሪ ሕዝብ ጋር መስማማቱ ተቀባይነት ስለሰጠው በየስብሰባቸው ላይ ለመገኘት ዕድል አግኝቶ፤ በአካባቢው በየተወሰኑ ቀናት ከሚደረጉት ሰብሰባዎች ከቃሲም ጋር በመሄድ ያደርጋል።

በሚኖሩበት አካባቢ ሁለት ኮሚቴዎች ሲኖሩ፤ አንደኛው የአካባቢውን ሕዝብ እንዲያስተዳደሩ የተመረጡትን ክፍሎች ያቀፈ ሲሆኑ ሁለተኛው የትጥቁን ትግል የሚያካሂዱትን ክፍሎች ያቅፋል። የአስተዳደሩን ሥራ የሚሰሩት ክፍሎች ብዙዎቹ በዕድሜያቸው ገፍ ያሉ ሲሆኑ፤ የኮሚቴው አባሎች ቁጥር የተወነ እንዲመራ የተመረጠው ግለሰብ የፈለገውን ያህል አባሎች ጠርቶ አካባቢውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ማወያየት ሃላፊነት አለው። የኮሚቴው አባላቱ «ማንጉደስ» በማለት ሲጠሩ ኮሚቴውን በሊቀመንበርነት የሚመራው ግለሰብ «ጉዲ» ይባላል። ቢበዛ ከሁለት ዓመት በላይ ስብሰባውን አይመራም። ስብሰባውንም የሚያደርጉት የተወሰነ ችግር በሕብረተሰቡ ውስጥ ሲፈጠርና ችግሩ የደረሰበት ክፍል ጉዳዩ በሽማግሌች እንዲፈታለት ሲሽ ብቻ ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜ በጋብቻ ምክንያት የሚፈጠሩትን ችግሮችን ለመፍታት ሲሰበሰቡ፤ችግሩን የሚያቀርበው በወንዱ በመሆኑ የሚመለከታቸው ሴች ምንም የሚያውቁት ነገር አይኖራቸውምም በስብሰባውም ላይ የመሰተፍ መብት የላቸውም።

ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ ወንዱ ከሶማሊያ ብረት ለማምጣት ሄዶ ለተወሰን ዓመት ሳይመለስ ይቀርናና፤ ሞቶ በሚል የሃጅ ሚስት ከአካባቢው ወይም ከአካባቢው ውጭ እንዱን አግብታ ሳለ፤ ያ ሞታል የተባለው ባሏ በሚመለሰበት ወቅት «የኒካያ» (የሰማኒያ) ሚስቱን እንዲያስመልሱለት ወይም ለጋብቻው ወጭ አድርጎት የነበረውን ከአዲሱ ባሏ እንደያስጡት ለሽማግሌዎች ሲያቀርብ፤ ሁኔታው ተጠንቶ ከቀረበው መጥይቅ ከሁለቱ እንደኛው በምንም ዓይነት ተፈፃሚነት ሲኖረው፤ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሚስት ምንም የምታውቀው ነገር የላትም።

ሁለተኛው ደግሞ የትጥቁን ክፍል ያቀፈ ኮሚቴ ሲሆን ይህ ኮሚቴ የለዩ ልዩ ቡድን መሪዎች ጥርቅም ሲሆን በበላይነት የሚመራው በሶማሊያ ውስጥ በሚኖሩና ቀደም ሲል ሲዋጉ በነበሩት ግለሰቦች የተመረጠው ግለሰብ ሆኖ የቀሩት የየቡድኑ መሪዎች ግን ቀደም ሲል በአካባቢው ታዋቂነት የነበራቸው፤ሲሆኑ፤ የጭቃ ሹም ወይም ባላባት የነበሩ ግለሰብ ሊሆንም ሲችሉ፤ የእስልምናን ትምህርት በሚገባ የተማሩ(ማዕሊምት) ግለሰቦችንም ያቅፋል።ጦሩንም በዲስፒሊን የሚያንጹት እነርሱ ሆነው ሳለ፤ትምህርታቸው ተቀባይነትና ተደማጭነት ያለው በሃገሬው ሕዝብ ሲሆን ከሶማሊያ ሠርጎ ገቦች ዘንድ ግን በታ የለውም። የእነርሱ ተቀዳሚ ዓላማቸው



ገለው ዘርፈው ያገኟትን ቋጥረው ወደሃገራቸው ለመመለስ ስለነበር ገንዘብና ንብረት ላይ ሲመጣ ሃይማኖቱ እንደማይሰራ ሲነገሯቸው፤ ያም ሁኔታ በመካከላቸው ትልቅ ቅራኔ ስለተፈጠረ ከዚየንም ተግባራቸው ተነስተው «ማዕሊምቲ» ወይም የተማሩ ክፍሎች የሶማሊዎች የእስልምና ሃይማኖት ተከታይነት የተጀመረው በቅርብ ስለሆነ ያለውም ጥልቀት እስከዚህም ነው በማለት የእምነት ጥንካሬአቸውን ያሰንሱታል።

ያም ሆነ ይህ እውነቱ በማንኛውም ስብሳባቸው ላይ ለመገኘት ዕደል ስለአገኘ ቃሲምን እየተከተለ በየኮሚቴው ስብለባ መገኘቱ ለዚያን አካባቢ ታሪክ ሲሆን፤ ፊደል የቆጠረ ሰው በስብሰባቸው ሲገኝ እርሱ የመጀመሪያው እንደሆነ ጠቅሰው፤ መሣሪያ ያስጣጠቋቸው ክፍሎች ደጋግመው የክሪስትያን ሃይማኖት ተከታይ የሆኑና የተማሩ ሰዎችን አጥብቀው እንዲያስወግዱ በተነገራቸው መሠረት ከሃይማኖታቸው ውጭ የሆነ ሰው በየስብሰባቸው እንዲገኝባቸው አይሹም ። ሆኖም ግን እውነቱን በተግባር አብሯቸው ቆይቶ ስላዩት ለሶማሊዎቹ የውሸትና የማለያያ ፕሮፖጋንዳቸው ሥፍራ አልሰጡትም። እውነቱም ከ፲፱፻፶፯ ዓመተ ምህረት ጀምሮ ይዋጉ ከነበሩና ከመሐል ሃገር ብዙ ይወራላቸው ስለነበረው ተዋጊዎች የሰማውን በቦታው ተገኝቶ ለማየት ዕድል በማግኘቱ ደስታው ከመጥን ያለፈ ሲሆን ቀደም በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ተማሪዎች «ፋኖ ተሰማራ» ብለው የዘመሩበትን በውጭ የነበሩ ምሁራንም «በበሌ ለምኔ ከልሆነ በባሌ» ብለው የፎከሩበትን በደርግም ዘመን «የኦሮሞ የነፃነት ንቅናቄ» ፤«የኢትዮጵያ ዲሞክራት አንድነት ግንባር» ፤ እየተባለ የተነገረለትን እንቅስቃሴ አንዱንም ሆኖ አላገኘውም። በእርግጥ የአካባቢው ሕዝብ ባጠቃላይ የኦሮሞ ሕዝብ ሲሆን «የሶማሌ አቦ» በሚል ስም የነፃነተ ተዋጊዎች ሆነው ያገኛቸዋል። እርሱም እንደሚያውቀው ይህ ሕዝብ በአንዳንድ የአስተዳደር ጉድለት ምክንያት ራሱን ሲከላከል የኖረ መሆኑን ለቃሲም ገልፀ፤ ከለውጡ በኋላ ይህ «የሶማሌ አቦ» የሚለው የነፃነት መጠሪያ ስም ከየት እንደመጣ ሲጠይቀው፤ቃሲምም ሌላ ሰው ባለመጠየቁ አመሰግኖት። ታሪኩን በሚከተለው መንገድ ይገልጽለታል። «ሶማሌዎች ባላቸው አቅም ሃገራችንን እንደፈለጋቸው ከፋፍለዋታል። «ሶማሌ ገልቤድ» ብለው የአጋዴን ክፍል ሲሰይሙ ይህንም አካባቢ «የሶማሌ አቦ» ብለውታል። ቀደም ብለህ እንደምታውቀው በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ከዚህ አካባቢ ሶማሊያ መሄድ ሶማሌዎችም ወደዚህ አካባቢ መምጣት ክልክል ስለአልነበረው፤ ለአካባቢ ሕዝብ ሶማሊያ ሁለተኛ ቤቱ ስሆን ለሶማሌውም እንደዚያው ነበር። በተለይ የእነርሱ ነጋዴዎች መናህሪያቸው ከዚህ ሲሆን ግን እንደዘንድሮው ልቀ አልወጡም። ዘንድሮም እንደምታየው ያኔም መሣሪያ በሸቀጥ መልክ እያመጡ በቡናችን በነብር ቆዳችን በግመላችን በደለቡ ሠጋችን ሲለውጡን በንግድ መልክ የመጡት ነጋዴዎች ውስጣችንን በደንብ አወቁን ቋንቋችንንም መናገር ቻሉ። የእነርሱ ቋንቋና የእኛን ለማዘመድ ሲችሉ፤ በሶማሌኛ የማታውቀውን ሰው ለማናገር ስትሻ ሰሙን

ስለማታውቀው «ወሪያ» ብለህ ትጠራዋለህ በእሮመኛ የማታውቀውን ሰው ለማናገር ስትፈልግ «አቦ» በማለት ታናግረዋልህ። ከዚያም ነው የሶማሌ ፖለቲከኞች እንደዘቢያና መጥረቢያ አዋደው የነፃነት ስም ብለው ሰይመው የሚያዋጉን። ሲፈልጋቸው የዘር ሐረጋችንን ቆጥረው አንድ ነን ከማለት ሲደርሱ፤ የእኩልነቱና መብቱ የተሰጠን ከሃገራችን ምድር የሚያገኙትን ጥቅም ለመጠበቅ ሆን ብለው ያቀዱት ዕቅዳቸው ነው።

በሃገራችን ሲመጡ አንድ ዘር ሆነን ስንገኝ ከሃገራቸው ስንሄድ ግን እንደ አሽከርና አገልጋይ ተቆርጠን፤ ይህ የተሰጠን«የሶማሌ አቦ»ስም ተነፍጎን «ቆቲ» የሚል ስም ተሰጥቶናል።ቆቲ አራሽ ሲሆን በሶማሌ በሬ ጠምዶ ማረስ ደማ እንስቶ መቆፈር የተዋረደ ሥራ ስለሆነ እኛን ከዚያ የመደቡን ሲሆን፤ እኔም በተግባር ካየኋቸው በኋላ ነው ልጠላቸው የቻልኩት ከዚህ ቀጭ ብሎ የሬዲዮ ጣቢያቸውን ለሚያዳምጥ ግን ቅቤ ናቸው።

የውሸትና የማታለያ መሣሪያቸውን ማለትም ሬዲዮ ጣቢያቸውን በመጠቀም ከዚህ ከደጋው ክፍል የሚወለዱትን ወጣቶቻችንን እያስከበለሉ ሃገራቸው ወደአረብ የምትልከውን የሙዝ አትዕክልት ሥራለይ እንዲሰማሩ ተደርገዋል። በአረብ ገበሬዎች የሚከሄዱት ሰፋፊ እርሻዎች በሙሉ የሚቆፈሩት ከዚሁ አከባቢ በሄዱ ወጣቶች ነው። በሬዲዮ ጣቢያውና በሃገራችን ውስጥ «የሶማሌ አቦ» ነን፤ ሶማሊያ ውስጥ ግን በሆዳችንና በሚሰጠን ሸርጥ አገልጋዮች እንሆናለን። ቀደም ባሉት ዘመናት ምርታችንን የቀመሱት አቀባበዮቹ የሶማሊያ ነጋዴዎች ዛሬ ደግሞ ልጆቻችንን ለዘመናዊ ባርነት እያጋዟቸው ሲሆን ከለመማራቸው የተነሣ የሚነገረው በሙሉ እውነት እየመሰላቸው ከዚች ለምለም ሃገር ተዋርደውና ተጎሣቁለው ለመኖር ወደጎረቤት ሃገራችን ሲከበልሉ፤ ቀደም ብለው የሄዱትንም በነፃ አውጪ ስም አስታጥቀው ሃገራችሁን ነፃ አውጡ በሚል ለማዋጊያ ባወጡልን «የሶማሌ አቦ» ይሄው ሽቅብ ቁልቁል ስንል የምታየው ነው።»

«አቦ የሚለው ቃል ላይ ሶማሌ የሚለው ስም ታክሎበት ሃገራችሁን ነፃ አውጡ ማለት ፌዝ አይሆንምን?» በማለት እውነቱ ሲጠይቅ፤

«ትልቁ ስህተት ያለው ከዚህ ላይ ነው፤«አቦ» የማታውቀውን ሰው ለመጥሪያ ሆኖ ሳለ ያልታወቁት ሶማሌዎች ተብለን በሌላ አቅጣጫ ሃገራችሁን ነፃ አውጡ ተብሎ ሲነገረን፤ ነፃ የምንሆነው ሶማሊ ስንሆን ወይም አቦን በወሪያ ስንለውጠው ነው ማለት ነው። ቃሉ እንደሚናገረው ያልታወቁትን ሶማሌዎች ነፃ ለማውጣት የሚታገሉ ክፍሎች ነን፤የደርግን መንግሥት ያህል እንኳን በእሮሞነታችን አልተቀበሉንም። ያልታወቅን ጠፍተን ተሸሽገን የነበርን ሶማሌ ነበር እና፤ ይህን ማን ደፍሮ ይጠይቃል። ሃገራችን



ውስጥ ስንቃወማቸው ከእኛው ውስጥ ለእነርሱ ያደሩት ክፍሎች «አማሮች» በማለት ያጥላሉናል። በሃገራቸው ውስጥ ጃጂስ(ሰላይ) በማለት ስማችንን ያጠፉናል፤ ሲፈልጉም ያስሩናል። ይህንኑ ሁኔታ በመረዳት በምንም መንገድ ከእነርሱ እንደማንውጣ ተረድተውት ሃይማኖታችን አንድ ነው በማለት ስም በተጨማሪ እያለባበሱት ባጠቃላይ በሕዝቡ እየተጠቀሙበት ነው። ባይገርምህ የሶማሌው መሪ የበታች ወታደሮች በሙሉ ከዚህ አከባቢ የሄዱ ወጣቶች ሲሆኑ ከበላይ ዘሮችን አዛዥ አደርጎ ከታች ግን «የሶማሌ አቦ» ነፃ አውጭዎች የተባሉትን የበታች አገልጋዮች አድርገዋቸዋል። የወትድርናውን ዕድል ያላገኙት ደግሞ የግለሰቦች ያለደመወዝ በምግብና በሸርጥ አገልጋዮች ሲሆኑ የቀሩት በሶማሊያ ውስጥ በዘኒ ሆነው ይኖራሉ።ይህ ሁሉ ሆኖ በሃገሬ መንግሥት እንጂ በጎሮበት ሃገር አላዝንም። ይህን ለም መሬት የያዘን ሕዝብ ኑሮውን እንዲያሻሽል ትምህርት ቤት ከፍቶ ከአከባቢው በሚገኘው ሐብት ለሕዝብ የሚጠቅሙ የሥራ መስኮች ቢከፈትልላቸው ሌላ ሃገር የሚወስዳቸው ምንም መንገድ አይኖርም። ሌላው ቀርቶ ትልቅ አማካኝ የሆነ የገበያ ቦታ ማቋቋም እንኳን ከባድ አይደለም። የህል ወፍጮ፤ የቡና መፈልፈያ፤ቢቀር እንኳን። ትምህርቱ እንኳን ለአንዳንድ የባላባቶች ልጆች እየተመረጠ ስለሚሰጥ ያው ወጤቱ እንደታየው ነው። የደሃው ልጅ በጥቂቱም ቢሆን ሃገሬ ብሎ ሲሰቃይ አባቶቻቸውም ልጆቹም አፍታ አልወሰደባቸውም ሃገሪቱን ለቀው ለመውጣት። ባይገርምህ አንድም ከዚህ አከባቢ ከተወሰዱት ወጣቶች ተምሮ የተመለሰ የለም። ይህ የአከባቢያች ታሪክ ነው። የሶማሌዎች በሃገራችን የሚያደርጉት ደርጊት ደግሞ «ትንሽ ቆሎ ይዞ ወደአሻሮ ጠጋን» ይመስላል።»

እውነቱም ቃሲም ስለአከባቢው ወጣቶች ተስምቶት የተናገረውን በመደገፍ እርሱም ባጠቃላይ ስለሃገሪቱ ወጣቱ ትውልድ ያለበትን በሚከተለው ሁኔታ የብራራለታል፤ «የሃገራችን ወጣቱ ትውልድ ሃገሪቱን እየተወ የሚወጣው በአንድ አቅጣጫ ሳይሆን በአራቱም ማዕዘናት ነው። ወደ ሶማሊያ ብቻ ሳይሆን ከመሐል ሃገርም ቢሆን በአንዳንድ አላቂ ዕቃዎች እያታለሉ ወጣቱን የሚያስከበልሉ ክፍሎች አልታጡም። ለሃገር ኅብኝነት የመጣው አረብ በአለው የነዳጅ ገንዘብ አባብሎ አገባሻለሁ በማለት ታናናሽ እህቶቻችንን ከሃገር ማስኮብለሎች የአደባባይ ምስጢር ነው። ቀደምን እንደተናገርነው አንድ ሕዝብ ባህሉን ካልጠበቀና የራሱን ቤት እሣምሮ ካልዘጋ ዝንጉነቱንና ተላላነቱን ተመልክቶ ሌላው መጥቶ ቢዘርፈው ጥፋተኛው ማን ሊሆን ነው? በአሁኑ ወቅት ባለው የርስበርስ ጦርነትና ረሃብ የተመለከቱ ሃገሮች አስተማማኝ መሪነትና ሕብረት ያጣውን ሃገር ወጣት በግለጭ ሲያገኙት ሊጠቀሙበት ፈለጉ።«የሃገር ልጅ ማደሪያ እንዳጣች ውፍ ተከራተተ»። ባጠቃላይ ስለሃገራቸን ችግር እንስተን ስንነጋገር እንደኛውን ከሌላው ገንጥለን የምናየው ነገር አይደለም። እያዳንዱ ሕዝብ ከቤተሰብ ጀምሮ የራሱን ሕልውናው እንዳይደፈርና የሌላው የበታች እንደይሆን መጣር ሲኖርበት፤ የፈለገው መንግሥት ቢቋቋም በግል እየተሽሎከለኩ በእጃችን ያለውን ሊቀሙን

የሚመጡትን የባዕድ አገር ሰዎች ዋርዲያ አቁሞ ሊከላከልልን አይችልም፤ እኛም በህላችንንም ሆነ ሕልውናችንን በተቻለን መንገድ እንዳይደፈር ማድረግ እንደሚኖርብን መነገር የሚኖርብን አይመስለኝም። የሃገራችንንም አመራር ስንቃወም የአንድ ሃገር መንግሥት ሊሠራ የሚገባውን ሥራ ሊያከናውን አልቻለም በሕዝብም አልተመረጠም የሚሠራ ይመረጥ ማለታችን እንጂ በግል ዘብ ያቁምልን ማለታችን አይደለም። ስለዚህ በየአቅጣጫው የሚከበልለውም ወጣት ቢሆን ደጋግሞ ራሱን መጠየቅ የራሱ መብት ነው። ስለዚህ አከባቢ ስለሚደረገው የሰው ጉልበት ዘረፋ ከብዙ ዓመታት በፊት መታወቅና መፍትሔ መፈለግ የነበረበት ጉዳይ ሲሆን ግን ያጤነው አልነበረም። በደርግም መንግሥት አንዳንድ ስለአከባቢው ከሰው የሰሙ ክፍሎች የሕዝቡን ትክክለኛ መጠየቁን ከማቅረብ ይልቅ ያልሆኑ ዜናዎችን በማቅረብ ያለውን መንግሥት ስሜት ብቻ በመከተል ሕዝቡን በይበልጥ እንዲያመር አድርገውታል። ሁኔታዎችን በተለያዩ አቅጣጫዎች መመልከቱ የአንድን ሃገር ሕዝብ ከብዙ አደጋዎች ሲጠብቁት፤ አንድ ሕዝብ መዋጋቱና አለመዋጋቱ አይደለም ወሳኙ ፤ ግን የቱን ያህል መደሰቱና አእምሮው ተረጋግቶ ራሱን ለመርዳት መቻሉ ሲሆን፤ ጦርነትን ከማሸነፍ ልቡን ማሸነፉ ሲኖርበት፤ በዚህን አኳኋን ያለን ሕዝብ ምንጊዜም ቢሆን ጠላት ብቻ ሣይሆን ወዳጅ የሆኑ ሃገሮች ሊጠቀሙበት ታሪክ አስተምሩናል። ይህ ሁኔታ በእምስቱ የጠላት ዘመን ታይቷል አሁንም እየተከሰተ ነው። እውነትን ተናግሮ በአንድነት መፍትሔ መፈለግ የሁላችን ሆኖ ሳል ለመንግሥት ብለን የምንተወው ነገር መሆን የለበትም።»

እውነቱም በቃሲም አስተያየት ብቻ ሳይወሰን በየሰብሰባቸው እየተገኘ የሚወያዩባቸውን ጽንሰ ሐሣቦችን ሲያጤነው፤ ሰብሰባቸው ሥነሥርዓቱ ተጠብቆ መደማመጦች ሲኖሩ፤ የሽማግሌዎች ሐሣብ መደምደሚያ ቢሆንም የወጣቱ ሐሣብ ትልቅ ትኩረት ሰጥተውት ያዩታል። ዘለፋ የለም። ወይይታቸው በአከባቢያቸው ስለአለው ችግር ያተክራል። ራሳቸውን ነፃ አውጪ ነን ብለውም አይናገሩም። እንደትልቅ ባሳጋራ አድርገው የሚያውግዙት ቀደም ሲል የወረዳ አስተዳዳሪ የፖሊስ አዛዦች በጊዜውም ከእነርሱ ተገንጥለው በሰፈራ ጣቢያ ተቀምጠው ሰንዱ እየተሰፈራቸው የሚወጏቸውን ክፍሎች ሲሆን፤ «የሶማሌ አቦ» የሚለውን ስም ሊጠሩት አይፈልጉም። ከሶማሌ ምድር ሲገቡ ብቻ ነበር ያንን ስም የሚጠቀሱት። ኦሮሞ የሚለውንም ስም ቢሆን አያነሱትም። ስለደጋው ሕዝብ ሲናገሩ «አርሲ» በማለት ሲጠቅሱ ብዙ ጊዜ ለማገደም ሆነ በብርድ ጊዜ ለመሞቅ ከእንጪት ጋር ክበት ስለሚጠቀሙ ቤቶቻቸው በጭስ ስለሚታፈን ያንን ተመልክተው የቆላው ክፍል የሰየመላቸው ስም ስለሆነ አቦውንም ኦሮመውንም ትተው በአርሲነት ሲጠራሩ፤ በአማርኛ እጭስ ሲሆን፤ ቆለኞችንም «ገሞጂ» በማለት ሲጠቅሷው፤ ከቆላው ክፍል የመጡት «ገሞጂ ቴና» በማለት ሲናገሩ የደገኛው ክፍል ደግሞ«አርሲ ቴና» በማለት ጠቅሰው ሲነጋገሩ፤ ያም የእኛ ቆለኞች የእኛ ደገኞች ለማለት



የሚጠቀሙበት ነው። መሣሪያ ይዞ የሚዋጋቸው ደገኛም ሆነ ቆለኛ በአጠቃላይ «አማራ» ተብሎ ሲጠቀሱ፤ በዚህ ላይ ብቻ ከሶማሊያ ከሚነዛው ዜና ጋር ተመሳሳይነት አለው ።«ኦሮሞ» የሚለውን ስም ከሚያነሱ በግልጽ የሚጠሉትን ቃል «አማራ» ብለው ቢያመሰግኑ የሶማሊያ ወታደሮች ፍቃዳቸው ሲሆን፤ አንድ ግለሰብ ኦሮሞ ነኝ ከለ በሰላይ ስም ከሜዳ ሊመታ ወይም ከመቅድሽ ሲደርስ ሶማሌ ተብሎ በሃገሩ ላይ የሰለለ በመባል እስከ ሃያ ዓመት ይፈረድበታል።በዚህን ዓይነት ተፈርደባቸው በእስር የሚማቀቁ ኢትዮጵያውያን አሉ።

ይህ ሕዝብ እንደወንዴ ቁጥሩ ትልቅ የጦር ኃይል የሚያስልክ ምንም ነገር የለም። ወጣቱ ክፍል በሙሉ መሣሪያ የታጠቀ ስለሆነ ጥይት መተኮሱን ሽብር መፍጠሩን እንደ ጀብደኝነት ቆጥረውት አከባቢውን ማወካቸው አልቀረም። ያንንም እንደትልቅ ችግር በመቁጠር ሺማግሌዎች መሣሪያቸውን እስከማስፈታትና ቀጣት እስከመወሰን ሲደርሱ፤ግን የመንግሥት ወታደር ከመጣ መሣሪያ ይዞን ከአገኙን አይተውንም በማለት ዱሩን መከታ በማድረግ ከራስ በመከለከል ስም ሲዋጉ፤ መውጫና መግቢያ ስለሚያውቁት ጥቂቶች ሆነው በብዙ ወታደሮች ላይ ጉዳትን ለማድረስ እንደሚችሉ ሲችሉሆኖም በትዕግስት በአከባቢው ዘልቆ ገብቶ በግራና በቀኝ በሚነዙት ዜናዎች ሣይደናቆር ጥናትን ሳከናወነ ሰው ምንም ወታደር የሚያስልክ አይሆንም። ብዙ ወታደሩች በብዙ ገንዘብ ቀጥሮ ከመለክ ይልቅ ጥቂት ባለሞያዎችን እንደሥራቸው ውጤት ተከፍሏቸው እንዲሠሩ ቢደረግ በቀላሉ ይወገድ የነበረ ችግር ሲሆን፤ትልቁ ችግር በአስተዳደርና በሕዝቡ መከከል የነበረው ግንኙነት በጣም ውስን በመሆኑና ከመንግሥት የሚሰጡት መመሪያዎች የሕዝቡን ችግር ስለማያፀባርቁ እንቀበለውም በማለት ግጭቶች ሲፈጠሩ ቆይተዋል። ሌላው ቀርቶ የሶማሊያ ሠርጎ ገባች«በሶማሌ አቦ» ስም ከመሐል ሃገር እስከገቡበት ወቅት ድረስ አፄ ኃይለሥላሴ በሥልጣን እንደነበሩ ሲገምቱ «ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚለውን መፈክር ተደጋግሞ ሲነገር ሲሰሙት «ጃኖሆይ ቡስኒ ትቅደሚ ኢረከየኒ» ጃኖሆይን ከዙፋናቸው አውርደው ትቅደምን አስቀመጧትን? በማለት ሲጠይቁ፤ እስከ ፸፪ ዓመተ ምህረት በድሮው ብር ይገበያዩ ነበር። የሚተርከው ስለአንድ ቀበሌ ሕዝብ አይደለም ቢያንስ የሶማሌን ሃገር ከሚያህል መሬት ላይ ስለሰፈረ ሕዝብ ነው። የችግሩን መንስኤ መርምሮ ጥናቶችን በሰፊው አድርጎ መፍትሔ ባለመፈለጉ ፍቃደኝነት ያለው ጥረት በለመደረጉ እነሆ ጦርነቱ ለዘመናት ሲካሄድ ቻለ። መሣሪያ ማንሣትን መንግሥት ያሣየው ሕዝብ በየአቅጣጫው የሚጎርፍለትን ብረት ተሸክሞ ነፃ አውጭ ነኝ በማለት እርስ በእርሱ ጉራውን ለይቶ ሲታኮስ ኖረ። ራሱን በራሱ ቢመራ ወይም መሪውን መርጦ አከቢቢውን የሚያስተዳድር ከሃገሪቱ ሳዕላዊ ማወቅር የሚያገናኘው በሕዝብ የተመረጡ ግለሰቦች ቢኖሩት ለብዙ ዓመት ሲካሄድ የነበረው ጦርነት ሳይኖር ይችል ነበር።

## ፵፯

እንደተለመደው ቃሲምና እውነቱ ከተረኛዋ የቃሲም ሚስት ቤት ቁርሰቸውን የበቶሎ ገንፎ ከቡና ጋር አድርገው ለቡና ለቀማ ቅርጫታቸውን ይዘው ከአትዕክልቱ ማሣ ሄደው፣ቃሲምም የጫቱን ቀንጠብ ቀንጠስ ቀንጠስ አድርጎ በጉንጩ ሞልቶ ለእውነቱም አጣሬራ ከደረገው ሰጥቶት በቅል ከያዙት ውኃ ሎሌ ብለው ቡና ለቀማቸውን ሲያደርጉ፣ ቃሲም ሁለት ቅርጫቶችን ሲሞላ እውነቱ ግን ገና አንደኛውን ለሞምላት ሲፍጨረጨር፣ የቀላውን ብቻ ሲለቅም ቃሲም ግን የጎመራውንም ጭምር ሲለቅም ተመልክቶ፣ ያልበሰለ መሆኑን ቢጠቁመው፣ «ይህ የምታየው ቡና ከጦርነቱ በኋላ ተለይቶ ባለመሰጠቱ፣ የቻለና የቀደመ መጥቶ ስለሚለቅመው እኛም አሁን ጨርሰ እስኪ ቀላ ብለን ብንተወው ተመልሰን ስለማናገኘው መሸማት ነውና የያዝኩት በጣም እንጭጭ ካልሆነ በስተቀር አትተወው።»

«በሚርቃና የምታደርገው መስሎኝ ነበር» ሲለው፣

ሣቅ ብሎ ያም አለበት።

«እንዲህ ከሆነ እንዴትስ ከእኛ በፊት መጥተው አለቀሙትም»

«ብዙ ጊዜ ንብረትን ለማጠናከር የምንሯሯጠው ብዙ ቤተሰብ ያለን ክፍሎች እንጂ እንደ አንተማ ያለው ወጣት አቶማቲክ መሣሪያውን ተሸክሞ ሺቅብ ቁልቁል ሲል የምታየው ነው። እውነቱ ይነገር ከተባለ በትክክለኛው በታና ጊዜ ካልተጠቀሙበት እንደጦር መሣሪያ የሰውን ልጅ አጥፊ የለም። በዚህን በጦርነት ዘመን እንደአየሁት የጦር መሣሪያ የሚገድለው የተተኰሰበትን ክፍል ብቻ ሣይሆን ተኳሹንም ጭምር ነው በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ። የዚህ አካባቢ ሕዝብ መሣሪያ ከመያዙ በፊት በጣም ሠራተኛና ብዙ አምራችም ሐብታምም ነበር። አሁን ግን እንኳንስ አዲስ ልማት ሊጀምር ይቅርና የደረሰ ቡናውን እንኳን መልቀሙ ከብዶታል። ችግር ሲመጣ ይህን ብረት መተኮሱ ይቅርና መሸከሙም እንደሚከብድ ያልተገለጸላቸው ክፍሎች አልታጡም።በተለይ ለዚህ አካባቢ እድገት ጠንቅ የሆኑት ከእኛ ተገንጥለው የሄዱት ክፍሎችና በየጊዜው ተመድበው የሚመጡት የክፍለሃገሩ ባለሥልጣኖች ናቸው። ከነመሣሪያቸው በጦር ሰፈር አስቀምጠዋቸው የእርዳታ ስንዴ ስለሚሠፍሩላቸው ውለው አድረውም ወደ ምርት እንደያሰሟሯቸው ውስጣችንን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ወንበዴዎች እያሉ በማጋነን ለባለሥልጣኖች ስለሚያወሩላቸው እነርሱም ዛሬ ነገ እንዘምትባቸዋል የሚል ዕቅድ ስለሚያራቸው በቅርብ መውጫ መግቢያውን ስለሚያውቁ በእክብካቤ ይይዟቸዋል። ዱሮዎቹም የመንግሥት ወታደር ነገ ዛሬ ውስጣችንን በሚያውቁ ግለሰቦች ተመርተው ይመጡብናል በማለት መሣሪያቸውን ተሸክመው ልማቱን አቁመው በተጠንቀቅ ሲጠባበቁ፣ እንዳንዴ ለመሥራት እንኳን ጊዜ ቢኖር ይህ እንደምክንያት ስለሚቀርብ፣ ጥቂቱ የብዙሃኑ ብረት ተሸካሚ ቀላቢ ሆኗል።»

እውነቱም መልሰ «በካንፕ የተቀመጡት ግለሰቦች ብቻ



አይደሉም የዚህን አካባቢ ጦርነት እንዲቀጥል የሚሹት። ከክፍለሃገሩ አስተዳደሪ እስከ ቀበሌ ሊቀመንበርና ከድሬዎች ጦርነቱን ይፈልጉታል። እንኳንስ ዘንድሮ ገሃድ ወጥቶ በነፃ አውጭ ስም ወገን ተለያይቶ በሚዋጋበት ወቅት ይቅርና ያኔ አልቤን ጠብመጃ ይዛችሁ በዚህን ጫካ በምትሽሎከለኩበት ወቅት በ፲፱፻፶፬እስከ፷፬ ዓመተ ምሀረት ለዚህን አካባቢ ለጸጥታ እየተባለ የሚወጣው ገንዘብ በቀጥታ ከአስተዳደሩ ክፍል ከነበሩት ግለሰቦች ኪስ የሚገባ ነበር። ወታደሩም በሚሰጠው የወር ደመወዙ እንጂ የተለየ አበል አልነበረውም።በአሁንም አስተዳደር ለጸጥታ ተብሎ የሚወጣውን ገንዘብ ልክ ዓምለክ ቁጥር ሰፍር የለውም። እንደማየው ወንበዴ እየተባለ የሚነገርበት ሕዝብ በሰላም የሚኖር ሕዝብ ነው። ንብረቴን አትንኩብኝ በመብቴ ልኑር እንጂ ርቆ ሄደ በሌላው መብት ላይ ጉዳት ሲያደርስ አላየሁም። እንደማንኛውም የሃገሪቱ ዜጋ ሃገሩ ወደ ፣በአንድነቱ እምኖ የሚኖር ነው። በሁሉም አቅጣጫዎች በዚህ ሕዝብ ሊጠቀሙበት የፈለጉ ክፍሎች ስላሉ ታሪክ ይፋረዳቸው ከማለት ሌላ በጊዜው የምናደረገው ነገር የለንም።»

«እውነት ይነገር ከተባለ ከመንግሥትም ከእኛም እየመሰሉ የራሳቸውን ኑሮ ያደበሩ የሚመስላቸው ክፍሎች አልታጡም።ይህንንም ያየሁት ልጆቼን ለማምጣት ከደጋው በወጣሁበት ወቅት፣ እንደኛው ባለሥልጣን በቋንቋዬ ጠጋ ብሎኝ ምን አግኝታችሁ ወጣቹሁስ ምን ተሰጥቷችሁ ተመለሳችሁ? ብሎ ሲጠይቀኝ አንናተን የመሰለ ባህላችንንም ሆነ ቋንቋችንን የምትናገሩ ክፍሎች እውነቱን ተናግራችሁ በሰላም የምንኖርበት መንገድ ከመቀየስ ይልቅ በጥይት በወንበዴ ስም የምታስደበድቡን አይደለችሁምን? በማለት በደም ፍላት ስመልስለት ከአጠገቤ እየተገላመጠ ሄደ።እንዳልከው ግልጽ ያልወጣ ብዙ ነገር ስላለ ታሪክ ወደፊት ያውጣው።

በማንኛውም አቅጣጫ ቢሆን ለሃገሪቱ ምንም የጠቀማት ነገር የለም። ከግራ ከቀኝ ያሉትም መንግሥታት ቢሆኑ ሕዝቡን በእሣት እያጫወቱት ነው። የመሣሪያ አቅራቢዎቹ ሃገሮች ሕዝቦች በተገኘው ገቢ ሕዝባቸው ተደላድሎና ተደስቶ ሲኖር የእኛ ግን ጨርሶ እንዳይጠፉ ቀለብ እየተሰፈረለት መሣሪያ ተሸክሞ መውጋት የሚያበቃው ጉልበት እስከአገኘ ድረስ እየተመገበ ርስ በርሱ ሲጫረስ የምናየው ነገር ነው። በአካባቢያችን እንደምናየው ከቀለብ እህል ይልቅ የጥይት ምርት መብዛቱን ነው። መሣሪያ የሚያቀርቡልንም ሃገሮች የተሸሸለ መሣሪያ ሲያወጡ በመጋዘናቸው ያለውን በሽያጭ መልክ በሃገራችን ለሚገኙት የመንግሥት ተቃዋሚዎችም ሆነ በሕገኛነት ስም ሃገሪቱን በማስተዳደር ላይ ላሉትም ቢሆን መሣሪያ እያጎረፈላቸው፣ መሆኑን የምናየው ሐቅ ነው። ከዚህም አካባቢ ከሴቶች በስተቀር ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆነ ወጣት ውኃ ጥሙንና ረሃቡን ከቻለ ከሶማሊያ መሣሪያ ማምጣትእንደሚቻልነው። ሁለት ሦስቴ ሄደው መሣሪያውን አምጥተው በድብቅ የሚሸጡ ክፍሎችም አሉ። ከላይ ከታች በአንድ መንግሥት የተሠሩ በመሆናቸው እጃቸውን ሰጥተው

የገቡትም ሆኑ የመንግሥት ወታደሮች የሚይዙትን አንድ ዓይነት ስለሆነ፤ እጅ ከሰጡት ውስጥ ወጣቶች የነበሩትንም ከነሙሉ ትጥቃቸው ከታጠቅ ጦር ሠፈር ወስደዋቸው የግራ ቀኝ ትምህርታቸውን ሰጥተዋቸው ለሚን የዘመቱም አሉ። በሁሉም አቅጣጫዎች ሕዝቡ ግራ እየተጋባ ቢሆን፤ ጦርነቱም አገሸግሿታል። ባለማምረቱም በረሃብ ላይ እየወደቀ ነው። ተቀምጦ ለማምረትም በመንግሥት ላይ እምነት ስለጠፋ ብዙዎቹ ንብረታቸውን እየያዙ ወደጎረቤት ሃገር እየተሰደዱ ናቸው። ሃገር ይረጋጋ ይሆናል ብለው የገመቱም ክፍሎች ግማሽ ቤተሰባቸውን ከዚህ ትተው ሕፃናትን ይዘው ሲሰደዱ፤ ሁልጊዜም የሰብል መሰብሰቢያው ወቅት ሲደርስና ሰማሊያ የሄዱት ክፍሎች አዲስ መሣሪያ ይዘው ሲመጡ ጦርነት ሲገመት፤ከመሐል አገር ያለው አስተዳደርም ይብሱን ሕዝቡን የማያርቅ እንጂ የሚያቀርብ መመሪያ የለውም። ዋናው ሕዝቡን የሚያገናኘው ያው አንዱ የሬዲዮ ጣቢያ ሲሆን በዚያም የሚተላለፈው ውሸትና የሌለ ነገር ስለሆነ ይበልጥ የሚያራራቅ እንጂ የሚያቀራርብ አልነበረም።

ለምሳሌ በየከቲት ፷፮ ዓመተ ምህረት በመጠኑም ጦርነቶች ገብ ባሉበት ወቅት፤ መንግሥትም በጦርነት የደቀቀውን የምጣኔ ሐብት መልሶ ለማቋቋም ዕቅድ አውጥቶ መፈክሮች በሬዲዮ መፈክር በጀመሩበት ጊዜና ሊቀመንበሩም የምርት ግቡን መምታቱን ለማየት በየክፍለሃገሩ ሲዞር ሰለ ይተላለፉ የነበሩት ዜናዎች ይበልጥ የሚያስከበልሉ እንጂ የሚየሰባሰቡም ሆነ ልማትን የሚያሰድጉ አልነበሩም። በየክፍለሃገሩም የነበሩት ባለሥልጣኖችም ታተሪ ሠራተኛ መሆናቸውን ለማስመስከር አከፋና ደማ በማንሣት ፊታቸውን ሲያስመቱ። የሊቀመንበሩም የልማት ሥራው አቀያየስ ዘዴ ሕዝብ ከሚያስበው ለየት ያለ፤በጣም ውጥረትና ፍጥነት የተሞላበት ጥናት የጎደለው በመሆኑ ለአዋቂዎቹ ሲያስፈራቸው ተገልጋዩን ሕዝብም ተሰፋ የሚያስቆርጥ በመሆኑ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከመሆን ዱሩ ይሻለናል ተብሎ የተመረጠበት ጊዜ ነበር።

ለምሳሌ በሲዳሞ ክፍለሃገር በትርፍ ጊዜው የንግድ ቤት ከፍቶ ያስነግድ የነበረን ግለሰብ እንደትልቅ ወንጀለኛ በመቁጠር የሃገሪቱ መሪ ግለሰቡን በጥያቄ የሚየራውጥ መግለጫ ቢያንስ ለሁለት ሣምንታት በማንኛውም የሃገሪቱ የመገናኛ ዘዴዎች ሲነገር የሰማ እንኳስ ወደሰላማዊ ኑሮ ተመልሶ ለልማት መሰለፍ ይቅርና በቅርብ የሚሰሩትንም ከፍራቻ እንዳር የሚያስኮበልል ነበር።

የሃገሪቱ መሪ እንድን የበታች ሠራተኛ እንደጥፋተኛ ማቅረቡ ብቻ ሲያየው ፤ግን የእርሱን ንግግር ያዳመጡት በነጋታው ምን እንደሚሠሩ አስቀድሞ ተገንዝበት ቢሆን ባሳደረገው ነበር። ይህንን የሰሙት የልማት ክድሬዎች የሚያስከትሉትን ጥፋት አልተረዳውም። ቀደም ለታቦታት ንግሥ «የማርከስን» «የኢንጂልስ»ና«የሌኒን» ፎቶ ተሸከማችሁ «ለገብሬልና» «ለቁዱስ ጊዮርጊስ» ንግሥ ውጡ እያሉ ሕዝቡን ያስቸግሩ የነበሩትን ዓይነቶች እንደ ጎጃሙ «ክፍሚማው»ና



እንደ አሣአናው «ጴጥሮስ» ያሉ ክድሬዎች በሃገሪቱ ውስጥ ሺ መተ ሺ ስለነበሩ ያንን የሊቀመንበሩን ንግግርና ዘለፋ እንሱም በነጋታው በቀርብ በሚያገኟቸው ሠራተኞች ላይ መጠቀም ሲጀምሩ አብሯቸው የሚቆየውን እግዜር ይወቀው።

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ማድረግ የሚችለውንና የማይችለውን ተግባር በዘርዘር በሕግ መንግሥቱ ተረቅ የወጣ ባለመሆኑ ለአደረገው ስህተት በድንጋጌ መታረም ሲኖርበት በበታው ተገኝቶ በአንድ ቀን ውሳኔ መስጠት በዚህን መንስኤ ለሚያስከትለው ጥፋት ተጠያቂው ማን ይሆን? ለወታደር ትዕዛዝ መስጠትና የልማት ዕቅዶችን ማውጣት እጅግ በጣም የተሳዩና የተለያየ የሞያ እውቀት የሚጠይቁ ሲሆኑ፤ሊቀመንበሩን በጊዜው ያሰምኑት የነበሩት እርሱን የሚያሞክሹና የጣፈጡ የክድሬዎች ቃላት እንጂ ትክክለኛ ተግባር አልነበረም።

ለምሳሌ ከነዚያ አረሙም ኩተኳተውም ላይ አልን ነበርን የሚሉትን ባለሥልጣኖች ያ ሁሉ ቀርቶ መቼም ደፋር ነው የሃገሪቱስ ይቅር ይህን ውፍረታችሁን ለመቀነስ የጊር አትክዕልትስ አልምታችሁ ታውቃላችሁን? ብሎ ቢጠይቃቸው ከዚያን ከወቀሰው ሠራተኛና ካመሰገናቸው ባለሥልጣኖች የትኞዎቹ ጥፋተኛ እንደሆኑ ማወቅ ይቻል ነበረ።

ሊቀመንበሩም በሁሉም የሥራ መስኮች ላይ ተሰታፊነቱን በተግባር ሲገልጽ ግን በአስከተለው ውጤት አልባነት ተጠያቂ ላለመሆን ሌሎችን በጥፋተኛነት በማቅረብና የሞት ፍርድ እንዲፈጸምባቸው በማድረግ ገልጾታል። ሁኔታው ፍርደገምድልነት ይመስላል። ያም ሆነ ይህ ሕዝቡም በቅርብ ሊቀመንበሩን እያወቀው ሲመጣ እየሸሸው እንጂ እየቀረበው አልመጣም። ይጎበኛቸው ከነበሩት ክፍለሃገራት ገብ ብለው የነበሩት ጦርነቶች እየተፋፋሙ ሲመጡ፤የመንግሥት ቀለብተኛ የነበሩት ወገኖች በውጥረት ተይዘው ለልማት ከሚሰለፉ ይልቅ ጦርነቱ እያስፈራቸውም። የሚያስሙት በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ስለሆነ የመሥራት ፍለጎቱ የላቸውም።

የሚሰፈርላቸው ቀለብ ወደማለቁ ሲቃረብ ወንበዴዎች ለማጥፋት አሰሳ እንወጣለን በማለት የተወጊዎችን ኃያልነት በመጥቀስ ሲያቀርቡ፤ በአካባቢው የነበሩትም ባለሥልጣኖች ችግራቸው ስንት ኮንታል እህል ተመረተ የሚለው ጥያቄ ሲቀርብ እንጂ በጦርነቱ ስንት ሕዝብ ሞተ ንብረት ወደመ ስላልሆነ ፤ ወንበዴዎች መጡ የሚለው ደስታቸው በመሆኑ ሕዝቡን ለሌላ ጦርነት ለማስተባበር ሽረጉዳቸውን ያደርጋሉ።

ያ ሊቀመንበሩ ያየው እርሻ ዘር ተገኝቶ መዘራቱን ዓምላክ ይወቀው ዘሩ በካንፕ ለነበሩ ቀለብ ተሰፋሪዎች በቅርብ ይተካል በሚል ስም ተሰጥቶ፤ ከዚያን በኋላ የልማትን ጉዳይ የሚያነሳ አይኖርም። የዓመቱ የልማቱ ሪፖርት በጸጥታው ምክንያት ልማቱ ሊፋጠን

አልቻለም። ወደደም ጠላም ሕዝቡ የጦርነት ባህል እንጂ የሥራ ባህል እንዲኖረው አልተፈለገም። በዱርም ያሉት ከሌላ የመጡ አይደሉም። እነርሱም ቢሆኑ በተለይ ወጣቱ ክፍል የደረሰውን ቡና ለቅሞ ከችግር ከመውጣት ይልቅ በነፃ እውጪ ስም መዋጋቱን ሲፈልጉት፤ በሁሉም አቅጣጫ የሥራ ጥላቻ አለ።



## ፵፰

ለመጨረሻ ጊዜ ወንበዴዎችን ለማጥፋት ተብሎ ከዱረኞቹ ተገንጥለው በነበሩ መሪነት ጠቅላላው ሕዝቡ ላይ ጦርነት ተከፍቶ፤ አቤቱን ማቃጠል ከብቱን መዝረፍ ደረጃ ሲደረስ፤ ዱረኞቹም ቀደም ይይዙት የነበረው የከላሽከቮ ጠብመጃቸውን በአዲሱ ማለት እነርሱ በሚጠሩት ስም የታወቀውን «ሚትሮቭ» የሚለውን የፈረሰይ መሣሪያ ገና ማምጣታቸው ስለነበር ያንን እንደ እሳተ ጎሞራ እሣት የሚተፋውን እንደመትረየስ የሚሞሆውን ብረት ለመፈተሽ አጋጣሚ በማግኘታቸው እነርሱም ጦርነቱን ወደዱት። ደግነቱ ያመረቱትን ምርት እየተመገቡ መዋጋታቸው እንጂ በልመና እህል የሚዋጉ ቢሆን ኖሮ ችለው የሚያነሱት መሣሪያ አልነበረም። ወገን ለይተው በጠብመጃ ገና የሚጫወቱ ሲመስል፤ ከገራ ተቀኝ ፉከራና ስድብም አለ። ዱረኞቹ ለንብረታቸው ትልቅ ቦታ ስለሚሰጡት ያንን ላለማስነካት በሚያውቁት አካባቢ መሽገው ሲከላከሉ፤ሴቶቻቸውም ከጎናቸው ተሰልፈው ወንድን የምታሳድግ ሴት ግመላችን ከምትሞት እናተ እለቁ በማለት የማበረታቻ ቃላታቸውን ሲሰነዝሩ፤ እውነታቸውን ነው ምንም ቢቸግራቸው ሴት ግመላቸውን አውጥተው አይሸጧትም ወይም አርደው አይበሏትም። ሴት ግመል ከሃገር ትመሰላለች።

በአካባቢው እሰሳ ብሎው ከወጡት ክፍሎች ብዙ ሕዝብ አለቀ። የሃገሬው ሕዝብ መውጫ መግቢያውን በሚገባ ስለሚያውቁት ያንን የሚከባከቡለትን በቅፍ የማይሞላውን ዘፍ መከታ በማድረግ ብዙ ነፍስ አጠፉ። በነጋታው በብሔራዊ ሬዲዮ ጣቢያ ለእሰሳ የወጣው ጦር በአካባቢው የሚገኙትን ወንበዴዎች አጥፍቶ የገበሬ ማሕበርን አቋቋመ በማለት ተነገረ።እውነቱና ቃሲም ከሬዲዮ ዜናውን ያዳምጡ ስለነበር ቃሲም እውነቱን «ተመልከት ይህን ውሸት ከዚህ ሳልነበረ ሰው እውነት ይመስላል» በማለት እየተገረመ እየደጋገመ ያነሣዋል።

«እውነቱም ወሸት ስትሰማ የመጀመሪያህ ይሆናል፤»ብሎት ጣቢያውን ወደሶማሊያው የአርመኛው ቋንቋ(የሶማሌ አቦ) የሬዲዮ ጣቢያ ለውጦት ሲያዳምጡ የአርነት ተዋጊዎች «የአዲስ አበባውን የአማራውን መንግሥት» ወታደሮች ድባቅ መትተው ብዙ በታዎችን አስለቅቀዋል፤የሚለውን ዜና ሲሰሙ እውነቱ ወደቃሲም ዞር ብሎ «ይህንን ውሸት ምን ትለዋለህ» ሲለው፤ «የነዚህንማ ቀድም አንስተን ተናግረነዋል፤ መደጋገሙ እየሰፈልግም ብሎ» መለሰለት።ያም ሆነ ይህ የዉረሱትም ሆነ የተዉረሱት ፤ ሁሉም ያአንድ ሃገርና አካባቢ ሕዝቦች ሲሆኑ ጠብንመጃውም ጥይቱም በውጭ ሃገር ጠብቶች የተሠራ ነበር። ጦርነት ተከሄደ በነበረባቸው አካባቢዎች የሚኖሩት ሕዝቦች ውሎ አድሮ የመንግሥት ወታደር መጥቶ ያጠፋናል ብሎ በመፍራት ወደመንግሥትም እጃቸውን ሰጥተው ለመግባት አስተማማኝ ነገሮችን ባለማየት ሃገራቸውንና ቀያቸውን እና አድርገው በሰው ሃገር በስደተኛነት ለመኖር ስንቃቸውን መሰነቅ ሲጀምሩ፤ሽማግሌዎችና

እሮጊቶች ሲቀሩ ጉልበት ያለው በሙሉ ከሃገር ለመውጣት ተነሳሳ። ቃሲምም የአረጁ እናቱንና የሙት ልጆቹን ትቶ ላለመሄድ ወሰኖ እውነቱን ግን ከሕዝቡ ጋር ሊልከው እንደአሰበ ያጫውተዋል። «እንደምታየው የመንግሥት ወታደር በየጊዜው እየመጣ ጦርነት የሚከፍት ከሆነ ዘመደቻቸው የሞቱባቸው ክፍሎች መበቀያ ሊያደርጉህ ሲችሉ፤ በተጨማሪም ካንፕ የገቡት አብዛኛው ክፍሎች ከደጋው ሕዝብ ስለሆኑ እንኳንስ አንተን እኛንም በጥርጣሬ አይናቸው ማየታቸው አልቀረም። ይህ ቅራኔ ሰፍቶ አንድ ቀን በመካከላችን ግጭት መፈጠሩ የማይቀር መሆኑ አያጠራጥርም። በየጊዜው ከሚደረጉት ጦርነቶች መልስ የከፉ ቅዋሜዎች በደጋው ሕዝብ ላይ ሲሰነዘር፤እኛም ደገኞቹ ችግሮን እንጅ ጦርነቱን እንደማንፈልገው ቆለኞቹ ስለሚያውቁት በእኛ ላይ ጠበቅ ያለ እምነት የላቸውም። እኛ ቢያንስም ቢያድግም ለዘመናት በአንድ በታ ተቀምጠን ትውልዳችንን መሥርተን፤ የምንጠራው ሥፍራ አለን። እነርሱ ግን ከበታ በታ ስለሚኖሩ የአንደኛው በታ መጥፋት አይሰማቸውም። ያም ሆኖ የደርግ መንግሥት ካንፕ በሚል ሥም ከአረዳችን ባይነቅለንና ባለችን ይዞታላይ ያለተጽኖ ብንኖር ከዱር የሚጨምረን ምንም ምክንያት ባልኖረ፤ ይህም በመሬት ላይ ለመኖር የምናቀርበው አማራጭ እንጂ ሌላ የምን ጠይቀው መብት የለንም ማለቴ አይደለም። እንዲህም ከቀጠለ በመካከላችን ጦርነት መነሣቱ የማይቀር ቢሆንም የእኛ አማራጭ በነሱ እጅ ከመውደቅ የጠላነውንን መንግሥት ምህርት ጠይቀን መመለሳችን አይቀርም። የባሰብንም ሃገሪቱን ትተን እንወጣለን። አንተም ከሁለት ያጠህ ከምትሆን ብትሄድ እመርጣለሁ። ግን ከደገኛው ክፍል የሆኑ ሰዎች ከአገኘህ አብረሃቸው ብትመለስ አይከፋም። መሪውም ጥሩ ሰው ነው የሚያቀርብህ ከሆነና ማሠልጠኛው በታ ከአስገባህ አብረህው መሣሪያ ይዘህ ተመለስ። ለአንተም ለሞራልህ ጥሩ ነው። ሕፃናቱ በሙሉ ብረት ሲሸከም አንተ ዱላ የምትይዝበት ምክንያት የለም። እንዴ ከዚያ ደርሰህ ከመጣህ ሁሉም ስለሚያሙኑህ ቢያስ አንድ ነገር እስከሚለወጥ ከዚህ መከረም ትችላለህ «አላህ» የመንግሥትን ዐይን ከያዘልን። ካልሆነም አንተን የመሰሉ ተማሪዎች ከሶማሊያ አሉ ስለሚባል ከዚያ በሰደት ልትቆይ ትችላለህ። ያን እንግዲህ ያንተ ምርጫ ነው።»

እውነቱም ቃሲም ባቀረበው ሐሣብ ተስማምተው ፤ ለሚመጣው ሰብል ለዘር ከራይ ሠርቶ የሰበሰበውን በቆሎ ለሶማሊያ ጉዘው እንዲያዘጋጁለት ቃሲም ለሚስቶቹ ነገሯቸው፤ እነርሱም በቆሎን በእጃቸው በመፍጪት ስንቁን መሰነቅ ላይ ሳሉ፤ የሚሊሻ ጦር መልመላ ሸሽተው የመጡ ወጣቶች በአካባቢው ተጠልለው ስለነበር እውነቱንም ከእነርሱ አስተዋውቆት፤ግለሰቦቹን በመቅረብ እርሱን አጋጥሞት የነበረውን ችግር በመዘርዘር እርስ በእርሳቸውም አጥብቀው መፈቃቀድ እንደሚኖርባቸው ጠቁሞ እውነቱንም እንደወንድማቸው እንዲመለከቱት አጥብቆ ተማጥኗቸው፤ «መንገድ ቢሞትም እንኳኳን በእስልምና ሃይማኖት መሰረት «ፋትያ» ደግማችሁ አፈር አልብሱት። የሚያጋጥማችሁን ችግር አውቀዋለሁ። ጉዞው በጣም ረጂምና ውጣ



ውረድ የበዛበት ነው።በተለይ እኛ ደገኞች የቆላውን ሐሩር ስለማንቋቋመው አስቀድመን በውኃ ጥማቱና ረሃቡ ስለምንፈታ ይህን እንደ ድክመት ቆጥረውብን ቆለኞቹ ሲንቁን፤ እነርሱ ግን የግመል ወተታቸውን ከጠጡ ያለምግብ ሁለት ሦስት ቀናት ለመጓዝ ችሎታ አላቸው። ለሁሉም እውነቱን በአደራ የተረከብኩት ስለሆነ ለመሪው አጥብቄ እነግረዋለሁ። ግን ተመልሣችሁም ለምምጣት እቅድ ካላችሁ አብራችሁ ተመለሱ።» ሌቱን ሲመክራቸው አድሮ በነጋታው ጀንበር ዘቅዘቅ ስትል የአካባቢው ተጏዦች የሚገናኙበትን ሥፍራ የሚመራ መልከተኛ ስለመጣ እውነቱና እምበቱ ወጣቶች ስንቃቸውን በትከሻቸው ተሸክመው ተነሱ።የቃሲምም ቤተሰቦች እውነቱን ለመሸኘት ከየቤታቸው ወጥተው፤ልጆቹም በወገቡ ተጠምጥመው ለቅሶ ሲሆን፤ የቃሲምም እናት ለሙን ሣር ነጭተው «ልጄ ስለአልወለድሁህ ደስ ይለኛል፤ባዕድ ስለሆክ አረሳህ ይሆናል፤በዚህ ራሴን አጽናናለሁ፤ብትመለስም እንኳን እንገናኝም፤ እንደምታየው አርጅቻለሁ፤ በአካባቢያችን ያለው ችግር እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አይሄድም፤ ለሁሉም «አላህ» አንተን ከአሰብከበት በታ ያድርስህ» ብለው የነጩትን ለምለም ሣር በእጁ አሲዘውት እንባቸውን እየጠረጉ ወደቤት ተመለሱ።

ቃሲምና ሚስቶቹ ስንቁን እየተረዳዱ ወንዙን ካሻገሩት በኋላ «ሶማሊያ ሲደርስ የሚወዱትን ዘፈን እንዲመርጥላቸው ነግረውት ተመለሱ።» ቃሲምም ስንቁ ከሚጫንበት አካባቢ ድረስ ሄደ እውነቱን ከሌሎቹ መንገደኞች ገንጠል አድረጎ ወስዶት «አታስብ ለዋናው መሪ ስለአንተ ማንኛውንም ነገር ነግሬዋለሁ፤ ምናልባት ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ ሰዎች ሊያጋጥሙህ ስለሚችሉ፤ብላ የሚሉህን ምግብ ብላላቸው ፤በተለይ እስላም ያረደውን አልበላም በማለት ግትር አትበል። መጠሪያ ስምህን ለውጥ ቢሉህም ለውጥላቸው እንተነትህን አይለውጠውም» ብሎት እጁን ጠበቅ አድርጎ ጨብጦት ተለያዩ።

## ፵፱

እውነቱና እምሰቱ የመንገድ ጓደኞቹ ስንቃቸውን በአንድ ግመል ላይ ጭነው ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ ጠቅላላው መንገደኛ እንዲገናኝ ቀደም ሲል ከተወሰነው ሥፍራ ደርሰው፤ መንገደኛው እስከሚሰባሰብ ተብሎ ለሁለት ሳምንታት ከዚያን ይከርማሉ።የሕዝቡን ወደ ሶማሊያ መሄድ የሰሙት የሶማሌ ነጋዴዎች የሃገራቸውን ሽልንግና ሸቀጥ ይዘው መጥተው ከሥፍራው ተገኝተው ልብስ ሰዓት ሲጃራ ወዘተ ለገበያ ሲያቀርቡ፤ ሃገሬውም የእርሻ ምርታቸውን ማር፤ ቡና ቅቤ ከብት የነብር ቆዳ አቅርበው ሁለቱን ሳምንት በመገበያየት ተከረመ። በጊዜው ዋና የመገበያያው ገንዘብ የሶማሌው ሽልንግ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብር ስድስት ጊዜ በዓለም እቀፍ ምንዛሬ የሚያንሰው ሽልንግ ከዚያን ግን መሣ ለመሣ ሲለወጥ፤ አዲሱ የኢትዮጵያ ብር ከአሮጌው እኩል ሲገበያዩበት ግን የንጉሡ ፎቶ ያለበት ብር ይበልጥ ተቀባይነት ነበረው።

የእውነቱና የጓደኞቹ ያለ ፍላጐታቸው አስራ አምስት ቀን በመቆየት ምክንያት የያዙት ስንቅ ከሃገር ሳይወጡ ተገባደ፤ ለጉዞአቸው ለማትረፍ በየመንደሩ እየዞሩ ለዕለት መለመኑን እንደአማራጫ ወሰዱት

በመጨረሻም የሶማሊያና የሃገሬው ነጋዴዎች፣ ስደተኞች ይዘውት የሚሄዱትን የሥጋ ግመል፣ ቡናና የነብር ቆዳ አዘጋጅተው፤ መንገደኛው በቡድን ተከፍሎ እንደሕዝቡ ቁጥር የጭነት ግመል ተመድቦ፤ ከአንድ ቀን ቀደሞ ከሚጠብቃቸው ከመሪው ዘንድ ለመድረስ ጉዞ ሲደረግ፤ የሚያቋርጡት ወንዝ ሞልቶ ስለነበር ዕቃና ሕዝብን በማሻገር፤አንድ ቀን ስለባከነ መሪው ካለበት ሥፍራ በሁለተኛው ቀን ደረሱ።እርሱም ለበታች ሠራተኞቹ መመሪያ ሰጥቶ ከአንድ ቀን ጉዞ በኋላ ከሚያቋርጡት ወንዝ ላይ እንዲገናኙ ቀጠሮ ተሰጣጥተው በአንድ መትረየስ ታጅበ በሌላ አቅጣጫ ሲሄድ ብዙሃኑ መንገደኛም በጠዋት የበቆሎ ቆሎውን ከቡና ጋር ቁርስ አድርጎ በተመደቡለት ግመሎች ላይ ስንቁን ጭኖ ጉዞ ሆነ።

ደጋውን ሃገር እየለቀቁ ወደቆላው ክፍል ዘቅዘቅ ሲሉ በተናጠል ይሰቡ የነበሩት ግመሎች አንዱን በሌላው ላይ አቀጣጥለዋቸው አንድ ሰው እየሣባቸው አህያና በቅሎዎች እየተነዱ በአንድ መትረየስ ታጅበው ረጅሙን ጉዞ ከቀን ወደቀን ሲጓዙ፤ጠዋት ቡና ተጠጥቶ ቆሎ ተበልቶ የጀመረ የፀሐዩ ሙቀት ሲግል ታይቶ የኩሬ ውኃ ካለበት ከፊታቸው ከሚመጣ መንገደኛ ተጠይቶ፤ ከኩሬው ሲደረስ ጭነት ተራግፎ፤ የበቆሎ ቂጣ ተጋግሮ ቡና ተፈልቶ ተበልቶና ተጠጥቶ፤ለሁለት ሰዓት ያህል እረፍት ተደርጎ ሁለተኛው ጉዞው ቀጥሎ የሚያበቃው የማታው ስግደት ሲቃረብና ጀንበሯ ዘቅዘቅ ስትል ነበር።

በጉዞው ለእውነቱ በጣም አስቸጋሪ የሆነበት ቆሎ መቁላቱም



ቂጣ መጋገሩም፣ ግመል መሳቡም አልነበረም፤ ግን ግመሎችን ቆንጥርና የግራር እሾህ ከበዛበት ጫካ ውስጥ ሰብስቦ ወደሠፈር ማምጣቱ ነበር።

ለአንድ ሣምንት በዚህን ዓይነት ከተጓዙ በኋላ የጉዞቸው አማካኝ ስፍራ ስለደረሱ ጠቅላላ ሰፈራ ተደርጎ፤ በነጋታውም «የኢድ»በአል ስለነበር ለጠቅላላው ስግደት በኩሬው ውኃ ሰውነታቸውንና ልብሳቸውን ሲያነጹ ውለው፤ ለበዓሉም የሥጋ ከብት ለመግዣ መዋጮ ተሰበሰበ።

እውነቱ ግን በኪሱ ቤሳ ቤስቲህ እንዳልነበረው፤ የሚያውቁት መንገደኞች አዋጣ ብለው አልጠየቁትም። ለስግደቱም ዝግጅት እንዲያደርግ ያስቸገረው ሰው ቢኖር ጣሂር ብቻ ነበር።

ጣሂር እውነቱ ከሚኖርበት አካባቢ ዘመድ ለመጠየቅ ከዓለም ማያ ከተማ መጥቶ ሳለ በመንገድ ላይ በጥርጣሬ ኪሱን ሲበረብሩት በነበረበት አካባቢ ገበሬ ማሕበር የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያና ለአራተኛው የአብዮት በዓል መታሰቢያ ከኩባ ወታደሮች ጋር የተነሣው ፎተግራፍ ስለተገኘበት በሰላይ ስም ተይዞ ወደሶማሊያ የሚሄድ ሲሆን ታማኝነቱን ለመግለጽ የማያደርገው ነገር አልነበረውም።

የሃይማኖቱ ተከታይ ያልሆነውን እውነቱን በማግኘቱ የእርሱን ፈለግ እንዲከተል ሲያስቸግረው፤ሁኔታው ከቁጥጥሩ ውጭ ስለሆነበት ጣሂርን «ከገበሬ ማሕበር ውስጥ የለመድከውን እወደድ ባይነትህን ተው፤ እስከዛሬ በደህና አብሬ ከኖርኪቸው ሕዝቦች አታጣላኝ» የሚል ኃይለ ቃል ስለተናገረው ነገሩ ከመሪው ደረሰ።

መሪውም ልዩነት የፈጠሩትን ጉዳይ ተመልክቶ የሚታየውን ሐሣብ ያቀርብላቸዋል። «ሰው ስለሆን እንሰሳታለን እውነተኛ አማኝ ነን እይደለንም በማለት መናገር እንችልም። ሆኖም ሁላችን አንድ ዓላማና የጋራ ችግር አለን ይሄውም በሰላም በሃገራችን ላይ መኖር ያለመቻላችን ነው፤ ከዚህ ባእሸገር ያሉት ጠቃቅን ነገሮች ሊያለያዩን ባልተገባ፤ ጣሂርም አንተ ታገለግላቸው የነበሩት መሪዎችና እኛ ትልቅ ልዩነቶች አሉን። እኛ እንደአገኘንህ አንድ የእኛ ሰው ገበያ ወጥቶ ቢገኝና ከዚህ አካባቢ መሆኑ ቢታወቅ ምን እንደሚደርስበት አንተም ውስጡ የነበርክበት ስለሆነ ያንን አንተው በራስህ መልሰው። ሌላው ደግሞ ይህን ግለሰብ ከአንተ ቀደም ብለን እናውቀዋለን ችግሩ ያለመተዋወቃችሁ ስለሆነ በሚገባ ተዋወቁ ከዚያን በኋላ ዛሬ ልዩነት የፈጠረባችሁ ነገሮች የቱን ያህል አገብጋቢ መሆን እለመሆኑን ትረዱታተላችሁ።»

«የኢድ አልፈጥር»በዓል ተከብሮ በማግሥቱ እንደወትሮው ጉዞ ሆኖ፤ ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ ወደ ሶማሊያ ግዛት እየተቃረቡ ሲሄዱ የፀሐዩ ግለት እየጨመረ ሲመጣ የሚጠጣም ውኃ እጥረት

ሲፈጠር፤ በመንገድ አካባቢ ከሚገኙ መንደሮች የሚሸጥ ወተት ሲጠየቅ በኢትዮጵያ ብር እንጂ በሶማሌ ሽንልግ እንለውጥም በማለት ሲመልሱት፤ ከሽንልግ ይልቅ ትንባሆ ለወተት መለወጫ ሲመረጥ፤የኢትዮጵያው ብር በጣም ተፈላጊነቱ ሲጨምር መሐል ሃገር የተዘረዘረው የሶማሌ ሽልንግ ተቀባይነት ያጣል።

የጉዞው ቀን እየጨመረ ሲሄድ የያዙት ስንቅ ወደማለቁ ሲቃረብ አብረዋቸው ከሚጓዙት ነጋዴዎች ግመሎችን ለመግዛት ሲጠይቁ ከሚገመተው በላይ ዋጋቸው ንሩ፤ ሃገር ቤት አራት መቶ ሽልንግ ለተገዛው ግመል እስከ ስድስት ሺ ሽልንግ ሲጠይቁ፤ የነበረው አማራጭ ከጫኗቸው ግመሎች ውስጥ ደከማውንና ያረጀውን አይቶ ማረድ ወይም በያዙት ነገር በሙሉ ወተት እየለወጡ መጠጣት ነበር። አጋዴዎችን አምኖ በተናጠል ወደ መንደራቸው ጎራ ማለቱ ዘርፈያን ወይም ገድያን ስለሚያስከትል ረሃቡ ቢጠናም ውኃ ጥሙም ቢያገበግም ችሎ መጓዙ ሲመረጥ፤ አንዳንዶቹም የሚወርደውን የጨው ውኃ በመጠጣት ይበልጡን በጥሙ እየተቃጠሉ ከተጓዡ ተነጥለው የቀሩም ነበሩ።

ጠቅላላ ሠፈራ ከሚደረግበት ሥፍራ ቀድሞ ለመድረስ የሚጠጣና የሚበላ ምግብ አግኝቶ ከረሃቡና ከጥማቱ ለመርከት ባላቸው አቅም በሙሉ ሩጫቸውን ሲያደርጉ፤የእውነቱም የመንገድ ጓደኞቹ ቃሲም በመከራቸው መሠረት ተጠባብቀው ከሰፈራው ሥፍራ ደረሱ። የሰፈሩትም ዳዋ ወንዝ አፍፍ ከኢትዮጵያ ክፍል ሲሆን፤ በአካባቢው የመንግሥት ወታደር ሊኖር ስለሚችል በተቻለ መጥን ጥንቃቄዎች እንዲደረጉ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ፤ የሚነደው እሣት እንዲዳፈን ተነገሮ፤ሁሉም በጣለው ዝናብ ምክንያት ብርድ እየተሰማቸው ረሃቡ እየመኾለጋቸው እሰላቸውን ተከናንበው በመኝታቸው ላይ ተቀምጠው መተከዝ ሆነ። ባጋጣሚ በጣለው ዝናብ ምክንያት የተደሰቱት የአካባቢው ሕዝብ የደስ ደስ በትልልቅ የብረት ድስቶች ሻይ አፍልተው መስተንግዶ ሲያደርጉላቸው እነርሱ ሲመጡ ሁሌ ዝናብ እንደሚጥልላቸው ጠቅሰው እናንተ ሕዝቦች እርጥቦች ናችሁ በማለት ሁኔታውን ያደንቃሉ። ;pi5

በነጋታው ሕዝቡ በዳዋ ወንዝ ላይ በተጠለጠለው ታንኳ ተሳፍሮ ከሶማሊያ ግዛት እንዲሻገር ሆኖ፤ግመልና የጋማ ከብቶችን ጭምር በታንኳዋ ላይ እንጠልጥለው ካሻገሯቸው በኋላ ምሽቱ ሲጀምር ለዘለቄታው ከሚከርሙበት ሥፍራ ለመድረስ በመንገድ አዋቂ እየተመሩ በጨረቃዋ ብረሃን እየተረዱ ለአራት ሰዓት ተጉዘው፤ወደሥፍራው እየተቃረቡ ሲመጡ፤ሥፍራው በኤሌትሪክ መብራት የሚገለገል ከተማ ይመስል ነበር። ግን ከዳስና ከጭራሮ ቤቶች ውስጥ ይበራ የነበረው ፋኖስ ነበር ድምቀትን የሰጠው። ቀርበ ሲታይ ግን ከዘንባባ እንጨት የተሰሩ ጎጆዎች ነበሩ።



## ከ ጉረቤት ሃገር

በቀኑ የገቡት ስደተኞች የሰፈሩት ከመሐል ሲሆን ከምዕራብና ምስራቅ ኢትዮጵያ የሄዱት ግራና ቀኙን ሠፍረው ይገኙ ነበር።

ጭነቱ ተራገፈ እሣት ተቀጣጠለ መንገደኛው በቡድን ተከፈሎ የሚነደውን እሣት ከበው ሲሞቁ የሚበላ ነገር ግን የለም። ጠዋት ከእንቅልፋቸው ሲነሡ ጥቁር ውኃ እንደቀመሱ ነበር።

ከሦስት ዓመት በፊት መሣሪያ ለመውሰድ መጥተው የነበሩት ግለሰቦች በዚያን ወቅት የተደረገላቸውን መስተንግዶ ከዕለቱ ጋር በማወዳደር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመጡት ሲያጫውቷቸው፤በዚያን ዘመን ተቀብለዋቸው የነበሩትን የሶማሊያ ከፍተኛ የጦር አለቆችን ስም ሲጠቅሱ፤ የተጣለው የግመል ፈሪዳ፤ የተቀቀለው ሩዝ፣ የተቃመውን ጫት የቀረበውን የሲጃራ ዓይነት ሲያስታውሱትና በዕለቱ ግን የሚጠጣ ውኃ እንኳን ጠፍቶ ረሃብም እየተሰማቸው በባዶ ሜዳ ላይ ድብዳብ እንጥፈው መተኛታቸው፤ ወደፊት የሚጠብቃቸው ተጨባጭ ሁኔታ መሆኑን ሲረዱት «በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መሣሪያ ከልሰጡን ወደሃገራችን እንመለሳለን» በማለት ሮሮአቸውን ማታውኑ ማሰማት ጀመሩ። «በየጊዜው በዚህን ደረቅ ብረት እያታለሉን የተደለደለ ኑሮ እንዳንኖር ይጫወቱብናል። በብረት ሰላምና ነፃነት ቢገኝ ኖሮ እስከዛሬ ከዚህ የተጋዘው መሣሪያ ባስገኘልን ነበር። የፈለግነው ነፃነትና ሰላም ቀርቶ ያገኘነው ጥቅም ቢኖር ረሃብና ባርነትን ነው። ባናውቀው እንጂ ያቀርቡልን የነበረው ግመሉም ሆነ ጫቱ ከሩዙ በስተቀር ከሃገራችን የተመረተ ነበር። ምን ያደርጋል ተስማምተን ማደርና ጥሩ መሪ ማጣታችን ሸቅብ ቁልቁል እንድንዋትት አድርጎናል። ችግሮን እንጂ መች የባዕድ ሃገር ከሃገር ያስመርጥ ነበር?» በማለት በእስተሳሰብ በሰል ያሉት አዛውንቶች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ።

መሪው በተናገረው መሠረት በአካባቢው እንደነሱ ሠፍረው ከነበሩት ሕዝቦች ድርሻ ለጥቂት ቀናት የሚሆናቸው ራሽን በሕዝቡ ቁጥር እንዲወጣ ሲያደርግ፤ ግን ለአስራ አምስት ሰው ለምሳ ሦስት ኪሎ ግራም ሩዝ ለአራት ጥሬ ማሽላ ለአንድ ሰው አንድ ፍንጃል ሲመደብ እንድ ኩባያ ሻይ ለቁርስ እንደሚሰጥ ተነገረ። ይህም ቋሚው የምግብ ፕሮግራማቸው ነበር።

ዘውትር ጠዋት ሻይ ከመጠጣቱ አስቀድሞ ማንኛውም ሰው በግምት አራት ኪሎ ሜትር ርቀት እንዲሮጥ ተደርጎ፤ ከዚያ መልስ ተቶጥረው የሰልፍ ልምምድ ሲያደርጉ፤ ሰልፉ ግን በሶማሌኛ ስለነበር ቋንቋውን ለማይናገሩ ችግር ፈጥሮ ነበር። በሰልፋቸው ልምምድ በተቻለ መጠን እግሮችን ወደ ላይ ማንሣትን ስለሚጠይቁ ግመል አልበው ለማያውቁ ስለሚያስቸግር በተለይ ለእውነቱ ችግር ፈጥሮበታል ። አስልጣኞቹም ቀርበውት «ግመል አልበህ

አታውቅምን?» በማለት ጥያቄአቸውን ያቀርቡለታል።

ከሰልፍ መልስ ሻይ ተጠጥቶ ከዛፍ ወይም ከደተኛው ከሠራው ዳስና ጉጆ ውስጥ ይተኛል። ምስ ሦስቱ ኪሎ ግራም ሩዝ ለአስራ አምስት ተበልቶ የፀሐዩ ሙቀት ቀዝቀዝ ማለቱ ታይቶ የፈለገው ለዋና ከጁ ወንዝ ይወርዳል።ያም በሰፈራው ጣቢያዎቹ ለነበሩት ሕዝቦች መገናኝትና መተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚ ቢሆንም ባለሥልጣኖቹ ስለማይፈልጉት በተቻላቸው መንገድ ግንኙነቶች እንዳይፈጠሩ በማስጠንቀቂያ መልክ ማሳሰቢያ ሲሰጡ፤ ግን ወደ ከተማ መሄድ ወይም ሄዶ መቅረት ክልክል አልነበረውም። ሕጋቸው ከምስራቅ መጥተው ለነበሩት(አጋዴዎች) አይሰራም።

በየዕለቱ የሚደረጉት ነገሮች ተደጋጋሚና አሰልቺ ከመሆናቸው በላይ የሚቀርበው ራሽን ከመጋዘን አለቀ እየተባለ ጦም ማደር ሲጀመር፤ ሁሉም አቅጣጫውን እንዲፈልግ ይገደዳል። አንዳንዶቹ የዕለት መኖ ለመመጽወት ከመስጊዶች እየሄዱ በዚያው ሲቀሩ ወጣቶቹ ክራይ እንሰራለን በማለት ባላቸው ገንዘብ እየተሳፈሩ ወደትልልቅ ከተማ ይሄዳሉ። ቃሲም በምግብና በሽርጥ እንዲሰሩ ይገደዳሉ ያለው እነዚህን አይነቶቹን ነበር። በሰፈራው ጣቢያ የቀሩትም ቢሆኑ ረሃቡን ቢችሉትም። በየጊዜው በወባ በሽታ ስለሚሰቃዩ ያንንም ለመከላከያ በቂ መድኃኒት አልነበረም። በነበረው ክሊኒክ ውስጥ የሚሰሩት ባለሞያዎች ጠንቅቀው ሥራውን አያውቁትም። ለምሳሌ በወባ ለተያዘው ሰው የሚታዘዘው ክኒን የተለየ መጠን የለውም። በዛኑም ላይ እንደ ቆሎ ዘግነው በተጣለ ጋዜጣ ጠቅልለው ለበሽተኛው ይሰጡታል። ያንንም ለማግኘት ዕድለኛ መሆን ያስፈልጋል።

በወቅቱም እንደአማራጭ የተወሰደው በአፋጣኝ መሣሪያ ሰተዋቸው መመለሱን ሲሆን ከዚያ በሰደት እንኖራለን ብለው ከሃገር የወጡትም ተጨባጭ ሁኔታውን በመመልከት ከእርዳችን ላይ በክብር ብንሞት ይሻለናል በማለት ሐሣባቸውን ለውጠው ወደሃገር ለመመለስ ይወስናሉ። ለመሣሪያ የሄዱትም በአስቸኳይ ተሰቷቸው ወደሃገር እንመለስ በማለት ጥያቄያቸውን በየዕለቱ ማቅረባቸውን አልቀረም።

ጉዳያቸው በአስቸኳይ እንዲፈጸምላቸው፤ ሃገር ቤት ስሙን ለማንሳት የማይፈልጉትን «የሶማሌ አቦ» የነፃነት መጠሪያ ስም በተደጋጋሚ ማንሳት በዚያን ወቅት ይሆናል።ከሰፈራው ጣቢያ ረሃቡም የጠናባቸው ክፍሎች በየመስጊዶች በመሄድ «የተሰደድን ሶማሌ አቦነን» በማለት መለመኛ አድርገውታል።

ቀደም ብለው መጥተው ከዚያን የሰፈሩትም፤ እየተሸሸጉ እየመጡ ምንም የሚሰጧቸው መሣሪያ እንደሌለና በከንቱ የሚያጉላሏቸው መሆኑን ከራሳቸው ልምዶች የደረሰባቸውን ሲነግሯቸው፤ አልፎ ተርፎም ከአጋዴን ክፍል የሄዱት መሣሪያችሁን



እንፈልግም በማለት የጁባን ወንዝ እያቋረጡ ሲሄዱ በሶማሌ መደበኛ ወታደሮች በመሣሪያ አስገዳጅነት ሲመልሷቸው የቀሩትም የሚያዩት ቢሆንም፤ ግን ከደጋው ክፍል የመጡት የዚያን ዓይነት ሙከራ ቢያደርጉ«አማሮች»በማለት የሚደርስባቸውን ችግር አስቀድመው ስለሚያውቁት ለአመፅ አልተነሳሱም።

፶፩

የጪረቃዋ ብረሃን መርፌ ታስከለች፤ ሰደተኛው በጓድ ተከፍለው ከሚሞቁት ምድጃ ፈንጠር ብለው ድብዳባቸውን አንጥፈው ተኝተዋል። በግምት እኩለ ሌሊት ይሆናል። ለምሽቱ ለዘብ የተመደቡት ግለሰቦች እውነቱን ከእንቅልፉ ቀስቅሰው የቀን ልብሱን ለብሶ እንዲነሳ ነግረውት፤እርሱም ከተጠራበት አከባቢ እስከ ሚደርስ ብዙ ሐሳቦች ወደአእምሮው እየመጡበት ሲያወጣ ሲያወርድ እንደአጋጣሚ በቅርብ የተፈጸመ ድርጊት ቢኖር አብረው ጉዞ የጀመሩት ጓደኞቹ ጠፍተው ወደሌላው ከደጋው ኢትዮጵያ ክፍል ወደመጡት ሰደተኞች ሄደው መቀላቀላቸው ሲሆን ወደእነርሱ እንዲመጣላቸው ለሄዱበት አከባቢ ተጠሪዎች መጠይቅ አቅርበው ስለነበር ለዚያ ይሆናል ብሎ ያስባል።

በሌላ አንፃር እርሱ የበጎችና የፍየሎች ተረኛ እረኛ በነበረበት ቀን በአጋዴኖችና እርሱ አብሮአቸው በሄደው ሕዝቦች መካከል በጎቹንና ፍየሎቹን እንወስዳቸዋለን በሚል ጸብ ተፈጥሮ ስለነበር ለጥያቄ ተፈልጌ ይሆናል የሚለው ሐሣብም በአእምሮው ውስጥ ሲደውል ፤ግን በወቅቱ የተፈጠረው ጸብ ሕዝቡ በመረጣቸው ተወካዮች እርቀ ሰላም ወርዶ ከዚያም የሄዱት ለእረኝትነት ሳይሆን ለዓላማ መሆኑን በአንድነት ገልጸው ፤ በጊዜው እነርሱ እየተራቡ ባለሥልጣኖቹ የምረቃን ቀን እያመሃኙ እያረዱ ሲበሏቸው እነርሱ ግን የበይ ተመልካች መሆናቸውን አስረግጠው፤ ተከፋፍለዋቸው እያረዱ በመብላታቸው ሁኔታው አሳሳቢና ሕግ ወጥ በመሆኑ ከዋናው ከተማ ድረስ ባለሥልጣኖች የመጡበት ጉዳይ ስለነበር፤ እውነቱ በነገሩ አለህበት ይሉኝ ይሆን? በማለት እራሱን ሲጠይቅ ከተባለ ደግሞ ወደያውኑ አውጥተው እንደሚመቱት እያሰላሰለ ከተጠራበት ጽሕፈት ቤት ደረሰ።

ከጽሕፈት ቤቱ ሲደርስ ተረኛው መኩንን በቢሮው ስላልነበረ በጪረቃዋ ወጋገን በደመቀው ክፍል ውስጥ እንዲቀመጥ ተነግሮት፤ይዘውት ወደ ጽሕፈት ቤቱ ከሄዱት አንደኛው ተረኛውን መኩንን ሜት ከሚቀምበት ድንኳን ውስጥ ለመጥራት ሄደ፤ መኩንኑም ተጠርቶ ሽርጡን እያጠባበቀ ፋኖሱን ይዞ ከቢሮው ተገኝቶ፤አረብኛና ሶማሌኛ ቋንቋ መናገር መቻል አለመቻሉን በአስተርጓሚ ያስጠይቀዋል። አለመናገሩን ሲገልጽለት፤ ሁለቱንም ቋንቋዎች መናገር ሳይችል ለምን ወደዚያን ሃገር ለመምጣት

እንደፈለገ ጠይቶት፤ እርሱም አብሯቸው የመጣው ሕዝቦች የአረብኛና የሶማሌኛ ቋንቋ ተናጋሪ እንዳልሆኑ ሲገልጽለት፤ የሀበሻ መንግሥት ስላይ መሆን አለመሆኑን ያስጠይቀዋል።

በዚህን ጊዜ ሲቃ እያተናነቃውና ትንፋሽ እያጠረው «ምን ዓይነት ስለላ ነው በእንተ ሕዝብ ላይ የማደርገው? የሰይንስ ምርምርን የዕደጥበብ ዕድገትን እንዳትለኝ የሁለታችንም ሃገሮች ያሉበትን የእድገት ደረጃ ታውቀዋለህ። በመከላከያ ኃይልና በጦር መሣሪያ ብዛት ርስበርስ ለመተዋወቅ እንዳትል ሁለቱ ሃገሮች የሚዋጉት በሰው ሃገር ጠበብቶች በተሠራ መሣሪያ ስለሆነ የአንተም ሃገር ሆነ የእኔ መሣሪያዎቹን በገዢቻው ማግስት በጋዜጣና በመጽሔት ቁጥራቸው ስለሚወጣ ያንን ለማወቅ ችግር የሚፈጥር አይሆንም። ከእለው ተጨባጭ ሁኔታ እንደምናየው የአንተን ሃገር መንግሥት መሣሪያ ያስታጥቅ የነበረው መንግሥት የእኔን ሃገር መንግሥት እያስታጠቀ ሲሆን ከእኔ ሃገር የነበረው ከአንተ ሃገር ነው ስለዚህ የማይተዋወቁት ነገር አለ ብለህ ትገምታለህን?» መኰንኑም ከጥርሱ ፈገግ ብሎ «በሶማሌኛ ይህ እውነተኛው ሀበሻ ነው» በማለት ከበውት እንዲያድሩ ነግሮአቸው ወደ ድንኳኑ ተመለሰ።

በነጋታው በእንደ ወታደር ታጅቦ በመኪና ተጭኖ ከአንድ የጠረፍ ከተማ ተወስደ ለግለሰብ ተሰጠ። የተረከበውም ግለሰብ እያዋራው ከየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል እንደመጣና ለኑሮው ምን ይሠራ እንደነበር ጠይቶት፤ አስተማሪ እንደነበር ቢነግረውም ከሁኔታው ሲመለከተው አምኖ ሊቀበረው አልቻለም። እርሱም ከመንገድ ይዞት ወጣ ብሎ፤በአካባቢው ሰው መኖር አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ በአማርኛ ሰሙን ጠይቶት፤ እውነቱ መሆኑን ሲነግረው ሌላ ተማሪ እርሱን ሊሸኝ መጥቶ ከያዘው አልቤርጎ እንደሚጠብቀው ነግሮት ወደዚያው አመሩ።በአማርኛ መናገሩን አቁሞ በኦሮመኛ ስለ አካባቢውና ከዚያን በፊት ስለአጋጠሙት ችግሮች ያገኛቸውን ልምዶች እውነቱ በቅድሚያ ጥንቃቄዎችን እንዲያደርግ በማለት ያጫውተዋል። «ከዚህን አገር በመጀመሪያ በመጣንበት ወቅት በኦሮመኛ መናገሩ በጣም ያስፈራን ነበር። በቋንቋው ስንነጋገር ሲሰሙን ከኢትዮጵያ መሆናችን ስለሚረዱ ወዲያውኑ የጸጥታ ጠባቂዎች አንጠልጥለው ከስር ቤት ይጨምሩናል።ችግሩ ያሰረህ ግለሰብ መጥቶ ካላዋጣህ እስከ መጨረሻው በስር ቤት ልትሞት ትችላለህ። ያሁኑን አላውቅም ቀደም ሲል ግን ሃገራችን ውስጥ ግለሰብ ተነሰቶ ግለሰብን ማሰር አይችልም። አሁንም በአማርኛ ከተነጋገርክ ያልኩህን ዓይነት ችግር ሊፈጠር ስለሚችል ተሰስተህም ቢሆን አሁን ከማስተዋውቃችሁ ተማሪ ጋር በአማርኛ እንዳትነጋገሩ። ችግሩን እርሱም ስለሚያውቀው ለሁሉም ጥንቃቄ እንድታደርግ ነው።»

ጀማል እውነቱን ከተባለው ተማሪ ጋር አስተዋውቋቸው ለመንገዱ የሚፈያስፈልገውን ዕቃ ለመግዛት ከአልቤርጎው ትቷቸው ሄደ።እነርሱም ከሌሎቹ መንገደኞች ነጠል ብለው ከበርዳው ወጥተው



የመጡበትን አካባቢና ከገበሬው ሕዝብ የተቀላቀሉበትን ጊዜ ይጠያየቃሉ። አብደም እውነቱን ሰሙን እንዴት ወደእስላም ስም እንዳልቀየረ ጠይቶት፤ «እርሱም ስምህን ለውጥ የሚል ችግር አላጋጠመኝም»በማለት ሲመልስለት፤«በቅርብ ይሆናል ከገበሬው ሕዝብ ዘንድ መቀላቀህ» በማለት ሲያስረግጥ፤ አንድ ዓመት መሆኑን ገልጾለት።

አብደስ መች እደተቀላቀላቸው እውነቱ ሲጠይቀው፤ «እኔና አምስት ጓደኞቼ የተቀላቀልናቸው፤የግራኝ ሙሐመድን አቋም በነበራቸው ወቅት ነበር። ከአርሲ ክፍለሃገር ለእድገት በሕብረት እንደዘመትን የወታደራዊ መንግሥት ባልፈጸምነው ጥፋት ከሕዝብ ሊያጣለንና የተማሪውን በሕብረተሰቡ ያለውን ተቀባይነት ዋጋ ለማሳጣት ባስተላለፈው የውሸት ፕሮፖጋንዳ በመናደድ በራሳችን ፍላጎት ከሕዝቡ ጋር እየሠራን ለመኖር በሁለት አቅጣጫ ተከፍለን ከሃገሬው ተቀላቀልን። በሌላ አቅጣጫ የሄዱት መጥፎቹን አጋጥሟቸው ኖሮ ስለይ ብለው ሲገሏቸው እኔና ሁለቱ ሃገር ቤት የቀሩት ጓደኞቼ ሰማችንን ቀይረን ይሄው እስከዛሬ ጎጆ ቀልሰን ቀለባችን እያመረትን ትኩስ አየር እየተነፈስን እንኖራለን። አሁንም አንድ የጋራ የራስ መጠበቂያ መሣሪያ እንዲኖረንና ይበልጥ እንዲያምኑን ስለፈለግን ለኔ ስንቅ ተዘጋጅቶልኝ ከነሱ ጋር ከርሜ ለመመለስ መጣሁ። ይገርመሃል ሕዝቡን በጣም ወደነዋል እርሱም ወደናል። የወጣንበትን ዓላማ በመጠኑም ቢሆን ጥሩ ፍንጭ አሳይቷል። በእርግጥ የቀሩት ጓደኞቻችን በአላዋቂ ግለሰቦች መገደላቸው ቢያሳዝነንም ያ ሁኔታ በመላው ሕዝብ ላይ በየትም አካባቢ የተፈጸመ በመሆኑ በተናጠል አላየነውም። ያንን ሁኔታ እንደማይደገም እኛን በቅርብ በተግባር ያዩን ግለሰቦች ጠቅሰው ይናገሩታል። መሞታቸውንም የሰማነው ከነሱ ከራሳቸው ነው። ለመሸሸላቸው አንተም ጥሩ ማስረጃ ትሆናለህ። የክርስቲያን ስምህን ሳትለውጥ ታምነህ ከማሠልጠኛቸው ድረስ መግባት ከዚህን በፊት ታይቶም ተደርጉም የማይታወቅ ነገር ነው። በነገራችን ላይ አባት እናቴ ያወጡልኝ ስም ገበየሁ ነው።አሁን በምንኖርበት አካባቢ ስም ቋንቋና ሃይማኖት እንደማይነጣጥሉን በሚገባ ተረድተን በሥራ ውጤታችን የአካባቢው ሕዝብ እየተፈታተነን ነው። የከተማው ናፍቆታችን ከልባችን ወጥቷል። አዲስ አበባ ሄጄ ከፒያሣ ቶሚ የመሐሙድን ትዝታ ሰምቺ በሞትኩ ይሉ የነበሩትን ጓደኞቻችንን እንደማፈዣ እያነሳናቸው እንስቃለን። ያ የሞቅ ሞቅ የወጣትነት ጊዜያችን አልፎ የሃገር ሃላፊነት በጫቃችን ላይ አርፏል። ሕዝቡ ገርቶናል በሱ ተውጠናል። በእውነቱ ሕዝብ አስተማሪ ነው የሚለውን በተግባር ተቀብለነዋል።»

ጀማል ዕቃውን ገዝቶ ስለመጣ ገበየሁ እውነቱን ምሳ ሊጋብዘው ስለፈለገ አስፈቅዶት ተያይዘው ከአንድ ሻይ ቤት ሄዱ። በሻይ ቤቱ ከለፓስታ ሌላ አማራጭ ምግብ ባለመኖሩ በሁለት ሣህን ተሰርቶ ቀረበ። ገበየሁ በእጁ እየጠቀለለ ሲመገብ እውነቱ ከሶማሊያ

ምድር ሸይ ቤት ሲገባ የመጀመሪያው በመሆኑ ተደናግሮት እንደሚበላው ቅጡ ጠፍቶት ገበየሁን ሲመለከት፤ገበየሁም እውነቱን ሸይ ቤት መግባቱ የመጀመሪያው መሆኑን ተረድቶት እንዴት እንደሚበላ መመሪያ ሰጥቶት፤ እንደምንም እየተንጠባጠበበት ተመገበው ሲያበቁ በሸይ ብርጭቆ መረቅ ቀረበላቸው። «ከንግዲህ የዶሮ ወጥ በማኛ ጤፍ እንጀራ ተመገበ የዶሮ ዐይን የመሰለ ጠላ ጠጥቶ ተመስጌን ማለት የለም። መረቁ በርደ ዝንቡ ሳይሰፍርበት በትኩሱ ጭርሰው» በማለት መረቁን በትኩሱ እንዲጠጣ ይነግረዋል። ገበየሁም እጆቹን በቀረበለት ጋዜጣ ጠራርጎ ለእውነቱም ሰጥቶት፤ በጪርቅ ቋጥሮ የያዘውን ትንባሆ ፈቶ ሁለት ጠቅልሎ አንደኛውን ለእውነቱ ይሰጠዋል።እርሱም እንደማያጤስ ሲገልጽለት በአፍንጫም የምትወሰደው ድቁሷ አለችኝ በማለት ከፍቅሬ ሽቶ መሸጫ ብልቃጥ ውስጥ የያዘውን ሱረት አውጥቶ ቢሰጠው፤ ያንንም አለመውሰዱን ሲገልጽለት ለትንባሆ ሱስ ያለመንበርከኩን አድንቆ በዚያው እንዲቀጥልበት ያበረታታዋል።

እንደዘንድሮው ሐሸና በታውን ሳይቀማው የሃገራችን ናያለ ዝነኛ በነበረበት ዘመን የለመድነው ሱስ ከዱር ስንገባ በጣሙን አስቸገረን። እንደምንም ሕዝቡ የሚያጠሰውን ቀረደውንም ሆነ ሱረቱን ስንወስድ ቆይተን በመጨረሻም የራሳችን ማሣ ሲኖረን ዘርተን ከእኛ ተርፎ ገበያ አውጥተን ለመሸጥ በቅተናል።

ገበየሁም የቀረደውን ጢስ ወደ ጣሪያው እየሰደደው እውነቱ ለምን መቅድሽ መሄድ እንደፈለገ ሲጠይቀው፤እርሱም ያንን የሰማው ከዚያን ከደረሰ በኋላ መሆኑን ገልጾለት፤ከሃገር ሲወጣስ በምን ዓላማ እንደወጣ ጠይቆት፤ በነበረበተ አከባቢ በየጊዜው የመንግሥት ወታደሮች በእሰሰ መልክ ሕዝቡን በማስቸገራቸው አማራጭ የሌላቸው መንግሥት ከቋቋመው ሰፈራ ጣቢያ ለመግባት ሲያቅዱ የቀሩት በስደት ከዚህ ለመኖር ሲወስኑ እኔም አብሬው የመጣሁት ግለሰብ አብረን ተመልሰን እንኖራለን የሚል ተስፋ ከልሰጠኝ በስደት ለመኖር ወስኜ ነው የመጣሁት በማለት ያጫውተዋል። ገበየሁም ለእውነቱ ጠቅሎት የነበረውን ቆረንዱ እያይዘ «ምነው ቀደም ብሎ ተገናኝተን ኖሮ አብረን ወደሃገር ቤት እንመለስ ነበር። እንደምገምተው አንተንም ከስደተኛ ጣቢያ የሚያኖሩህ አይመስለኝም። እስር ቤት የምትገባበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ምስጢራቸውን ጀማል አጫውቶኛል የማትሰግድ የክርስቲያን መጠሪያ ስምህን ሳትለውጥ ከስደተኛው ጣቢያ መግባት አትችልም። የስደተኛው ጣቢያም አሁን ካለንበት ምንም የተለየ አይደለም። በሃገር ውስጥ በገፍ የለመደው ሕዝብ ከዚህን አጥሚት በኩባያ እየተሰፈረ ሲሰጠው ተቀብሎ በዚያን ተደስቶ የሚኖር አይምሰልህ። ሃገር ቤት ሰላም ቢሰፍንለትና ሰፈራ እያሉ ባያስቸግሩት በዕለት ኑሮ ውስጥ ጣልቃ ባይገባበት በአንድ ቀን ጀንበር ከዚህ ያለው ሕዝብ ወደሃገሩ ለመመለስ አያመነታም። እንዳንደቹም የተመለሱት ከሁኔታው ተመረው ኑሮአቸውን በማጠናከር ላይ ይገኛሉ። ከበራፋችን መጥተው ተክስ ካልከፈቱብን ከእንግዲህ



መሣሪያ ይዘን ሽቅም ቁልቁል እንልም ከማለት ደረጃ ደርሰዋል።

እኔና ከሃገር ቤት የቀሩት ጓደኞቼ በውጭም በገቢም ያለውን ሁኔታ አይተን አመዛዝንን ከሃገር መውጣቱ ፋይዳ ቢስ መሆኑን ተገንዝበን የመጣው ይምጣ ከሃገር የተሸለ ምን ሥፍራ የለም በማለት ከአርዳችን ለመኖር ወስነናል። በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ችግር ይኖረዋል።ምሁሩ ያለውን ዕውቀት ሊጠቀምበት ባለመቻሉ ተበሳጭቶ ከሃገር ለምውጣት ይወስናል።ትጉህ ሃገር ወዳድ የሚያደርገውን የሚያውቅ በማያውቀው ግለሰብ ይህ አድርግ ያንን አታደርግ በመባሉ የማያምንበትን ሕይወቱን ለማዳን ብቻ ሲያደርገው ቆይቶ ውጤቱ ሳያምር ሲቀር ከሃላፊነቱ ለማምለጥ ሃገር ትቶ ይሰደዳል። በተለያዩ የፖለቲካ መስመሮች ውስጥ ይሳተፉ የነበሩት የማያምንበት መንግሥት ነው በማለት ከሃገር ለመልቀቅ ምክንያት ሲያቀርቡ በራሳቸው ሠርተው ለማደርና ከሥልጣን ሹኩቻው ምንም ፍቅር የሌላቸው ከፍሎችም ሠረቶ ለመበልጸግና ሃገርን ለማበልጸግ አስተማማኝ ሁኔታዎች ባለመኖራቸው ሃገርን የመሰለ በታ ትተው በሰው ሃገር ሁለተኛ ዜጋ ለመሆን ቆርጠው ይወጣሉ። ገበሬውንም እንደምታየው ቀለቡን ከጎተራው እንዳልዘቀ ኩባያውን ይዘ ይሰለፋል። በአጠቃላይ እነዚህን ሁኔታዎች እኔና ሃገር ቤት የቀሩት ጓደኞቼ አውጥተን አውርደን ከራሳችን ሕዝብ ጋር ከባህላችን ከቋንቋችን ጋር ለመኖር ወስነናል። ጊዜው ተፈታታኝ ነው። የሃገሪቱን እፍታዋን በልቶ በችግር ወቅት ትቶ መውጣቱ አግባብ አይሆንም። «ቅብቅብና ምላስ ዘውትር አያበላም» በችግር ጊዜ ከጎኑ ያልቆምከውን ሕዝብ አዋቂ ነኝ ብለህ ራስህን ብታስተዋውቅ የሚቀበልህ አይመስለኝም። መማርም የሚረዳው ይህን መሰል ችግሮች በወገን ላይ በሚፈጠሩበት ወቅት መፍትሔዎችን በብዙ አቅጣጫዎች መርምሮ ለማግኘት እንጂ በሰላም ጊዜ ብቻ «ታጅማሃን» በመሰለ ሕንፃ እየተኖረ ማርሰዲስ ለመንዳት ከሆነ ሃገሪቱ ትተዋት ለወጡት ልጆቿ የማትቆጭበት ወቅት ሊመጣ ይችላል።አበው ሲተርቱ «ያለወለድኩት ልጄ አባባ ቢለኝ አፋን ዳባ ዳባ አለው» እንደተባለው አንተም በሄድክበት ይህን ንግግሬን አስታውስልኝ እኔም ሃገር ቤት ስመለስ ለጓደኞቼ አጫውታቸዋለሁ።»

ጀማል ይጠብቀን ይሆናል ብሎት ተያይዘው ወደ አልቤርጎ ሄደው፤ጀማልም የገዛውን ዕቃ አንድ በአንድ እያወጣ ለአብደ አሣይቶት፤በኢትዮጵያ የተሠራ የሚለውን የእስክ ጫማ አውጥቶ «ይህ ጫማ ሃገር ቤት አስራ ሁለት ብር ያወጣል ከዚህ ግን መቶ ሽልንግ ይሸጣል። በሱቁ ውስጥ ያለው ማንኛውም ሲጃራ ስም ናያለ ነው። ክራቨን ሆነ ሮዝማስ እንዲሰጡህ ስጠይቅ የትኛውን ናያለ ነው የምትፈልገው በማለት ያማርጡሃል።የሃገራችን ዕቃ ሶማሊያ ውስጥ ያለውን ያህል ተወዳጅነት ሃገር ቤት ቢኖረው ኖሮ ብዙ የሃገር ምንዛሬ ከውጭ እንዳይወጣ ባደረግን ነበር።ጀማልም በመደነቅ እንዴት ወደዚህ እንደሚገባ ነው የሚያስደንቀኝ» ሲል ገበየሁም በመቀጠል «ጮርነቱ የመሪዎቹ እንጂ የሕዝቡ አይደለም። ሁለቱም

ሃገሮች በሕዝብ የተመረጡ መሪዎች ቢኖራቸው ኖሮ ጦርነት ሳይኖር ይችሳል።»

«ተማሪዎች የማታመጡት የላችሁም ከሶማሊያ ወጣቶች ጋር ግንባር እንፍጠር የሚልም ዕቅድ አላችሁ።»

«ከሆነ ማን ይጠላል ግን አስቀድመን ቤታችንን እናሰምር» በማለት እንደቀልድ ቁምነገር ያለው ጫወታ ተጫዋውተው ገበየሁም ይዞት ወደሰፈር የሚሄደው ግለሰብ ስለመጣ ተሰናብቷቸው ሲሄዱ በአልቤርጎውም ያሉት መንገደኞች ወደመቅድሾ የሚሄዱበት ሰዓት በመድረሱ ተያይዘው ከመኪናው ተራ ይሄዳሉ።

## ፶፬

እውነቱና ሌሎቹ መንገደኞች ቡናና ዝንጅብል በተጫኑ መኪናዎች ላይ ተሰፍረው ጉዞቸውን ወደ ሶማሊያ ዋና ከተማ ወደሆነው መቅድሾ ሲያመሩ፤ ዋና ከተማው ከዚያን የወሰን ከተማ ቢያንስ ስድስት መቶ ኪሎ ሜትር ይርቃል። የመንገዱ በውል አለመሰራት ይበልጥ ጉዞውን ሲያጓትተው ከደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍል ተገዝተው ወደውጭ ሃገር ለመላክ ከሐመር ወደብ የሚነዱት የሥጋ ከብቶችም ጉዞውን አጓተውታል። ጀማልም የሚነዱትን ከብቶች ለእውነቱ በጣቱ እያመለከተው «እነዚህ የበረና ከብቶች ናቸው። በቀንዳቸው ርዝመት ልትለያቸው ትችላለህ፤እነዚያ ቀንዳቸው አጠር አጠር ያለውና ጥቋቁር መልክ የላቸው ከደጋው ደሎ አካባቢ እንደሆኑ አያጠራጥርም። ፍየሎቹና በጐቹ ግን ከሞያሌና ዶሎ አካባቢ ሳይሆኑ አይቀሩም። የሳሞቹንና የበሬዎቹን እጧጧሕ ስሰማ ሃገሬ ትይዝ ይለኛል።» እንዳዱም ተቀጥረው ከብቶቹን የሚነዱትን ለማናገር ወደመኪናው ጫፍ ተቀምጦ በኦሮመኛ «አበሊየን ዮም ብያ ካተን» ወንድሞች መች ከሃገር ተነሳችሁ? እያለ ሲጠይቃቸው። እነርሱም ከሃገር የተነሱበትን ቀን ሲነግሩት፤ እርሱም እየተቆጨ ድምፁን ዝቅ አድርጉ «ወደ አዲስ አበባ የሚነዳውን ከብት ከሃገር ኬላ ላይ ቆሞው ከመከልከልና የእናቶችን መቀነት የቄሶችን ጥምጥም የሼከዎችን ኢማማ ከማስፈታት በዚህን ዓይነት ከሃገር የሚወጣውን የሃገር ሐብት መቆጣጠሩ ቅድሚያ ቢሰጠው መልከም ነበር። የተቀመጠበትን ጀኒያ በእጁ እየነካ ይህም የሃገራችን ሐብት ነው።ሶማሊያ ውስጥ እንኳንስ ቡናና ዝንጅብል ሊተከል ይቅርና ለምግብ እህል አለመዝራታቸውን ለማረጋገጥ ይህን ያህል መንገድ ስንጓዝ በሬ ጠምደው የሚያርሱ ሰዎች አላጋጠሙንም። ሁሉም የእርሻ ምርት የሚመጣው ከሃገራችን ነው። የቡናውማ ነገር ያከተመለት ይመስላል። ግን ዝንጅብሉ ከገሙጎፋ ድረስ ተጭኖ ሐመር እስከሚደርስ እንዴትስ የሃገራችን ኬላ ጠባቂዎች አላዩትም?»

ቀደም ሲል አንድ አበሻ በመኪናው ላይ ተሰፍሯል የሚል



ዜና በየኬላዋ ለሚገኙ የወታደር ሠፈሮች ተላልፎ ኖሮ «(አዌ አማርኪ) አማራው የታለ?» በማለት በበታው የነበሩ ወታደሮች ሲጠይቁ አንዳንዶቹም በጦርነቱ ወቅት እስከ ድሬደዋ ከተማ መግባታቸውን ለእውነቱ ይነግሩታል። ሶማሌዎች ዜናዎችን በጣም ስለሚከታተሉና አንዱ የነገራቸውን ተቀብለው እንደነበሩበት ሆነው ስለሚያወሩት እውነትና ውሸታቸውን መለየት ያስቸግራል። ስለኢትዮጵያ ዕለት በዕለት የሚደረገውን አንድ ኢትዮጵያዊ የሚያውቀውን ያህል ያውቁታል። ሌላው ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ሥፍራ የመሄድና የመኖር የመቆየት መብት ስላላቸው ከሃገሬው እኩል ስለሃገራችን ያውቃሉ። ምንም የአማርኛ ቋንቋ መናገር የማይችለው ሶማሌ ከመቅድሾ ድሬ ደዋ ካለው ዘመዱ አማርኛ ከሚናገረው ጋር አስራ አራቱን ክፍለሃገሮች መዘር ይችላል። ግን አንድ አማርኛ የሚናገር ሶማሌኛም ቢናገር ዋና ከተማቸው መግባቱ ቀርቶ ወሰናቸውን ሲረግጥ ወዲያውኑ ይያዛል። ሌላው ቀርቶ ሶማሌነቱ ታውቆ ከኢትዮጵያ ከሄደ የጉሰውን ሐረግ እስከ ሃያ ቤት ካልቆጠረ በአማራነት ይመደባል። መንግሥታችውም የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝባቸው ልልና ተቀባይ መሆኑን በመገመት ወደዚያ እንዳይከበልሉበት ጥላቻ በኢትዮጵያኖች ላይ ለሕፃናት ሳይቀር ከትምህርት ቤት ጀምሮ ያስጠኗቸዋል። በተለይ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ችግራቸው ያ ነበር። ያንንም የማጥላላት ፕሮፖጋንዳቸውን ያሰመናቸው ሶማሌዎች ሀበሻ ሲሏቸው እንደልዩ ፍጡር አድርገው የመመልከት ሁኔታም አለ።

በጉዞውም ላይ መንገደኛው ለሻይና ለምግብ ከመኪናው ሲወርድ እውነቱን እንደታምር ይመለከቱት ስለነበር፤ እርሱም ያንን ሁኔታ በማጤን ሌሎች ወርደው ሲዝናኑ ከመኪናው ሳይወርድ ከሶማሊያ በከተማነትና በስፋት ሦስተኛ ከሆነችው ከባይዳባ ከተማ ይደርሳል።

የተጫነውን ዕቃ ለመመዘንና ለመመርመር ወደጉሙሩክ ጽሕፈት ቤት ሲወሰድ የጫኑትም ነጋዴዎች ቀረጥ እስከሚከፍሉ ተብሎ ተሳፋሪዎቹ ቁርሳቸውን ለመመገብ ወደመሐል ከተማው ሲሄዱ እውነቱ ከአንድ ግለሰብ ጋር ከጉምርኩ ጽሕፈት ቤት ደጃፍ ላይ ከምትገኝ ዛፍ ሥር ተቀምጦ ይቆያል።

ለቁርስ የሄዱትም ተመልሰው ከመሥሪያ ቤቱ ጋር የሚደረገውን ውጣ ውረድ ተፈጽሞ መንገደኛው ከመኪናው ላይ መሰፈር ሲጀምር የጉምርኩ መሥሪያ ቤት አላፊ እውነቱን በምን እንደለየው አይታወቅም ከሎሎቹ መንገደኞች ገንጥሎት በሶማሌኛ አናገርት፤ መልስ ስላልሰጠው ከመንገደኞቹ እንደኛው ቋንቋውን አለመቻሉንና ሀበሻ መሆኑን ይነግረዋል። እሱም ወደቢሮው ተመልሶ ስልክ ለክፍለሃገሩ ጸጥታ ጽሕፈት ቤት ደውሎ፤የጸጥታው ጽሕፈት ቤት ከዚያው አካባቢ ኖሮ አንድ ሲቪል የለበሰ ግለሰብ ሽጉጡን ታጥቆ መጥቶ፤እውነቱን ከቀሩት መንገደኞች ነጥሎት ወደ ጸጥታው ጽሕፈት

ቤት ወስደት፤ ከአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ እንዲቀመጥ ተደርጎ፤የተለያዩ ግለሰቦች ወደክፍሏ እየመጡ ለጥቂት ሰዓት ከተመለከቱት በኋላ፤ ሦስት ሰዎች ከጠረጴዛ ዙሪያ ከተቀመጡበት ክፍል ተጠርቶ፤ መቀመጫ ተሰጥቶት ሃገር ቤት በነበረበት ወቅት የየትኛ ብረጌድ ጦር ክፍል ይሠራ እንደነበር ቢጠይቁት፤ ወታደር እንዳልነበር ቢነግራቸው አምነው ሊቀበሉት አልቻሉም። በተለያዩ መንገዶች ማንነቱን ለማወቅ ጥያቄዎችን ቢያቀርቡለትም፤ የእርሱ መልስ አንድ ነበር። «አስተማሪ እንጅ ወታደር አልነበርኩም» የሚል ሲሆን አንዳንዴ የሚጠይቁትን ለመመለስ ይሰነዋል፤ ሌሊቱን ሲጊዝ በማደሩ እንቅልፍ ያንገላጅጀዋል፤ በዚያ ኑም ላይ ምግብ ከወሰደ ሃያ አራት ሰዓቶች አልፈዋል። ሁኔታቸው ሃገር ቤት በ፫ ዓመተ ምህረት ካያቸው ከድሬዎች ምንም አይለዩም። እንጥልጥለውት አለመግረፋቸው እንጂ ማስፈራራቱና ሰውን የሚሰብሩ ቃላቶችን በመሰንዘር በኩል አንድ ነበሩ።

ምርመራው ለጥቂት ሰዓቶች ይቁም ተባለና የሚጠጣው ቀዝቃዛ መጠጥ ቀርቦለት፤ ይጠይቁት ከነበረው ክፍል ውጭ በኮሪደሩ ውስጥ እንዲቀመጥ ተደርጎ አንድ ወጣት ከሶማሌዎቹ መልክ ለወጥ ያለ ሀበሻ የሚመስል፤ በአይኑ ቁራኛ እንዲጠብቀው የተደረገ በክፍሉ ውስጥ የተዘረጋውን የውኃ ቧንቧ እየተመለከተ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ታሪክ መተረክ ሲጀምር፤ እውነቱም ምን ማለቱ ነው በማለት ሲመለከት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልክ ከብረት በቧንቧ ላይ ተቀርጾ ይመለከታል። ግለሰቡ ሊያናግረው እንደፈለገ ይረዳውና ፈገግ ሲል፤ ግለሰቡም ያንን የጸጥታ ጽሕፈት ቤት አፄ ኃይለሥላሴ ለሶማሊያ መንግሥት በችሮታ መልክ እንደአሠሩላቸው እየነገረው ሳለ፤ጀማል በአንሶላ የተጠቀለለውን ልብሱን አምጥቶ ከኮሪደሩ እንደተቀመጠ ሰጥቶት እግዚአብሔር ያውጣህ ብሎት ይሄዳል።

ወዲያው ከዋናው አዛዥ ቢሮ ተጠርቶ ከቀረበ በኋላ፤ በቢሮው ከነበረው ሰሩ ላይ እንዲቀመጥ ተነግሮት፤ አዛዡም የእናት አባቱን ስም ከየትኛው ብርጌድ እንደመጣ ቢጠይቀው ፤ ወታደር እንዳልነበር ነግሮት ፤ ጠዋት የተጀመረው ምርመራ ከሰዓት በኋላ አብቅቶ በላንድ ሮቨር መኪና ተጭኖ ከአንድ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ።የወሰደው ግለሰብ ከወረቀት ጋር ለጣቢያው አዛዥ አስረክቦት ሲመለስ የጣቢያውም አዛዥም ዘብ ከቆሙት ፖሊሶች አንደኛውን ጠርቶ ወደማረፊያ ቤት እንዲወስደው በነገረው መሠረት ከአንድ መብራትና ምንጣፍ በሌለው ልሙጥ ከሆነ ክፍል ውስጥ አስገብቶ ዘጋበት።

ያም ሆኖ ግን የመጨረሻው የሕይወቱ ማለፊያ ሥፍራ እንደሆነ ገና ራሱን አላሳመነም። ድካሙ ረሃቡ የቀረቡለትን ጥያቄዎች በአእምሮው ሲመላልሳቸው ተሰፋ የሚያስቆርጡ ነበሩ።የክፍሉ ክርፋት እያደርሰ ምስጋን ሽንት ቤት ያሰኛል፤ ቀንና ሌሊቱን መለየት አይቻልም። ቀን ይሞቅ የነበረው የወለሉ ሲሚንቶ ማታ ቅዝቃዜው አጥንት ዘልቆ ገብቶ ይነዝራል። ሆኖም መለወጫ



ልብሱን የጠቀለለበትን አንሶላ ፈቶ በወለሉ ላይ ዘርግቶ መለዋጫ ቁምጣውን ደርቦ ለብሶ ይተኛል። ባደረገው ጉዞ ተዳክሞ ስለነበር ቅዝቃዜው፣ ሽታውና ረሃቡ ሳይሰማው እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ ብሎ፤ ጠዋት ለእስረኛው ለሽንት ሲከፈትለት ለሱም ተከፍቶለት ሲወጣ፤ በአራቱ ክፍሎች ውስጥ ታስረው የነበሩት እስረኞች አንድ ሀበሻ በአምስተኛው ክፍል ውስጥ ታስሮአል ተብሎ ከዘቦቹ ተነግሮአቸው ኖሮ ሁሉም ሲወጣ በክፍሎቹ ቀዳዳዎች እየተመለከቱ፤ «ከነካ ጂጂስ ምዬ» «ይህ ሰላይን ነው» በማለት ድምዳሜአቸውን ሲሰጡ፤ የቀሩት እስረኞች ከውጭ ንፍስ እንዲቀበሉ ሲፈቀድላቸው እርሱን ግን ወደክፍሉ መልሰው መልዘሰው ዘጉበት።

እኩለ ቀን ሲሆን የእስር ቤቱ የምግብ አቅራቢ መጥቶ ስሙን መዝግቦት በሚቀጥለው ቀን የሱ ራሽን እንደሚወጣለት ነግሮት ሄደ። በጊዜው ምግብ ከወሰደ ቢያንስ አንድ ቀን ተኩል ሲሆነው ለምግብ ያለው ፍላጐቱም እየቀነሰ መጥቶ በሰውነቱ መጎዳት ምክንያት የወባ በሽታው ተቀስቅሶበት የሰውነቱ ሙቀት ጨምሮ፤ ራስ ምታቱ ሲፈልጠው፤ ሌላው ሰውነቱ በብርዱ ሲዘፈዘፍ፤ ምንም እርዳታዎችን እንደማይሰጠው ሲያውቀው የተዘጋበትን በር እንኳን እንኳኩቶ እርዳታ እንዲደረግለት አልሞከረም።

በሁለተኛው ቀን ሦስት ዳቦዎች እያንዳንዳቸው በግምት ሃምሰ ግራም የሚመዝኑ ከማባያው ሦስት ማንኪያ መረቅ ጋር ቀረበለት። ለሞት ለሚያጣጥር ሰው ለጥቂት ሰዓትም ቢሆን ነፍስ ይዘራል። ግን በዚያች ሃገር ውስጥ በልቶ የመጥገቡን ነገር ዓምላክ ይወቀው።

በዚያን ዓይነት ለአንድ ሳምንት ከቆየ በኋላ በመጀመሪያ ከተጠየቀበት መሥሪያ ቤት ተወስደ ቀደም ሲል የጠየቁትን ጥያቄዎች ቢያቀርቡለት የእርሱ መልስ ምንም የተለየ አልነበረም ። ምንም የተለወጠ ነገር ባለማግኘታቸው ከእስር ቤቱ መልሰውት፤የጣቢያውም አዛዦች እየለመዱት ሲመጡ እንደማንኛውም እስረኛ ለተወሰነ ሰዓት ከውጭ ንፋስ እንዲቀበል ያደርጉታል። ቀደም ሲል በሶማሊያ የሬዲዮ ጣቢያቸውና ጋዜጣቸው ስለኢትዮጵያኖች ይነገራቸው የነበረውን ለማረጋገጥ ሁሉም እስረኞች ከነበሩት ክፍሎች በመውጣት ሲመለከቱት «እኛ ኑ ይመስሳል የሚነገረው ነገር( ቤን ) ውሸት ነው» በማለት መንግሥታቸውን የሚያገልጡም ነበሩ። አንዳንዶቹ ከእስር ቤቱ የሚሰጣቸውን ምግብ በሙሉ እንዲሰጠው ያደረጉም ነበሩ። የሚያነጥፈውና የሚለብሰው ልብስ በማምጣት ያስተናግዱት ጀመር። እንደአጋጣሚ ሁለት ኢትዮጵያዊን «በሶማሌ አበ» ስም ከሶማሊያ የገቡ ከአንድ ሐብታም አረብ እርሻ ላይ በቁፋሮ ሥራ የተሠማሩ አብረው ከሚሰሯቸው ጋር በፈጠሩት አለመግባት በጩቤ ተዋግተው ከፖሊስ ጣቢያ ታስረው ኖሮ አንደኛው እውነቱን ከሽንት ቤት ሲገባ ጠብቆ እርሱም ለሽንት የሚወጣ መስሎ እውነቱን ቀርቦት በአርመኛ «የሃገርህ ልጅ ነኝ» ብሎ ያናግረዋል። እስከዚያን ጊዜ ድረስ ቀርቦት ባለማናገሩ ይቅርታ ጠይቆት፤ «ዋናው ምክንያቱ ግን ሶማሌዎቹን

በመፍራት ነው። እነርሱ እንደኛ አይደሉም ከዚህ የሚመጣ ሁሉ ሰላይ ይመስላቸዋል። እኛም ሳናውቀው ከሃገር ወጥተን የሰው ባሪያ ሆነናል። ወደ ሃገር እንመለስለን ያልን እንደሆን ሰላዮች ተብለን ከእስር ቤት እንጨመራለን ይህን እንዳይደርስብን በምግብና በሽርጥ እናገለግላለን። ጉልበታችን በጣም ጥሟቸዋል። እስከምንሞት የሚለቁን አይደሉም። ሃገሬው ሥራ ስለማይወድ ያሉት በእኛ ጉልበት ነው ማለት ይቻላል። እኔና ሌላው ጓደኛዬ ተበሳጭተን በሥራ ቦታ ያናደዱንን በጩቤ ወግተን ነው የታሰርነው። ሆኖም የምንሰራለት አረብ ከነገና ዛሬ መጥቶ ያስፈታናል። ሥራውን በሚገባ ስለምንሰራለት መታሰራችን ከእኛ ይልቅ እርሱን ይጎዳዋል። እኛማ ሁሌ እስረኞች ነን። እኔን የሚገርመኝ እኛ ገበሬዎቹ ባለማወቅ በነዚህ ሰዎች ፕሮፖጋንዳ ተወናብደን እንምጣ እናንተ የተማራችሁት ክፍሎች ለምን ወደዚች ሃገር እንደምትመጡ አይገባኝም።»

## ፶፫

እውነቱም ከፖሊስ ጣቢያው ታስሮበት ከነበረው ክፍል ልብሱን ይዞ እንዲወጣ ተነግሮት በአንድ ሰንድ ሮሽር መኪና ተሰፍሮ በመጀመሪያ ቀን ቃል ከሰጠበት የጸጥታው ጽሕፈት ቤት ተወስዶ፤በሶማሌኛ በተፃፉት ሦስት ገጾች ወረቀት ላይ እንዲፈርም ነጋሮት፤ከዚያንም በመኪናው አሳፍሮት ከከተማው በስተምስራቅ ወጣ ብሎ ብቻውን ከተሠራ በግብ ከታጠረ ቤት አውርዶት በግቢው ውስጥ ካለው ትልቅ ዛፍ ሥር ከነበረው መቀመጫ ላይ እንዲቀመጥ ተደረገ። ግለሰቡም ሬሽርሽር ሽጉጡን ከኪሱ አውጥቶ በማሽከርከር እውነቱ እንዲመለከት አደረገ። ሁኔታው ከመንገድ ለማምለጥ ብትሞክር ይህ ጥይት ይከተልሃል ይመስላል። እውነቱም በልቡ «እንኳስ ለሙቁ ለገንፎውም አልደነግጥ»፤ «እድሜ ለደርግ አባሎችና ለካድሬዎች የሽጉጡን ትዕይንት ቿቅ እስከሚለኝ እስከሰክሰውኛል ብዬ እንድነግረው ነው የሚሸው» በማለት ከራሱ ጋር ሲነጋገር፤ ግለሰቡ እግር መንገዱን አብሮት የሚኖረውን ጓደኛውን መቅድሸ ይዞት ለመሄድ ኖሮ ልብሶቹ ያሉበትን ሸንጣውን ይዞ ከቤቱ ወጥቶ ሦስቱም ከመኪናው ተሰፍረው ጉዛቸውን ጀመሩ።

በየመንገዱ ከሚገኙት አንዳንድ ሻይ ቤቶች ገብተው ሻይና ቡና በመጠጣት እየተዝናኑ ሦስት መቶ ኪሎ ሜትር የሚሆነውን መንገድ ተያያዙት። በመጨረሻም እውነቱ ከመቅድሻ ከተማ መድረሳቸውን የተረዳው የኤለክትሪክ መብራት በማየቱ ብቻ ነበር። በሁለቱ ከተማዎች መካከል መብራት የነበራቸው ከተማዎች አልነበሩም።

ከከተማው ሲደርሱ በግምት አራት ሰዓት ይሆናል። ሕዝቡ ሽርጡን አሽረጦ ነጠላ ሜማውን ተሜምቶ ስስ ሽሚዙን አጥልቆ ያንን ቀዝቃዛውን ከሕንድ ውቂያኖስ የሚተነውን አየር ለመቀበል ሽቅብ



ቁልቁል ሲል እውነቱም በመኪናው መስኮት ውጭውን እየተመለከተ የሃገሩ ትዝታ ወደአእምሮው መጥቶ ያለፋቸውን ውጣ ውረዶች እያሰላሰለና በሰው ሃገር መሬት ላይ መሆኑን መቀበል አቅቶት ከራሱ ሲሟገት ግለሰቡ መኪናዋን ወስዶ ከአንድ ረጅም ሕንፃ ሥር አቆማት።ክላስክ ሲያሰማ በአጥር ግቢው የነበረው ዘብ መጥቶ በሩን ከፈተላቸው።ሕንፃው ከውጭ ሲታይ ትምህርት ቤት ይመስላል።ከአጥር ግቢው እንደገቡ ያመጣው ግለሰብ እውነቱንና ደብዳቤውን ለተረኛው ዘብ ሰጥቶት በነጋታው መጥቼ እጠይቅሃለሁ ብሎት መኪናዋን አስነስቶ ሲሄድ የተረከበው ግለሰብ ሽጉጡን አውጥቶ ደግኖበት ወደፊት እንዲቀድም ነግሮት በሕንፃው መካከል አሳልፎት ከጀርባው በተሠሩት ተርታ ክፍሎች ውስጥ ወስዶ አስገባው።

ትምህርት ቤት ይሆናል ብሎ የገመተው ሕንፃ የሶማሊያ ብሔራዊ የጸጥታ ዋና ጽሕፈት ቤት እንደሆነ ይረዳል። ከረጅሙ ሕንፃ ጀርባ የተሰሩት ክፍሎች እስር ቤቶች ሲሆኑ ወደእስር ቤቶቹ መውጫና መግቢያ በዋናው መሥሪያ ቤት በር ብቻ ነበር። እስር ቤቱ በክፍል ይከፈል እንጂ አጠቃላይ መውጫው አንድ በር ብቻ ነበረው። በጠቃላይ ከነበሩት አራት ክፍሎች ታስረው የነበሩት እስረኞች የሚሰግዱብት አንድ ክሪደር ይገኛል። አራቱ ክፍሎች ሲሞሉ ያም ክፍል ለማሰሪያ ይገለገሉበታል። ለእስረኛው መገልገያ አንድ ሽንት ቤትና መታጠቢያ ይገኛል።

የዋናው በር ላይ ዘብ እውነቱን ከጠቀሰላው ክፍል በር አስገብቶት ቆልፎበት ሲሄድ የእስረኛው ካቦ በመቻከል ከክፍሎቹ ከአንደኛው በመጣደፍ ወጥቶ «ከየት እንደመጣ ለምን እንደታሰረ» ጠይቆት፤ ከኢትዮጵያ መሆኑን ሲረዳ ወደቀሩት እስረኞች በመሄድ «አንድ ሀበሽ ተይዞ መጣ» በማለት ሲነግራቸው፤ ሁላቸውም ሽርጣቸውን እያጠባበቁ ማንነቱን ለማየት ከየክፍሉ ግር ብለው ወጡ። በአንደኛው ክፍል ውስጥ አምስት ኢትዮጵያውያን ታስረው ኖሮ ከእንቅልፋቸው ቀስቅሰአቸው «አንድ ዘመዳችሁ መጣ» በማለት ነግሮአቸው፤ ሁሉም በመቻኮል ወደነበረበት መጥተው፤ ማናቸውም የሚያውቁት ሆኖ ስላላገኙት ከኢትዮጵያውያኑ እስረኞች አንደኛው ከየትኛው ብርጌድ እንደመጣ ሲጠይቀው፤ የቀሩት አታስቸግረው ብለው ደክሞታል በማለት የስር ቤቱ ካቦ ከሰጠው ገላጣ ወለል ላይ አስነስተውት እነርሱ ለሦስት ተጣበው ከሚተኙበት አንዲት የተቀዳደደች ፍራሽ ላይ ተብቃቅተው ጉኑን እንዲያሳርፍ ያደርጋሉ። በነጋታው ሦስቱ ሚሊሻዎች በእለቸው ገንዘብ ምግብና ሻይ እንዲመጣልት ልከው ሰውነቱንም እንዲታጠብ ሳሙና አቅርበውለት፤ የቀመለውን ፀጉሩን ላጭተውት ትርፍ ሽርጣቸውን ሰጥተውት በሚገባ ከአስተናገዱት በኋላ የሃገር ቤቱን ሁኔታ እንዲነግራቸው ጥያቄዎችን ያቀርቡለታል።

እርሱም ወታደር እንዳልነበር ሲገልጽላቸው ሃገር ቤት ምን ይሠራ እንደነበር እንዲነግራቸው በጉጉት ይጠይቁታል። እርሱም በዚያን ሁኔታ አስተማሪ ነበርኩ ቢላቸው እንደማያምኑት

ቢረዳውም፤ሰይነግራቸው ቢያልፈው ቋንቋችንን የሚናገር የሰማሌ ሰላይ ላኩብን በማለት የሚያርቁት መሆኑን ገመቶ፤እንደምንም ውሎ ሲያድር አስተማሪ መሆኑን ሲነግራቸው፤አብረዋቸው ከነበሩት አንዱ አስተማሪ ሲሆን ሌለኛው ግን ከሐረር ጦር አከዳሚ የተመረቀ መኰንን መሆኑን ይነግሩታል።እነርሱም ለብዙ ጊዜ በእስር ቤት ከመቆየታቸው የተነሳ የአእምሮ ቀውስ ስለደረሰባቸው ርስ በርሳቸውም ሆነ ከቀሩት ጋር ምንም አይነት የንግግር ልውውጥ አያደርጉም።

አስተማሪው ገድሉና መኰንኑ አዳሙ በ፲፱፷፱ ዓመተ ምህረት ሃገራቸውን ለቀው ከኬኒያ ተሰደው፤ ሁለቱም በተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ከፍተኛ ኮሚሽን ሲረዱ ሳለ የኬኒያው መሪ ኢትዮጵያን በመጉብኘቱ በሃገሩ የነበሩትን ስደተኞች ወደሃገራቸው ይመልሳቸዋል የሚለው ውዥንብር በናይሮቢ በመነዛቱ ሁለቱም በተለያየ ቀንና አቅጣጫ ገድሉ ከሞንባሰ አዳሙ ከናይሮቢ ወደሶማሊያ ይከበልላሉ።አዳሙ ቀደም ሲል በኬኒያ የንግድ መርከብ ላይ ይሰራ ስለነበር ሞንባሰ ከገድሉ ጋር በእረፍት ጊዜአቸው እየተገናኙ ይዝናኑ ነበር ። በነበረው ውጥረት ሳቢያ ሁለቱም ከኬኒያ መውጣቱን እምነውበት ሳለ ግን ወዴት ለመሄድ እንደሚችሉ ሁለቱም አውጥተው አልተናገሩትም።

በጊዜው ከነበረው መንግሥት ጋር ያለመግባባት የነበረው የሰማሊያ መንግሥት ስለነበር ወደዚያ ያመራሉ። አዳሙ ያፈራው መጠነኛ ገንዘብ ስለነበረው መንገድ እንዲመራው የቀጠረው ግለሰብ ከጠረፍ ሲቃረብ ልብሱና ገንዘብ ያለበትን የጉዞ ሻንጣውን ይዞበት ሲሰወር፤ የሚሄድበት አቅጣጫ ጠፍቶት በዚያን ጭልጥ ባለ በረሃ በውኃ ጥም ተይዞ ለመሞት ሲያጣጥር በሰማሊና በኬኒያ መከከል በሽሽግ የሚነግዱ ነጋዴዎች ያገኙትና ከኬኒያ ጠረፍ ባአሻገር ከሰማሌ ግዛት ይሰዱታል። የሰማሌ የጠረፍ ጠባቂ ፖሊሶች አግኝተውት ከፖሊስ ጣቢያ ሲያስሩት፤ገድሉም በሌላ አቅጣጫ ከሰማሌ ግዛት ገብቶ ኖሮ እርሱም ከአንድ የወሰን ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ይታሰራል። ሁለቱም ከየነበሩት ጣቢያ መጠይቅ ተደርጉላቸው ሲያበቃ ወደሶማሊያ ዋና ከተማ ለመወሰድ ከየአሉበት አምጥተው በአንደነት ሲያሰፍሯቸው፤ ቀደም ከነበራቸው ጓደኝነት ከመፈቃቀርና ከመቀራረብ ይልቅ ጸብ ያነሳሉ።ይዘዋቸው የሚሄዱት ፖሊሶች በሁኔታቸው ተገርመው እናንተ ሰዎች የአንድ ሃገር ሰዎች አይደላችሁምን? በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው፤አንደኛ ከሌለኛው ይበልጥ ተፈላጊነቱን ለመግለጽ ሲሰልለኝ ነው የመጣው በማለት ርስበርሳቸው መወነጃጀል ሲያደርጉ መተዋወቃቸውንና ጓደኛሞች መሆናቸውን ተከክደው፤ በባለጋራ ስም ይተያያሉ። በመጨረሻም ከመቅድሾ ከተማ ደርሰው በአሰዩት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ኮሚሽን መታወቂያ መሠረት ለማስፈጸም በፖሊስ ጣቢያ እንዲቆዩ ተደርገው ሲጠኑ፤ ከዕለት ወደዕለት ከመቀራረብ ይልቅ እየተራራቁ መምጣታቸውን የተመለከቱት፤ባለሥለጣኖቹም ሁኔታው አደናጋሪ ሆኖባቸው፤መፍትሔ ሊያገኙለት ባለመቻላቸው ስድስት ወር በፖሊስ



ጣቢያ አቆይተዋቸው ወደትልቁ የሃገሪቱ የጸጥታ ጽሕፈት ቤት እንደላኳቸው በአከባቢው ባገኙትና እነርሱም ጠይቀው በተረዱት መሠረት ለእውነቱ ያጫውቱታል። እውነቱም ጣሰውን ተስፋዬንና ሐጉስን እነርሱስ በምን ምክንያት ሃገራቸውን ለቀው እንደወጡ ሲጠይቃቸው፤ ጣሰው በመቻከል ምክንያት እንዲህ ያቀርበዋል።
«በመጀመሪያ ከሃገር ቤት ከወለጋ ክፍለሃገር ወደታጠቅ ጦር ሠፈር የገባሁት ባገባሁ በስምንተኛው ቀን ሲሆን ሚስቴንም ትቻት የወጣሁት ከጫጉላ ቤታችን ውስጥ ነበር። እኔም እሷም ፍቅራችንን ሣንጨርስ የገበሬ ማሕበር አባሎች መልምለው ወደሥጋ ሜዳ ላኩኝ። ከዚያንም ከደቡብ ኢትዮጵያ እንድዘምት ተደረገ።ጦርነቱ ሲቆም ከጠረፍ ከተማ ተመድቤ ሳገለግል አድራሻዬን ለይቼ ሳውቅ ከቤተሰቤ ደብዳቤ መላላክ ጀመርኩ።ባለቤቴም ሰንጠጋገብ መለያየታችንን እያነሳች ደብዳቤዋን እያከታተለች ትሰድልኝ ጀመር።አባትና እናቴም ከእነርሱ ዘንድ እንደአኖሯት ገልጸው በአስቸኳይ ሄጄ ዐይኔን እንዲያዩኝ ፍቃድ እንድጠይቅ በመደጋገም አሳሰቡኝ።እኔም ከክፍሌ ባለሥልጣኖች በመደጋገም ፍቃድ እንዲሰጠኝ ብጠይቅ እንደማይሰጠኝ ተነገረኝ። እንግዳውስ የምወዳቸውን ዘመዶቼንና ሚስቴን በዓመት በሁለት ዓመት ሄጄ ካላየኋቸው በሃገሬ ውስጥ መኖሩ ምን ፍቺ አለው በማለት ክላሼን እንግቼ ከነሙሉ ጥይት በጠረፍ ላይ ዘብ ለቆመው የሰማሌ ወታደር እጄን ሰጠሁ።የከፍሉም መኰንን «እንኳን ደህና መጣህ የምትፈልገውን እናደርግልሃለን ጠብመጃውስ የእኛንም መጋዘን ያጣበበ ነው። ለሁሉም የሃገርህ ገበሬዎች ከዚህ ወስደው ለመንግሥትህ ያስረከቡትን በተዘዋዋሪ አገኘነው» በማለት አሹፎብኝ፤ከወታደሮቹ መመገቢያና መኖሪያ እንድቆይ ተደረገ።ብዙ ሳይቆይ ተስፋዬም ከእኛው ብርጌድ መጥቶ ለሦስት ወራት በደህና ከቆየን በኋላ በመጨረሻም ይሄው ከምታየው ሥፍራ አመጡን።»

ተስፋዬም ታጠቅ ጦር ሠፈር የገባው ከጎጃም ክፍለሃገር ሲሆን ከብርጌዳችን «ጣሰው ከዳን ስለሰማ እኔም ተከትየው ወጣሁ» ይላል። ሐጉስን የወጣበትን ምክንያት ሲጠይቀው «እንዳየሁት ከሆነ የእኛ ብርጌድ በጣም መጥፎ ብርጌድ ነው። ይህን ያህል ዓመት ስንቀመጥ ለአንድ ሰው እንኳን ፍቃድ ተሰጥቶት ቤተሰቡን የጠየቀ አልነበረም።ስለዚህ በሃገር ውስጥ ኖረህ በሜዳ ላይ ዘርግፈሃቸው ሃገር ተወረረ ስትባል መጥተህ ዘሬ ሃገር ሰላም ሲሆን አሮጊት እናትህን ሽማግሌ አባትህን ካላየህ ሚስትህና ልጆችህም በሕይወት መኖርህን አይተው ካልተጽናኑ በሃገር ወስጥ መኖሩ ትርጉሙ ምንድነው በማለት ሃገሬን ትቻት ለመውጣት በቃሁኝ።»

ምሳ መጣ ተባለና መቀበያቸውን አዘጋጅተው ሁሉም ውይይታቸውን አቋርጠው ምግባቸውን እየተቀበሉ ሳለ፤ እውነቱ በእስር ቤት የሚሰጠው ምግብ መጠን አንድ መሆኑ አስደንቆት ሚሊሻዎቹን ቢጠይቃቸው ፤ ከእስረኛው እንደተረዱት የእስር ቤቶች ምግብ ኮንትራት ተቋራጮች የእስር ቤቱ አዛዦች በመሆናቸው ሲፈልጋቸው መንግሥት ከወሰነው ሂሣብ ዝቅ አደርገው ሊያቀርቡ

ይችላሉ።ለምሳሌ የዚህ እስር ቤት ምግብ አቅራቢው ኮሎኔል ሲሆን ከፈለገ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የሚሰጠውን ራሽን ላያቀርብ ይችላል። ተመጋቢው እኛን መሰሉ ሃገር የለሹ በመሆኑ ማንንም አይፈራም። ሃገሬው ከቤቱ የሚመጣለትን ይመገባል።ግን በስማቸው መውጣቱ አይቀርም።በአጠቃላይ ውስጥ ውስጡን ንግድ ነው።ለዚህም ነው ከመንገድ ያገኙትን በሙሉ ሰላይ ነው በማለት የሚያስሩት። እኛንም በዚህን ሰሞን ያዝናናን ገንዘብ የተገኘው ሃይማኖት ቀይረናል እስላም ሆነናል በማለታችን አዋጥተው የምንሰግድበት ሽርጥና ለየንዳንዳችን አስራ አምስት ሽልንግ ስለሰጡን ምግብም ሲጃራውንም ከውጭ አስልከን በማስገዛት ተዝናናንበት። አንተም ብትሆን ዕድለኛ ነህ ። ከእጃችን ያለው ገንዘብ ሳያልቅ በመድረስህ ምላጭ እንኳን መግዣ ለማግኘት ቻልን።



## ፶ ፬

እስረኞችም ምግባቸውን ተመግበው በፍራሻቸው ላይ ጋደም ብለው ስለዘለቄታቸው እየተነጋገሩ ሳለ፤ እውነቱም ክፍሉን በአይኖቹ ሲቃኝ ፤ በግድግዳው ላይ ከ« ኤፍ አምስት» ና«ከሚግ» አይሮፕላን የትኛው ይመረጣል? የሚል በአማርኛ ተጽፎ ያነባል። ከበታቹ ወሣኙ አይሮፕላኑ ብቻ ሳይሆን አብራሪውም ጭምር ይሆናል የሚል ተጽፏል።እውነቱም ማን እንደፃፈው ይጠይቃል? እነርሱም ከስር ቤቱ ሲገቡ ተጽፎ እንደነበር ይነግሩታል። በመሐል ጣሰው ቀጠል አድርጎ «አሁን የኢትዮጵያን አየር ኃይል የሚያክል አለ?» በማለት ሲናገር፤ ተስፋዬ በመቆጣት «ዝም በል ያ ሰይድ ይሰማህና ጣጣ ታመጣብናለህ፤ እንደምታውቀው ይህ በታ የሃገሪቱ ዋናው የጸጥታ እስር ቤት ነው፤መዘንጋት የሌለብህ በክፍሉ ውስጥ የተዘረጉት ሽቦዎች እኛን ለመቆጣጠር አገልግሎት ይኖራቸው ይሆናል።» ጣሰውም ደንግጥ ብሎ፤ «ተወኝ እኛ ሚሊሽዎች ምን እናውቃለን ብለህ ነው።» እውነቱም ሰይድ ያልከው ሰው ምንድነው? በማለት ሲጠይቅ፤ ተስፋዬም መልሳ «ሰይድ የእስረኛው ካበ ሲሆን ሃገር ቤት በነበረበት ወቅት የሠራውን ግፍ ሲናገር ምንም ከፉ ነገር እንደፈጸመ እንኳን ቅር የማይሰኝ ግለሰብ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከአብዮቱ በፊትም ሆነ በኋላ በሕዝብ ደህንነት ውስጥ ይሠራ እንደነበር ሲናገር፤ በለሥልጣኖቹን ከነሰለሞን ከዲር እስከ ኮሎኔል እሰፋ ያውቃቸዋል።በወጣቱም ጭፍጨፋ ላይ « ከነፃው እርምጃ»እስከ«ቀዩ ሽብር» እንደተሳተፈና ያድርግ የነበረውን በፈዝ መልክ ሲያወራው ደም ያፈሳል። የልጅአገሮደችን ጡት ሳይቀር ቆረጥሁ የሚል አረመኔ ነውና ፊት አትስጠው። ጨርሶ በሀልና ወግ ፍራ እግዚአብሔር ያለው ሰው አይደለም። ለስሙ ግን እውነተኛ ሃይማኖተኛ ለመምሰል ይሰግዳል፤ ሙዝሙራቸውንም ሲዘምሩ ከሁላቸው በላይ ሲያበርቀው ትሰማለህ።»

«ከሃገር ለምን ወጣ?» በማለት እውነቱ ሲጠይቅ፤

«ሁኔታው አላምር ሲለው ሥራውን ትቶ በስለይነት ለመስራትም ይሁን አይታወቅም ጉዱ መጥቶ የሕብረት ሱቅ ሃላፊና ሽጭ ሆኖ ሳለ፤ከዚያም ገንዘቡ ጠርቀምቀም ማለቱን ሲያይ ዘርሮ ወደዚህ ሃገር ይመጣል። እንደሚናገረው ከሆነ ይዞት የመጣው ገንዘብ ሰላሳ ሺ ይጠጋል።»

«ታዲያን የታሰረው ሃገር ቤት በሠራው ወንጀል ነውን?» በማለት ሲጠይቅ፤

ጣሰው በመቻከል «አይደለም ይዞት የመጣውን ገንዘብ ምስጢሩን ለሚያውቅበት ግለሰብ አላከፍልም በማለቱ ለጸጥታ ሠራተኞች ነግሮበት፤ከዚያንም አምጥተው በቁጥጥር ሥር ያውሉታል።ለጊዜው በቁጥጥር ሥር ያውሉት እንጂ ገንዘብ ቢሰጣቸው ይለቁታል።እንደውም ለመላው እስረኛ ሃላፊ አድርገውታል።የተለየ ምግብ ሲቀርብለት፤ሲሸው ከተማ ውሎ ይገባል።

ሐጉስም በመቀጠል «ግለሰቡ አደገኛ ነው፤ የማያውቀው

ቋንቋ የለውም፤ ሰዎችን ተናግሮ ማናገር ይችልበታል። እኛንም ይጫወትብናል፤ ሲፈልገው በመብቱ ክፍሉን ዘግቶብን ውጭውን ሰናይ የምንውልበት ቀንም አለ፤ አንድ ሰው እንዴ ክፉ ነገር መሥራት ከጀመረ በል በል ሳይለው አለመቅረቱን የተረዳሁት ከሰይድ ነው፤ሳይጠየቅ በየዕለቱ በጠዋት በራችንን እያስከፈተን ለስግደት እንደንነሳ ሲየደርግ፤ሃገር ቤት ሰልችቶን የመጣነውን የጠዋት የወታደር ፎሌ በተዘዋዋሪ ከዚህም አልቀረልንም። አንድ መፍትሔ እናገኛለን በማለት ሃይማኖታችንን ብንለውጥም ባሰ እንጂ የተሻለ ነገር አላጋጠመንም።» የተሻለ አክብሮትና ተቀባይነትን ይኖረናል በማለት ሃይማኖታቸውን የለወጡት ግሰው ተሰፋዬና ሐጉስ በይበልጥ ቀራኔን ፈጠረባቸው። በአጋጣሚ በጠዋት ተነስተው ከልሰገዱና ተሰብሰበው ሃይማኖታዊ መዝሙርችን ከሃይማኖቱ ተከታዮች ጋር ካልዘመሩ ያሰለሚቻው ግለሰቦች ሆኑ የቀሩትም የሃይማኖቱ ተከታዮች ግልጽ ጥላቻቸውን አሳዩቸው። የተለየ ሽንት ቤት እንዲመደብላቸው መጠየቅ አቀረቡ። ሁኔታው ኢትዮጵያውያኑን አስቆጣ። አሳንሰውና አልፎም ተርፎም ሲያቋሽሿቸው በመናደድ እጅ መሰናዘር ደረጃ ተደረሰ። ሁኔታው ለጽሕፈት ቤቱ ደረሰ። በኢትዮጵያን እስረኞች ላይ አመራሩ ጠንከሩ፤የቀረው እስረኛ ከሰዓት በኋላ ከውጭ ወጥቶ ንፋስ እንዲቀበል ሲፈቀድለት ለእነርሱ ግን ተነፈጋቸው። በአጠቃላይ አገለሏቸው በየጊዜው ይከሷቸው ጀመር። ዋናዎቹ ምክንያቶቹ ቆመው ይሸናሉ፤ ከሸኑም አይታጠቡም፤ለሽንት ቤት ወረቀት ይጠቀማሉ የሚሉ ሲሆኑ ለሽንት ቤት ተራ መጠበቁ ለእነርሱ ሲሆን ይጣሰል።

በዚያን ምክንያት በደም ፍላት ሐጉስ ከአንደኛው የሶማሌ እስረኛ ጋር የእጅ መለዋወጥ ያደርጋሉ። ተረኛው መኮንን ተጠርቶ መጥቶ፤ መላው እስረኛ ሐጉስን ጥፋተኛ አድርገው ሲያቀርቡት፤መኮንኑም በመናደድ እናንተ ሀበሾች ክብር አይወድላችሁም፤ትናትና ተኩሰችሁ ስትገድሉ የነበራችሁ ወታደሮች ናችሁ። ያንን ረስተነው ከዚህ በክብር ብናሰቀምጣችሁ ሊዋጥላችሁ አልቻለም።የእንናት መንግሥት ቢሆን ለእኛ ሰው የአንድ ቀን ጀንበር እድሜ አይሰጠውም።ይህን ተናግሮ ሰይድን ከመኝታ ቤታቸው ውስጥ አስገብቶ እንዲዘጋባቸው አዘ ሲወጣ የሚወደው ሥራ ነውና አስገብቶ ዘጋባቸው።

ሐጉስ በተበደለ በራሱ ተፈርደበት ሁሉም ኢትዮጵያን እስረኞች ለብቻቸው የነበሩትን አዳሙንና ገድሉን ጨምሮ ለምግብ ለመቀበል ብቻ ሲፈቀድላቸው ሃያ አራቱን ሰዓት ተዘግቶባቸው እንዲውሉ ተወሰነ።

ይህ በዚህ እንዳለ አንድ ኢትዮጵያዊ እስረኛ ተይዞ መጥቶ ኖሮ አንድ የኪዩባ ክፍል ከምትባለው ውስጥ አስርውት ስለነበር፤የእነርሱን ጉዳይ ችላ ተብሎ፤ ከክፍላቸው ውጭወጥተው እንዲናፈሱ ተፈቀደላቸው። አዲስ የመጣውም እስረኛ ሌሎቹ



በአማርኛ ቋንቋ ሲነጋገሩ ከውጭ ሰምቶ ኖሮ በተዘጋበት በር ላይ ተጠላጥሎ ወንድሞቼ መች ነበር ይህ እኔን የገጠመኝ አደጋ የገጠማችሁ ብሎ ሲጠይቅ ለወገን ያለውን ፍቅር ለመግለጽ ምንም የማያግደው ግሰው የተሰጠውን ማሰሰቢያ ደንታ ሳይሰጠው ወደበሩ በመጠጋት መች ወደዚያን እስር ቤት እንደመጣ ሲጠይቀው፤

«እርሱም ምናልባት አውጥተው ከነርሱ ሲቀላቅሉት ማንኛውንም ጉዳይ የሚያጫውታቸው መሆኑን ተናግሩ፤ ለጊዜው ይህችን ሲጃራ አያይዝልኝ» በማለት ከተጣሉ የሲጃራ ቁራጮች አውጣቶ በብጣሽ ወረቀት የጠቀለለውን ለጣሰው በቀዳዳ ያቀብለዋል። እርሱም እያይዞ ሰጥቶት፤ከዚያንም የሱስን አስቸጋሪነት ከልምድ የሚያውቁት ሐጉስ ተሰፋዬና ጣሰው በምን ዓይነት ይህን ወገን እንርዳው በማለት ሁኔታው አሳሰቧቸው ሲያውጡ ሲያወርዱ ሐጉስ በእጁ ላይ አስሯት የነበረችውን የሮመር ሰዓት ለምግብ አቅራቢው እንዲሸጥላቸውና ገንዘቡን እምጥቶላቸው በዚያን ሲጃራውን እየገዙ እንደሚያቀብሉት ተስማምተው፤ሃገር ቤት ስድሳ የኢትዮጵያ ብር የተገዛው ሰዓት አርባ የሶማሌ ሽልንግ ተሸጦ መጣላቸው። በዚያን ሲጃራውን ገዝተው እየሰጡት እንዳንዴም ከአካባቢው ተሸሽገው በመሄድ ሲያጽናኑት፤ ተይዞ መምጣቱን ከእስረኛው ሰምተውት ስለነበር፤ መያዙም ሆነ እጅ መስጠቱ ምንም ልዩነት እንደሌለው ነግረውት በዚያን አንፃር ምንም ስጋት እንዳይገባው ያበረታቱታል ።

በምርከ ስም ተይዞ የመጣው የመቶ አለቃ ለአስራ አምስት ቀናት ከጨለማ ቤት ተዘግቶበት ከቆየ በኋላ ከሌሎቹ እስረኞች እንዲቀላቀል ሲደረግ፤ ሰውነቱ የፀሐይ ብርሃን ባለማግኘቱ ገርጥቷል፤ ሉጫው ፀጉሩ ተቆጣጥሮ ከትከሸው ወርዷል፤ ምድሪቱን ሲረግጣት ጉልበቶቹ ይወላጨማሉ፤ በእጆቹ አንድ ነገር ለማድረግ ይሰቀጠጣል፤ ሲጃራውን የሰበበት ከንፈሩ ከሰል መስሏል፤ጥርሶቹ ወደ ቡናማነት ተለውጠዋል፤አይኖቹ ከእሸንጉሊት የተሰኩ ይመስላሉ፤ ጠቅላላ ገጽታው አጽም እንጂ ሕይወት ያለው ሰው አይመስልም። ከፊቱ ድንጋጤ ሽብር ስለሚታይበት፤ማናቸውም ስለአመጣጡ ጥያቄ ሊያቀርቡለተ አልፈለጉም።የሚጠይቁት ነገር ቢኖር ምን ያስፈልግሃል የሚል ነበር።እንዲህም ሆኖ ለጥያቄ እንፈልግሃለን በማለት እኩለ ሌሊት ላይ እየቀሰቀሱት ከቢሮ ወስደውት ጥያቄ አቅረበውለት ሲመለስ ተሸሎት ይታይ የነበረው ገጽታው ከቀድሞው በታ ላይ ተመልሰ ሲያዩት ሁሉም ምን ጠየቁህ የሚለውን ተወት አድርገው ዐይን ዐይኑን ሲመለከቱት ሁኔታው እያሳዘናቸው ዐይኖቻቸው ሳያውቁት እንባቸውን ሲያቀሩ አንደኛው የሌላውን እንባ እንዳያይበት ሁላቸውም ጀርባቸውን ተሰጣጥተው ይተኛሉ።

መቶ አለቃ በጣም ለጋ ወጣት ቢበዛ ሃያ ዓመት ቢሆነው ነበር። እርሱም የመኰንነቱን ማዕረግ ያገኘው በአራት ወር በሚሰጠው የለብለብ ኮርስ ሰልጥኖ እንደነበር፤ ይናገራል። አካባቢውን እየተላመደው ሲመጣና ከመሥሪያ ቤቱ የሚደረገው ጥሪ ሲቆምለት በመዝናናት የሕይወት ታሪኩን የመጣበትን የተያዘበትን ምክንያት

እንዲህ ያቀርበዋል።

«የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እንደአጠናቀኩ የመኮንንነት ኮርስ ለመሰተፍ ማመልከቻዬን አቀረብኩ። ሞያውን ቀደም ሲል ብጠላውም አማራጭ ስለአልነበረኝ ለሁሉም በሞያው ለመሠልጠን የፖሊስ መኮንን ሆኜ ለመመረቅ ሰንዳፋ ከሚገኘው የፖሊስ ማሠልጠኛ ኮሌጅ ገባሁ። ኮርሱ የሚሰጠው ለአራት ወር ስለነበር ጨርሼ ተመረኩ። ከዚያንም በሕዝብ ደህንነት እንድሰራ ከሐረረጌ ክፍለሃገር ተመደብኩ።ይህንን መሥሪያ ቤት ስሙን ስጠራው እንደምትጠሉት ይገባኛል። ሆኖም ሰላምንበት አማራጭ በማጣት ብቻ ሥራውን ተረክቤ ልክ የክፍለሃገሩ አስተዳዳሪ ቢሮ ጐን ክፍል ተሰጥቶኝ መስራት ጀመርኩ።ዛሬ እንደዚህን ተጎሣቁዬና ከሰውነት ጎዳና ወጥቼ ያያችሁኝ ግለሰብ የክፍለሃገሩ አስተዳዳሪ ሰይቀር የሚፈራኝ ሰው ነበርኩ።እንደህ ብዬ ስናገር ከእርሱ በላይ እውቀት ወይም የአስተዳደር አሳፌነት አለኝ ማለቴ ሳይሆን በውቅቱ እሰራ የነበረው በሥልጣን ላይ ላለው መንግሥት ደህንነት ስለነበር አንድ ነገር ተናግሮ ያስመታናልን በመፍራት የተለየ እንክብካቤና አክብሮት ይሰጠኝ ነበር።ምን ልገራችሁ የኑሮዬ ደረጃ በሦስት ወር ውስጥ እሉ ከሚባሉት ባለሥልጣኖች ደረጃ ደረሰ።ሐረር ውስጥ ያልገባሁበት ቡና ቤት ያልተገናኘኋቸው ሴቶች አልነበሩም።ያልጠጣሁት የመጠጥ ዓይነት አልነበረኝም። ያ ነበር የእኔ በዓለም ላይ የመኖር ፍቺው።በተማሪነቴ ጊዜ ትምህርቴን ጨርሼ ሥራ ይዤ የቀይ ጥቁር ሆና ያሰደገችኝን እናቴን ለመርዳት ሃገሬን በቅንነትና በታማኝነት አገለግላለሁ በማለት ለራሴ ቃል የገባሁት ሰውዬ ይገርማችኋል ከሦስት ወር ደመወዜ ቡና ግዢበት ብዬ ለእናቴ ቤስ ቤስትህ አላኩላትም።አሁን ሱሱ እንደዚህ ያስቸገረኝን ሲጃራም ማጤስ የጀመርኩት ሥራ ከጀመርኩ ነው።በወር የማገኘው ደመወዝ ወጪዬን አይሸፍንልኝም። በይበልጥ የሚያዝናናኝ በነበሩት ትልልቅ በታዎች እንድውል የሚሰጠኝ ወጪና ይህን ሥራ እንደምሰራ የሚያውቁት በለሥልጣኖች የሚያቀርቡልኝ ስጦታዎች ሲሆኑ ከቤቴ ይመጣልኝ የነበረው የመጠጥ ብዛት በተናጠል ሳይሆን በካርቶን ነበር።

ከትምህርት ቤት ሆኜ እቃወማቸውና እወግዛቸው የነበሩትን በሕበረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ጐጂ ነገሮች እኔው ራሴ አደርጋቸው ጀመር። በወቅቱ እቃወማቸው የነበረኩት ስላላገኘኋቸው ወይም በጊዜ ስላልነበሩኝ መሆኑን ዛሬ ራሴን ለማሰመን በቅቻለሁ። በአጠቃላይ ከአገኘሁት ልምድ አንድ ሰው አንድን ነገር የሚቃወመውና የሚኮንነው ስለጠላውና ነገሩ እስነዋሪ የሰውን ሕልውና ነኪ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን እስቦት ሳይሰከለት ወይም ሳያገኘው መቻሉን ተረድት ተሰፋ ሲቆርጥ ሊሆንም እንደሚችል በዚያን እቅጣጫ ለማየት ችያለሁ።በእሁኑ እስተሳሰቤ ሰው ማለት አደርገዋለሁ ያለውን መልካም ነገር ላይ ጸንቶ ሲገኝና መጥፎ ብሎ የገመተውን እስከ መጨረሻው ሳያደርገው ቆርጦ ሲወስንና በተግባር ሲፈጽመው ብቻ ነው። ያለበለዚያ ግን በመሐል ተቀምጦ ወደ እደላው እያደላ



ዝውዝው የሚጫወት ዘሮ ዘሮ አደጋ ላይ እንደሚወድቅና ርከሸ ውዳቂ እንደሚሆን ከእኔ መረዳት ይቻላል።»

ንግግሩን ከሚያዳምጡት እውነቱም ስለነበር የሚታየውን እስተያየት ይሰጣል።«የፖሊስን ሞያውን ከንነህ መናገርህ አላሳመነኝም ፖሊስ የሚሠራው ሥራ ያለ ቢሆንም ሞያውን መጥፎም ሆነ መልካም ስም ሊያስጠው የሚችለው ሥራውን የሚሠራው ግለሰብ ሲሆን በአጠቃላይ ሥርዓቱ ወሰኝ ይሆናል። አንተም በሞያው ሰልጥነህ በተግባር የገለጽከው ሁኔታ የተለየ ሊሆን ይችላል። በእርግጥ የተሰጠህ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ትክክል ነበር ብለን ፍጹም ባንሆንም ግለሰቦች የራሳቸውን እስተሳሰብና ፍላጎት በሞያቸው ላይ እያፀባርቁም ማለት አንችልም።አንተም ለዓላማህ ጽኑ ነበርክ ማለት አይቻልም። በሚያምኑበት የመጽናት ችሎታ ያላቸው ሰዎች በጣም እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ስንቸገር ብቻ የወገን ችግሮችና ፍቅር የሚታዩን ከሆንና ሲደላን ግን የምረሳቸው ከሆነ ቀድሞውንም ውሸታም መሆናችንን አንተም ጠቅሰኸዋል። ያደረከው ኑዛዜ በዚች በችግር ላይ ለምንገኘው ጓደኞችህ እንጂ ለበደልከው ክፍል አይደለም። ለሁሉም አሁንም ደግመህ ደጋግመህ ራስህን የምትአምንበትን ነገር ለመሥራት ማስመኑ ነው። ያለበለዚያ እንዳልከው ኑሮ ዝውዝው ይሆናል።»ግሰውም እንዴት ተይዞ ሊመጣ እንደቻለ ሲጠይቀው፤

ሲጃራውን እያይዘ ጣሪያ ጣሪያውን እየተመለከተ፤ «እንደምታውቁት «የምዕራብ ሶማሌ ነፃ»አውጭ ስም የሚዋጉት ክፍሎች ከክፍለሃገር የአስተደዳር ክፍል ጋር የሰላም ንግግር እናደርጋለን በማለት በተወከዮች በኩል መጠየቅ ያቀርባሉ። ከዚያንም የሰላሙን ንግግር ለማድረግ ከክፍለሃገሩ ውስጥ ከሚገኙት ቅርጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሰዎች ተወጣጥተው ጉርሱም ላይ ያለውን ጦር በሚያዘው ኮሌኔል መሪነት ከተባለው ሥፍራ እንሄዳለን። የወታደር ክፍሉም ከነትጥቁ ሲሆን ሲሸል ለባሹም በኪሱ ሽገጡን እንደያዘ ከተቀመጥንበት ሕዝባችንን ሳይነቃነቅ ወዲያውኑ አበቁት። ኮሌኔሉን የክፍለሃገሩን የሕዝብ ድርጅት ከድሬ የበታች ሺማምንቶችን ለመግደል እፍታ አልወሰደባቸውም። እኔና የወረዳውን ሕዝብ ድረጅት ከድሬ ይዘው መጥተው ከሐርጌሰ ትልቁ እስር ቤት ጨመሩን ሐርጌሰ ከዚህ የተሻለ እስር ቤት ነው። ምግብ በቀን ሦስቴ ይቀርብልናል። ብዙው እስረኛ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያውቅ ስለሆነ ስቃያችን ይሰማቸዋል።

ተስፋዬም ለመቶ አለቃው «ይህን አይነት ማጭበርበር ሲፈጸም ብዙ ጊዜ ነው ለምንድነው የእኛ መሪዎች ከአለፈው መማር የማይችሉት?» ብሎ ሲጠይቀው፤

መቶ አለቃውም ተከዝ ብሎ «እኔ እንደማየው እኛ ኢትዮጵያውያን ምንጊዜም ጦርነት ብንገጥም እናሸንፋለን የሚለው እስተሳሰባችን ሲወርድ ሲዋረድ ከአባቶቻችን ተላልፎ በደማች

በመኖሩ ያ ወኔ ወደፊት ለሚመጡብን ችግሮች ጥንቃቄዎችን እንዳናደርግ ዝጉ አደርጉናል። ለምሳሌ ታሪክን መጥቀስ ይቻላል ጣሊያንን፲፱፻፳፰ ዓመተ ምህረት አደዋ ላይ ድል መተን ከአሸነፍነው በኋላ ያንን ቂሙን በለመርሳት ለአርባ ዓመት ተዘጋጅተው በጠራ የጦር መሣሪያ በምድርም በአየርም ሊያጠፉን በ፲፱፻፷፱ ዓመት ምህረት መጣ። እኛ ግን በዛው በጥንቱ ጎራደና ጎዴአችን ተሰልፈን ጠበቅነው ወጤቱም ታየ።በአሁንም ጊዜ ቢሆን ምንም እንኳን ቷሚው ሠራዊታችን ቢሰለጥንና ዘመናዊ መሣሪያ ቢታጠቅም ከለ መሣሪያው በባደ እጅ ጠላቱን እንደሚያጠፋ ሆኖ ነው የሚቀርበው። ከጦርነት መልስ ሁላችሁም እንደምታውቁት እገሌ ፈሪ ነው ተኝቶ ነው የሚቶክሰው ተብሎ ሲፌዝ፤ እስከ ቀርብ ጊዜ ቶሞ መተከስ እንደጅግንንት ይቆጠር ነበር። ይህን ዝርዝር ሐተታ ውስጥ የገባሁት ላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች በሙሉ በዛሬው ዘመን አይሰሩም ለማለት ያቀረብኩት ምክንያት ሲሆን፤ ያዘናጋሉ። የሩቅ ጊዜ ጥናቶች እንዳይደረጉ መንገድ ይዘጋሉ።

ወደዋናው ጥያቄ ልመለስና ዱሪኛቹ በደንብ ጥናታቸውን አድርገው በሰላዮቻቸው ማን እንደሚመጣ ተነግሮአቸው ጠበቁን ወጤቱ ያው እንደነገርኳችሁ ሆነ። የእኛ ሰው ስለላን የሚያየው ለግለሰቦች አገልግሎት ከመስጠት አኳያ በመሆኑ ለሃገር መሰለልም የተለመደ አይመስለኝም ለመሪው እንጂ። ይህችም ሃገር ከቀኝ ገዢዎች የተማረችውን በሰለሰ ኃይል የጠላት ጦር ማጥቃትን ዘዴ ብተጠቀምብን አያስደንቅም። የሚያስደንቀው የእኛ ከአለፉት ድርጊቶች በግትርነታችን ያለመማራችን ነው። እኛም ያደረግነው ጥፋት ሳይሆን ስህተት ነበር። በመጀመሪያ መሣሪያ ታጥቆ ከዱር የመሸገን ክፍል ለማናገር ከነሙሉ ትጥቅ መቅረቡ ስህተት ሲሆን ወታደር አስፈላጊነቱ አንድ ነገር በሰላማዊ መንገድ በብዙ አቅጣጫዎች ተሞክሮ አማራጭ ሲጠፋ ነው። በርግጥ በጥቂቶቻችን አስተሳሰብ ለእውነተኛ የሰላም ድርድር የሄድን ቢመስልም፤ በነሱ በኩል ሆኖ ላየው ብትቀበሉን ተቀበሉን ካልሆነም እናጠፋችኋለን ሊመስል ይችላል። ሆኖም እንደዚህ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ስለአካባቢው ጠንቅቀው በሚያውቁና ከጦሩ ውጭ በሆኑ ግለሰቦች መሆን ነበረበት። ከዚህን ላይ ነው ስህተት የተደረገው።

ከዚያንም ሁለት ወር እንደቆየን ወደሐመር አመጡን። እኔን ከዚህ እስር ቤት ሲያመጡኝ አብሮኝ የነበረውን ጓደኛዩን ከሌላው እስር ቤት ወሰዱት።»

አይኖቻቸውን እየተመለከተ «የእኔ ታሪክ መች በዚህ ያከትማል፤እንደተነገረኝ ከሆነ ከሌሎች ሞርኮኛ ብለው ካሰሯቸው ወገኖች እንደሚቀለቅሉኝ ነው። ከዚያው ሕይወቴ ታልፋለች። የሃገሬ መንግሥት ከሆነ ለሕዝቡ ደንታ የለውም። እኔን ፖሊሱን መሣሪያ ይዤ የተያዝሁትን ይቅርና የአንድ ወረዳ ሕዝብ እሮጊት ሸማግሌ ሕፃናት፣ ዶክተር ነርስ የጤና መኰንን ተማሪው መምህር የእርሻ



ባለሞያው፣ ቀሰውስቱ ሳይቀሩ በሞርከኛ ስም ታስረው ደናሌ ከሚባለው የወባ በሽታ በበዛበት ድንጋይ እንደሚያስፈልጋቸው ሃገር ቤት ሆኜ ሪፖርቱን አንብቤዋለሁ። የሁለቱ መንግሥታት መሪዎች በሥልጣን እስከአሉ ድረስ የምርከኛ መለዋወጦች ይኖራሉ ብዬ አላምንም። ሁለቱም ከሕዝባቸው ሙሉ ድጋፍ ስሌላቸው በመካከላቸው የሚደረገውን መቆራቆስን ይፈልጉታል። መሣሪያ የሚያቀብሏቸው መንግሥታትም ቢሆኑ በተዘዋዋሪ የሚያማክሯቸው ያንኑ ነው። የእኛም መንግሥት ሁኔታው ትንሽ ለዘብ ካለለት ስለሞርከኛው ደንታ ያለው አይደለም። እንግዲህ «ዳግማዊ ሙሴ» በኢትዮጵያ ምድር ተፈጥሮ ከባርነት ነፃ እንዲያወጣን መጸለይ ነው።

የወታደሩም ክፍል አንዳንድ ቅዋሜዎችን እንዳያነሳ ከደቡብ ሰሜን ከሰሜን ደቡብ ያዘዋውሩታል። በዚያውም ላይ ቤተሰቡን በሬዲዮ እናገናኛለን የሚል ፕሮግራም በመጀመራቸው መቼ ይደርሰኛል በማለት በናፍቆት ልቡ ተሰቅሎ እንዲኖር ተደርጓል። ከዚያ ሌላ በገፃቸው የደጎሱ መጽሐፍት በሬዲዮ ይነበብለታል። ለጊዜው «ፍቅር እስከመቃብር» የሀዲስ ዓለማየሁ ሲመረጥ፤ «አርሙኝ» የመኰንን እንዳልካቸው፤ ተነበው፤«ጎባጣው ትዳሬ» የስዩም ሠርፀ መድህን መጽሐፍ ማስረጊያ ይሆን ይሆናል።በአጠቃላይ ልገልጽ የፈለኩት እንዴ ለሌላው በሚመለከተው ሃላፊነት አተኩሮ እንዳይመለከት መንገዶቹ መታጠራቸውን ለመግለጽ ያህል ነው።»

ሁሉም የመቶ አለቃን ንግግር ከዳመጡ በኋላ ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ ያገኙታል።የመንግሥት ለውጥ ተደርጎ ወደሃገር እንመለሳለን የሚለው ተስፋ ያከትማል።በሶማሊያ ከእስር ቤት ውጭ እንደማይኖር ያውቁታል።የወደፊቱ የመውጣት ተስፋቸው አክትሞ እንደ መምህሩ ገድሉና እንደ መኰንኑ አዳሙ የአእምሮ መታወክ ደርሶባቸው መቀራረብንና መመካከር ተስኖአቸው እንዴ ሌላውን የችግሩ መንስኤ መሆኑን ገምቶ በባላአጋራ መልክ ተያይቶ በጊዜው የነበረቻቸው ፍቅር እንደምትጠፋ፤ ሁሉም ተለያይቶ የራሱን ችግር የሚያሰላስልበት ጊዜ እንደሚመጣ ይገምታሉ።

አዲስ የመጣው መቶ አለቃም ቢሆን በሶማሌ እስረኞች የተለየ መከባከብና እርዳታዎች ባይሰጡት ኖሮ እርሱም ከደረሱበት ችግሮች አንፃር የአእምሮ መታመክ የሚደርስበት ነበር። ተይዞ በመምጣቱ ሶማሌዎቹ ትልቅ አክብሮትን ሲሰጡት የወታደር ወጉ መሆኑንም በመንገር ያጽናኑታል። በስደተኛ መልክ ከመጡት ይበልጥ እንክብካቤዎች ሲያደርጉለት ይታያል።

በዚህን ሁኔታ ላይ እንዳሉ በእስር ላይ የነበሩ ኬኒያዊያን የመፈታትና በሶማሊያ ውስጥ ከእስኞቸው ሥፍራ መኖር እንደሚችሉ ሲነገራቸው ኢትዮጵያኑ ግን በቅርብ የበቶሎ ገንፎ በበርሜል ሸይ በባልዲ ከሚቀርብበት እንደሚወሰዱ በስር ቤቱ አካባቢ መወራት ተጀመረ።

ሰይድም የሚወሰዱበትን ሥፍራ ቀደም ብሎ ሰምቶት ኖሮ

ብዙ ኢትዮጵያውያን ካሉበት የወታደር ቶጠራ ከሌለበት በአልጋ ላይ ከሚተኛበት ትወሰዳላችሁ በማለት ሲነገራቸው ከእርሱ መልከም ነገርን ስለማይጠብቁ ከባሰ ሥፍራ እንደሚሄዱ ይገምታሉ።



## ፶፮

ዕለቱ ዐርብ ጥር ፲፱፻፷፱ ዓመተ ምህረት ነበር። በዚያን ሙቀቱ በየለበት ወር መስከቶች በሌሏቸው ክፍሎች ኢትዮጵያውያኑ በሙቀቱ ተደክመው ተኝተዋል። ሼህ መሕሙድ የጸጥታው ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ ወደ እስር ቤቱ መጥቶ፤ ከበራራፉ ቆሞ «አዌ እምርኪ» እማራዎቹ የታሉ በማለት ሲጠይቅ፤ ኢትዮጵያውያኑም ምግብ አቀባዩ የመጣ መስሏቸው መቀበያቸውን አንጠልጥለው ሸርጣቸውን በማጠባበቅ ወደበሩ ሲወጡ ሼህ መሕሙድም የመጣው ከእስር ቤት ሊያወጣቸው ስለሆነ ያላቸውን ንብረት ይዘው እንዲነሱ ነግሮአቸው፤ እነርሱም ሸርጣቸውን አሸርጠው በጎ አድራጊዎች የሰጧቸውን ሸሚዘቻቸውን ደርበው፤ነጠላ ጫማቸውን አደርገው መለወጫቸውን በእንሶላቸው ቋጥረው ከእስር ቤቱ በራፍ ላይ ወጥተው ተሰለፉ።

ሼህ መሕሙድም መቶ አለቃን ከመሐላቸው ነጥሎት ወደክፍሉ እንዲመለስ ሲያደርግ፤ወገኖቹ ፊታቸውን መልሰ አድርገው ሲመለከቱት አይኖቹ እንባን ሲያቀሩ፤ እነርሱም ስሜታቸውን ለመቆጣጠር እየተናነቁ አንዳንዶቹ ከአናታቸው በሚወርደው ላብ አማሀኝተው ሰያስቡት የሚወርደውን እንባቸውን በሸርጣቸው እየጠረጉ፤ እርሱም ሲቃ እየተናነቀው፤«ወንድሞቼ መልከም ዕድል ይግጠማችሁ፤ምናልባት ዕድል ገጥሟችሁ በሕይወት ሃገራችን ከተመለሳችሁ በነገርኳችሁ አድራሻ ተጠቅማችሁ እናቴ በሕይወት ካለች ልጅሽ በሶማሊያ ውስጥ በእስር ላይ ይገኛል በሉልኝ። እኔ ብጪክንባትም እሷ አትጭክንምና ያለሁበትን አውቃ እርሟን ታውጣ።»

መቶ አለቃው ሊናገር የፈለገውን ተናገር ሳይጨርስ ሰይድ ገፍቶ ከክፍሉ አስገብቶ ሲዘጋበት፤አንድ ሰቪል የለበሰ ግለሰብ ወደ ሸህ መሕሙድ ቀርቦ ከተነጋገሩ በኋላ ስድስቱን ኢትዮጵያውያን በጸጥታው ጽሕፈት ቤት መካከል በሚያስወጣው በር ወጥተው፤ ከውጭ ቆሞ ከሚጠብቃቸው ጅብ መኪና ላይ ተሳፍረው፤ በሸህ መሕሙድ እየተሸፈሩ ሸጉጥ በታጠቀ ግለሰብ ታጅበው በዚያን ጠራራ የጥር ሙቀት ከእስር ደቂቃ ጉዞ በኋላ ከውጭው ሲመለከቱት የድንጋይ ቁልል እንጂ ቤት ከማይመስለው ከትልቁ የሃገሪቱ እስር ቤት ተወሰዱ።

ትልቁ የሶማሊያ እስር ቤት «ሴንተራሌ» ከመሐል ከተማው በስተምዕራብ ወጣ ብሎ ከሕንድ ውቅያኖስ ፭ ሜትር ያህል ርቆ የተሠራ እስር ቤት ነው።የሃገሬው ሕዝብ እንደሚናገረው እስር ቤቱ የተሠራው ሕዝቦች እንደ ዕቃ በመርከብ እየተጫኑ ከውጭ ተወስደው በሚሸጡበት ዘመን እንደነበር ሲጠቅሱ፤ ያሠራውም የአረብ ተወላጅ የበሪያ ፈንጋይ በ«በርቀስ» ስም የሚጠራ መሆኑንም ሲጠቁሙ፤ እርሱም በሶማሊያ ግዛት አካባቢ ይኖሩ የነበሩትን ሕዝቦች እያጠመደ ይዞ ከ«ሴራተራሌ» ከአጎራቸው በኋላ የንግድ መርከብ ሲመጣለት በቀላሉ ጭኖ ወደአረብ ሃገሮች እሻግር ለመሸጥ ያመቸው ዘንድ መርጦ እንደሠራው ይተርካሉ።

«ሴንተራሌ» በሦስት አቅጣጫዎች በሕንድ ውቅያኖስ የተከበበ ሲሆን መውጫውና መግቢያው በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነው። ዋናው እስር ቤት «ሴንተራሌ» ሁለት ቅርጫፍ እስር ቤቶች በግብ አጥር የተለዩ አሉት። «ብዮሙንደ» ቀጠርተኛና ሴት እስረኞች ሲገኙበት፤ «ቀምታ» የሃገሪቱ የፖለቲካ እስረኞች የታሰሩበት ነው።

ስድስቱ ኢትዮጵያውያን በሸህ መሕሙድ ሹፌርነት በአንድ ሰው አጃቢነት ከ«ሴንተራሌ» ሲደርሱ ከመጀመሪያው በር ላይ ቆመው ከነበሩት ዘበኞች አንደኛው ያንን ከጠፍጣፉ የብረት ዘንጎች የተሠራውን መዝጊያ በአለው ኃይል በመጠቀም ገፍቶ በመክፈት መታወቂያቸውን ጠይቆአቸው ካሣዩት በኃላ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው፤ከገቡ በኋላ ሸህ መሕሙድና አጅበ ይዟቸው የሄደው ግለሰብ ዘልቀው ወደ መሥሪያ ቤቱ ሲገቡ፤ እስረኞቹ ወደ ሁለተኛው በር ከመግባታቸው አስቀድሞ በመጀመሪያ በር ላይ የነበሩት ዘቦች በአስላቸው የቋጠሩትን ልብስ አስፈትተው ፍተሸ አደረጉ። ኢትዮጵያውያን ተይዘው ወደእስር ቤቱ ሲመጡ ወታደሮች ናቸው የሚል ግምት ስለነበር ያንን ቅጠለኛ የወታደር የደብ ልብስ ለመውሰድ ፋኩቻው እያደርስ ነበር። በዕለቱም ሦስት የደብ ልብሶችን ከሐጉስ ከተሰፋዩና ከግሰው አገኙ። ሁለተኛው በር ተከፍቶ እንዲገቡ ተደረገ።በስተግራ የእስር ቤቱ መዝገብ ቤት ሲኖር በስተቀኝ የእስር ቤቱ ቤሮና የኢትዮጵያውያንና ነፍሰ ገዳዮች ታሰረው የሚገኙበት ክፍሎች ናቸው።

አዲስቹም እስረኞች ከመዝገብ ቤቱ ተወስደው ስማቸውን የነበራቸውን ሞያ የመጡበትን አከባቢ እድሜአቸውን ሲያስመዘግቡ፤ ሸህ መሕሙድም የስም ዝርዝራቸውን ለተረኛው መኰንን አስረክቦ መልካም ዕድል ይግጠማችሁ ብሎ ወጥቶ ሄደ።

በወቅቱ ኢትዮጵያኑ ከእስር ቤቱ ደጃፍ ሲደርሱ የተሰማቸው ስሜት ይህን ነበር ለማለት ያስቸግራል።የደብ ልብሶቻቸውን በቀሟቸው ወቅት የወታደሮቹ ክፍሎች ከንፈራቸውን በመንከስ «ይበለን ያለ አበታችን በገዛ እጃችን ያደረግነው ነው» በማለት ሲቆጩ መምህሩ ገድሉ ግደሉኝ እንጂ ከበሩ አልገባም በማለት ትንንቅ ሲያደርግ፤ እውነቱም አንደኛውን ዘበኛ በመገላመጡና የወሰደበትን ማበጠሪያውን ለማስመለስ ባደረገው ግብግብ ጥጋበኛ «አግራ» በሚል ስም ጎሸማውን ቀምሶ ከበር ገባ።

ከእስር ቤቱ ሲደርሱ እስረኛው ምሰውን በልቶ ከክፍሉ ተዘግቶበት ስለነበር ሦስተኛውን በር ከፍተው ከሺ እስረኛ በላይ ከሚዝናናበት አውድማ ከሚያክል ሜዳ ላይ አውጥተው ለቀቋቸው። በአስራ ሁለቱ ክፍሎች የሚገኙት እስረኞች ኢትዮጵያውያንና ነብሰ ገዳዮችን ሳይጨምር የነበሩት በክፍላቸው መዝጊያ እሾልከው እየተመለከቱ «እግር»፤ «እግር» በማለት ጥሪያቸውን አደረጉ።



ከእስር ቤት ከነበሩት ኢትዮጵያውያን ለዘበኞች በልብስ አጣቢነት ከበር ውጭ የነበሩ በትልቅ ባልዲ የበቆሎ ገንፎ ከበርሜል ቀድተው አምጥተው ከመጠጫው ኩባያ ጋር አሲያዟቸው። የመጡት ከዋናው ጸጥታ ክፍል ስለነበር ረሃብ አለባቸው።ከዚያን በሃያ አራት ሰዓት ይሰጣቸው የነበረውንም ምግብ አልተቀበሉም።የቀረበላቸው ምግብ አይተውት የማያውቁት ነገር ስለሆነባቸው ሊያለምጡት ወይም ሊጠጡትም አልቻሉም። እስተናጋጆቹም በመጀመሪያ ቀን እነርሱም ያን ዓይነት ችግር እንደገጠማቸው ነግረቸው፤ ለሁሉም ሆድ ባዶ ይጠላል በሚል ስም እንዲውጡት ገፋፏቸው።

መሰው እስረኛ ለራት መቀበል ከውጭ ከመለቀቁ ቀደም ብሎ ከእስር ቤቱ መኰንን ቢሮ ተጠርተው ፤አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት አማርኛና ሶማሌኛ የሚናገር ለአስተርጓሚነት ቀርቦ እርሱም ከሁለት ዓመት በፊት ከአስራ ሁለት ጓደኞቹ ጋር ወደዚያ እስር ቤት እንደመጡ አጫውቷቸው፤ ያም ያለፍርድ መሆኑን ተናግሮ ምክንያቱንስ አዲሶቹ ሲጠይቁት አለማወቁን ሲገጽ እነርሱም መኰንኑን ለምን እንደታሰሩ እንዲጠይቅላቸው ሲያደርጉ፤«የተነገረኝ ነገር ቢኖር አስቀምጧቸው የሚል ስለሆነ በዚያን አንፃር አትጠይቁኝ ግን አሁን የጠራኋችሁ የመኝታ ክፍሎች ከካቦዎች ጠይቄ ስለአገኘሁኝ ዘበኞቹ ከክፍሎቹ ሲያስገቧቸው እንድትተባበሩ ለመግለጽ ነው።በዕለቱ የሌሊት ልብሳችሁና ምግባችሁ ስላልወጣ ይቅርታ እንጠይቃለን። የምታነጥፉት ሰሌንና የምትለብሱት ብርድልብስ በቂ የመኝታ ሥፍራ ሲመደብላችሁ ይሰጣችኋል በማለት አሰናበታቸው።»

ዘጠኝ ሰዓት ሆኖ ያ ለሁለት ለሦስት የሚገፋት በሮች ተከፍተው፤በአስራ ሁለቱ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት እስረኞች «ቦርክ» እየተባለ ከሚጠራው ሜዳ ላይ ሲወጡ፤ ከኦጋደዴን አከባቢ የታሰሩ አማርኛና ሶማሌኛ የሚናገሩ ኢትዮጵያውያን ወደወጣቶቹ ተጠግተው ተይዘው ወይስ ወደው መምጣታቸውን ጠይቀዋቸው፤በውዴታቸው መሆኑን ሲያረጋግጡግሯቸው እንዴትስ «ከዘንዶ ወደ እዞ» ይመጣል በማለት በማሽፍ «የቀሩት ወገኖቻችሁ ያሉበትን የመከራና የሰቆቃ ኑሮ ትቀምሱታላችሁ» በማለት የተሰማቸውን ይገልፃሉ።

«ሺሎ» ከሚባለው ክፍል ውስጥ ታስረው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ዘቦችን አስፈቅደው ሌላውን በር አልፈው አዲስ የመጡትን ለመመልከት ወደ«ቦረካው» ቢመጡ፤እስረኛው እንደከበቧቸው ከርቀት ተመልክተው እይሮቻቸው እንባን አቅረው ሲጠባበቁ ቆይተው፤ ሕዝቡ ገለል ማለቱን አይተው፤ ቀርበው ሰላምታ ተለዋውጠው፤ባላቸው ገንዘብ፤ሊጋብዟቸው እስር ቤቱ ውስጥ ሻይና ቡና ከሚሸጥባቸው ክፍሎች ይዘዋቸው ሄዱ።

ቀኑ መሰቶ እስረኛው ተቆጥሮ ሲያበቃ ስድስቱን እስረኞች ከየትኞቹ ክፍሎች እንደሚያስገቧቸው ግራ ይጋባሉ። ከመደበኛው ኢትዮጵያውያን ታስረው ከነበሩበት ሁለቱ ክፍሎች ለማስገባት

የነበሩትም መኝታ ቀርቶ መቀማጫ አጥተው ቆመው ማደራቸውን የእስር ቤቱ የአስተዳደር ክፍል ያውቀዋል። «በረከ» ከሚበለው ውስጥ ከሚገኙት አስራ ሁለቱ ክፍሎች ውስጥ በሦስቱ ውስጥ እንኳን ሀበሽ ሶማሌው እስረኛ ሐብታና ከሁለቱ ከታወቁት «መጀርቴን» ወይም «መረሐን» የዘር ሐረግ ከሌለው አይፈቀድለትም። አንድ ቁጥር« ነበር ኡዋ» ከሚባለው ውስጥ መመደብ ወደያው ኑ የሞት ፍርድ መፍረድ ስለሆነ ሀበሽ ተይዞ ሲመጣ ከዚያን ክፍል አይጨመርም።በቀሩትም ክፍሎች ውስጥ ታስረው የነበሩት ብዙዎቹ በኢትዮጵያና በሶማሌ መከከል በተደረገው ጦርነት በ፸ ዓመተ ምህረት እንዋጋም በማለት የእመጹት ወታደሮች ስለነበሩ ከዚያም በተለይ የወታደሩን ክፍል ማስገባቱ ችግር መፍጠር ስለመሰላቸው አልሞከሩትም። ሆኖም በመጨረሻ በደረጃቸው ዝቀተኛ ናቸው ከሚሏቸው ሦስት ክፍሎች ውስጥ ሲያስገቧቸው ፤ መኝታው ግን ከሽንት ቤት ደጃፎች ላይ ሲሆን ለመተኛት አስቸጋሪ ነበር። ምክንያቱም ክፍሎቹ ስለሚሞቁ እስረኛው በውኃ ሰውነትን ለማቀዝቀዝና ለስግደት ለመዘጋጀት ሌሊቱ ሲመላለሱ ሲለሚያድሩ፤ ከእርግጫው ለመዳን ግርግዳውን ተደግፎ መቀመጥ የነበረው አማራጭ ያ ብቻ ነበር። ኑሮ ነበርና ነፍስ ከሥጋ እስከምትለያይ የሲቃይና የሰቆቃ ኑሮ ተጀመረ።

## ፵ ፯

በነጋታው በእስር ቤቱ የቆዩት ኢትዮጵያውን የእነርሱን ክፍሎች ሲያሏቸው የእነርሱ ደግሞ የባሰ የሲዖል ኑሮ ነበር።ከውጭ መውጣት የተከለከለ፤ መታጠቢያና ሽንት ቤት የሌለው፤ሲሆን አይን ምድር የሚወጣው በጉርድ በርሜል ውስጥ ሆኖ ብረሃን ለማግኘት የሚቻለው ያንን በሽቅድድም በጠዋት ለመድፋት ዕድል የገጠመው ብቻ ነበር። «የማይቻል ነገር የለም ሁሉንም ችለን እንኖራለን» በማለት እንደኛው ወጣት ስለክፍላቸው ለአዲሶቹ ስለአሉበት ሁኔታ ገለፃ ያደርግላቸዋል። «ቀደም ሲል በዚች አንድ አልጋ እንኳን በማታዘረጋ ክፍል ውስጥ እንደዘንድሮው አይብዙ እንጂ ምሁራን ተማሪዎች ወታደሮች ታስረውባታል።ዝነኛው ኢትዮጵያዊው የአየር ኃይል ባልደረባ የነበረው ለገሠም በዚች ክፍል ውስጥ ታስሮባታል። ለሁሉም ወገን በውጭም ሆነ በሃገር ውስጥ የደረሰበትን ስቃዩን በቦታው እንደሀ ተገኝቶ ያያውን መዝግቦ ጊዜ ሲገጥም ምንም ሳይሸሽግ መግለጹ፤ ለማንኛውም የሃገር ሕዝብ ሁለቴ እንዲያስብ ይረዳዋል ብዬ እስባለሁ፤ ያለበለዚያ ግን በሃገር ወዳድነት በወገን ፍቅር በየአቅጣጫው ተሰልፎ አድማጭ በማጣት ተበትኖ በየአለበት «ማደሪያ እንዳጣች ውፍ» ተከራቶ የሚቀርበት አጋጣሚ ሊኖርም ይችላል።ሆኖም ግን በዚች የመከራ ሥፍራ ያለን ወጣቶች ለችግሩ ገና አልተበረከክንም። ሁላችንም ከዚህ ያለነው አንድ ተስፋ አለን ይህቺን የሲዖል ቦታ ሁኔታ የምንናገርበትም ሆነ የምንጽፍበት ዓለም ላይ እንወጣለን ብለን እንገምታለን። ጊዜው እየተራዘመ ስቃዩ እየበዛ ሲሄድ ፍጹም የመጨረሻዋ ሥፍራችን ትሆናለች እንላለን።ሆኖም ሰው



ነንና መከራንም ደስታንም በተለያዩ ወቅታት አብረናቸው እንኖራለን።ግን ይበልጥ የሚያሣዝነው ወደዚህ እስር ቤት የሚመጣው የወገን ቁጥር እየጨመረ መሄዱ ነው። በ፸ ዓመተ ምህረት በዚህ እስር ቤት የነበሩት ወገኖች በጣም ጥቂት ሲሆን ይሄው በሁለት ዓመት ልዩነት ውስጥ ቁጥሩ «ብዮሙንደ» ያሉትን ቤትና ወንደቹን ጨምሮ እዚህ «ሴንተራሌ» ካለነው ጋር መቶ አርባ ደርሰናል። ይህ ከሞርከኛ ጣቢያ ድንጋይ ሲፈልጡ ፍንጣሪው ተሸንቆሮባቸው ለማስወጣት የሚመጡትን ሳይጨምር ነው።የእነርሱን ሁኔታ ደግሞ ፈጽሞ ጆሮ ችሎ የሚሰማው አይደለም። በዚያን በረሃ ውስጥ የሃገሪቱ እውነተኛ ልጇ «ኢትዮጵያዊው ሙሴ ዶክተር ጥበቡ»ባይኖርልን ኖሮ ካለነው ከአስር ሺ የምንበልጠው ኢትዮጵያውያን እንዳችንም የለንም ነበር፤ በማለት እንዳንዶቹ ለእርዳታ በመጡ ቁጥር ያደረገላቸውን እያደነቁ ያጫውቱናል። አንዳንድ ወገኖች ባላቸው ሞያ ለወገናቸው የራሳቸውን ጊዜዊ መኞት ተተው በየመስኩ አገልግሎታቸውን ይሰጣሉ የሚለውን በጎ አድራጎቶች በዚህ ቦታ ሆነን ስንሰማ ሰዎች ለሰው ሲኖሩ እኛ ለራሳችን መኖር እንዲት ይሳነናል በማለት ሞራላችን ወድቆ ተስፋችን ተቀጭቶ ነፍሳችንም መከራን መቀበል አቅቷት ልታልፍ ስትውተረተር የነበረችውን፤ ቃሉ መልሶ ነፍስ ይዘራባታል። የዶክተራችን እርዳታ ለእኛም ደርሶናል ማለት ነው። «የሃገሩን ሠርዶ በሃገሩ በሬ» ማለት እንዲያ ነው።

በሃገራችን ሕዝብ ላይ በውጭም በግቢም የደረሰው ስቃይ በተናጠል የምንወጣው ነገር አይደለም። የሁላችንን የሃገሪቱን ልጆች ከንድ ትብብር የሚጠይቅ ነው። ሰው በዓለም ሲኖር ይሳሳታል ይቸገራልም ግን የእኛን ዓይነቱ ችግር ተደጋግሞ ባይደርስ ይመረጣል።እኛም ብንሆን ወደዚህ አካባቢ ለምምጣት ምክንያቶች አይደለንም።በምክንያቱ ግን ብዙ ተጎዳን።አሁንም ለጊዜው በገጠመን ችግር መበርከክ የለብንም። ረጋ ብለን ለማሰብና ብሩሁ ጊዜ እንደሚመጣ ለመመልከትና ዕድሉ ገጥሞን ሌሎች ወገኖች ከዚህን ዓይነት ወጥመድ ውስጥ እንዳይገቡ የምናበረክተው አስተዋፅኦ ለማፍለቅም ይረዳን ይሆናል። ማወቅ ያለብን ችግራችን አገር አቀፍ ችግር መሆኑን ነው። ሁሉም በችግሩ ወላፈን ተለብልቧል ስለሆነ ይህንን የጋራ ችግር ለመቋቋም የጋር ግንባር ሊያስፈልገን ነው።

በእርግጥም ማናችንም ብንሆን ሃገራችንን ጠልተን አልወጣንም። ወጥተን እንቀራለን ብለን አላሰብንም። እንደምንተያየው ሁላችንም ወጣቶች ነን የአባቶቻችን ተኪዎች መሆን እንችላለን። እስር ቤቱነም የመከራ ቦታ ብቻ አደርገን መውሰድ የለብንም። እንደዚህነ ዓይነት ሥፍራ ማየቱም ቀላል ነገር አይደለም። አባቶች በጠላት ዘመን ይህን ዓይነት ችግር ደርሶባቸው እንደነበር ከታሪክ በመጠኑም ቢሆን ተምረናል። ግን የእነርሱ ከውጭ ጠላት ጋር ሲሆን የእኛ የዘመኑ ትውልድ ግን ራሳችን በፈጠርነው ችግር መሆኑ ነው። ሁኔታውን በአጠቃላይ ለመመልከት ሳይረዳን አይቀርም። በሃገር ቤትም እስራቱን አይተነዋል። በጎረቤትም ሃገር

ያለውምን እየኖርንበት ነው። ከሥሩም ሆነ ከረሃቡ አላመለጥንም።

የአፍሪካ ቀንድ ችግር በማለት የውጭም ሆኑ የሃገራችን ምሁራን ከወረቀት ወረቀት ገልብጠውም ይሁን በተግባር ከውስጡ ገብተው ከፃፉት ይልቅ እኛ በሃገራችን ሆነ በጎረቤት ሃገር ያለውን ሁኔታ ለመገምገምና የምስክር ቃላችንን ለመስጠት ሳያስችልን አይቀርምና ችግሩን ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ የሚጠቅምን ነገር ከውስጡ ለማግኘት እንችላለንና አዲስ መጦችም ብትሆኑ በሁኔታው አትደናገሩ» በማለት ንግግሩን ደመደመ።

ቀደም ብለው «ሴንተራሌ» ታስረው የነበሩትም እስረኞች በምግብ መቀበያ ዕቃ ተደራጅተው ስለነበር መጠጫውን ኩባያና መቀበያ ሣህኖችን አቀረቡላቸው።ብዙዎቹ በሁለቱ ሃገሮች መካከል ጦርነቶች በሚካሄዱበት ወቅትና በከተማም ወጣቱ ላይ በኢሕአፖ ስም ይደረጉ የነበሩትን ግድያዎች እስራቶችን በመፍራት ከሃገሬው ተጠልለው ሳሉ የሶማሌም ወታደሮች አካባቢውን በመውረር በምርኮ ስም ከደቡብና ምስራቅ ኢትዮጵያ አፍሰው የወሰዷቸው ወጣቶች ነበሩ።

እነርሱም ከሃገር ከወጡ በመቆየታቸው የሃገር ቤቱን ሁኔታ በዝርዝር እንዲነግሯቸው አዲሶቹን ሲጠይቁ፤ወታደሮቹም ያደረጉትን ጦርነት ሲገልጹላቸው እውነቱም አዲስ አበባ የተካሄደውን ጭፍጨፋ «ከነፃው እርምጃ» እስከ «ቀዩ ሽብር» የተደረገውን ይነግራቸዋል። እነርሱም ምንም እንኳን ከሃገር ቢወጡም በወገን ላይ የተፈጸመውን ኢሰብዊ ድርጊት ከነበሩበት ጋር ሲያወዳድሩት የነበሩበትን ይመርጣሉ። ምክንያቱም የሃገራቸው መንግሥት አይደለምና።

በእስር ቤቱ ትልቁ ችግር የምግቡ ነገር ነበር። አይተው ረሃቡ ይመኾልጋል አይወሰድ ለሕይወት ያስፈራል። በጉርድ በርሜሎች የተገነፋው የበቆሎ ገንፎ በትልልቆቹ በርሜሎች ውስጥ ይገለበጣል። ቀጠጥን ብሎ ብዙ ሕዝብ እንዲመልስ ተብሎ ለእጅ መታጠቢያ ከተጠራቀመው ውኃ እየተቀዳ ይደልበታል። ውኃው የእግርም ሆነ የእጅ እጣቢ ሊሆን ይቻላል። ይሄው ገንፎ አይሉት እጥሚት ከሁለት የቀረውን ምግብ ለመውሰድ እስረኛው መቅጃውንና መቀበያውን ይዞ ሲሰለፉ፤ በርሜሎቹ ተስተካክለው እስከሚሞሉ ዘበኞቹ ቆመጣቸውን ይዘው ሲከላከሉ፤ አንዳንዱም እጥሚቱ እያደርሰም ተብሎ ከተገመተ የእስር ቤቱ ሽንበል ከዘበኞቹ ጋር ቆመጡን ይዞ ሥርዓቱን ያስከብራል። ሀበሸው ከመጀመሪያው ሽግ ላይ እጁን አያስገባም ። አቅም ማነስ ሲሆን ቀደም ብለው የሞከሩትም በፈላው እጥሚት እጆቻቸው ወይም እግሮቻቸው በመቃጠላቸው ይቅርብን በማለት አይመለሱበትም። አንዳንዶቹ በእከክና በልዩ ልዩ የቆዳ በሽታዎች ይሰቃዩ የነበሩት ዘግየት ብለው ቀጠጥን ያለው አቅም በላቸው ተጨልፎ ሲያበቃ ትንሽ ወፈር ያለውን ከእንጀት ጠብ የሚለውን ለመውሰድ የኢትዮጵያውያኑ ሽግ ከዚያ ላይ ሲሆን



ከዚያም ወረድ በማለት የተጣደበትን በርሜልም ከሥሩ ማጧጠጥ አሉ። ለዚህም ቀን ቀን አለው። ዐርብ ጉልበት ያለው ትግሉን ከአንድ ጉርድ በርሜል መረቅ ላይ ስለሆነ ያን ዕለት ገንፎው በሽበሽ ሲሆን፤ከመረቅ ላይ የሚደረገውን ትንንቅ እንኳንስ ሽንበሉ የሣት አደጋም አያቆመውም። ያንን ዕለት ከሥራ ውጭ የሆኑትም ዘበኞች የደንብ ልብሳቸውን ቀይረው ከሽማው ተሰታፊ ናቸው።

ለስሙ ለያንዳንዱ እስረኛ ሰላሳ ግራም ሥጋ ተመድቦለታል። ግን ከበላተኛው የሚደርሰው እስር ግራምም አይሆንም። ከዚያን ከሰላሳ ግራም ሥጋ በስተቀር ማንኛውም ይቀርብ የነበረው ምግብ ከውጭ ሃገር መሆኑን ጆንያው ላይ የተፃፈው የሃገር ስም ይገልፃል። ለማበያ በውኃ ቀጠጠን ብሎ ከሚታደለው የዱቄት ወተት እስከ ተገንፎቶ እስከሚቀርበው በቆሎ ከውጭ የመጣ ነበር። የታሰሩበት እስር ቤት ሕንፃ የተለሰነበት ሲሚንቶ የተበከው በግመል ወተት መሆኑን የሚናገሩት ሶማሌዎች በእንፃሩ የእርዳት እሬራ መቀበላቸውን ተሰምቶአቸው የሃገራቸውን መሪዎች የሚያማርሩም ነበሩ።

የምግቡ አቀራረብ ሁኔታ ያስመረራቸው ኢትዮጵያውያን እስረኞች ኀመን በጤና በማለት ለእራት የሚሰጣቸውን አንድ ጭልፋ ሩዝ በመቀበል የሚኖሩም ነበሩ።

እንዳንዶቹ የተቃጠሉትን በመመልከት ኀበዝ «የሃገራችን ሕዝብ ጆርባው በአክሮባጅ ከመተለም በዘይት ከመጠበስ አመለጥሁ ቢልም ይሄው ዛሬ ራሱን ቀይሮ በፈላ ውኃ ሲቀቀል፤ በረሃብ አለጋ ሲገረፍ እየነው» በማለት በመፀጸት የሚናገሩ ነበሩ።

ሌላው ትልቁ ችግር ለሶማሌ እስረኞች መፈታት የሚደረገው ከዚያው ከእስር ቤቱ መጥተው ሲሆን በዚያን ወቅት በእስር ቤቱ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን በሙሉ ሥነስርዓቱ ሲከናወን እንዳያዩ በእስር ቤቱ ሌሎች ክፍሎች የሚገኙትን በሙሉ ሰብስበው በሁለቱ መደበኞቹ ክፍሎች ውስጥ ይዘጉባቸዋል። በእንደነዚያ ያለው ጊዜ ስቃዩ ከፍተኛ ይሆናል። ክፍሎቹ መስኮቶች ስላልነበራቸው ይሞቃሉ፤ ውኃ ቢጠማም ወጥቶ መጠጣት አይቻልም። ክፍሎቹ ውስጥ የነበሩት የሠገራ በርሜሎች ይሞላሉ፤ የተቅማጥ በሽታ እስረኛውን ያልተለየው ችግር በመሆኑ «ቶሎ ጨርሰህ ልቀቅልኝ» በማለት መጋፋቱ በየዕለቱ የሚደረግ ቢሆንም የጠቅላላ እጎራ የተደረገ ዕለት ደግሞ ይበሳል። የሚገርመው ለመውጣትም ይሁን ከነበረው ችግር አንፃር ኢትዮጵያውያን አይደለንም በጭራሽ ሀበሻ አታስዩን የሚሉትንም ቢሆን ከሌሎቹ ነጥለው ከውጭ አይተዋቸውም። ከአረብም መጣ ከቆቦ ሁሉም እኩል የመከራውን ገፈተ ይጋተዋል።

የእስረኛው መፈታት ለጥቂት ቀናት የመኝታ ስፋትና የምግብ ጭማሬን ቢያስገኝም ሳምንት ባልሞላበት ጊዜ ውስጥ ከሃገሪቱ በሙሉ ካሉት እስር ቤቶች እምጥተው ክፍሎቹን ይሞሏቸዋል። ያኔ የምግብ እጥረት ይፈጠራል፤ መኛታ ቀርቶ መቀመጫ ይጠፋል። እስረኛው

አብዛኛው እብደት ይሞክክረዋል። በተለይ እንለቀቃለን ብለው እስበው ሳይፈቱ የቀሩት ክፍሎች የጸብ ያለሽ ዳቦ ነው። ያን ውቅጥ አልፎ አልፎ ከነሱ ውስጥ ታስረው ለነበሩ ኢትዮጵያውያን መከራቸው ሲሆን፤በፈሰ ውኃ መቃጠል ጥርስ መሰበር በሰንጢ መወጋትም ሊገጥም ይችላል። ከተቀመጡበት ወይም ከተኙበት መረጋገጥ በየዕለቱ የሚጠበቅ ሲሆን በእስር ቤቱ የነበሩት ሀበሻዎች ችግሩን እንደፈጠሩባቸው የሚከንኑም አልታጡም። ይህን ወቅት ሶማሌዎቹ «ዋ!ወሬር ኔ» ተበሳጭተናል በማለት ይጠቅሱታል። ግን ኢትዮጵያውያኑ ለእንዳደቹ ንዴት ማብረጃ መሆናቸው አልቀረም።

የእስረኛ ብዛት መጨመር ምክንያት በማድረግ ሊያመልጡ ያቀዱ እስረኞች አሉ፤ በሚል ስም እስረኛውን ከመኝታው ላይ ውጭ አውጥተው ፍተሻዎችን ያደርጋሉ። በዚህም ጊዜ ይበልጥ የሚጎዳው ሀበሻው እስረኛ ነበር። ብዙዎቹ ለመድኃኒትና አንዳንዴ የምግብ እጥረቶች ተፈጥረው ጾማቸውን እንዳያድሩ ለዳቦ መግዣ በማለት ሲጃራውን ትንባሆውን ቸርችረው ያተረፏትን የሚወስዱባቸው ያኔ ነው።

## ፶፯

ጊዜው እየረዘመ የመውጣት ተስፋ እየጠፋ ሲመጣና እያንዳንዱም በሚመስለው አቅጣጫ ከእስር ቤቱ ለመውጣት ለጊዜው በእመነበት ይሁን ባለእመነበት ቢሞክርም ያው ያረጀ ታሪክ ሆኖ ያገኘዋል።

ውሎ አድሮ ግን ከሃገሪቱ መሪዎች እስከ እስር ቤት ያሉት ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያኑን እያለያዩ እንደሚጠቀሙባቸው ያለእዳች ነጋሪና ቀስቃሽ ተጨባጭ ሁኔታውን ከተግባር እየተገለጸላቸው ሲመጣ፤ ርስበርስ ተለያይቶ በተናጠል ችግሬ ይፈታልኛል የሚለውን ተስፋ በግልጽ ማናቸውም በእስር ቤት የነበሩት እስረኞች መገንዘብ ደረጃ ሲደርሱ፤ የአበው ተረት «ሰው ከመከረው መከራ የመከረው»ትክክለኛውን ፍች አግኝ በግልጽ እየተቀራረቡ አፈሩ ተዘግኖ ቅጠሉ ተበጥሶ የሚበላበትን ሃገራችንን የራሳችን ሰዎች በፈጠሩት ችግር ከዚህ ደረጃ ከደረሰን በኋላ ሌላ ችግር ውስጥ ለመግባት እርሱ የዚህ ድርጅት አባል፤ ከዚህን ክፍለሃገር የመጣነው ወታደር ተማሪ አስተማሪ በማለት መከፋፈሉ በሕይወት ሆነ በኑሮአችን ላይ ያስከተለውን ችግር ከወጤቱ ልናየው ችለናል፤ የጅብ እራት ሆነናል።ወደዚህ እስር ቤት ከመጣን ሐብታሙ ልብስና ሣሁን እጣቢ አግኝቷል፤ ዘበኛው የደብ ልብሶቹ ታጥበውና ተተኩሰው ሊቀርቡለት ችለዋል። በዚህ በረሃ ባለው ሙቀት ከኩሽና ገብተን ለመለው እስረኛ ምግብ አብሳይ ደረጃ ደርሰናልን ። በእንፃሩም እያመሰግኑን እንጂ የሥራንም ትልቅነት አሳይተናቸዋል። ስሌን እንጥፈው ይተኙ የነበሩትን እንዴት ፍራሽ ሠፍቶ እንደሚተኛ አስተምረናቸዋል።የዕቃ መያዣ በርሳ በእጃቸው ሰፍተው እንዲኖራቸው አድርገናል። ግን ጌታ



ከባሪያው ተማርኩ በማለት የዕምነት ቃሉን አይሰጥምና የእኛም ጉዳይ እንደዚያው ነው። ስለዚህ ያለፈውን እረስተን ከእስር ቤት የምንወጣበትን ወይም የዘመን እስራት ፍርዳችንን ጠይቀን በአንድ ጎኑ መኖር ይበጀናል እንጂ በተነናጠል የተለየ የመፈታት ቸሮታን ይደረግለናል የሚለው አስተሳሰብ በቃ አከተመ ።

ጥቂት ተማሪዎችና መምህራን የታሰሩበትን ምክንያት ለማወቅ ባለሥልጣኖችን እናነጋግራለን በማለት የምግብ ማቆም አድማቸውን ሲያደርጉ፤ ከሰባት ቀን እዳማ በኋላ የቀረበላቸው ሰው ቢኖር በእስር ቤቱ የሃገሪቱ የጸጥታ ጽሕፈት ተወካይ የሆነው ሸንበል ነበር። እርሱም ምግብ ለአቆሙት ሀበሻዎች የሰጠው መልስ በሃገራቸው፤ ሕግ መንግሥት በሚከተሉት ሃይማኖት የተወገዘ ስለሆነ በእስቸኳይ ምግባቸውን እንዲመገቡ፤ ከዚህን የተሻለ ሥፍራ ስለሌ የሚሰጣቸውን ራሽን እየተቀበሉ መኖር እንደሚኖርባቸው በማስተንቀቂያ መልክ ማሳሰቢያ ቢጥም፤ ወጣቶቹ ከዚያን ዓይነት ኑሮ ሞት ይመረጣል በማለት ለጥቂት ቀን አገራገሩ። ሸንበሉም በግል መጥቶ «ጅብ ከማያቁት ሃገር ሄደ ድብዳብ እንጥፉልኝን» አይነት ይመስላል የእናንተ ጥያቄ በማለት በደረቅ ልምጭ ከእፍረተ ሥጋቸው በስተቀር እርቃኑን የነበረውን ሰውነት በደረቅ ልምጭ ሲቀረድደው ቆዳው ከሥጋው እየተገለፈፈ ሲነሳ የተመለከቱ በእስር ቤቱ የነበሩ ሽማግሌዎች በነገሩ ገብተውበት ለመሪያቸው እነርሱ ራሳቸው ሰዎች እንደሚልኩና ጉዳያቸውን እንደሚያስፈጽሙላቸው ነግረዋቸው አድማውን አቁመው ምግባቸውን እንዲቀበሉ ያደርጋሉ። በዕለቱ አድማውን ያቁሙት እንጂ በእርግጥም አንድ መፍትሔ ይሰጠናል የሚል እምነቱ አልነበራቸውም ።

የእስር ቤቱ ሁኔታም በጣም አሰልቺ በመሆኑ ለመውጣት በልዩ ልዩ መንገዶች መጣራቸውን አላቋረጡም።እስር ቤቱን እውነትም እስር ቤት የሚያሰኘው ነገር ቢኖር ምንም የሚያዝናኑ ነገሮች የሉትም።

ቀደም ሲል እንኳን አሜሪካኖች አቋቁመውት የነበረው ቤተ መጽሐፍት በአብዮታቸው ወቅት ዘግተውት መጽሐፍቱ በእስር ቤቱ በርዳ ተቆልለው እንዳንዴ ግለሰቦች ለሕክምና በዚያን አካባቢ ሲሄዱ ለትንባሆ መጠቅለያ በጉራሽ ትንባሆች ሲለወጡ ከመታየታቸው ሌላ በወግ ተጠብቀው ለእንባቢ ሲቀርቡ አይታዩም።

ማዝናኛ ነገሮች ባለመኖራቸው ችግሩም ደግሞ ተደጋግሞ በወጣቶቹ አእምሮ ውስጥ ስለሚጉላላ ሕይወታቸውን ለማጥፋት ሙከራ የሚያደርጉም ነበሩ። በተናጠል ራስን ለማጥፍት ሙከራ ማድረግና አንደኛው ክፍል የምግብ አድማውን ሲያቆም ሌላው መጀመር፤ በግልም እንደአዳሙና ገድሉም እስር ቤቱ ከገቡበት ጀምሮ በየጊዜው ራሳቸውን በረሃብ እያደከሙ ለማጥፋት መሸቱ እንደቀጠለ ነበር። በአጠቃላይም መፈክር እንግበው በእስር ቤቱ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግም

ሲኖር ያም ትልቁ ከሶማሊያ እስረኞች ድጋፍን አስገኝቶላቸዋል። ይህም ሆኖ ግን ያሉበትን ሁኔታ ይከርራል እንጂ አይቃለልም።

ጊዜው እየተራዘመ የእስረኛው ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በቁስል አልከልና በሕጽ በየጊዜው ከሚሰከሩበትና በጩቤ ከሚዘራከቱበት ክፍል ውስጥ አንድ ቁጥር(ነበር ኡኖ) ከሚባለው ኢትዮጵያኑን የሰሯቸዋል። የተመደበላቸው መኝታ ግን ቀን ለውኃ ሽንት ከሚጠቀሙበት ሥፍራ ላይ ሲሆን ማታ በውኃ አለቅልቀውት ሰሌን እንጥፈውበት ይተኛሉ በዚህን ወቅት ብዙዎቹ በተቅማጥና በሳንባ ነቀርሳ እየተያዙ ሲሞቱ በእስር ቤቱ እስታትስቲክ መሠረት ሲሰው እስረኛ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የተለከፈ መሆኑን የእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎች በግልጽ ይናገሩታል። ኢትዮጵያውያኑም ከበሽታው ነፃ አልነበሩም። ብዙዎቹን ሆስፒታል እንወስዳቸዋለን በማለት «ቀምታ» ከሚባለው ከማገገሚያ በታ ያኖሯቸዋል።

በምግብ ማቆሙም በሰላማዊው ሰልፉም ከእስር ቤቱ ለመውጣት ተሞከረ። የሶማሊያ ባለሥልጣኖችም ጆሮ ዳባ ልበስ አሉ። ሀበሻው እንዳለፉት ጊዜያት ለብቻው ተቀምጦ ትንበሆን እየጎረሰ መተከዝ ሆነ። መምህር ገድሉም የመጨረሻው መቱ ስለተቃረበ ወገኖቼን ጥሩልኝ በማለት ከክፍሉ የነበሩትን የሶማሌ እስረኖች ሳከ። ቀደም አትቅረቡኝ ይል የነበረው ገድሉ ተንጋሎ ከሚፈራፈርበት እርዱኝ ወገኖች የሚሉትን ሁለት እጆቹን ዘረጋ። እነርሱም ያን የሚሸተውን ሰውነቱን ሳይጠየፉት ተሸክመው ከውጭ አወጡት። ከሆስፒታል እንዲወሰድላቸው በአካባቢው የነበሩትን ዘበኞች ጠየቁ ግን ምንም መልስ አልተገኘም። ቀኑ መሽቶ እስረኛው ተቆጥሮ ከክፍሉ ሲገባ ዘበኞቹ ከክፍሉ ሊያስገቡት ቢሞክሩ እስረኞቹ አይገባብንም በማለት በሩን ዘግተው ያዙ። የሕክምናው ክፍል መኩንን ተጠርቶ መጣ ሁለት ኢትዮጵያውያን እስረኞች ከመኪናው ላይ እንዲደግፉት ተደርጎ ከሆስፒታል በተወሰደ ማግሥት ሕይወቱ አለፈች።

፶፰

በምግብ ማቆም ምክንያት ብዙው ኢትዮጵየውያን እስረኞች ሕይወታቸው ሊያልፍ ስለሚችል የተለየ መንገድ እንፈልግ በማለት ግለሰባች ሐሣቦችን መንደፍ ጀመሩ። ሐሣቦች በወረቀት ላይ ተነደፉ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያውያን ተነበበ። ከጥቂቶች ተቃውሞ ቀረበ። ቅዋሜውም በድርጅት አንድነት ከሌለን ግለሰቦች ጋር በአንድነት ተሰልፈን የመፈታት መጠየቅ እናቀርብም የሚሉ ነበሩ።

የፖለቲካውን ልዩነት በጊዜው ከሚጠፋው ሕይወት በላይ መወሰዱ በእርግጥም በፖለቲካው አለመብሰልን ሲገልጽ ለጠቅላላው እስርኛ መለያየት ምክንያት መሆኑም ተከሰተ። ሆኖም ጥረቱ ቀጠለ። ጥቂቶችን በሃይማኖት አታለዋቸው ተጨባጩን ሁኔታ አስከደዋቸው



በሃገራችን ላይ የሰደተኛ መብት እንጠይቅም ያስፓቸው ነበሩ። ያም ሆነ ይህ ዕቅዱ ሃገር ለመምራት ወይም ወሰን ለማከለል ሳይሆን ሕይወት የሚድንበትን ለመሻት ስለነበር ከመቶ ዘጠና እጅ ለቀረቡት መደርደሪያ ሐሣቦች በመፈርማ ድጋፋቸውን አረጋገጡ። ጉዳያቸውን ከግቡ ሊያደርሱላቸው ይችላሉ የሚሏቸውን የአምስት ሰዎችን ስም ዝርዝር እንዲሰጡ ተደረገ። መምህር ተማሪ መደበኛ ወታደር ሚሊሺያና የቢሮ ሠራተኛን የሚያጠቃልል ኮሚቴ ተቋቋመ። እውነቱም የኮሚቴው አባል ሆኖ ተመረጠ።

ምንም እንኳን ነፃነት የሌላቸው እስረኞች ነፃ ያልሆኑ የኮሚቴ አባሎችን መርጠው ውጤትን እናገኛለን የሚል ሙሉ ተስፋ ባይኖርም ምርጫቸው ያለ ተጽኖና ግፊት ስለነበር የመምረጥ መብታቸውን በትክክል በመጠቀማቸው ሁለቱንም ወገኖች ሳያስደስታቸው አልቀረም። ተመራጮቹም የተሰጣቸውን ሃላፊነት ተቀብለው ጥረታቸውን ጀመሩ።

ኮሚቴው በመጀመሪያ መደርደሪያ ነው ብሎ ያቀረበው ሐሣብ በብዙሃኑ ድጋፍን ያገኘ በመሆኑ የጎን ከአንድ ቦታ ላይ ለማድረስ ሐሣቦች እንዲቀርቡ ተጠየቀ።ጽንሰ ሐሣቡ ያሉትን ችግሮች በአመጽ ከመቋቋም ይልቅ በዲፕሎማሲ መንገድ መፍትሔዎችን መፈለጉ አማራጭ የሌለው እንደሆነ ተስማምተው፤ ይህም መጠይቅ መቅረብ የሚኖርበት ለእስር ቤቱ አስተዳደር ክፍል ሳይሆን ለሃገሪቱ መሪዎች መሆን እንደሚኖርበት በድምፅ ጸደቀ። ለጉዳዩ ማስፈጸሚያ ገንዘብ ዋነኛውን ስፍራ ስለሚይዝ ያንንም በፍራሽ ማደሉ በበርሳ ስፌቱና በስጃራው ችርቻሮው የተሰለፉትን የኮሚቴው አባሎች ብቻ እንዲያቀርቡ ሲወሰን፤ ከሶማሊያ ምሁራን ጋር ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች የሃገሪቱን የፖለቲካ ሳዕላዊ መዋቅር የጨበጡትን ግለሰቦች ሆነ የመሥሪያ ቤታቸውን አድራሻ እንዲያጠናቅሩ ተደረገ። ዕቅዶቹ ተነድፈው አዳራሻዎቹ ተለቅመው ለኮሚቴው ቀረቡ። ኮሚቴው በሁለት ተከፈለ። አንደኛው ክፍል የሶማሌውን መሪ ከኢትዮጵያዊው መሪ ገንጥለን እናየውምና የፈጸሙትን ኢሰብዊ ድረጊታቸውን አጋልጠን መፃፍ አለብን ሲል ሌላው ክፍል ያንን ቀደም ሲል የራስን ነፍስ በማጥፋት ምግብ በማቆም ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ተገልጸው ብዙ ወገኖቻችን በመሞታቸውና በሕመም በመለከፋቸው ሳቢያ ለዘብ ያለ መንገድን መቀየስ እንጂ በደልን መከድ እንዳልሆነ ተስማምተው ለሚከተሉት ተፃፈ።

፩ ለሃገሪቱ ፕሬዘዳንት
፪ ለሕዝባዊ ሸንጎ ሊቀመንበር
፫ ለሴቶች ማሕበር ለሊቀመበር(የሃገሪቱ መሪ ባለቤት)
፬ ለሠራተኛው ማሕበር ሊቀመንበር
፭ ለሃገሪቱ የወጣቶች ማሕበር ሊቀመበር በተጨማሪ በግል

እላይ ለተገለጹት መሥሪያ ቤቶች ሲፃፍ አንደኛው መሥሪያ

ቤት የሌላውን እንዲያውቀው በማለት በግልባጩ ተገለጸላቸው።

የደብዳቤው ይዘት የሃገሪቱ ፕሬዘዳንት ሆኑ የልዩ ልዩ ድርጅቶች ሃላፊዎች ወደ ሃገራቸው ነፍሳቸውን ለማዳን የመጡትን የጎሮቤት ሃገር ሰዎች በእስር ቤት እጎሮ ያለ በቂ ምግብ መድኃኒት ያለፍርድ ለዘመናት አስረው በበሽታ ማሰቃየታችውን የዓለም ሕዝብ ቢመለከተው ምን አስተያየቶችን እንደሚወስድባቸው ለአንዲት ደቃቃ አስበውበታልን? ። ሃገራቸው የተባበሩት መንግሥታት አባል ሆና ባለ ከመመሪያው ውጭ መሥራቱ አስነዋሪ መሆኑንን ሲያብራሩ በተለይ በሃገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ኢንባሲዎች ዓለም አቀፍ ደርጅቶች ከራሳቸው ከፕሬዘዳንቱ እንዲያማልዷቸው በደብዳቤ የሚጠይቁ መሆናቸውንም እንዲያውቁላቸው ገለጹ ።

በተጨማሪም የሶማሊያ የወጣቶች ማሕበር ሊቀመንበር ችግራቸውን ከሃገሩ መሪዎች ዘንድ ቀርበ ብሶታቸውን እንዲገልጽላቸው በማሕበሩ ስም ሲገልጹለት በግሉም፤ከሁለቱ ገሮቤታማ ሃገሮች በላይ የሚቀራረብና የሚዋደድ የማንም የአፍሪካ ሃገር ወጣት እንደሌለ እያወቀው ለምን ችላ ሊለው እንደቻለ የሚጠይቅ ነበር።



## ፶፱

ለፕሬዘዳንቱ የተረቀቀ ደብዳቤ ከቀሩት ባለሥልጣኖች ለየት ያለ ሲሆን የተፃፈበት ወረቀት እንዱ ቅጠል ዋጋው እስከ አንድ መቶ የሶማሊያ ሽልንግ የሚያወጣ ነበር።ለቀሩትም እንደ ደረጃቸው ታይቶ ደብዳቤው ተዘጋጅቶ ቴምብር ተለጥፎበት ቀረበ፤ግን ለማን እንደሚላክ ሰው ማጠያየቁ ሌላ ራሱን የቻለ ችግር ሆነ። በሐሣብና በአንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች ይረዱ የነበሩትን ግለሰቦች ደብዳቤዎችን ላኩልን ብሎ መጠየቁ እነርሱን ችግር ውስጥ መጨመረ መስሎት ኮሚቴው ስለታየው ደብዳቤዎቹ ሳይላኩ ወራቶች አለፉ። እስረኛውም ተመራጮቹን ነገሩን ከምን እንዳደረሱት በጉጉት በየዕለቱ በተገናኙ ቁጥር ማንሳታቸው ጀመሩ። ስለእስሩ ከማሰብ ይልቅ በጊዜው ለመውጣት ስለሚደረገው ጥረት ማሰላሰላቸውን የተመረጡት ኮሚቴዎች እንደመልካም ምልክት ወሰዱት።

ሆኖም ግን ከሶማሌ እስረኞች ጋር የነበረው ግንኙት በሕብዕ ስለነበር እንደልብ በማንኛውም ጊዜ ቀረበ የሚፈልጉትን እንዲፈጽሙላቸው መጠየቁ እንደሚከብድ ብዙዎቹ አልተረዱትም። ሌላው ዋና ምክንያት እስር ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሀበሾች የታሰሩት በሰላይነት ተጠርጥረው እንደሆነ አስቀድሞ ለሰፊው እስረኛ ተነግሮት ስለነበር በግልጽ ተገናኝቶ መነጋገሩን አይሹትም። በተለይ መንግሥታቸውን በመቃወም የታሰሩት ክፍሎች ኢትዮጵያኑን በአካባቢያቸው ማየት አይፈልጉም። ሆነም ቀረም ደብዳቤዎቹን ሊያደርስላቸው የሚችል ሰው ቢኖር ከእስር ቤቱ በሆነ ምክንያት መውጣት የሚችል ሰው መሆን እንዳለበት በማመን ከውጭ ለሥራ ያለአጃቢ በየቀኑ ከእስር ቤቱ የሚወጡትን መቅረብን እንደአማራጭ ተወሰደ፤ ከብዙ ሙከራዎች በኋላ ግለሰብ ፍቃደኛ ሆኖ ስለተገኘ ጠቅላላውን ደብዳቤ ከፖስታ ቤት እንዲያስገባላቸው ተሰጠው።

እንደአጋጣሚ ደብዳቤው በተላከ ዕለት በሃገሪቱ አሉ ከሚባሉት ትልልቅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በንብ ፈንድቶ ፤ በተፈጠረው አደጋ ምክንያት ወታደሮች አካባቢውን ይቆጣጠሩት ስለነበር ግለሰቡ ከፖስታ ቤቱ ለማስገባት አመቺ ሆኖ ስላላገኘው ደብዳቤዎቹን መልስ አመጣቸው። ተመራጮቹም እስረኞቹ የደብዳቤውን መመለስ ከሰሙ የተለመደውን የምግብ ማቆም አድማ ያደርጋሉን በማሰብ ሁኔታው በምስጢር ሲያዝ፤በከተማው በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች የተጣለው በንብ ዳፋ ለእስር ቤቱም ተረፈው።እስረኛው እንደወትሮው ወጥቶ መናፈሱ ቀረ። ለጥበቃው የዘበኛ እጥረት ስለነበርና በዚያን ግርግር እስረኛ ያመልጣል በሚል ፍራቻ ጥበቃው ከረረ ። ተገናኝቶ ሐሣብ ለሐሣብ መለዋወጡም ተቋረጠ። ሶማሌዎቹን መቅረቡ አደጋ የሚያመጣ ሆኖ ተገኘ፤ ምክንያቱም በንቡን የጣሉት ክፍሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ያለውን መንግሥት የሚቃወሙት እንደሆኑ በሰፊው ስለተነገረ ሀበሾችን ማነጋገር የእናንተ መንግሥት ደግ አደረገ ማለት ይሆናልን በመፍራት

ጀርባቸውን አዞሩባቸው።

ያም ሆነ ይህ ሶማሊያ ውስጥ ከታየው መልካም ነገር ቢኖር ጠበቅ ያሉ ውሳኔዎች በሕዝቡ ላይ ለብዙ ጊዜ አይቆዩም። ያ ሆነና በሩች ለሃያ አራት ሰዓት መዘጋታቸው ቀርቶ እስረኛው እንደቀድሞው በ«ብረከው» ውስጥ ወጥቶ እንዲዝናና ተፈቀደለት። የተመረጡት ክፍሎች ደብዳቤውን የሚያደርስላቸው ሰው ማፈላለግ ሲያደርጉ የመጀመሪያውም አለመሳኩን የቀሩት ሲሰሙ ያው የተለመደው መለያየት ተፈጥሮ፤ተስፋቸውን ቆርጠው ተኳርፈው በየመዐዘኑ ተቀምጠው መተከዝን ሲያደርጉ፤ ግን ባሉበት ሁኔታ ጊዜን በቁጥጥር ሥር ማዋል የሚችል ስለሌለ ያንን እንዳለ ተቀብሎ መፍትሔ ለማግኘት መጣሩ የያአንዳንዱ እስረኛ ግዴታ ጭምር መሆን እንዳለበት ተመራጮቹ ሲያስገነዝቡ፤ የመረጧቸው ክፍሎች ተመራጮቹን በሐሣብና በሚያስፈልጉ ነገሮች ከረዷቸው ከሚቴው ከብዙሃኑ ተነጥሎ በተናጥል የሚያመጣው ለውጥ እንደሌለ ጠቁመው ለመጨረሻ ሙከራ ተብሎ ሌላው ቢቀር የፕሬዘዳንቱን ብቻ ደብዳቤ እንዲያደርስላቸው የቀድሞውን ግለሰብ በልመና መልክ ጥያቄአቸውን ቢያቀርቡለት፤ እርሱም ሁሉንም ደብዳዴዎች ሊያደርስላቸው ተስማምቶ ወስዶ ከፖስታ ቤት አስገባላቸው።

ሶማሌዎች በግል ሰው ከወደዱ ሊመጣባቸው የሚችል ችግር ቢኖርም እንኳን ያንን ተገዝበው ሊያደርጉ የፈለጉትን ከማድረግ ወደኋላ አይሉም። ያ ሆነና ደብዳቤው ተላከ፤ ግን መልስ የለውም። ለሁሉም በአንድ ተስፋ«ለም አለኝ በሰማይ» ስም እድሜ ተራዘመ። እስረኞቹም የተመረጡትን በተገናኙ ቁጥር ያንን ጉዳይ ከምን አደረሳችሁት በማለት መጠየቃቸውን አላቋረጡም።

ለመጨረሻ ጊዜ ሙከራ ተብሎ የሌሎቹን ባለሥልጣኖች አስቀርተው በግል ለሃገሪቱ ፕሬዘዳት ችግራቸውን ለማቅረብ በተስማሙት መሠረት፤ ለሶማሊያ ፕሬዘዳት ለዚያድ ባሬ ደብዳቤ ተረቀቀ።

«ፕሬዘዳቱ ራሳቸው በሰው ልጆች ልዩነቶች የሚያምኑ ካልሆነ በስተቀር በሃገራቸው በሃይማኖትና በሚናገሩት ቋንቋ በመጡበት አካባቢ ምክንያት ይህን የመሰለ ኢሰባዊ የሆኑ ድርጊቶች በሚያስተዳድሯት ሃገር ውስጥ ሲፈጸም ዝም ብለው ባልተመለከቱት ነበር።በግልጽ ለስደት ወደሃገራቸው የመጡትን ኢትዮጵያውያን ለብቀላና ለመያዣ የያዟቸው ያስመስላል።ያ ካልሆነ በስተቀር በዓለም ሕብረተሰብ ውስጥ የሚገኘን የአንድ ሃገርን ሕዝብ ከጎረቤት ሃገር ተሰዶ ወደሃገር ውስጥ ነፍስ ለማትረፍ ለሰላማዊ ኑሮ ሲገባ ያለፍርድ ከእስር ቤት መጨመር ሃገሪቱንም ሆነ አመራሩን መሪውን ጭምር የሚያስወቅስ አይሆንም እን?» በማለት ለሊቀመንበሩ ለዚያድ ባሬ ተፃፈላቸው። ደብዳቤው ቢደርስም፤መልሱ ሳይሆን የተላከው ደብዳቤው ከሊቀመንበሩ ቢሮ ወደ ሃገሪቱ ጸጥታ ጽሕፈት ቤት



ተመርቶ፤ የጸጥታው ጽሕፈት ቤት ወደዋናው የእስር ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ልኮት፤ ከዚያም ለእስር ቤቱ አስተዳደር ክፍል በወቀሳ መልክ ተልኮ፤ ከኮሚቴው አባላት አንደኛው ፊርማውንና ስሙን ከተቦ ኖሮ ተይዞ ከነፍስ ገዳዮች መታሰሪያ ክፍል ተጨመረ።

የሶማሌ እስረኞች ሁኔታው አዲስ ነገር ሆኖባቸው «ሀበሻዎች ለመሪያችን ችግራቸውን ቢገልጹለት እስሩን አከረረባቸው።» በማለት ሲተቹት፤ አንዳንዶቹም የኮሚቴውን አባላት ቀርበው ለሃገራቸው መሪ ምን እንደፃፉለት ቢጠይቋቸውም የምስጋና ደብዳቤ እንዳልሆነ ከመግለጽ ሌላ መልስ አልነበራቸውም። ኮሚቴውም ወደመፍረሱ ተቃረበ ግን ለመውጣት ሙከራን ለማድረግ ብዙ መፍናፈኛ መንገዶች እንደሚኖሩም በመገመት ለችግሩ እጅ ለመስጠት ራሳቸውን ገና ያለሰመኑ ግለሰቦች ስለነበሩ በግልም ቢሆን እንደሚቀጥሉ ወሰኑ።

ከሶማሊያ እስር ቤት ለመውጣት ያልተደረጉ ጥረቶች አልነበሩም።ከእስር ቤቱ ሸንበል እስከ ሃገሪቱ መሪ ድረስ በመፃፃፍም ሆነ በአካባቢው ሕይወትን እስከ ማሳለፍ ደረጃ ተደረሰ። ግን ምንም ተጨባጭ የሆነ መፍትሔ አልተገኘም። ያም በመሆኑ በምግብ እጥረት በመኝታ እጦት በእርዛት ብዙዎቹ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ እየተያዙ የመዳን ዕድል ሲኖራቸው ከሆስፒታል ከመውሰድ ይልቅ በተለዩ ክፍሎች አስረው እስከሚሞቱ ሲያኖሯቸው በመጀመሪያ ከእስር ቤቱ ሲገቡ ሸመል ሸመል ይመስሉ የነበሩት ወጣቶች ሰውነታቸው ሙጥጥ ብሎ አልቆ ጣረሞታቸው ውልጭም ውልጭም ሲል መመልከቱ ምነው ከዚያች ኢትዮጵያ ከምተባለው ሃገር ባልተፈጠርኩ የሚያሰኝ ነበር።በተለይ የአከዳሚውን ሙሩቅ መኩንን አዳሙን ያየና ዳገመኛ በሐሣብ ሰመመን ወደሐረር ጦር አከዳሚ ዘር ብሎ እነዚያን ወጣት መኩንኖች ዳለቻውን ሱሪያቸውን ለብሰው ሰማያዊውን ከታቸውን ደርበው ባጃቸውን ለጥፈው ሁለት ሁለት ሆነው እርምጃቸውን አስተካክለው ወደፈረስ መጋላ ሲሄዱ መሬቷን የሚያነቃንቋትን የአከዳሚ ምርቆች በታየበት ዐይን ዛሬ አዳሙን ራሱን መሸከም ተስኖት ሲውተረተር ማየቱ በእውነቱ በዓለም ከሰው ጋር ነኝ የሚያሰኝ አልነበረም።

፳

ከሶማሊያ ባለሥልጣኖች የመፈታት ዕድል አከተመ። ኮሚቴው ሌላ መንገድ ቀየሰ። ይህውም በተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ከፍተኛ ኮሚሽንን ጽሕፈት ቤት በሐመር በሶማሊያ ዋና ከተማ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥና ከኖረም የጽሕፈት ቤቱን ሙሉ አድራሻ ለማግኘት ዕቅድ ወጣ። የሶማሌ እስረኞች ተቀርበው ሲጠየቁ ሃገራቸው የአረብ ሊግ አባል እንጂ የተባበሩት መንግሥታት አባል እንዳልሆነች ሲገልጹ፤ ግን የተባበሩት መንግሥታት አባል መሆኗ እያጠያይቅም ሆም በዜና አገልግሎታቸው ይበልጥ ተጋኖና በሃገሪቱ

ውስጥ የሚገኙትን ስደተኞች የሚረዳው ቀዩ ጨረቃ(Red Crecent) እንደሆነ ስለሚነገር የተባበሩት መንግሥታት ቅርጫፍ መሥሪያ ቤት ይኑር አይኑር እንብዛም አይታወቅም፤ በዜና አገልግሎቶችም ተጠቅሶ አይነገርለትም።

ከብዙ ማጠያየቅ በኋላ አንድ ግለሰብ በተባበሩት መንግሥታት የስደተኛ ከፍተኛ ኮሚሽን ውስጥ ይሰራ የነበረ፤ ገንዘብ አጉድሏል፤ ተብሎ የታሰረ ሰው ከዚያው ከእስር ቤቱ ተገኘ። ሁኔታው ተነገረው። እርሱም በተቻለው መንገድ በሙሉ እርዳታውን እንደሚያደርግላቸው ለግለሰብ ቃል ገባ።

ደብዳቤው ተረቀቀ። ለሶማሌ መሪዎችና ለኮሚሽኑ የተፃፈው ደብዳቤ ልዩ ነበር። ደብደቤው ጠቅላላ እስር ቤቱ ውስጥ ከሚደረጉባቸው ልዩነቶች በመነሳት ብዛታቸውን ያሉበትን አሰቃቂ ሁኔታዎች ተዘረዘሩ።

ለምሳሌ የእስር ቤቱን ሥሩት የግድግዳውን ውፍረት የሚቀርበውን የምግብ ዓይነትና ክብደት፤የኢትዮጵያኑን ቁጥር፤በእስር ቤት የሞቱትን በሰንበ ነቀርሳ የተያዙትን በታሰሩበት አምስት ዓመት ውስጥ ምንም ዓይነት እርዳታ ከመንግሥት እንዳልተሰጣቸው በመጠቆም፤በመጡበት አካባቢም ሆነ በሚጠቀሙት ቋንቋ ተጽኖ መደረጉን ጠቀመው ጠቅላላ አበሳትን በቀረበው ጥያቄ ያመኑትን ዘጠናውን እጅ አስፈርመው ግለሰቡ በቤተሰቡ በኩል እንዲያደርስላቸው ተሰጠው።

ደብዳቤው በተላከ ሰሞን በሶማሊያ ጋዜጦች በእንግሊዘኛውም ጭምር ስደተኛን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አስመርኩዘው በአምዶቻቸው ላይ ጹሑፎች አወጡ። በጊዜው የአፍሪካ አንድነት ማሕበር ጉባኤ በኬኒያ የሚካሄድበት ቀን በመቃረቡ የኢትዮጵያን መሪዎች ለማጋለጥ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ሲሆን በተጨማሪም የሶማሌ መንግሥት ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ለማስተናገድ በአደረገው አስተዋፅኦ በሃገሪቱ ላይ የምጣኔ ሐብት ውድቀት መድረሱን ጉባኤው በቅድሚያ ትኩረት እንዲሰጠው ታስቦ የቀረበ ሲሆን፤ «በግልጽ ወታደራዊ መንግሥት ሕዝቡን በቦንብና በመድፍ ስለአጨደው የተረፈው ነፍሱን ለማትረፍ በሶማሊያ ግዛት ውስጥ መጠለያ ተሰርቶለት እንደሚኖር ጠቅሰው ሃገራቸው የአፍሪካን አንድነት ማሕበርና የተባበሩትን መንግሥታት ቻርተር በማክበር ስደተኛውን በማስተናገድ ላይ ሳለች የወታደራዊ መንግሥት በግዛቴ ክልል ውስጥ በመግባት በመጠለያ ሠፈር የገቡትን ሕዝቦች በቦንብ እስከመደብደብ ደርሶልና ይህንን ጉባኤው እንደመለከትልኝ እሻለሁ» የሚሉ ነበሩ።

ከወታደራዊ መንግሥት ይሰጡ የነበሩት ማስተባበያዎች ከሬዲዮ ከአዳመጡት እንደተጠቀሰው፤ «በሶማሊያ መንግሥት የሚነገረውና የሚዘከረው የስደተኛ ቁጥር ውሸት ሲሆን በመጠለያ



ሰብስበው ያሰፈሯቸው የራሳቸውን በድርቅ ከተመታው አካባቢ የሚኖሩትን ሕዝቦች በመሆኑ ለዚህም ጠቀም ያሉ እርዳታዎችን ከዓለም ሕብረተሰብ ለማግኘት ሆን ተብሎ የተነገረ እንጂ ኢትዮጵያኑ ስደተኞች በትልልቆቹ የሶማሊያ እስር ቤት ታስረው ነው ያሉት» በማለት ለማስተባበያ ያቀርባል።

ያም ሆነ ይህ ለኢትዮጵያኑ እስረኞች ሁለቱም መንግሥታት በድረጊታቸው አንድ ነበሩ። «በጣም የምናማርረውና የምናወግዘው ይላሉ እስረኞቹ የሃገራችንን መሪዎች ነው። ትውልድ ያቀየልንን ለምለም ሃገራችንን በጠንካራ ክንዳችን እየሠራን የራሳችን ጌቶች እንዳንሆን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሃገር ትተን እንድወጣ ተደርገናል።ከሃገራችን ያስወጣን ኢሰባዊ ድርጊታቸው ስለሆነ ከሶማሌው መንግሥት በግፉቸው አስበልጠን እንጂ አሳንሰን አናየውም። ሶማሊያ ውስጥ ሳለነው ኢትዮጵያውያን ከመቆርቆር ይልቅ ለምን ከአጠገባቸው ለዘመናተ ያለፍርድ በገዛ ሃገራቸው ላይ የሚያሰቃዩቸውን አይፈቷቸውም? ሶማሌዎችስ በሁለቱ ሃገሮች መካከል ያለውን ጥላቻ ለማካረር ሆን ብለው እንደሚያደርጉት የታወቀ ነው። የእኛዎቹስ የሕብረተሰቡስ ይቅር ይሸቀንጠር፤ ለልጆቻቸውስ ምን እያደረጉላቸው ነው? በዚህስ እንየር ተመልከተውት ይሆን? ለሁሉም «የአዘ እንባ ነው»።»

## ፳፩

ወራቱ ሰኔ ዓመተ ምህረቱ ፹፫ ነበር። የሶማሌ ጋዜጦች በሶማሌኛውና በእንግሊዘኛው አምዶቻቸው ላይ ኢትዮጵያውያን መምህራንና ተማሪዎች በሶማሊያ እስር ቤቶች ውስጥ በጥበቃ ሥር እንደሚገኙ አወጡ። ደስታው ለኢትዮጵያኑ ብቻ ሳይሆን ለመላው እስረኛ ጭምር ነበር። ዕለቱ ዐርብ የሶማሊያ እስረኞች ቤተሰባቸውን ቀርበው የሚያነጋግሩበት ቀን በመሆኑ ጠያቂዎቻቸው ይዘውላቸው የመጡት ምግብና አትክዕልት ሲጃራ ብቻ ሳይሆን ጋዜጦችን ጭምር ስለሆነ እስር ቤቱ ያለወትሮው በጋዜጣ ተጥለቀለቀ። በሁኔታው በወቅቱ እንደታየው በመታሰራቸው የተሰማቸው ኢትዮጵያኑ ብቻ ሳይሆኑ መላው እስረኛው ጭምር መሆኑን በግልጽ ታየ። በተለይ ጉዳያቸውን ለፍፃሜ ለማድረስ የረዷቸው ግለሰቦች መቁጠሪያቸውን እያፍተለተሉ የሚያልፉ መስለው ጠጋ በማለት «በመጨረሻ ተሰከላችሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ» በማለት የበጎ ፍቃድ ምኞታቸውን ሲገልጹ፤የአካባቢው አየር ሁኔታ ተለወጠ።በኢትዮጵያውያኑ መካከል ሆነ በሶማሌዎቹ ፍቅሩ በጣም ናረ። ችግር የሰውን ልጆች ሆድና ጀርባ እንደሚያደርጋች ቀደም ብሎ ቢታይም በመጨረሻ ግን ፍቅር አሸናፊ መሆኑ በግልጽ ተከሰተ። ቃል ኪዳን መገባባት ተጀመረ። ሶማሌዎችም ሀበሻው እስረኛ ሲፈታ የሚያደርግላቸውን ነገር ካለ ቃል ኪዳን ማስገባት ጀመሩ። ሲፈቱ በሃገራቸው ውስጥ ስለሚያደቸው ነገሮች በቅድሚያ ገለፃዎችን ሲያደርጉላቸው፤ በተለይ ስለሃገራቸው

ዋና ከተማ ድምቀት ስለሴቶቻቸው ውበትና ሥነስርዓት በማደነቅ ገለፃቸውን አደረጉ።

ስለመፈታት አዘውትሮ ማውራትና መመራመር ሲጀምር በጋዜጦቹ አምዶች ላይ የተገለጸው ተማሪና መምህራንን እንጂ የወታደሩን ክፍል ስለማይገልጽ በዚህን ሰቢያ ደግሞ ሌላ መለያየቶች ተከሰቱ። ይህውም በሲቪሉ እስረኛና በወታደሩ ክፍል መካከል ሲሆን የወታደሩ ክፍል እንፈታም በማለት ጥርጥሬ ሲገባቸው፤መፈታታቸውን ማሰመኑም ሌላ እራሱን የቻለ ሥራ ነበር። ከሀበሻው እስረኛ አብዛኛው ክፍል ወታደር ሲሆን ይህ ክፍል አይፈታም ተብሎ ከተገመተ ጭራሽ መፈታትም የለም ማለት ይቻላል። ሁኔታውን ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ በጥሞና ሁሉቸውም በአንድነት እንደሚፈቱ በተለያዩ መንገዶች ለወታደሩ ክፍሎች ሊያሰምኗቸው ቢሞክሩም ለጊዜው የተቀበሉት መስለው ርሰበርሳቸው ሲገናኙ ያኑኑ ርዕስ እንስተው ማውራታቸውን አይተውም። በተለይ በመኝታቸው ላይ ጋደም ብለውም ይሁን ተቀምጠው ሲጃራ እጫሹም ሲጃራውን እያደዘ ትንባሆ ጎራሹም ትንባሆውን ጎርሰ ያለፈውን የስቃይና የስቆቃ ዘመን ከመጪው የደስታ ዘመን ጋር እያገናዘቡ ሲያሰላስሉት፤ እልፎ እልፎ መፈታታቸው የሚያጠራጥራቸው የወታደሩ ክፍሎች፤ትንባሆአቸውን ለመትፋት ከመኝታቸው ቀና ሲሉ፤የአንዱን ተማሪ ወይም መምህር ስም በመጥራት «ጎበዝ ይህችን የሲያል በታ አብረን ቀምሰናታል፤ ዕድል ለእናንተ ቀንታ ከወጣችሁና ሃገር ሰላም ሆኖ ከተመለሳችሁ በእንደዚህን ያለ ስቃይና መከራ ላይ እንደነበርን እውነቱን ከመናገር አትበዝኑ።አልሰሜ ነገም ሌላው መጥቶ ይህን ሲቃይ ከሚያይ በሃገሩ ላይ እውሬም ቢሆን እያደነ እየተሽሎከለከ ለመኖር ይረዳዋል።እንደ እኛ ግን ሙሉ ትጥቁን እንግበ እጅ ቢሰጥ ሞርከኛ ተብሎ እስር ቤት ይጨመራልና አደራችሁ ፤እናንተ ተማሪዎች ያየችሁትን ለመናገር ሆነ ለመፃፍ ወደኋላ አትሉምና አደራ ለወገን እንዲያውቀው አድረጉት። ግን ጊዜያዊ ጥቅምና ምቾት ያለፉትን የመከራ ጊዜ አዘናጊ ናቸውና እንዳትዘናጉ፤ ይህ ሁኔታ ነገም በወገን ላይ ሊደገም ስለሚችል በእኛው ላይ ተወስኖ እንዲቀር ከማድረግ እንደማትቆጠቡ እናምናለን፤» በማለት አንዳንድ ምራቃቸውን ዋጥ ያደረጉ ከወታደሩም ውስጥ ስለነበሩ ይህን መሰል የታላቅ ወንድምነታቸውን ምክር ይለግሱ ነበር።

የወታደሮቹ ለመውጣት መጠራጠር ግን ለተማሪዎቹና ለመምህራኑ አበሳጭ ጉዳይ ነበር። ይህን የተሰማው እውነቱ በመናደድ «ከወጣን አብረን እንወጣለን ከአልወጣንም ደግሞ አብረን እንቀራለን።ከለበለዚያ ግን እኛን ለማበሳጨት ካልሆነ በስተቀር ይህን እንወጣም የሚለውን ባሳነሳችሁት ነበር፤ዘውትር ራሳችሁን ከሌላው ሕብረተሰብ ዝቅ አድረጎ መመልከቱ ይበልጥ በአሁኑ ወቅት ጎልቶ ይታያል።አንዳንድ ጥቃቅን ተግባሮች ሲፈጸሙባችሁ ወታደር በመሆኔ ነው በማለት ስታማርሩ ትታያላችሁ።ይህ ዛሬ በእናንተ የታየ ሳይሆን በሃገር ቤትም የሚታይ ነበር።እንናትም በአሁኑ ጊዜ ብዙ



የተማራችሁ ይመስለኛል። ተማሪ አስተማሪ ጸሐፊ ገበሬ ሚሊሻያ ሁላችንም በአነድነት በአንድ መኝታ ቤት ይህን የመሰለ ስቃይ ውስጥ ማን ከማን ሳይልይ እየተሰቃየን ነው። ይህ ራሱ የሚያሳየው የአንድ ሕብረተሰብ አካል መሆናችንና ችግር ሲመጣ ከማነህ ማነህ ሳይለይ በማንኛችንም ጫቃ ላይ ማረፉን እስከዛሬ አብረን ስንኖር የተገነዘባችሁት መስሎኝ ነበር፤ ግን አንዳንዶቻችሁ አሁንም ያንኑ ከሃገር ቤት የነበረውን የሞያ ልዩነት እንደመሠረታዊ ልዩነት ማንሳቱ ከአካባቢው አለመማራችሁን ይገልፃል። የሞያ ልዩነት የሥራ ክፍፍል እንጂ ከዚህ ሌላ የሚሰጠው ነገር የለውም። ሞያው ካላስደሰተንና ይበልጥ ውጤታማ ካልሆነ ልንቀይረው እንችላለን። ገበሬ የነበረው ወታደር ወታደር የነበርው ገበሬ መምህሩ ገበሬ ተማሪው ወታደር መሆን ይችላል። በዕርግጥ አውጥታችሁ አትናገሩት እንጂ በአእምሮአችሁ የሚጉላላ አንድ ነገር አለ። ይህውም ትናንት ተኩሰን ስንገላቸው ቆይተን ዛሬ ከእስር ቤት እንዴት ያወጡናል የሚለው ሐሣብ ነው። በጦርነት ላይ መሰለፍም መዋጋትም የነበረ ነው። ማንኛውም የዓለም ሕዝብ ያውቀዋል። ለዚያ ምክንያቱ አመራሩ እንጂ መሣሪያ የያዘው ወታደር አለመሆኑን ማናቸውም ያለፉበት ጉዳይ ስለሆነ ያውቁታል። ኢተዮጵያም ሆነች ሰማሊያ የዓለም ሕብረተሰብ ክፍል እንደመሆናቸው መጥን ይህንን ሁለቱም ሃገሮች ይረዱታል። ስለዚህ እናንተን በተናጠል ወንጀለኛ የሚያደርጋችሁ ምንም ነገር የለም። ለጦርነቱም ምክንያቶች አልነበራችሁም። »በማለት እውነቱ የተሰማውን ይገልፃል።

ምንም እንኳን ተደጋግሞ ሁሉም በእንድነት መለቀቃቸውን ለወታደሩ ክፍሎች ቢነገራቸውም ርሰበርሳችው ሲገናኙና በጥሞና ያስረዱናል ከሚሏቸው ዘንድ በመቅረብ ችግሩን ከማንሳት እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ተቆጥበው አያውቁም። ግን እነርሱ ተለይተው ቢቀሩም እንኳን ጥቂቶች ተፈተው ከወጡ ይህንን ሁኔታ እስር ቤት ሆነው ወገን ለማስፈታት ይጥሩ የነበሩት ወገኖች በቃን ብለው እጃቸውን አጣፍተው እንደማይቀመጡ ያረጋግጡላቸዋል።

## ፳፱

ከሰኔ መጀመሪያ እስከ ሐምሌ መጨረሻ በእስር ቤቱ ትልቅ የምግብ እጥረት የሚፈጠርበት ወቅት በመሆኑ፤ እንኳንስ ሀበሻው የሰማሌው እስረኛ ሐብታሙ ሳይቀር ሽርጡን ሰብሰበ የበቆሎው እጥሚት በበርሜል ተሞልቶ ከሚቀርብበት አካባቢ ቀድም ብለው የሚሰለፉበት ወራቶች ናቸው።

እንደአለፉት ጊዜያት ወፈር ብሎ የገንፎ ወግ ያለውን የሚጠበቅበት ወራት ባለመሆኑ ሀበሻዎቹም የተቻላቸውን ለማድረግ ቀድመው ተሰልፈው ሳሉ ከእስር ቤቱ አስተዳደር ክፍል መልክት ተሳልፎ ኖሮ በእስር ቤት ሰማቸው «አማር» ተፈለጋላችሁ የሚል

መልክት ወደ«በረከው» ተሳለፈ። ምግብ መቀበላቸውን ትተው ከአንደኛው በር አልፈው ከእስር ቤቱ መዝገብ ቤት በራፍ ላይ ከማነህ ማነህ ሳይባል ተኮለኮሉ።ማናቸውም ከኢትዮጵያ መልክዐ ምድር በስደትም ይሁን በምርኮ ወደዚያች ሃገር የገቡ በሙሉ ተጠርተው ቀረቡ። ከመዝገብ ቤቱ መጠራታቸው እንጂ ለምን እንደተጠሩ አልተገለጸላቸውም።

እነርሱም በዚያን በሐምሌ ወር ሙቀት ከሲሚንቶው ግለት ወደ ላይ እየተነነ ከሚነሳው እንፋሎት ፣ በምግብ እጥረት የተጎዳውን ከአፈረተ ሥጋቸው በስተቀር በጨርቅ ያልተሸፈነውን ሰውነት ለሙቀቱ ተጋልጠው ሲቃቁ በጊዜው ለተመለከተው ልክ ያንን ስለእስር ቤቱ የሚተረከውን የ«በርቀስን ባሮች» ወደአረብ ሃገር ለመለክ በቆጠራ ላይ እነደነበሩት ይመስሉ ነበር።

በዚህን አጋጣሚ ለብዙ ጊዜ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ተይዘው ከእነርሱ ተለይተው የነበሩትን ጓደኞቻቸውን ያገኟቸዋል። ሰውነታቸው ከድቶአቸዋል፤በጣም ከስተዋል ለመናገር ትንፋሽ እያነሳቸው «ጎበዝ ደህና ናችሁ፤» እያሉ ሰማቸውን አስሞልተው ሲሄዱ በእውነቱ ዳግመኛ እንደማይገናኙ ድነው በዐይነ ሥጋ እንደማይተያዩ በቃል ባይናገሩትም የተሰፋ መቁረጥ ፀጸት የተሞላበት የሐዘን እንባቸውን ሁለቱም ወገኖች ሲያቀሩ ምን ያህል ያሣዝን ነበር።እስር ቤት ውስጥ ይነገር የነበረው ሆስፒታል ለእርዳታ ተወስደዋል ሲሆን በዕለቱ ግን እንደተረዱት ከማገገሚያው ሥፍራ መሆናቸውን ነበር። ታከመው ሊድኑ ሲችሉ ከእስር ቤቱ ላለማውጣት ብቻ ቀናት በነገ ዛሬ ሲራዘሙ ፣ ቀን የማይሰጠው በሽታ ስንቱን መንድሞቻችንን እንደዘበት ወጥተው አፈራቸውን በባዕድ ሃገር አደረጉት። የተገመተው አልቀረምና ሳይገናኙ ቀሩ።

በዕለቱም የተጠሩበት ምክንያት ሳይነገራቸው እንደው በፀሐይ ሲንቃቁ ውለው ተመልሰው ወደምኝታ ሥፍራቸው ሄዱ። ከክፍሎቻቸው ሲሄዱ ለእስረኛው ተፈተዋል ተነግሮት ኖሮ ማንኛውንም የነበሯቸውን ዕቃዎች በሽማ ተከፋፍለዋቸው ደረሱ።እስረኛ ሲለቀቅ ቀሪው እስረኛ የተፈታውን ግለሰብ ዕቃ መውሰድ የተለመደ ቢሆንም ለሀበሻው እስረኛ ግን በጣም ትልቅ ጉዳት ነበር።የሚተኙበትን ሆነ የሚለብሱትን ሽርጥ የምግብ መቀበያዎችን ለአምስትም ሆነ ለሁለት ዓመት የያዟቸውን እጥተው በባዶ እጃቸው መቅረቱን ሲያዩት ዳግም ቢጠሯቸው ላለመሄድ የወሰኑም ነበሩ።

ሆኖም ጥሪው በየቀኑ ቀጠለ። ሀበሻው ከምግብ መቀበያው ሰዓት ላይ መስናከል እንጂ በየዕለቱ ምን ነገር እንደሚሰራ ለእነርሱ ግልጽ አልነበረም። የመዝገብ ቤቱም ሠራተኞች እስረኞች ስለሆኑ የያንዳንዱን እስረኛ ዶሴ በሥርዓት ካለማስቀመጣቸው በቀን ውስጥ ከአምስትና ሦስት ግለሰቦች ጉዳይ በላይ አይፈጽሙም። በዚያን ወቅት ብዙ ሀበሻ ይታመማል ራሱን እያዘረው ይወድቃል። ያም የግለሰቡ



እንጂ የማንም ችግር አልነበረም።

በመጨረሻ የመዝገብ ቤቱ የስም የማመሳከሩ ሥራ አብቅቶ እያንዳንዱን እስረኛ በመኪና እየተጫና ወደሃገሪቱ የውስጥ ጸጥታ ጥበቃ እየተወሰደ በመጀመሪያ ወደዚያች ሃገር ከአምስት ዓመት በፊት አቅርበውለት የነበሩትን ጥያቄዎች መልሰው ሲጠይቋቸው፤ አንደኛውን እስረኛ ስለሌላው የሚያውቀው ነገር ካለ በማለት ከፋፍለዋቸው መጠየቃቸውም አለቀረም። እውነቱም ልክ በመጀመሪያ ሲያዝ የተጠየቀውን ዓይነት ጥያቄ ከማቅረባቸው ሌላ በባዶ ክፍል መብራትና መስኮት በሌለው ውስጥ አስቀምጠውት የተለያዩ ሰዎች እንዲመለከቱት በማድረግ ምርመራቸውን አክነውነውበት ነበር። አንዳንዶቹም ላይ በመለሳለስ ከእስር ቤቱ ቢፈቱ ከየትኛዎቹ የዓለም ሃገሮች ለመሄድ እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ያልፏቸዋል።

በዚህ አይነት በመቶ የሚቆጠሩ እስረኞችን በየዕለቱ ከሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ከእስር ቤቱ ከአለው መሥሪያ ቤት እያጓጓዙ መጠየቁ እድከሚና ጊዜ ወሳጅ መሆኑን በመገመት ይሁን አይታወቅም ምርመራቸውን በዚያው በእስር ቤቱ የአስተዳደር ጽሕፈት እንዲደረግ ተወስኖ ኖሮ ያልተጠየቁት ከፍሎች እየተጠሩ ስለአመጣጣቸው ይጠይቋቸዋ። አብዛኛውን ጊዜ ባልሥልጣኖቹ ቢሮ ለሥራ ስለማይገቡ ነገሩ ይጓተታል። ከሦስቱ እስር ቤቶች ያሉትን ጠይቆ ለመጨረስ ቢያስ ወር ወሰደባቸው።ከዚያንም እስረኛው ውጤቱን በናፍቆት ይጠባበቅ ጀመር።

## ፳፫

ዕለቱ ዐርብ ነሐሴ ፳ ፲፱፻፹፫ ዓምተ ምህረት ነበር። ኢትዮጵያን እስረኞችም የምትሰጣቸውን ሰላሳ ግራም ሥጋና የበቆሎ እጥሚታቸውን በጓድ በጓድ ተከፍለው በመመገብ ላይ ሳሉ «አማሮች» ይፈለጋሉ የሚል ጥሪ ወደእከባቢው መጣ። በዕለቱ የሃገሪቱ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው የሚውሉበት ቀን ስለሆነ ጥሪውን ብዙዎቹ አምነው አልተቀበሉትም።

እሸቱ የኢትዮጵያ ኢንባሲ ሹፌር የነበረ እውነቱና ሌሎች ጓደኞቹ ቁጭ ብለው ከሚመገቡበት ሄደ «ልጆቼ የዛሬውስ ቁርጥ ሳይሆን አይቀርምና በሩን ሳይዘጉባችሁ ፈጥናችሁ ሂዱ» በማለት እንዲሄዱ ሲነግራቸው፤እውነቱም በመበሳጨት «እንተንስ እተወጣም ያለው ማነው?» በማለት ሲጠይቀው፤ እርሱም «የሚሏችሁን ለመስማት አብሬአችሁ ልሂድ እንጂ የእኔ እንኳን አይሆኑም» ሲላቸው ተሰምቷቸው የነበረው ደስታ ወደሐዘን ተለወጠ።

በእውነቱ የእሸቱ ታስሮ መቅረት የሚያሳዝነው አብረውት የቆዩትንና የእርሱን የወገን ፍቅርና ችሮታውን የተካፈሉት ብቻ

ሳይሆኑ ለአንድ ቀን እድሜ ከእስር ቤቱ ውስጥ ለአዩት ጭምር ነበር።

እሸቱ የኢትዮጵያ ኢንባሲ ሹፌር ሲሆን በሁለቱ ሃገሮች መከከል ሰኔ ፷፱ ጦርነት ሲጀመር፤ የኢንባሲው ጽሕፈት ቤት ሲዘጋ እሸቱና ሌሎች ሁለት ኢትዮጵያውያን የኢንባሲው ዘበኞች ተይዘው በተለያዩ እስር ቤቶች ይጪመራሉ። ለእስራቱ ምክንያት ሲቀርብ የኢተዮጵያ መንግሥት የሰማሌውን ኢንባሲ ሹፌር ስለአሰረ ነው ተበለ። ሁለቱ ዘበኞች ግን ሃገራቸውን የሚመለከት ሠነድ አቃጥለዋል የሚል ነበር።

እሸቱ ሰማሊያን ባይጠላትም ስለሃገሩ ያለውን ፍቅር ለወገኖቹ ያደርግ በነበረው ተግባሩ ገልጾታል።በእስር ቤቱ የነበሩት ሰማሌዎች ያንን ሥራውን በጣም ይወዱለታል።እውነተኛ ሀበሻ እኛ የምናውቃቸው እሸቱን የሚመስሰሉትን ነው፤ ዛሬ ደርግ እነዚህን ከየት አመጣቸው በማለት አንዳንዴ ሀበሻው እስረኛ ሲያጠፉ በዚያን አይነት ይወቅሱታል።

እሸቱ በእስር ቤቱ ታስረው የነበሩትን ወገኖቹን ለመርዳት ያላደረገው ጥረት አነበረውም።በተለይ በበሽታና በመታረዝ በመራብ ይሰቃዩ የነበሩትን ሕይወት ለማዳን ባለው አቅሙ ጥረትን አድርጓል።የሰማሌ እስረኞች ያንን ጥረቱን በመገንዘብ ከሚመጠሉቸው ምግብ ከፍለው «እሸቱ ይህን ምግብ ለነዚያ ምስኪን ወገኖችህ ሰጣቸው» የሚሉትን ማንኛውንም ነገር ወስደ በየእሉበት ክፍሎች ሲያድላቸው «የዐባይን ልጅ ወኃ ጠማው» የሚለውን ተረት ተርቶ የሽምግልና ዐይኖቹ እንባን ሲያቀሩ ለተመለከተው ኧረ የጎበዝ ያለህ መላ ፍጠሩ ያሰኛል። በተለይ ያቺን ነጭ ቁምጣውን ታጥቆ ከወጣቶቹ መከከል ሆኖ በዚያች አውዱማ በምታክል ሜዳ ላይ ሲዘዋወሩ፤አባት ልጆቹን ይህን አድርጉ ያን አታድርጉ የከሌ ልጆች በእንደንዚህን ያለ ልክስክስ ሥፍራ ይውላሉ አታሰኙኝ እያለ ምክር የሚለግሳቸው ይመስለል።

መችያ ብቻ «ልጆቼ የሃገራችሁ እንጀራ ናፍቆአችሁ ይሆናል፤» በማለት እንጀራውን አስጋግሩ ያ በቅመም የጣፈጠው ወጥ ተደርጎበት በሃገር መሰብ ተሰርቶ ከእስር ቤቱ ሲገባ ያንን ምግብ ለመቅመስ የሚራሯጡት ኢትዮጵያኑ ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያን ምድር የረገጡ ሰማሌዎች ጭምር ነበሩ።የቅመሙ ሽታ ገቢውን ስለሚያውደው ማንኛው እስረኛ«ወሪያ» «አንተ የእሸቱ እንጀራ መጣ» በማለት ለመብላት ከየአቅጣጫው ሩጫ ይሆናል። አንዳንድ ሰማሌዎች የእሸቱን ሁኔታ ያጤኑ የሃገራቸው መሪዎች በሁለቱ ሃገሩች መከከል ጦርነቶች በተነሱ ቁጥር ሀበሻውን ብቻ ሳይሆን ጅጅጋን የረገጠውን ሰማሌ ሰለይ ብለው ማሰራቸው ትክክል እንደሆነ ይናገራሉ። ሄደው የማያቁት «ያች ሃገር ምን ነገር አላት ? ሕዝቧ እንደዚህን የሚዋደዱት በወጭ ሲሆን ነው፤ ወይስ በሃገራቸውም ውስጥ ጭምር» በማለት ጥያቄ ያቀርባሉ። አንደንደቹ እንደቀልድ «እሸቱ ሰማሊያ ውስጥ አርባ ዓመት ኖረሃል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖርከው አስራ አራት ዓመት ብቻ ነው፤ አንተ ሰማሌ እንጂ መንዜ አይደለህም፤ የፈለከውን ዘር ምረጥና በዚያን እንጥራህ በማለት ያሾፉሉ።

በጠቅላላው ሀበሻው እስረኛ እሸቱን የሚመለከተው እንደ ጓደኛውም እንደአበትም ስለሆነ ሲጠይቁት የፈለጉትን ማንኛውንም ነገር ከመጠየቅ ወደኋላ አይሉም።

አንድ ቀን በተለመደው ሜዳ ላይ ሲዘዋወሩ እንደኛው መምህር እሸቱን በባንክ ያለውን ገንዘብ ሲጠይቀው፤እርሱም ፈገግ ብሎ ያንን ለማሃለ እንኳን ጥቁር የሌለውን ዘማ ፀጉሩን እያሸሸ «በመጪረሻ ልያዝ አካባቢ የቤት ከራዬን ከፍዬ በባንክ ደብተሬ ላይ የነበረኝ አስር የሰማሌ ሽንልግ ብቻ ነበር።እኔ ሰማሊያን የምወደው ሰው ያለውን ተከፍሎ የሚበላበት ሃገር ነው። ለዛሬና ለነገ የሚበቃ ምግብም ሆነ ገንዘብ ካለቸው የተቸገረ ካዩ ለመስጠት ወደኋላ አይሉም። የሰማሌ ኑሮ ይህን ይመስላል።እናንተም ስትለቀቁ ታዩታላችሁ።

አንድ ሰው ሃገሩን ትቶ ከወጣ ንብረት ለማቋቋም በጣም ይከብዳል።በዘመድና በወገን መደጎም የለም። ራስህ ጥረህ ውጣው ነው። የመጀመሪያዋ ባለቤቴም የዚህን ሃገር ኑሮውን ስላልወደደችው ሁለት ልጆቼን ይዛ ከሃገር ቤት ተመለሰች። እንደሃገር ጭሩ ሥፍራ የለምና መቼም የደግ ልጅ ደግ ነው ዮዲት እምሩ በዚያው በውጭ ጉዳይ ሚንስተር መሥሪያ ቤት ሥራ አግኝታለት እየሰራች ልጆቿን ታሳድጋለች። እኔም በእስር ቤት እማቅቃለሁ። ግን በሃገሬ ስም ስለሆነ የታሰርኩት እኔ ብሞትም ልጆቼ በሃገራቸው ላይ ናቸውና ያወሩታል። እኔ ዕድለኛ ነኝ እናንተንም ቢሆን አግኝቼ እልፎ እልፎ ስለሃገር እናወራለን ሁለቱ ጓደኞቼ ማንንም የሃገራቸው ሰው ከማያዩበት ታሰረው የለም? ቀምታ ያለውም ዐይኑን ከልሎት ያው ወደመታወሩ ነው። እንደኛውንም ከገጠር ከተማ እንደ እኛ እንኳን ወገን አይቶ ከማይጽናናበት ታስሮአል። የሀበሽ ዘር እንደጪው ዘር ተበትኖ ይቀር ይሆን?»

እንግዲህን ከዚህ አንፃር ሲገመገም እስከመቼ በዚያች ሃገር የተፈጠሩ ልጆቿ በየጥሻው ተሸግጠው ይቀራሉ? በውጭ ያለው ሕዝብ ወደሃገር የሚመለስበት ሁኔታ በሃገር ውስጥ ባለመፈጠሩ እንደውም ከሃገሪቱ እየከበለለ የሚወጣው ቁጥር ዕለት በዕለት እየጪመረ መሄዱ ይታያል። በየአቅጣጫው በገዛ ሃገራችን ላይ እየሰራን መኖር አልቻልንም የሚሉ ሮሮዎች ይቀርባሉ። በሥልጣንም ላይ ያሉት ሕዝቡ ራሱን እንዲያስተዳድር መጠይቆችን ሲያቀርብ የመሰሪያ ተጽኖቸውን ከማድረግ አልፈው በግዱታው በሃገር ቤት እንዲቆይ አዋጅ ያወጡበታል። ያ ደግሞ ጠቅላላ ደር እስከ ዳር ሃገሪቱን እስር ቤት ማድረጋቸው እንደሆነ የታያቸው አይመስልም።

## ፷፬

ዐርብ ቀን የሃገሪቱ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው የሚውሉበት ሲሆን የእስር ቤቱን ባለሥልጣኖች ወደእስር ቤቱ ያስመጣው ጉዳይ ከባድ ይሆናልን በመገመት በእስር ቤቱ የሚገኙት ሀበሾች በሙሉ ወደአስተዳደሩ ጽሕፈት ቤት በራፍ ላይ ሄደው ተሰልፈው፤አንድ በአንድ እየተጠሩ ጠረጴዛ ዙሪያ ለተቀመጠው ኮሚቴ ቃላቸውን እየሰጡ እንዲያልፉ ሆነ። አንዳንዶቹም በስደተኛ ስም ለመውጣት ሲችሉ እኛ ሙርከኛ እንጂ ስደተኛ አይደለንም በማለት ለኮሚቴው ቃላቸውን ሰጡ።

ለሁሉም ከሰዓት በኋላ በአስር ሰዓት የተጀመረው ጥያቄ ከምሽቱ አራት ሰዓት አብቅቶ በሊቀመንበርነት ሰብሰባውን ይመራ የነበረው ሻለቃ ጋርዱል ሁሉንም ሰብስቦ «ነገ ለእንናተ ወንድሞቼ ያዘጋጀሁት ትልቅ ስጦታ ስላለኝ ልብሳችሁን አጽድታችሁ ጺማችሁን ተላጭታችሁ ፀጉራችሁነ ተስተካክላችሁ ጠብቁኝ፤በዚህች ሌሊት ማንኛውም መታጠቢያ ቤት ለእንናተ ቅድሚያ እንዲኖረው ለዘቦች ትዕዛዜን እሰጣለሁ፤» እንዳለ ቀና ብሎ ሲመለከት እሸቱን ያየዋል። ወደእርሱ ጠጋ ብሎ «እሸቱ የአንተን ጉዳይ ይህ የምታየው ኮሚቴ የሚወስነው ሳይሆን በመንግሥት ደረጃ የሚታይ ስለሆነ ጊዜህን ጠብቅ።» የቀራችሁት ግን ነገ እንገናኝ ብሏቸው ሲሄድ እነሱም እንደተነገራቸው ለማድረግ በየእቃጣጫው ተበታተኑ።

ዐርብ ነሐሴ ሁለት ፸፫ ዓመተ ምህረት የሃገሬው እስረኛ የፌሽታ ሌሊት መሆኗ ቀርቶ የአሀሻው ምሽት ሆነች። ሌሊቱ እንዲትሰ ነግቶ በተለይ በሃገሬ እስረኛ ውስጥ ተቀላቅለው የነበሩትን ከቢዋቸው በሃገራቸው ውስጥ በእስራት ያሳለፉትን ዘመን ባይረሱትም በሕዝቡ ላይ ቂም ይዘው የሰማሊያ ሕዝብ እንደፈጸመባቸው አድርገው እንዳይመለከቱት ቃል ያስገቧቸዋል። «የሁለቱ ሃገሮች ግጭት የወንድማማች ግጭት በመሆኑ ሁለቱም ሃገሮች እውነተኛ የሕዝብ ፍቅር ያላቸው መሪዎች በሚያገኙበት ወቅት ችግሩ የሚፈታ ነው። በአሁኑ ጊዜ ያለው አይነት ጥላቻ ዘለዓለም አብሮን እንደሚኖር አድርገን መውሰድ የለብንም። እንዲሁም እየተጋጨን ከእኛ ከሁለቱ ሃገሮች በላይ የሚዋደድ እንደሌለ እናውቀዋለን። ሆኖም ይበልጥ እንዳንቀራረብ የውጭ ኃይሎች በመካከላችን እየገቡ መሣሪያ እየስታጠቁን ያዋጉናል። ለእነሱም ንግድ ለእኛ ለሁለቱ ሃገሮች ግን መራራቅ፣ መናከስ፣ በመሐሉ ሕዝባችን በረሃብ ማለቅን ነው፤ ያገኘነው ትርፍ። እዚህ ላይ የሚደረገውን አሻጥር በሚገባ የሚያጤኑ አስተዋይ መሪዎች ያስፈልጉናል የምንለው። መጋደያ መሣሪያ ለሚሰጧቸው ክፍሎች አይደለም ለልማት የሚረዱን ነገሮች በስተቀር እንፈልግም የሚሉ መሪዎች የሁለቱን ጎረቤታማ ሃገሮች ማቀራረብ ስለሚችሉ እንናተም በዚያን እንፃር እንድታዩት እንሻለን» በማለት የተሰማቸውን የሃገሬው እስረኞችም እስተያየታቸውን ሲሰጡ ሀበሾቹም የሚታያቸውን ሐሣብ በማከል ሌቱን ሳይተኙ ቁጭ ብለው



እነጉ።በነጋታውም በሙርከኛ ስም ተነጥለው የቀሩትን ጓደኞቻቸውን ለመሰናበት ከጠዋቱ ማልደው በየክፍሉ እየዞሩ «ጎበዝ ደህና ከረሙ» ለማለት በየክፍሎቹ ሲዞሩ አረፈዱ። በቀኑም ቀደም ሲል በመታሰራቸው ሆነ በግል በደረሰባቸው ስቃይ ምንም እንዳልተሰማቸው ሆነው ይኖሩ የነበሩት ተለይተው የቀሩት ሙርከኞች የመጨረሻው የመለያየት ቀን ሲመጣ ስሜታቸውን ሲያምቁት አልቻሉም።

ለምሳሌ አወል በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል በተደረገው ጦርነት የተካፈለ ሲሆን እሱም በጦርነቱ ላይ በቦንብ ከቀኝ እግሩ ላይ ቆስሎ በምርኮኛ ስም ተይዞ ከሆስፒታል ከተኛ በኋላ፤ ቁስሉ ጠፈፍ ማለቱ ተይቶ ከ«ሴንተራሊ» እስር ቤት ተጨምሮ፤ ከዚያንም ጨርሶ ያልዳነው ቁስሉ በየጊዜው እያመረቀዘ ቢያስቃየውም፤ «ለሃገሬ ስዋጋ ነው» ከማለት ሌላ የሚያሰማው ሮሮ አልነበረውም። በዚያኑም ላይ አንዳንድ በጎ አድራጊዎች በሚሰጡት ገንዘብ ከውጭ ምላጭ፤ ሲጃራውን፤ ዳቦውን በማስገዛት ሲቸርቸሩ፤ባተረፈው ገንዘብ ራሱን ረድቶ ለቀሩትም ወገኖቹ ተርፎ ነበር።እርሱም በአንድ እጁ ቁሱሉን ከዝንብ በጭራ እየተከላከለ በሌላው ገበያተኞቹን እያስተናገደ ሳለ፤ ቁሱሉ ሰውነቱን ከቀን ወደ ቀን እየጎዳው መምጣቱን የተመለከቱ ወገኖቹ ከመኝታው ላይ ሆኖ ራሱን እንዲያስታምም ቢነግሩትም፤ ሳለመቀበል «መች ነው ጉራጌ ከገበያ ተለይቶ የሚያውቀው ከአልሞተ በስተቀር» በማለት ይቀልድ ይጫወት የነበረው፤ አወል በዕለቱ ምላጭ ሊገዙትና ሊሰናበቱት የሄዱትን የእናንተን ገንዘብ አልፈልግም ብሎ በነፃ ሲያደላቸው፤ ያ አሞተ ከስታራና ጠንካራ የነበረው አወል ተክዞ «ወገኖቼ ሞቼ ሳታዩኝ መሄዳችሁ ነው? ምነው ያኔ በጦር ሜዳ ተመትቼ እንደወደኩ ጓደኛዬን ጨርሰኝ እንዳልኩት ጨርሶኝ ኖሮ? ይህን ሁሉ ሰቃይ አላይም ነበር። እስከ ዛሬ ከመኝታዬም ሆነ ከውጭ እናንተን ወገኖቼን በአካባቢዬ በማየቴ መታሰሬ ሳይሰማኝ ቆይቶ ይህው ዛሬ «ሀ» ብሎ ሊጀምር ነው።»በዕለቱ የተለቀቁት ሀበሾች ከእስር ቤቱ ግቢ ወደ ገሳጣው መስክ ለመውጣት በስተደቡብ በሚገኘው ጠባብ በር እንዲወጡ ስለተነገራቸው፤ የእስር ቤቱን ክሊኒክና በ፸ ዓመተ ምህረት መፈንቀለ መንግሥት ሙከራ ያደረጉትን መኰንኖች የታሰሩበትን ግቢ መግቢያና መውጫ በር በስተቀኝ በኩል በመተው ወደ መስኩ ሲወጡ፤ የሀበሾችን መፈታት የሰሙት መኰንኖቹ ከመውጫው በር ተጠግተው በአማርኛ መልካም ዕድል ይግጠማችሁ እያሉ እጃቸውን ሲያውለበልቡ፤ በተለይ የምግብ እድማ በማድረጋቸው ለቅጣት ከነእርሱ ዘንድ ታስረው የነበሩትን በስማቸው በመጥራት (Good Luck) ማለታቸውን እንጂ ዞር ብሎ የተመለከታቸው አልነበረም። ቃል ቢወጣን ተመልሰን እንታሰራለንን በመፍራት ወደኋላ ሳይገላመጡ ወደፊታቸው አሽቆልቁለው እየተመለከቱ በአዛዡ ቢሮ አድርገው ወደመስኩ ወጡ።

ከእስር ቤቱ በራፍ ከሚገኘው መስክ ተቆሞ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ሲቃኝ የሃገሪቱ ዋና ከተማ ሐመር ከቀልጣጣ ሜዳ

ላይ ተዘርግታ ትታያለች፤ ከቆሙበት በስተደቡብ ሃያ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ሲሆን አሽቆልቁሎ ለተመለከተው የሰማይ ከፋይ ሲመስል፤ ሀበሾቹ ያንን በአሸገር እየተመለከቱ ትዝታ ልባቸውን በሕንድ ውቅያኖስ ላይ እየቀዘፈው ፍጹም እዚህ ነን ብለው መናገር ከማይችሉበት ሃገር ይዘአቸው ጭልጥ ሲል፤ «ወይ! ሃገሬ እንደዘበት ወጥቼ ቀረሁኝ የሚሉ ነበሩ።» ብዙዎቹ ሳይታወቃቸው ፤

«አልታይህ አለኝ የሃገሬ ሰማይ፤
ለካንስ እንደሀ ርቄ ሂጃለሁኝ ወይ»

የሚለውን የፀጋዬ መርጊያን ዘፈን በፉጭት ያንጎራጉሩ ነበር።

ከእስር ቤቱ ደጃፍ ርቀው ሳይሄዱ መሣሪያ በታጠቁ ፤ ወታደሮች ተከበው ከሌሎች እስር ቤቶች ከፖሊስ ጣቢያዎች፤ ከወታደር ማሠልጠኛ፤ ከሆስፒታል፤ ከሴቶች እስር ቤት፤ በተለይ በአጥር ከሚለያቸው «ብዮሙንደ» የነበሩትን ለማየት መቻከላቸው ከእስር ቤት ለመውጣት ያላቸውን ያህል ነበር። ለቀጠሮ ከ«ብዮሙደ» ታስረው የነበሩት የሰማሌ እስረኞች ተፈርደባቸው ከ«ሴንተራሌ» ሲዘወሩ የጥቂቶቹን ሀበሾች ስም በመጥቀስ ይናገሩ ስለነበር እነሱን ለማየት ጉጉት ሲኖራቸው በተለይ ከሴቶች እስር ቤት ከነሴት ልጃቸው ታስረው የነበሩትን በእስር ቤት ሰማቸው እናት መጠሪያቸው ሔዋንን ለማየት የነበረው ጥድፊያ እጅግ ከፍተኛ, ነበር። ሔዋን በየጊዜው ምግብ በማቆም ለተጎዱትና ለታረዙት በ«ሴንተንሌ» ለነበሩት የሀበሾች እስረኞች ባለውለታ ነበሩ። እሳቸውም በእስር ቤቱ ክራይ ሠርተው ልጃቸውንና ራሳቸውን ረድተው የቀሩትን ለመርዳት ያደረጉትን ጥረት በቅርብ ይከታተሉት የነበሩት እግዚአብሔር ይስጥልኝ ለማለት ተፈተው አብረው ለመቆየት ምኞታቸው ስለነበር ሰዓታት ወራት ሆኑባቸው ነበር።

ይህ በዚህ እንዳለ ተከበው ከሚጠባበቁት ውስጥ የነበሩት የወታደሩ ክፍሎች ወደ ሲቪሉ በመጠጋት «ጉዞው የወታደር ጉዞ ነው፤የወታደር ጉዞ የሚጀምረው ከቀኑ መሸትሸት ማለቱ ታይቶ ነው።» «ወዴት ነው ጉዞው?» መልስ የሌለው ጥያቄ። አንዳንዶቹ «ከወሰን ላይ ወስደው ሊጥሉን ነው» ሲሉ «እድርጎት ነው ከዚህ በበሽታ እየማቀቅን ከመሞት ከወንዛችን ብንሞት ይሸለናል» በማለት ከምሬታቸው የተነሳ የተሰማቸውን እየገለጹ ሳሉ ከየሥፍራው ታስረው የነበሩት አበሾች እየተያዙ መጡ።

ምንም እንኳን ተይዘው የመጡት ወገኖች በመሆናቸው ቢደሰቱም በጉጉት ይጠብቋቸው የነበሩት ከመጡት ውስጥ ስለእል ነበሩ አዲስ የመጡትን ስለቀሩት ሲጠይቋቸው ድንጋጤውና ፍረሃቱ ገና ስላአለቀቃቸው ምንም አናውቅም እንጂ ሌላ መልስ ሊሰጡ አልፈለጉም።ወዲያውኑ ከፖሊስ ጣቢያም፣ ከከተማም፣ ከሆስፒተልም የነበሩትን እምጥተዋቸው፤ በመስኩ ላይ እንዲቀመጡ ተደርጎ ባለሥጣኖቹ ከሆስፒታል በመኪና ተደግፈው የመጡትን



ሲመለከቷቸው፤ በፍጹም ችለው የሚጓዙ የሚድንና የሚያሰራራ ሰውነት እንደሌላቸው ተመልክተው ወደመጡበት እንዲመለሱ ተወሰነ። ከሆስፒታል ከመጡት ውስጥ በመጀመሪያ ከእስር ቤት ሲገባ ጠርብ የሚያክለውና ሃገሩ በነበረበት ጊዜ ጎንደር ክፍለ ሃገር በሽፍትነት ይታወቅና ይፈራ እንደነበር አብረውት የነበሩት ከሃገር ቤት ጀምረው የሚያውቁት የሚናገሩለት ኩሩውና ነፍጠኛው ጉራራ ከስቶ በጣረሞቱ ሲወዘወዝ ያዩት ሚሊሻዎች እርሱነቱን አመነው ሊቀበሉት አልቻሉም። የአከዳሚው ምሩቅ አዳሙማ ከሳቱ ብቻ ሳይሆን አእምሮውም ተነክቷል፤ የሩቅ ጊዜ የእስር ቤት ጓደኛው እውነቱ ሲያናግረው እነደረሳውና እንደማያውቀው ነበር የሆነበት።

ከሆስፒታል ተከበው የመጡት እንደማይችሉ ባለሥልጣኖቹ ወስነው፤ እስረኛው የነሔዋን መቅረት እያበሳጫቸው የነጉራራን ሁኔታ የመኖር ተስፋቸውን እያስቆረጣቸው፤ከሆስፒታል መጥተው የተኮለኮሉትን እየቀረቡ «ጎበዝ ደህና ሁኑ» በማለት እየተሰናበቷቸው ተዘጋጅተውላቸው ከነበሩት ሁለት ማክ የፖሊስ መኪና ላይ ተሳፍረው፤ አጃቢዎቹም መሣሪያቸውን ጥይት አጉርሰው ሣንጃቸውን በአፈሙዙ ወድረው ለተሳፋሪዎቹ ከመሐል እንጂ ከዳር መቀመጥ እንደሌለባቸው በማስጠንቀቂያ መልክ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ ባልተሸፈኑት መኪናዎች የነሐሴ ዝናብ የማያደርሰው የምስራቅ አፍሪካ ሃገር የለምና እነሱም በዚያች በረሃ ሃገር በሚጥለው ዝናብ እየረሰረሱ ተፈታችኋል በሚል ስም በዚያች ነሐሴ ሦስት ፸፫ ዓመተ ምህረት ወደ ማያቁት ሥፍራ ጉዞ ያደርጋሉ።

፷፭

በየጊዜው ከዚህን ማዕከላዊ እስር ቤት ለሥራ ወደ ነዑስ እስር ቤቶች በወታደር እየታጀቡ መወሰድ የተለመደ ስለነበር፤ በመንገድ ላይ የሚያልፏቸው በሙሉ እጃቸውን እያውለበለቡ «እግዚአብሔር ያውጣችሁ ነው» የሚሏችሁ በማለት ቋንቋውን የሚናገሩት ክፍሎች ሲያስተረጉሙ፤ አብዛኞቹ እስረኞች ለሚበለው ጆሮ አልሰጡትም። በወቅቱ በሐሣብ ተውጠው፤ ከወዴት እንደሚወስዷቸው ነበር፤ የሚያሰላስሉት። ለሦስት ሰዓት ከተጓዙ በኋላ ከአውላላ ሜዳ ላይ አውርደዋቸው ወገባቸውን እንዲፈትሹ ሲነገራቸው፤ ወታደሩ በየአቅጣጫው ተሰራጭቶ መሣሪያውን አነጣጥሮ ወደ እነርሱ ደግኖ መያዙን ሲያዩት፤ወደ እስር ቤት መወሰዳቸው ቀርጥ ሆነ። ለሁሉም ወገብ ፍተሻው አብቅቶ ከመኪናዎቹ ተሳፍረው ጉዞ ሆነ።

በህልም ይሁን አይታወቅም ሶማሊያ ውስጥ ከአንድ በታ ተነስቶ ወደሌላ አከባቢ ጉዞ ሲደረግ፤ ስንቅ መያዝ ወይም ከተነሱበት ሥፍራ ምግብ ተመግበ መነሳት በብዙ ጉዞዎች እንደታየው የተለመደ አይደለም። ለዚያም ዋናው ምክንያትከአንድ ሥፍራ

ተነስተው ወደሌላ ሲጓዙ በየመንደሩ ጎራ በማለት ስለሚመገቡ ስንቅ ቋጥሮ መጓዝን ወይም ተመገበ መነሳት ባህላቸው ስላልሆን ሃገራቸው ውስጥ ለገቡትና በየጊዜው ከቦታ ቦታ ለሚያዘዋውሯቸው ችግር ሳይፈጥር አልቀረም። ያም ሆነና ከእስር ቤቱ እራት ያልተመገቡ በጠዋቱም ቁርሳቸውን ያልተቀበሉት ሀበሾች በጉዞው ላይ ረሃብ ቢሰማቸውም፤ የሀበሻ ወኔ አለና ማን ራበኝ ብሎ ራሱን ያጋልጣል ያው የተኳረፈ መስሎ ይጓዛታል እንጂ። ለማንኛውም ጀምበሯ ዘቅዘቅ ስትል ኢልጃሊ ከሚባለው ከወታደር ማሠልጠኛው ሰፈር ደረሱ።

ኢልጃሊ ልክ እንደ ኢትዮጵያው ዓለም ማያ ኮለጅ የእርሻ ሥራ ጠበብቶችን ለማሠልጠኛ የተቋቋመ ተቋም ሲሆን ከአብዮታቸው ፲፪ ዓመተ ምህረት በኋላ ግን የወታደር ማሠልጠኛ የተደረገ ሥፍራ ነው።

አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ከማሠልጠኛው ግቢያ ሲደርሱ በሥፍራው የነበሩት ወታደሮች ሀበሾች እንደሚመጡ ቀድሞ ተነግሮአቸው ኖሮ ዙሪያውን ተሰልፈው ጠበቋቸው። ስደተኖቹዋ የያዙትን ዕቃ እያስፈተሹ ሰባት ክፍሎች ወደአለው ትልቅ ቤት ገቡ። አራቱ ክፍሎች ለጤነኞቹ አንድ ለጥፉተኛ መቅጫ አንደኛው ለሕመምተኛ ሲመደቡ የቀረው ለወታደሮች ልብስ ንጽህና መስጫና መማሪያ ክፍል ሆኖ ተመደበ። ከእስረኛው ውስጥ የነበረችው እህት አንዷት የሴት ዘበኛ እንድትጠብቃት ተደርጎ ከወንዶቹ ክፍሎች በግምት አስራ አምስት ሜትር ርቀት ላይ ተለይቶ ከተሰራ ቤት ተወሰደች።

ሁሉም የያዙትን ዕቃ ካስቀመጡና ክፍላቸውን ካወቁ በኋላ ከክፍሎቹ ፊት ለፊት ካለው መስክ ላይ እንዲሰበሰቡ ተነገሮ፤ የማሠልጠኛው አዛዥ ሽለቃ የሚያጽናና ንግግሩ ከዚያንም ቀን ጀምሮ እስረኞች እንዳይደሉ ጠቁሞ፤በአካባቢው የነበሩትም ወታደሮች የእነሱን ደህንነት ለመጠበቅ እንጂ ሌላ ተልዕኮ እንደሌላቸው ሲገልጽ ፤ እነሱም ወታደር በአካባቢያቸው እስከአለና ከተማ ወጥተው እስከአልተዝናኑ ድረስ ያው እስረኞች እንደሆኑ ራሳቸውን ቢያሰምኑም ከሴንተራሌ መቶ በመቶ የተሻለ መሆኑ አጠያያቂ አልነበረም።

ከሻለቃው ንግግር በኋላ በቀጥታ ወደትልቁ የማሠልጠኛው መሰብሰቢያ አደራሽ ሄደው እራታቸውን እንዲመገቡ ተነገሯቸው፤በዕለቱም ለንግድነታቸው፤በሃገሪቱ ውስጥ ከዚያን በፊት አይተው የማያውቁት በጥሩ ሁኔታ የተቀቀለ ሥጋና ሩዝ አትክልት በየአይነቱ ተሰርቶ ቀርቦላቸው፤ ምግባቸውን እየተመገቡ አዳራሹን በአይኖቻቸው ሲቃኙ ግርግዳው በልዩ ልዩ መፈክሮች ተሸጎርጉሯል። መፈክሮቹ ሃገር ቤት በ፸ ዓመተ ምህረት ከነበሩት መፈክሮች የሚለዩት «ቀይ ሽብር ይፋፋም»ሲሆን ያ በሶማሊያ ውስጥ አልተፈከረም። የሰሜን ኮሪያው መሪ ከኢልም ሱንግ(Kim II Sung)



በተጠቀሱት ንግግሮች ሲያሸበርቅ ያ ደግሞ በኢትዮጵያችን በወቅቱ አልነበረ። የከኢልም ሱንግም መጽሐፍቶች በወቅቱ በአካባቢው ከመብዛታቸው የተነሳ ውለው አድረው ሚሊሻው ገፃቸውን እየተገነጠለ ትንባሆ ሲጠቀልባቸው የሶማሊያ ወታደሮችም ከምግብ በኋላ እጃቸውን ሲጠርጉበቸው ይታያሉ

የመፈክሮቹን ብዛት ያጤነው እውነቱ አጠገቡ ተቀምጦ ለነበረው ሚሊሻ «ይህ ሁሉ መፈክር ከዚች ሃገር በግመል ተጭኖ ወደሃገር ቤት ሲገባ እናንተ ሚሊሻዎች ምን ትሠሩ ነበር፤» ብሎ ሲጠይቀው፤ ሚሊሻውም መልሶ «ወደ ማን ልከክ ያ የእናንተ ሥራ ነው ብሎ በቀልድ ከመለሰለት በኋላ፤ «እንደምታውቀው በሃገራችን ዘመን ሲለወጥ በቅዱስ ዮሐንስ ወንድ የሆነ ሁሉ ከአባት እስከ ዛሬ የተወለደ ሕፃን ችቦ ተበጅቶለት፤አባት ረጅሙን ችቦ ይዞ በግንባር ቀደምትነት በሰለፍ በእሣት እያያዘ ሦስቱን ጉልቻ እያስነካ «የጉመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ» በማለት የተቀጣጠለውን ችቦ እያበሩ ወደመስኩ መወጣቱ አሮጌውና ረሃብተኛው ዘመን አለፈ የጥጋብና የደስታ ዘመን ተተከ ለማለት የሚደረግ ባህላዊ ወግ ነው። አሁንም የሶማሌዎቹንና የእኛን ሃገር ሁኔታ ብታገናዝበው ሶማሌዎች «የጉመኑን ምንቸት ውጣ የገንፎው ምንቸት ግባ» ሲሉ እኛ ደግሞ «የገንፎው ምንቸት ውጣ የጉመኑ ምንቸት ግባ» በማለታችን ያው እንዳየህው ሆነ ምን እነግርሃለሁ? ለዚህን ነው እነሱ ከሌላ አምጥተውት የነበረውን የመፈከር ጽዋ ከእኛ ቤት የገባው። በምንስ እህል ብቅሉ ተበቅሎ ቂጣው ተጋግሮ ጌሾው ተጠንሶ ጠላው ተጠምቶ እንደሚከፈል አምላክ ይወቀው፤ ዘንድሮ ጉመኑም ሳያርብን አልቀረም። እንዳየህው ዶማ ይዞ ወይም በሬ ጠምዶ ሕዝቡ የአቅሙን ያህል እንዳያመርት እነዚህን የምታያቸውን መፈክሮች እየዘሩ እንደውዳሴ ማሪያም እንደድርሰነ ሚካኤል ይደግሙለታል። ደጋሚዎቹ እንደባህላችን የገብስ ጠላ እየጠጡ ሲሆን አደሃሪ ከሚሏቸው ሃገሮች በመጡ መጠጦች ከንፈራቸውን እያራሱ ነው። አንተም ተሜ ጸባይ ነሰቶህ እንጂ ከእኛ ከማህይማን ጋር ሽቅብ ቁልቁል ከምትል ከምታያቸው ውስጥ ጡሩምቹን መርጠህ ብትደግማቸው ኖሮ ከዚህን ባልደረሰክም ነበር፤ በማለት እንደቀልድ የምግብ ላይ ወግ ይጫወቱ በቁ።

የአራት ግብዣው አብቅቶ ከመኝታ ክፍሎቻቸው አካባቢ እንዲሰለፉ ተነገሮአቸው ፤ ከዚያንም ለያንዳንዳቸው ሁለት የአቡጀዲድ አንሶላዎች ከአንድ ብርድ ልብስና ለምንጣፍ ሰሌን ለመኝታ አልጋ ተሰጣቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያች ሃገር ከገቡ በአልጋ ላይ መተኛታቸውን እየጠቀሱ የተደረገላቸውን እንክብካቤ ማድነቅ ጀመሩ።

## ፵፩

ለአምስት ዓመታት በጽኑ እስራት ያለፍርድ ታስረው የነበሩትን በቅርብ ወደ ኢልጃሌ የመጡትን ኢትዮጵያውያን በክብካቤ መያዛቸውን ለማሰየት የሃገሪቱ የውስጥ ጸጥታ ጥበቃ ከለኔል የሃገሪቱን የዜና ማሰራጫ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በመጋበዝ ወደ አከባቢው በመምጣት በሚገባ በንክብካቤ መያዛቸውን ችግር እንዳለጋጠማቸው መግለጫቸውን ከሰጠ በኋላ እነርሱም እንዲሰጡ ጠይቋቸው ስደተኞቹም ከቤት እቤት እንደመጡና ትተውት ከመጡት ከሃገራቸው የተለየ ሆኖ እንዳላገኙት መግለጫቸውን ለሬዲዮ፤ በሃገሪቱ ለነበሩት ሁለቱ ጋዜጣዎች ሰጡሉት። እነሱም አስታከው ተነጥለው ያስቀሯቸውን ጓደኞቻቸውን እንዲፈቱላቸው በልመና መልክ መጠየቅ አቀረቡለት። እሱም በጥቂት ቀናቶች ውስጥ እንደሚያመጣቸው ቃል ገብቶላቸው ወደመጣበት ተመለሰ።

ከለኔሉም በገባው ቃል መሠረት ተነጥለው ቀርተው ከነበሩት ውስጥ ጥቂቶቹን ፈቶ ወደሥፍራው ሲአመጣቸው፤ደስታቸው ከፍተኛ ሆነ።

ብዙም ሳይቆይ የዓለም የዜና አገልግሎት ሠራተኞች የተባበሩት መንግሥታት ስደተኛ ከፍተኛ ኮሚሽን ነገረ ፈጅም ከሥፍራው በመገኘት የደረሰባቸውን ችግር በዝርዝር እንዲያስረዷ በየፊናቸው እየጠሩ ጥያቄ ያቀርቡላቸው ጀመር። ከኮሚሽኑ ነገረ ፈጅ ዘንድ ከአጠገቡ በጊዜው ያስቀመጧት ሰማሊያዊ በመኖሯ ማንም በትክክል የሆነውን ለመናገር አልደፈረም።እሱም አጥብቆ ዝርዝር ጉዳዩ ውስጥ ሊገባ አልፈለገም። እስረኞቹም በበኩላቸው ለተወከዩ የዚያን ያህል ስደተኛው በእስር ቤት ሲሰቃይና ብዙ ሕይወት ሲጠፋ መሥሪያ ቤታቸው እንዴት አንድ ነገር ሊያደርግ አልቻለም? በማለት ቢጠይቁትም ብዙ አስቸጋሪ ነገር እንደነበረ ተናግሮ ለወደፊቱ ግን በተቻለው ሁሉ ኮሚሽኑ እንደሚረዳቸው ቃል ይገባል።

ሁለት የቢ.ቢ.ሲ(B.B.C) የኢንግሊዝ ዜና አጠናቃሪ ባልና ሚስት ሕዝቡን በሁለት ከፍለውት ቋንቋቸውን የማይናገሩትን በአስተርጓሚ ሚስትየዋ ስትጠይቅ፤ ባልየው ቋንቋውን የሚናገሩትን ግለሰቦች ነጠል አድርጎ ወስደ አብረዋቸው የመጡትን የጸጥታ ሠራተኞች በዐይኑ እየቃኘ ራሱን ያስተዋውቃል። በትርፍ ጊዜው በተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ ኮሚሽን ውስጥ እንደሚሠራ ጠቁሞ፤ ቀደም ሲልም በዩጋንዳ ለዚሁ ድርጅት ይሥራ እንደነበር ተናገረ፤ «ብዙ ዩጋንዳዊያን በእስር ቤቶች ይደረጉባቸው የነበሩትን አሰቃቂ ድርጊቶች ለተባበሩት መንግሥታት ደርጅት ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል በድብቅ ደብዳቤዎችን ይፃፉ ስለነበር ያም ሁኔታ ብዙ ውጤት አስገኝቷል። ለመሆኑ የእንናተንስ ከእስር ቤት ለመውጣት ምክንያት የሆናችሁን ደብዳቤ የፃፈው ማነው?» በማለት ጥያቄ ቢያቀርብም፤ ደብዳቤውን ያረቀቁት ክፍሎች በአከባቢው ከሚጠየቁት መከከል ቢኖሩም እኛ ነን ወይም እኔ ነኝ በማለት ራሱን ለመግለጽ የፈለገ



ማንም አልነበረም።በጊዜው ከሶማሊ መንግሥት እጅ ወጣሁኝ ብሎ የሚያዝናና ምንም ተጨባጭ ነገር ባለመኖሩ በዝምታ ሲታለፍ፤ሌላው ደግሞ ሁሉም ለመውጣት በተዘዋዋሪ መንገድ ተባትሮአቸውን ያበረከቱ በሆናቸው በጊዜው ረጅም ጣት ሆና ለመታየት የፈለገ አልነበረም። ሁላቸውም በአንድነት ምንም ነገር እንደማያውቁ ሲገልጹለት፤ «በሃገራቸው ውስጥ በወቅቱ ጎልተው የሚታዩ የፖለቲካ መስመር ልዩነቶች እንደነበሩ ጠቁሞ፤ በቅርብ እንደማየው ግን አንድ አይነት አቋም እንዳላችሁ ነው፤ ያ እንዴት ሊሆን ቻለ?»በማለት የሶማሌው የጸጥታ ሠራተኞች ሳይመጡበት መልስ ለማግኘት መቻኩሉን እውነቱ በሚከተለው ፤ «የጠቀሰከው ዓይነት የመስመር ልዩነቶች ልክ ሃገር ቤት ሆነን እንዳየነው በእስር ቤትም ተነስተው ነበር፤ግን በነበሩት ልዩነቶች ላይ ብዙ ፍጭቶችን አደረግን፤ በመጨረሻ ሁሉም ትክክለኛውን መንገድ ከየዕለት ኑሮው ጋር ሲያገናዝበው እርስ በእርሱም በቅርብ ስለሚገናኝና ስለሚተያይ ልዩነቶቹ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እንደሚያመዝኑ ተረድተን፤እንደውም ልዩነቶቹ በእስር ቤት ለመቆየታችን ምክንያት መሆናቸውን ለመገንዘብ ቻልን።ለእስር ቤቱ የአስተዳደር ክፍል መጠይቆችን በአንድነት ስናቀርብ መዝገብ ላይ በሰፈረው ሰምና የመጣንበትን አከባቢ በመጥቀስ አንተ ከዚህ ነው የመጣህው ዘርህ ያ ነው እንዴትስ ከነዚያ ትውላለህ የሚሉትን ቃላት ከሠሩን ክፍሎች ስንሰማቸው ልዩነታችንን እንደሚፈልጉት ንቃት ሰጠን።ሌላው ደግሞ ከሕዝብ ውጭ የሚደረገው የፖለቲካ ልዩነት ሆነ ፍጭት ለራስ ጥቅም ታስቦ ካልሆነ በስተቀር ለሕዝብ ምንም ገንቢ እንዳልሆነ ተረዳን። በሕዝብ ስም ሳይመረጡ እለሁ ማለቱንም መብት መጋፋት መሆኑን ተገነዘብን። የፖለቲካም መስመር ዘውትር በአንድ ነገር ላይ የሚለጠፍ የንግድ ምልክት ያለመሆኑን ተገንዝበን ወደአንድነት በሚያመጣን መንገድ ቀይስን ይህው ወደጡሩ ነገር እንድንወጣበት ተገለገልንበት። በእንፃሩም መከፋፋሉም የተቃዋሚያችንን እድሜ ማራዘሚያ ዘዴ መሆኑን ከተግባር ለማየት ቻልን።እንዳችን ሌላውን የምንጠይቀው ወይም የምንጠያየቀው መብት ባለመኖሩ ይሄው በጥረታችን በአንድነት ከእስር ቤቱ ወጣን።» በማለተ ይመልስለታል። ጋዜጠኛው «ሕብረት ያጠንክር» ብሎ መርቆ ሰዓት ስለደረሰበት ተነስቶ ሄደ።

በወቅቱ ከየትኛው ድርጅት አባል መሆናቸውን ግልጽ አያድርጉት እንጂ ለነፃነታችን የምንታገል ክፍሎች ነን በማለት አስቴክ ሲጃራቸውን እያዙ እንደአስረኛ ጠያቂ ከሃገሪቱ ዋና ከተማ ብቅ ብቅ ያሉም ነበሩ።

## ፵፪

መርካ( ኢልጃሌ) ኑሮው መልካም ነው። ለመኖር አስፈላጊ የሆኑት መሠረታዊ ነገሮች በመጠኑም ቢሆን ተሟልተዋል። ስደተኛው የራሱ መኝታ አለው። በውኃ አገልግሎት በኩል የሚቀርብ ምንም ሮሮ የለም። የልብስ ማጠቢያ ውኃ በገንዳው ዘወትር የሚሞላ

ሲሆን ለሰውነት መታጠቢያ አምስት ክፍሎች ተመድበው ሳሉ፤ሽንት ቤቱም እንደሃገሪቱ የኑሮ ደረጃ የሚያስከፋ አልነበረም። ምግብ ግን ለጥቂት ሳምንታት የተሻለ ቢቀርብም ከዚያው እስር ቤት ይሰጥ ከነበረው ራሽን ተመለሱ።

ጠዋት ሃምሳ ግራም ዳቦ ከአንድ ሙዝ ከጥቂት ቃሪያ ጋር ታድሎ፤ ምሳ የበቆሎ ገንፎ በወታደር ጋቤጣ ከወገቡ ላይ ቀረት ያለው ሲታደል፤ እራት ሁለት ጭልፋ ሩዝ ይሰጣል።

የማታውና የጠዋቱ የእስር ቤቱ ቆጠራ አልቀረም። በእስር ላይ ለቆዩት የተሻለ ቢመስልም ከከተማና ከፖሊስ ካንፕ ለመጡት እስር ቤት እንደገቡ ነበር። ያም በመሆኑ ከከተማ ከመጡት ውስጥ ሌት ሁለት ግለሰቦች እጥር ዘለው ሲያመልጡ፤ ሁኔታው በጠባቂዎቹና በአዛዡ ዘንድ ሽብር ፈጥሮ፤በቀሩት ላይ ጥበቃው ከረረ።በእልጋቸው ላይ ተጋድመው እንዲውሉ ተደረገ።ጠባቂዎቹም ይበልጥ ጨከኑ፤ «ሀበሽ ክብር አይወድለትም» የተለመደ ስድብ ነውና ደጋገሙት። «በአልጋ ላይ እስተኝተን ብንቀልበችሁም ልበችሁ ረግቶ መቀመጥ አልቻለም» በማለት ባለውለታ መሆናቸውን በመደጋገም አወሱት። ስደተኛውም ከእኛ የጠፉት ይሻላሉ፤«እይጥ በበላ ዳዋ ተመታ» ሆነ ታሪካችን በማለት ምሬታቸውን ገለጹ።

በጊዜው ግለሰቦቹ መስሏቸው እንጂ ከስደተኛው ጣቢያ ወጥተው የሄዱት፤ ቋንቋና መንገድ ለማያውቅ ሰው ከሶማሊያ ተነስቶ ኢትዮጵያም ሆነ ኬኒያ ለመድረስ በጣም ያስቸግራል። ሃገሪቱ ሜዳና እሸዋማ በመሆኗ የእንድን መንገደኛ ዱካውን ተከትሎ ለመያዝ ብዙም የሚያዳግት ባለመሆኑ በአመለጡ በሦስተኛው ቀን ተይዘው መጡ። የሶማሌ ወታደሮች ከሠሩት ትልቅ ሥራ ቢኖር ከመንገድ ሳይገድሏቸው ይዘዋቸው መምጣታቸው ነበር። ከነዚያ ስደተኞች መካከል በማይመለከታቸው ሌላው ምርኮኛ በጠፉ ከመንገድ ተይዘው እምስት ዓመት በእስር ከማቀቁት ጋር ሲነፃፃር የነዚህ በጣም የሚያስደስት መጨረሻ ነበር። ውሎ አድሮ እንደታየው ግን የሽለቃው ርህሩህነት መሆኑ ተገለጠ።

ሽለቃው በሁለቱ ሃገሮች መካከል በተደረገው ጦርነት የተካፈለ ሲሆን እንድን ወጣት እባት እናቱ ሞተው ሽቅብ ቁልቁል ሲባዝን ወታደሮች ተኩስ ሲከፍቱበት እስጥለው ከእርሱ ዘንድ እስቀምጦት ትምህርት ቤት አስገብቶት ሲታይ የነዚያ ስደተኞችም ነፍስ መዳን በእርሱ ጠረት መሆኑ ግልጽ ሲሆን ይረዳው የነበረው ኢትዮጵያዊም ከወገኖቹ ዘንድ እንዲውል ሙሉ መብት የሰጠው እንደሆነ ሲናገር የሸለቃው ጥሩ ሰውነት የሚያጠያይቅ አለነበረም።

ሰው በእህልና ውኃ ብቻ እየኖርምና ስለዚህ ሲውል ሲያድር ኑሮው ለሁሉም አሰልቺ ሆነ። እስር ቤት ውስጥ ልብስ በማጠቡም ፍራሽ በማደሱም፤ በሲጃራው ንግድም፤ በመጠኑም ስለሚያዙ ቀኑ ይመሻል። ከኤልጃሌ ጠዋት ከንቅልፍ ተነስቶ ቁርስ ተበልቶ ምሳ እስከሚደርስ ያንን ሁለት ሜትር እንሶሳ እጣፍቶ ተቀምጦ መዋሉ ለብዙዎቹ ኑሮ የመረረ ሆነባቸው። በዚያን ላይ የትንባሆው፤ የሲጃራው ሱስ አድርስ የሚባል ሲሆን፤ችግር ብልሃትን ይፈጥራልና፤ እንዱን እንሶሳ ለሁለት ከፍለው ሽሚዝ ሰፍተው እንደኛውን ለምግብ



አቅራቢው እንዲሸጥላቸው እስደርገው፤ በዚያን ትንባሆ እስመጥተው ሲጎርሱ፤ በቀረው ሲጃራ በማስገዛት ሲቸረችሩ፤የሚሰጠውን የልብስ ሳሙና መልሰ ለሽያጭ ሲያቀርቡ፤ የሚሰጠውን ሙዝ ትንባሆ ለማይጎርሱና ሲጃራ ለማያጤሱ በመሸጥ፤ እስር ቤት እንደሚደረገው ጨርቆችን ከከተማ በማስገዛት የዕቃ መያዣ በርሳ መስፋት ሲጀመር፤በማነህ ማነህ ገንዘብ በመጠኑም ቢሆን ወደ ስደተኛው ጣቢያ ለመግባት ቻለ።

ሰውነትን ለማንቀሳቀስ እራት የመረብ ኳስ ቡድኖች ተመሠረቱ። ኳሱ ከተጣለ የወታደር ሜጋ ተሰብስቦ በውኃ ታጅሎ እንዲለሰልስ ተደርጎ ተሰፋ። ከመነዳሪው ከተጣለ ኳስ ከወታደሮቹ ዘንድ ተገኘ። ሁሉም ያለውን የፈጠራ ችሎታ ለነበረበት ሕብረተሰብ በራሱ ፍላጎት እስተዋፆእውን ለማበርከት ጥረቱን ሲያደርግ ከስፖርቱ ጋር ዘፈን ተከተለ። ያሸናፊው ቡድን በጨርቅ ላይ የተጠለፈውን ዋንጫ ይዞ ጭፈራውን እቀለጠው፤ዙሩም ቀጠለ፤ ከተጣሉ የዘይት ቆርቆሮና ከጆኒያ ክር ተገምዶ ክራሩ ተቃኘ፤ የስደተኛው ጣቢያ በክራር ተጥለቀለቀ። ከስደተኛው ውስጥ በምታቸው የታወቁት የክራር ተጫዋቾች ክራሯን ሲያሳብሯት ሁሉም በእልጋው ላይ ተጋድሞ ሚስትና ልጆቹን እምኛውን የእረጁ እናት እባቱን በሕይወት እሉ የሉም የሚተከዝበት ጊዜ ሆነ። ሁሉም መች ቀኑ መሽቶልን ክራራችንን እዳምጠን ማለት ተጀመረ።

ውሎ ሲያድር መድረኩ የኪነትም ሆነ የትያትር መድረክ ተፈጠረ።ድርሰቶች የጠቅላላ ሕዝቡን በሚመለከቱና ልቡን በሚነኩት መንገድ ተቀነባብረው እንዲቀርቡ ተደረገ።የመድረክ ተዋናኝ ያላቸውን ችሎታ ለሕዝቡ አበረከቱ።ስደተኛው ስሜቱን ከመድረክ ላይ በመውጣት በቀረርቶና በልዩ ልዩ መነገዶች ገለጸ።በባዕድ ሃገር መሆኑን ዘነጋው። ያ «ሸርጣም ሶማሌ» በማለት የፎከረም አልጠፋም። ዘበኞቹም በሚደረገው እንቅስቃሴ ከመደሰታቸው አልፈው ተርፈው በማያውቁት ቋንቋ የተዘጋጀውን ትያትር እስደስቷቸው ከሥፍራው ተገኝተው ይመለከቱ ነበር።ይህ ሁሉ ነገር ይካሄድ የነበረው፤ በፍቅርና በፍጹም መግባባት በመሆኑ፤ምንም እንኳን ከሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎችና የሥራ ሞያዎች የመጡ ቢሆንም ይደረጉ ለነበሩት ነገሮች ለማንኛቸውም ባዕድ አልነበሩም። ተሰትሮ መቶ በመቶ ነበር። በማንኛውም አቅጣጫ የራሳቸውን ሕብረተሰብ መሥርተዋል።

ስደተኛውን ለማገልገል የተመረጡ ግለሰቦች ስህተቶችን ሲሰሩ ጠቅላላው ስደተኛ ስብሰባ አድርጎ ጥፋተኛው ያለምንም ይሉንታ በሰራው ስህተት እርማት እንዲያደርግ ሲጠየቅ፤ ጥፋቱ ከተደጋገመ ግን በምትኩ ይመረጣል። ከበስተጀርባ የሚደረግ ነገር የለም።ይከናወኑ የነበሩት ተግባሮች በሙሉ ግልጽነትና ታማኝነት በተሞላበት ስለሆነ ዘለቄታነት ነበራቸው። ትልቁ ነገር ሁሉም ለሚያደርገው ነገር እምነትና በራስ እነሳሺነት በመሆኑ ውጤትም ያማረ ነበር። ዋነኛውና ከእስር ቤት ከገቡበት እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ሲደረግ የነበረ ነገር ቢኖር የፊደል ማስቆጠሩና መደመር መቀነስን ማስተማር ሲሆን የትምህርቱም ሥራ ይካሄድ የነበረው፤

በቁጥር በቁጥር ተከፍሎ በመኝታ ላይ ተቀምጦ ሆኖ ሳለ፤ ኢልጃሊ ከተዛወሩ በኋላ ግን አንድ የመማሪያ ክፍል ስለተገኘ መደበኛ ትምህርት መስጠት ተጀመረ። የሃገራቸውን ቀርቶ የሶማሌውን ፊደል ተምረው ለማስተማርም የበቁም ነበሩ።

ሚሊሸው አብዛኛው ማንበብና መፃፍ ቻለ፤የትንባሆውንና የሲጃራውን ሂሳብ የሚያሰላበት ሒሳብን አወቀ። ዕድል ገጥሞን ወደ ሃገር ብንሄድ በማለት የባዕዱንም መማር የጀመሩትም ሐሳባቸውን ከግቡ አደረሱት።

፷፫

በማነህ ማነህ ስደተኛው ግማሽ ዓመት ሆነው። አዲስ ነገር ቢኖር ከመሰሉ ስደተኛ ሃያ ስድስት ለሚሆኑ ለእንግሊዘኛ ቋንቋ መፃፍና ማንበብ ለሚችሉ በካናዳ በስደት የመኖር ዕድል በመገኘቱ ማመልከቻቸውን በኮሚሽኑ በኩል ሲያቀርቡ፤ እህት አሰረኛዋም ተለቃ ከሐመር ገባች።

ተረጋግቶ የነበረው ልባቸው ዳግም ተቀሰቀሰ። የቀረነውስ መቼ ነው የምንለቀቀው? የሚለው ጥያቄ በያንዳንዱ ስደተኛ መጠየቅ ጀመረ። በተለይ ከዚያን በፊት የመፈታቱን ጉዳይ አንስተውት የማያውቁት መሐመድ ሳኒና ጎቤ የመለቀቁን ጥያቄ አጥብቀው ያቀርቡ ጀመር። እነዚህ ሁለት ግለሰቦች የታሰሩበትን ሁኔታ አብረው በቆዩበት ወቅት እውነቱ ቀርቦ ጠይቋቸው እንደተረዳው የገፍ ገፍ ነበር። ጉቤ ትልቅ አባጭ ከወገቡ ላይ ወጥቶበት ሳለ በመጀመሪያ የያዙት ወታደሮች ያቀረቡበት ምክንያት በጀርባው ላይ ወጥቶ ያለው አባጭ ሳይሆን የመገናኛ ሬዲዮ ስለሆነ በዚህም እየተጠቀመ ለኢትዮጵያ መንግሥት ማስረጃዎችን ያስተላልፋል የሚል ነበር። መሐመድ ሳኒም በአካባቢው ይደረግ የነበር ብጥብጥ አስመርሮት «በሶማሌ አቦ» ስም ከደቡብ ክፍለሃገር ወደዚያች ሃገር ሄዶ በስደት ሳለ ከሞርከኛ ጣቢያ ያመለጠ ኢትዮጵያዊ ለመያዝ የተሰማሩት የሶማሊያ ወታደሮች በመንገድ ላይ አግኝተውት ሲያናግሩት፤ ቋንቋውን አለመናገሩን ሲረዱት «የሀበሻ ሰላይ ከለኔል ነው» በማለተ ከእስር ቤት ወምረው ለዘመናት ያጉላሉት ነበር ። ሁለቱም ግለሰቦች ከአምስት ዓመት በላይ በአስራት ላይ የቆዩ ሲሆን ከእስራቱ ብዛት አእምሮአቸው አልፎ አልፎ ይስታል፤ ግን አንዳንዴ ከቀልባቸው ሲሆኑ ስለሕይወት ታሪካቸው ሲያወሱ በእውነቱ የሰው ልጅ መከራን ለመሸከም ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ያስገነዝባል። ጉቤ ስለችግሩ አውርቶ ሲጨርስ «የሐረሩ አባዲር» ያውቃል ብሎ ንግግሩን ሲቋጭ «መሐመድም የባሌው ሼህ ሁሴን» እንደሚያውቅለት እምነቱን በሱ ላይ ይጥላል።

የመፈታቱ ጥያቄ የሁለቱ ግለሰቦች ብቻ መሆኑ ቀርቶ የጠቅላላው ስደተኛ መጠይቅ እየሆነ በመምጣቱ ፤ ሻለቃውን በማስጠራት ስለዘለቄታቸው ጥያቄ ሲያቀርቡለት፤ እሱም ችግሩን ለበላይ ማስተላለፍ እንጂ በግል የእነሱን ጉዳይ ለመፍታት ሥልጣን



እንደሌለው ያስረዳቸዋል።

ቀደም ብለው የመጡት ስለመፈታታቸው ሲጠይቁ ደባስ ብሎ ሁለት ማክ መኪና ሙሉ ሌሎች ሀበሾች ተጭነው መጡ። ብዙው በሐርጌሳ በኩል በቅርብ የወጡ ሲሆን ጥቂቶቹ እንደሴንተራሊዎቹ ለአምስት ዓመት በጽኑ እስራት ላይ የቆዩ ነበሩ። ከአዲሶቹ ውስጥ ሰባቱ ሴቶች ሲሆኑ አንዲት የአምስት ዓመት ሕፃን ከነእናቷ ትገኛለች። ሕፃኗም እስር ቤት እንደተወለደች ከዚያው ከመጡት ውስጥ ተነገረ። ችግሩ የተፈጠረው ከድሬደዋ አካባቢ የሶማሌ ወታደሮች ሕዝቡን በምርኮኛ ስም አፍሰውት ከሐርጌሳ እስር ቤት ጨምረዋቸው፤ እናት በጊዜው ከሕጋዊ ባለቤቷ ቅሪት ኖራ ከእስር ቤት ትገላገላለች። ሕፃኗም ከእስር ቤት ተወልዳ ከዚያው ታድጋለች።ከተወለደች ጀምሮ ውጭውን ዓለም አላየችውም፤ ሁኔታውን ይከታተል ከነበር ወጣት ሲጠየቅ ተከዝ ብሎ እንደጦርነት «መጥፎ ነገር አለ? ይልና በሃገር ቤት ለእናቶች የሚደረገው ወግና ሥርዓት ተከናውነውለታል ለማለት ያዳግተኛል። ያ የምናውቀው ጭራ የሚመስለው የእጃ ገንፎ በባለሞያ ተገንፍቶ ቅቤ እስከ እናቱ ተሞልቶ፤ የእጃው ሙቅ ተሞቆ ተልባው ተመቶ ትኩስ ዱሉት ሁሉም እንደአቅሙ የሚያቀርበውና ለታራሿ የሚደረገው እንክብካቤ አልተደረገላትም። ሕፃኗም የወጋችንን ጠሬ ቅቤ አልዋጠችም ያንኑ የእናቷን ደረቅ ጡት እንደጎረሰች አልጠራጠርም፤» በማለት በሥፍራው የነበረ ወጣት የወገኑን ችግር ያቀርበዋል።

በቅርብ ከሃገር ቤት የወጡትን ምን የተሻሻለ ነገር እንዳለ ሲጠየቁ እንደቀድሞ ሰዎች እየገደሉ በመንገድ መጣልና ለአስከሬኑ ገንዘብ መጠየቁ እደሌሉ ሲሆን፤ግን በጣም ስውር በሆነ መንገድ እስተዋይና ለሕዝብ ለመሥራት ፍላጎት ያላቸውን ግለሰቦች እያጠመዱ ከወንጀል ማስገባትና ከሥራ ማፈናቀል ሆን ተብሎ ተጀምሯል።ያለውን ችግር በመመልከት ከሃገር መውጣቱ እንደእግራጭ ሆኖ ስለተወሰደ ወጣቱን ገንዘብ እየተቀበሉ ከሃገር ማስወጣቱ ደግሞ ወቅታዊ የገቢ ምንጭ ማግኛ ዘዴ በመሆኑ ሰዎች ሥራዬ ብለው ለዚህ ተሰማርተዋል።«የአፍሪካ ቀንድ ትልቁ ጭያ ሰዎችን ፍንገላ» በሚል የንግድ ስም ታውቋል። ቀድሞ በጅቡቲ በከፊል ከሶማሊያ ሲጃራ፣ ልብስ፣ መጠጥ በኮትሮባንድ በማስገባት ሰዎች የከበሩት ያህል፤ ዘንድሮ ሰዎችን ከሃገር በሆነው መንገድ ማስኮብለሉ የገቢ ምንጭ ሆኗል። በመጀመሪያ በመጠነኛ ገንዘብ የተዋዋለው እስኮብላይ ከጠረፍ ሲቃረብ በኮብላይ እጅ ላይ ያየውን ሰዓትም ይሁን ወርቅ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤ ካልተሰጠው ከበረሃ ትቶአቸው ሲሰወር፤ በዚህ ዓይነት ሞክረው፤ ሳይሳካላቸው ቀርቶ ሃገሬው በግድ አግብቷቸው ሙሉ ጠፍቷቸው እንደወጡ የቀሩ እህት ስደተኞች ብዙዎች ናቸው።

በተለያዩ ጊዜያት ከሃገር ወጥተው በተለያዩ እስር ቤቶች ታስረው የቆዩትም ሆኑ በቅርብ ከሃገር የወጡት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ያገኟቸውን ልምዶች ከሰዓት በኋላ በጓድ በጓድ ተከፍለው ለመነጋገር ፕሮግራም አውጥተው፤እውነቱና ሌሎች አራት ስደተኞች ሆነው ከሃገር ቤት ለምን እንደወጡ ሲነገገሩ እንደኛው ተማሪ የራሱን እንዲህ ያቀርበዋል። «ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ

አልገባሁም፤ከሃገሬ የወጣሁት እውነት በመናገሬ ብቻ እገደላለሁን በመፍራት ነበር። በሃገራችን ውስጥ ለውጥ ለውጥ እየተባለ ሕዝቡ አጥናፍ ከአጥናፍ የሚያስተጋባበት ሲሆን፤ ወጣቱም ወገን ለይቶ ያለውን መንግሥት የሚቃወምበት ወቅት ነበር። እናቴም ከአንዳንድ ልጆች ገጥሞ ከዘመኑ ነገር ውስጥ ይገባብኛልን በመፍራት ትምህርት ቤት ለፋሲካ ሲዘጋ ከታላቅ ወንድሜ ዘንድ ከባሌ ጎባ ላከችኝ።ከእርሱም ጋር ለጥቂት ቀናት ጥሩ ቀን በሥራ ሳሳልፍ ወንድሜም እርሻ ሚንስትር ውስጥ ይሥራ ስለነበር፤ በተወረሰ የእርሻ መኪና ሲያርስ እኔም በሥራው ካለ ሜት መሽሩፍ ስረዳው ከርሜ ደብሮኝ ተበሳጭቼ ወደ ሐረር ከእናቴ ዘንድ እመለሳለሁ በማለት እምርሬ ስነሳ ሐሣቤን ሊያስለውጠኝና ሊያዝናናኝ ከክፍለሃገሩ ዋና ከተማ በመሥሪያ ቤቱ መኪና ተሳፍረን ከአለንበት አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ይርቅ ስለነበር እምሽተን ለመምጣት ጉዞአችንን ወደዚያ አደረግን።ከከተማው ክልል በግምት አንድ ኪሎ ሜትር ሲቀረን ልክ እንኳን ደህና መጣችሁ የሚል የመልክም ምኞት መግለጫ የሚያበስረው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠሌዳ ከተሰቀለበት ዝቅ ብሎ ሦስት ሰዎች በአንድ ሽፍን ቶዮታ መኪና ሥር ቆመው ከሩቅ እሽግረን ስንመለከት፤ ሁለት የፖሊስ የደብ ልብስ የለበሱ አንደኛው ቀይ ከፍያ ከእናቱ የደፋ መኪናዋን ከበው ቆመው ስናይ፤»ወንድሜም መኪናውን ቆም አድርጎ «መታወቂያ ይዥ እንደሆን ጠይቆኝ እንደሌለኝ ስገልጽለት ስለአሳመነኝ፤» «ለመሆኑ የባብሌ ከተማ የቀበሌ መታወቂያ እንኳን የለህም?» ሲለኝ «መታወቂያ ምን ያስፈልገናል የባብሌ ሕዝብ ሁሉም ይተዋወቃል ስለው በጣም ተናደብኝ፤ እኔም ተናድጄ፤ ከኬኒያ ወይስ ከሶማሊያ ጠረፍ አይደለም ያለነው ከሃገራችን ነን ስለው ረጋ ብሎ» «ያ ቀይ ከፍያ ያደረገው የደርግ አባል ነው። ከዚህን አካባቢ ትልቅ ወንጀል ባይፈጸም አይቀርምና ሁኔታው አሳሳቢ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የደርግ አባሉ ራሱ ከከተማው መግቢያ ውጭ ወጥቶ አይጠብቅም፤» ሲል «ከሥራ መምጣታችንን እጃችንን እናሳየዋለን ስለው ተናደብኝ ነዳጅ ሰጥቷት እየተቃረብን መምጣታችንን ሲያዩ እነሱም የራሳቸውን አስነስተው እኛ ወደመጣንበት ጉዞአቸውን ጀምረው፤ ከአጠገባችን ሲደርሱ ወንድሜ መኪናውን አቁሞ ዱብ ብሎ ወርዶ ጌታዬ «ኢትዮጵያ ትቅደም» ለክንስ እንደምን ዋላችሁ እንደሚባለው የሰላምታ መለዋወጫ ዜቤ ኖሮ የደርግ አባሉም መኪናውን ቆም አድርጎ ያለምንም ደም ብሎት አለፈ።

እኔና ወንድሜም ቀደም ብሎ የደርግ አባሉ መኪና ከቆመችበት ስንደርስ አካባቢው በደም ተጠለቅልቋል፤።ከዚህን ሥፍራ ሰው ተገጭቷል ብሎ መኪናውን ነዳጅ ሰጥቶ ሊያስነሳ ሲል አስቁሜው ከእነሱ ነጠል ብሎ ከአዘረዘረው የገብስ ቡቃያ ሲገባ ከሩቅ አይቼው የነበረውን ሰው በሩጫ ከቡቃያው ገብቼ ገለሰቡን ባናግረው፤ የሞተች ሕፃን ልጁን እሬሳ አሳየኝ። የሞቱን ምክንያት ብጠይቀው»

«ይህን ወንዱን በትከሻዬ እንኮኮ ብዬ በእግሯ የምትሄደውን በእጄ እየመራኋት ሳለሁ ከየት መጣ ሳልል ከእጄ ላይ ጠልፎ ገጭቷት። ተደናግጭ ለእርዳታ ብጮህ የደርግ አባል ነኝ እደሃሪ በንብ ልትቀብር ነው ከዚህ የቶምከው ብሎ ሺጉጥ ሲመዝብኝ የልጄን ሬሳ አስቼ የማደርገው ቅጡ ጠፍቶኝ ቆሜለሁ።ባለቤቴ እህል በጀርባዋ ተሸክማ ቀድማኝ ለጥቂት ሄዳለች ይህንን መዓት ይዥላት ከቤት ስሄድ ምን ይመስላት ይሆን?»«ብሎ እንባውን ዱብ ዱብ ሲያደርገው እኔም ራሴን መቆጣጠር አቅቶኝ እያለቀስኩ ወንድሜን ወስጄ አሳየሁት።ወንድሜም ሁኔታው አስደንግጦት ለመዝናኛችን ከያዘው ገንዘብ ጥቂቱን አስቀርቶ ለሰውዬው ሰጥቶት ወደጎባ ከተማ አመራን። እኔም ማታውን ያእውቶቡስ ትኬቴን እንዲገዛልኝ ጠይቄው ወደሐረርጌ እመለሳለሁ እልኩት።ቢለምነኝ ቢለኝ ቢሰራኝ እሺፈረኝ፤ አሊ ሙሣ ካለበት ሃገር አንዲት ቀን አላድርም ብዬ በማግስቱ ወደሐረር ጉዞዬን አድርጌ በሦስተኛው ቀን ከባቢሌዬ ደረስኩ።

ባብሌ እንደደረስኩን የደርግ አባል ይመጣል ተብሎ ሕዝቡ በቀበሌ ለዝግጅቱ ሽርጉድ ይላል።ባሌ ጎባ ያየሁት በባብሌም ይደገም ይሆን እየልኩ በየጊዜው ሳሰላስል፤ወጣቱም ይፈለጋል በማለት እኔም ከጓደኞቼ ጋር ከቀበሌው ስብሰባ ለመገኘት ሄድኩ። ሕዝቡ ስለዝግጅቱ ስለአቀባበሉ ሁሉም በየተራ እየተነሳ ሐሣቡን ሲሰጥ፤ በማነህ ማነህ የሚቱ ሰዓት ደረሰ ስብሰባው ተበትኖ ለሐራራችን ሚት ተራ ለመሄድ ተቻኩለናል። ሐራራም አለብኝ የት እንዳለሁም አላውቅም እኛ የደርግ አባል አንፈለገም። የደርግ አባል ማለት ነፍስ ገዳይ ነው ብዬ ቁች ስል፤ጓደኞቼ በሙሉ አብደሃል ብለው ጮኹብኝ። የቀበሌው ሕዝብ በየቤቱ ሲመለስ ጎረቤቶች ለእናቴ ልጅሽ የደርግ አባል ተሳድቦልሻልና እንዳይገድሉልሽ የቀይ ጥቁር ሆነሽ ያሳደግሽውን ልጅሽን ማጣትሽ ነው ቢሏ ለምን እንደ እብድ ሆና ከጥናት ቤት አተመጣም።እኔም ከጓደኞቼ ጋር ከጥናት ቤታችን ፈርሽን ስለ ባሌ ጎባ የሆነውን ሳጫውታቸው ጠርታኝ ከቤት ወስዳኝ ዛሬውኑ ድሬደዋ ድረስ ሄደህ ነገ ከእህቴ ዘንድ አዲስ አበባ ተሳፈር ብላ አድራሻዋን ሰጠችኝ። እኔም በማመታት እማዬ እንዴትስ እነሱ ወደአሉበት ከተማ ትልኪኛለሽ ስላት ነገሩ ተሰምቷት ሐሣቧን ለውጣ ከወተት ማሚላዎቿ ዘንድ ከገጠር እንደቆይ ተደረገ። በመሐል በሁለቱ አገሮች መከከል ጦርነት ተጀመረ ወደከተማም ለመሄድ አልተቻለም። እንዚህም በምርኮኛ ሰም ከሐረጌስ እስር ቤት ከዚያም ከሞርከኛ ጣቢያ ከደናሌ በመጭረሻም ከኤልጂሌ መጣሁ እላችኋለሁ።» እንዴት እንድነገር እንደሚደርስበት ከመናገሩ በፊት እንዳሰሰበ ከሚያዳምጡት አንደኛው ሲጠይቀው፤ «እንደኃይሌ ጊዜ መስሎኝ ነዋ! በኃይሌ ተማሪ ሲረብሽ አዴሌ አማሬሱ ከበዛም ጭናክሰን ለብ ለብ አደርገው ይተውናልን እንጂ እንደዘንዶሮቹ ሽጉጥ መዘው እንደጠላት ወገን ይገላሉ ብለን መቼ አስብን።ሐረር እንዲህ ያለ ችግር እናውቅም ሐራራ ላይ መንግሥቱ ራሱ ቢሆን ማን ይፈራዋል? ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወታደር የሚባል ሰው ችግር ሆኖብኝ እንጂ እንዘህን እብረን የምንኖረውን ሚሊሻዎች ሆኑ የሚጠብቁንን የሶማሌ ወታደሮች ባሳይ ፍቃዴ ነው።»

በውይይታቸው ላይ የነበረው ወታደር በመናደድ ከመቀመጫው ተነስቶ ለመሄድ ሲቃጣው ሁሉም በአንድ ቃል «በነገው ውይይታችን እንደማትገኝ እመነህ ሂድ» ሲሉት፤ እሱም ደንገጥ ካለበኋላ «ምን

አጠፉሁ?» «እነርሱም ያጠፉህውን እንነግረሃለን በመጀመሪያ የብዙሃኑን ቃል ተቀበል» ሲሉት፤እሱም ተስማምቶ ተቀመጠ። እውነቱም እንዲናገር ተፈቅደለት፤ የተሰነዘረው ሐሣብ የግለሰብ እንጂ የሁለቸውም አስተያየት እንዳልሆነ ሲገልጽ፤እርሱም የቆየ ልምድ በአንድ ቀን እንደማይለወጥ ጠቀሞ ይቅርታ ጠይቆ አንበሳውን አጣፍቶ ትንበሆውን ጉርስ ውይይቱ እንዲቀጥል ይሆናል።

እውነቱም በመቀጠል «ቀደም ሲል በጓደኞችን የተገለጸው አሰዘኝ፤ አሰቃቂ፤ ሁኔታ ወገን ይፈጽመዋል ብለን የምንገምተው ድርጊት ባይሆንም፤ ሁኔታውን የፈጸመው ግለሰብ ሲሆን ግን ተግባሩን የሞያው ባልደረቦች እንደፈጸሙት አድርጎ መደምደሙ የምንነቅፈውን ድርጊት የቀሩትም እንዲያደርጉት የሚገፋፋ በመሆኑ በዚያን አኳያ ሁላችንም አንቀበለውም። ጠቅላላ ያለውን ሥርዓት ከመቃወም አንቆጠብም። እንዱ በአንዱ ሥር እየተከለለ ለራሱ ጥቅም ሲል ወገንን የሚበድል በማንኛውም የሥራ መስክ ውስጥ አይኖርም ብለን ለመናገር አንችልም። በእርግጥ በሃገራችን አጥፊውን በግልጽ የመውቀስ መልከም ሠሪውን የማመስገን መብት ቢኖረን እንዱ በአጠፋ በጅልማ ሁሉን መቀፍ ባልተገባን ነበር። አሁንም እዚህ ቁጭ ብለን ማንኛውንም የተሰማንን ለመግለጽ በመቻላችን ሊመጣ ይችል የነበረውን ልዩነት በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ልንቀጪው ቻልን። እላይ የተገለጸውን ግለሰብ ዓይነት ተግባር የሚፈጽሙ ብዙዎች ናቸው። ያ ባይሆን ኖሮ እኛም ሃገር ጥለን ባልተሰደድን ሃገራችን በእንዲህ ያለ ችግር ባልወደቀች ነበር።»

ወታደሩም በበኩሉ ሐሣቡን ሲገልጽ፤« በአጠቃላይ ከበታች ባለው ሠራዊት ላይ መፈረድ ያስቸግራል። ግን ጥፋት አልተሰራም ማለት አልችልም። ጥፋቱ የሚጀምረው እንደውም በወታደሩ ሳይሆን በምሁሩ ነው። ምሁሩ ከእኛ ከወታደሩ በላይ ሕዝቡን ያውቀዋል ታሪክንም ቢሆን ከተራው ሕዝብ በማንበብም ይበልጥ የማገናዘቡ ዕድል አለው። እናም ጠላትን ለማጥቃት ተብሎ የሚሰለጥንን ሠራዊት ወጤታዊ በሆነ ትምህርት መታነጽ ሲኖርበት በሁለት መንገድ እንዲያገለግል ሆን ተብሎ ፤በረቀቀ መንገድ እርስ በእርሳችን እንድንናከስ የተደረግነው መዋቅሩን በአወጡት ግለሰቦች ሲሆን ተራውን ወታደር መኰነኑ ተገቢ አይደለም። ለምሳሌ በወታደሩ ክፍል ሲሰለጥን ጠላት ለማጥቃት ወሰን ለማስከበር ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነቱን ለመግለጽ ሆን ተብሎ ለዚያን ተከትኩቶ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ሕዝቡ ጠላት ሲባል የሚያውቀው የውጭ ወራሪን በመሆኑ ፤ በዚያን ስም ሰልጥነን በወገንም ላይ እንድንዘምት ተደርጓል። ቃሉ እሽሚ ነው ፖሊሱ ተማሪውን ተከሰ ቢገለው ጠላት አጠፉ ማለት አይሆንም ግን በሳጋራ መፍጥር ሊሆን ይችላል። ጦር ሠራዊት በአንድ ክፍለ ሃገር ላይ ሲመደብ የሃገሪቱን ጸጥታ ለማስከበር ሊሆን ይችላል፤ ግን ሕዝቡ በግልጽ ችግር የፈጠረውን ባለማወቁና በትክክለኛው መንገድ ባለመረዳቱ በሁለቱም መንገድ ችግሩ በመከረሩና ደም በመፍሰሱ የአስተዳደሩ ክፍል ሕዝብን ለመቀስቀስ ጠላት በማለት ወገንን እርስ በእርስ በማፋጀት እድሜውን ያራዝማል። የዘመኑም የአብዮቱ ምሁራን ደግሞ ሚሊሽውን ለማሠልጠን ያወጡለት ሥርዓተ ትምህርት



ስንመረምረው፤ ጠላት የሚለውን አስቀርተው አደሃሪ በሚል ቅጽል ለውጠውታል። አደሃሪውን የሰማሌ ጦር ከሃገር ለመከላከል የሰለጠነውን ወታደር አደሃሪያን በሸዋ በኢሊባቦር አደሃሪያን መምህራን ወዘተ ተነስተዋል በማለት ለማዝመት አመቺ ሆኖ ተዘጋጅቷል። በዚህን በኩል ይህች ሃገር ትበልጠናለች። ወታደራቸውን ግልጽ በሆነ መንገድ አንጸውታል ሀበሻን ለመዋጋት አበቃ። ታዲያ ወገኖቼ በእኔም ውስጥ ያለውን እውነት ተገዝበቻሁልኝ ይሆን ?ውኃ ከምጨ ነገር ከሥሩ በሚለው ወጋችን አንፃር አልታየም በሚል ነበር እኔም ተናድጄ ስብሰባውን ረግጬ ልሄድ የነበረው።»

ከሠራተኛው ክፍል የዘመተው የሦስት ልጆች አባት የነበርው ተገኝ ከሃገር የወጣበትን ምክንያት እንዲህ ያቀርበዋል።«እንደምታውቁት ከብዙዎቻችሁ ጠና ሳልል አልቀርም። በዚህ እድሜ ከሃገር ወጥቶ እፈርን ከባዕድ ሃገር ማድረግ አገባብ ነው ብዬ ለሰው አልመከርም።ችግሩ በዝቶ መውጫ መፈናፈኛ ሲጠፉ ሰው የሚወስደው እርምጃ በሙሉ ተደስቶበትና አምኖበት ነው ለማለት ከራሴ አንፃር አይደለም። እንደው ራስን ዘንጋ ለማድረጋ ብቻ ነው። እኔም እንደብዙቹ በወታደር ማሠልጠኛ ገብቼ አልሰለጠንኩም። በሃገር ተወረረች ስም የዘመትሁ ሃገር ወዳድ ነበርኩ ልበለው። ከምሰራበት ከሲሚንቶ ፋብሪካ ተመልምዬ ወደጦር ግንባር ተላኩ፤ምንም እንኳን ሃገር ተወረረች ወሰን ተደፈረ ሲባል አባት ዘምቶ መቶ ወይም ነፃነቱን አስከብሮ ለተተኪው ልጁ ማሰየት የቆየ ልምድ ቢሆንም በመሐልና በአከባቢዬ በወቅቱ ይደረጉ የነበሩትን አስነዋሪ ሃገር አሰዳቢ ደርጊቶችን ስመለከት የማን ሃገር የምንስ ሃገር ብሎ ደጋግሞ የሚያስጠይቅ ነበር። ሆኖም ዘመትኩ የሃገርም ወሰን ተከበረ። እኔም ወደ ቀድሞ ሥራዬ ለመመለስ ደጋግሜ ብጠይቅ ነግ ዛሬ በማለት ሲያጉላሉኝ ሌላው ቀርቶ ፍቃድ እንዲሰጠኝ ጠይቄ ከአዲስ አበባ ሄድኩኝ። ቤተሰቤን ባልጠበቁት ችግር ላይ ወድቆ አገኘሁት።ልጆቼ ታርዘዋል። ጤነታቸው እየታወከ፤ ባለቤቴ ከሃገር መድኃኒት አዋቂ ዘንድ በመውሰድ በተለይ የመጨረሻዋ ከመሞት እንደዳነችለን ታጫውተኛለች። እቶ ተገኝም ቀና ብሎ ወደሴቶቹ መኝታ ክፍል ተመልከቶ ያቺን መሠረት ነው የምታከለው፤ ሁለመናቸው አንድነው። ይህችን ሕፃን ባየሁኝ ቁጥር ቤተሰቤ ትዝ ይለኛል። ይህ በዚህ እንዳለ ምናልባት ብመለስ በማለት ወደ መሥሪያ ቤቴ ሄጄ ጥቂት በዕድሜ ገፋ ያሉትን አገኘኋቸው። ሠራተኛው በየአቅጣጫው ተበታትኗል።ያሉትም መሣሪያውን ማቀሳቀስ ተስኗቸው በጉልበት ይሥሩ የነበሩትም ሠራተኞች በአብዮት ጠባቂ ስም መሣሪያ ታጥቀው ቀደም ጸብ የነበራቸው ከመቀበል አልፈው በበታችነት ስሜት ብቻ ፀረ-አብዮተኞች ናቸው በማለት ታታሪዎቹን ሠራተኞች ከእስር ቤት አስጪምረዋቸው እንዳደቱም እንደተገደሉ ከዚያው ተነገረኝ። ይህን ሁሉ አመዘዝኝ ቀደሞም ከዘመኑ ጣጣ ተወግጄ ሠራዬን አክብሬ የታዘዝኩትን እሽ በማለት ልጆቼን ብቻ ሳሳድግ ብዬ ከሁሉም ተነጥዬ ኀበስ ቃና ስል ከማናቸውም ቡድን ባለመሆኔ ይሙት ብለው የላኩኝ አሁን ብመለስ ያው ወደሌላ የጦር ግንባር መላኬ አይደል በማለት ተሸሽጌ የሰው ወሰን ጥሼ ወደዚህን ልመጣ ተገደድሁ።»

# ፷፱

የካቲት ፳ ቀን ፸፱ ዓመተ ምህረት ነበር። ይህ ወራት በሶማሊያ ውስጥ ሞቃት ከሚባሉት ወራት አንደኛው ሲሆን፤ስደተኛው በሙቀቱ ተዳክሞ ከክፍሉ ውስጥ ገብቶ ተኝቷል። ይህ በዚህን እንዳለ የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛው ከሚሽን አርማ ያሳባት መኪና በማያታቸው ብቻ ወታደሩቹ ስደተኛውን ከክፍሉ እንዲወጣ ትዕዛዛቸውን አስተላለፉ። ሁለት መቶ ስድሳ የሚሆነው ስደተኛ ወጥቶ ከመስኩ ላይ ተሰለፈ። በካናዳ በስደተኛነት የመኖር መብት እንዲሰጣቸው ያመለከቱት ሃያ ስድስቱ ወጣቶች ተጠርተው ወደአዳራሹ ተወሰዱ። ለጥያቄ ከመቅረባቸው በፊት አንደኛው የሶማሊያ የጸጥታ ሠራተኛ ሰብስቧቸው በሚገባ እንድትተባበሩን እንፈልጋለን፤ የሆነ ያልሆነውን እንኳ ብላችሁ ብትቀባጥሩ ሃላፊነቱ የእናንተ ይሆናል በማለት ያስጠነቀቃቸዋል።

የከሚሹም ነገር ፈጅ አብሮ መጥቶ ስለነበር የካናዳውን መንግሥት መልክተኛ ለስደተኛነት መብት የጠየቁትን ወጣቶች አስተዋውቋቸው፤ እነሱም አንድ በአንድ እየቀረቡ ሊያውቅ የፈለገውን በሙሉ ነገሩት። እሱም በግራና በቀኝ የቆሙትን ወታደሮች በአይኑ እየሸፈ በሙቀቱ ምክንያት ከፊቱ የሚወርደውን ላቡት በተለያዩ ፎጣዎች እየጠራረገ፤ «ወዳችሁ ግቡበት ከእኔ ሃገር በዚህን ወራት በረደው ወጭ አያስወጣም። የአየሩ ጸባይ ከዜሮ በታች ነው» በማለት ከዚያኑ ማስፈራራቱን ጀመረ። ለመጠየቁ ከቀረቡት ከሃያ ስድስቱ ውስጥ አስራ ስድስት ብቻ የቃል መጠይቁን ሲያልፉ፤ የጤና እክል ካልገጠማቸው በስተቀር ካናዳ ለመግባት ባለሙሉ መብት መሆናቸውን ከዚያው አረጋገጠ።ትልቁ የሥራ ክፍፍል ያለው ከአሉበት ሃገርና የከሚሽኑ ስለሆነ በዚያ ካለቀ ምንጊዜም እንቀበላችኋለን ብሎ ተስፋ ለጥቂቶቹ ሰጥቶ ወደኪኒያ ተመለሰ።

ተፈታ ከተማ የገባችው እህት በዕለቱ ለቃለ መጠይቁ መጥታ ስለነበር ፤ በከተማ ያለው ችግር በአማርኛ መነጋገር ያለመቻሉን ትናገራለች። «ግን የአማርኛ ሙዚቃ ሶማሌዎቹ ሳይቀሩ ያዳምጡታል።አዲስ ካሴት ሲወጣ ክፍለሃገራችን ሳይደርስ አስቀድሞ በሳውዲ አድርጎ ሐመር ይመጠል። በሙዚቃ በኩል አዲስ አበባ እንደሚኖር ነው። ብዙ ሀበሻ በከተማ ውስጥ ይኖራል። እኔም ብዙ የሴት ጓደኞች አግኝቻለሁ።»

«እንዴትስ ሳያስሯቸው ቀሩ?» በማለት እውነቱ ሲጠይቅ፤
«ስም ለውጠው፤ሚሚ፣ቲቲ፣ ኩኩ፤ የለም።»
«እህስ?» «ፋጡማ፣ዜነባ፣ከዲያ፤ናቸው።»
«እንቺስ ለወጥሽ?» «አዎና!»
«ማን ትባያለሽ?» «አሚና፤»
«ከም ኔው?» «ጉዳዬ ነው።
ከእይሮፕላን ስወጣ እውልቂ እጥልላቸዋለሁ።»
ከነበሩት ከሁለት መቶ ስድሳ ውስጥ አስራ አምስት ወንድችና



አንዲት ሴት የስደተኛ መብት ማግኘታቸው ቢያስደስትም ለብዙሃኑ መለያየታቸው ሐዘን ነበር። እንዚያው ጥቂቶቹ ከአብዛኞቹ ጋር በብዙ ችግር ውስጥ ያለፍ ሲሆን በአንድነት ከአንድ አካባቢ ከወጡት ውስጥ አንደኛው ሲቀር በቀሪው ላይ ቀሬታን መፍጠሩ አልቀረም። የሚሊሸው ክፍል መምህራንና ተማሪዎችን በመቅረብ «ጎበዝ በዚህን በረሃ አፍስሳችሁን መሄዳችሁ ነው፤ በማለት የመቆጨትም የመውቀስም አይነት ሐሣባቸውን አልፎ አልፎ መሰንዘራቸው አልቀረም።»

ኢንግሊዘኛ ተናጋሪው ከብዙሃን ተነቅሶ የማይናገረው ክፍል መቅረቱን የተገነዘቡት በነፃ እውጭ ስም በሶማሊያ ዋና ከተማ ይቀመጡ የነበሩ ጥቂት ጎበዞች ይህንን አቅጣጫው ጠፍቶበት የሚዋልለውን ሕዝብ ሊጠቀሙበት መጠየቁ እንዳበቃ ብቅ ብለው ነበር። በእርግጥ ብዙው ሕዝብ ግራ ተጋብቶ ስለነበር በሥራቸው ተሰልፎ ለመዋጋትም ይሁን በአጋጣሚ ተሸሎክልኮ ሃገር ለመግባት ከዚያ ሌላ ምንም አማራጭ አልነበረምና ጥቂት ተከታዮችን ሳያገኙ አልቀሩም።

ወደካናዳም ለመሄድ ዕድል የገጠማቸው ስለወደፊት እቤታቸው ዘውትር እየደጋገሙ ማውሳት ጀመሩ። ስለካናዳ አንድ የዘጠኘን ክፍል የጨረሰ ተማሪ ስለሕዝቡ ስለሃገሩ የአየር ጠባይ፤ በስንዴ አምራችነት በጂዎግራፊ ጥንቅቆ ያውቀዋል። አነዳንደችም በሃገር ቤት «የካናዳ ድራይ» ማስታወቂያውን እየደጋገሙ ማለት ጀመሩ። የሃገራችን ወጣት ብዙውን የትምህርት ክፍለ ጊዜውን ያዋለው ስለውጭ ሃገሮች በሚያወሳ ታሪክ መሰል ሥርዓት ትምህርት ስለሆነ ያንን በመጽሐፍ ተጽፎ በአስተማሪ ተተንትኖ የተነገራቸውን በተግባር ለማየት በመቃረባቸው ደስታው ከፍተኛ ነበር። በእርግጥ ከወታደር ጥበቃ ሥር መውጣቱና ነፃ መሆኑን ማንም የሚፈልገው ቢሆንም ፤ «አፍቀረ ውጭ በአእምሮ ተቀርጾ» ያለ በመሆኑ ደስታው ደርብ ድርብርብ ነበር ማለት ይቻላል።

## ፫

በከናዳ በሰደት የመኖር መብት አግኝተዋል የተባሉትን ወጣቶች ወደ ዋናው ከተማ መቅድሾ(ሐመር) ለመውሰድ ሁለት የኮሚሽኑ አርማ ያለባቸው ቶዮታ መኪናዎች ሚያዚያ ፲ ቀን ፫ ፬ ዓመተ ምህረት ወደ ሰደተኛው ጣቢያ ሲመጡ የተመለከቱት ወታደሮች ሰደተኞች በሙሉ ከክፍሎቹ ወጥተው ከመስኩ ላይ እንዲሰለፉ ካደረጉ በኋላ፤ አስራ አምስቱ ብቻ ተመርጠው ወደ ማሠልጠኛው አዳራሹ ተወሰዱ። በዕለቱ የመጣው የጸጥታ ሠራተኛ ንግግር አድርጎላቸው የስም መሰሰት ካለም በማለት እያንዳንዳቸውን በመጥራት አስተካክሎ በሁለቱ መኪናዎች እንዲሳፈሩ ተደርጎ፤ከመኪናዎቹ ሲሳፈሩ፤ሰደተኞቹ በሙሉ ከሜዳው ላይ ወጥተው እጃቸውን ሲያውለበልቡላቸው እነሱም አየሩውን በመመለስ ዳግመኛ እንደማይገናኙና ቀሪዎቹም ለዓመታት በዚያን እንደሚቆዩ በመገመት ልባቸው በደስታና በሐዘን መከከል በመዋዥቅ ሰያውቁት ያንን የግብ አጥር በር በወታደር ይጠበቅ የነበረውን ያለአንዳች ጠባቂ ወጥተው ሲሄዱ መፈታታቸውን አምነው ሳይቀበሉት አልቀሩም።ከወራት በፊት በወታደር ማክ ተጭነው በታጠቁ ወታደሮች ታጅበው የመጡትን ከሐመር መርካ ጉዞ በዕለቱ ግን በቤት መኪና በተመቻቹ መቀመጫዎች እየተዝናኑ መስኮቶችን በመከፈት ከሰዓት በኋላ ከሕንድ ውቅያኖስ በሚተነውን በቀዝቃዛው የሚያዚያ አየር እየተናፈሱ፤ አስልቺና ረዥም መስሎ ታይቷቸው የነበረውን ጉዞ ሳያስቡት ከዋና ከተማ ደረሱ።

በሐመርም መኝታቸው በጥሩ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ኖር አንድ ክፍል ለሁለት ተመድበላቸው፤የምግብ ኮንትራት ከዚያው ተይዞላቸው፤ ከሆቴሉ የተቻላቸውን ያህል እንዲመገቡ ሲደረግ በሶማሌ ውስጥ ተወዳጁንና የሚደነቀውን ምግባቸውን ወሰላ(ሰባት የበዛበት) ለመቅመስ ቢችሉም ሆዳቸው በድርቀት ለዓመታት ቆይቶ ነበርና የሆድ መታወከን ለወጣቶቹ ሳያስከትል አልቀረም።

ለሁሉ የመጡት የጤና ምርመራ ለማድረግ መሆኑ ተነግሮአቸው፤ በነጋታ ወደታወቁት የሶማሊያ ሆስፒታሎች ሲወሰዱ ከየአንዳንዳቸው ፊት ላይ ጽልመት ሐዘንና ተስፋ መቁረጥ ሲነበብ፤ በተለይ ለኤክሰሬ መነሣት ከሳንባ ነቀርሳ ሆስፒታል ሲወሰዱ፤ ጨርሶ እስር ቤት እንደነበሩት ዓይነት ሁኔታ ላይ ተመለሱ።ምክንያቱም ከእስር ቤቱ በነበሩበት ወቅት የእስተዳደሩ ክፍል ባለሥልጣኖች ከጠቅላላው ሕዝባቸው ሲሰው በሳንባ ነቀርሳ በሽታ መለከፉን ያወሱት ስለነበር ወጣቶቹም «ይህን ዕድል ገጥሞን በበሽታ ተለክፈን ተነጥለን እንቀር ይሆን» በማለት በአእምሮአቸው ስለሌለ ችግር ራሳቸውን ሲያጨንቁ፤የጤናው ምርመራ ደግሞ ጠበቅ ያለ ለመሆኑ ማስረጃ ሲሰጥ አጠቃለይ ምርመራ ከደረጉ በኋላ በተጨማሪ የኮሚሽኑ ልዩ ዶክተር ዘንድ እንደሚቀርቡ ሲነገራቸው ሁኔታው ይበልጥ አሳሰባቸው። ሁሌ አንድ እርምጃ በሄዱ ቁጥር የሐሣብ ውዥንብር



የዚያኑ ያህል ነበር። አንዳንዶቹም ይህን ሁሉ ውጣ ውረድ አልፈን ካናዳ ከሚባለው ሃገር የመሄዳችን ተስፋ ግማሽ በግማሽ ነው ብለው ሲወስኑ፤ በሽታው እንኳን ታውቆ ለመታከም መቻሉን በጊዜው ያዩት አይመስልም።

በመጨረሻም ሁኔታው በጣም ስለአሰጋቸው የእነሱን ጉዳይ ይከታተል ከነበረው ከለኔል ዘንድ እንደአጋጣሚ ታሞ ከተኛበት ሆስፒታል ድረስ በመሄድ የምርመራው ሁኔታ ጠበቅ ያለ መሆኑን ሙሉ ጤነኛ መሆናቸው እንዲሰጋቸው ሲገልጹለት፤ እርሱም ካናዳ በጤና ምርመራቸው ከሌሎች ሃገሮች ልዩ መሆናቸውን ገልጾ «ለእኛዎቹ ዶክተሮች እነግራቸዋለሁ» በማለት አሰናበታቸው። ከሆስፒታል አከባቢ የሚደረገው ውጣ ውረድ ተፈጽሞ ኤክስሬ የተነሳው የሳንባቸው ፊልም፤ ናይሮቢ ኬኒያ እንደሚላክ ተነግሮአቸው ከኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ተጠርተው ከዋና ኮሚሽነር ዘንድ ቀርበው፤የእነርሱን ጉዳይ ይከታተል የነበረው የኮሚሽኑ ነገረፈጅ ለስብሰባ ጄኔቭ መሄዱን ገልጾላቸው፤ ያአለባቸውን ችግሩች ጠይቋቸው፤ በዕለቱም ፎቶ ተነስተው ወደመጡበት ወደኢልጃሊ እንደሚመለሱ ሲነገራቸ፤ ሽብር ሆነ። ተፈተናል በማለት ልባቸውን አጽናንተውና አዝናንተው ሳሉ ትመለሰላችሁ ሲባሉ ሌላ ሐዘን ውስጥ ገቡ። እርሱንም በመቅረብ ለምን እንዲያ ሊሆን እንደቻለ ሲጠይቁት «የሶማሊያ መንግሥት የጸጥታው መሥሪያ ቤት በከተማው እንደትገቡበት አይሻም፤ ስለእናንተ ሙሉ መብት አላቸው፤ ገና ለኮሚሽኑ አላስረከቧችሁምና እኔም ምንም የምረዳችሁ ነገር ስለሌለኝ የሚሏችሁን በትዕግስት ተቀብላችሁ ወደ መጣችሁበት ተመለሱ» በማለት ቁርጥ ያለውን ነገር ነገራቸው።

ወጣቶቹም ሁኔታውን አስተዘዝነው፤ በተቻለው መንገድ ሁሉ ተጠቅሞ ከመመለስ እንዲያድናቸው ሲማጠኑት፤ ስልኩን አንስቶ ለሶማሊያ ብሔራዊ ጸጥታ ጽሕፈት ቤት የተለወጠ ነገር ካለ በማለት ቢጠይቃቸው፤ ወዲያኑ አንድ ግለሰብ ከመሥሪያ ቤቱ ተልኮ ወጣቶቹንም ሰብስቦ «ምርጫው የእናንተ ነው፤ ወይ ወደ መጣችሁበት መመለስ አሊያም ቀድሞ ከነበራችሁበት እስር ቤት መግባት» በማለት ምርጫቸውን እንዲያደርጉ ሐሣቡን አቀረበላቸው።የሶማሊያን የጸጥታ ሠራተኞች ያሉትን በሙሉ መቀበል ካልሆነ በስተቀር ትንሽ ማገራገር አደርጋለሁ ማለት ያለምንም ጥያቄ ለዘመናት በወህኒ መከረምን ስለሚያስከትል ወጣቶቹም አማራጭ ስላልነበራቸው በመመለሱ ተስማሙ። እነርሱም ከመሄዳቸው በፊት ፎት መነሳት ስለነበረባቸው ፎቶውን ተነስተው ከአበቁ በኋላ ወደ ሃገሪቱ ጸጥታ ጽሕፈት ቤት ተወስደው በድጋሚ ቃለ መጠይቅ ቀረበላቸው። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሰደትም ሆነ በምርኮ ከዚያች ሃገር ሲገባ ከዚያ መሥሪያ ቤት ቀረቦ ስለሚጠየቅ የግለሰቡን የሕይወት ታሪክ የያዘ መዝገብ ይኖራል።ለምሳሌ እውነቱ ከሁለት ዓመት በፊት በጭለማ አይቶት የነበረውንና በጊዜው ትምህርት ቤት ይሆናል ብሎ የገመተውን የጸጥታ ጽሕፈት ቤተ ዳግመኛ መጥቶበት ለጥያቄው

ተጠርቶ ሲገባ በመጀመሪያ ከዚያን እስር ቤት ያመጣው ግለሰብ የእሱን ጉዳይ ይዞ ያገኘዋል። እርሱም ከቢሮው ሲገባ ግለሰቡም የግል ማሕደሩን እየተመለከተ ቀና ብሎ አይቶት፤ የሶማሊኛ ቋንቋ መናገር መቻል አለመቻሉን ሲጠይቀው፤ «እውነቱም እስራችሁኝ እንዴትስ ቋንቋችሁን እማራለሁ» ሲለው በቋንቋው ተሰድቦ ያሰናብተዋል።

እያንዳንዳቸውን በመጥራት ከአምስት ዓመት በፊት የሰጡትን ቃለ መጠየቅ ማመሰከር ሲያደርጎ ብዙዎቹ ድንጋጤ ላይ ወደቁ። የሃገሪቱ የጸጥታ ሠራተኞች በጥያቄ ሲያፋጥጧቸው በሌላ በኩል ወደመርከ መመለሳቸው ያሳሰባቸው አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን እህቶች የውስጥ ጸጥታ ሃላፊው ከተኛበት ሆስፒታል ድረስ በመሄድ እንዲያስቀራቸው ቢጠይቁት፤ «እሱም ተመልሰው አይሄዱም» ከማለት ሌላ አስተማማኝ የሆነ ዋናውን ከሚሸነር የሚያሰምን ምንም ነገር አልሰጠም።

ልብሶቻቸው ያለቁና የተቀዳደዱ በመሆናቸው እህቶች ከአንዳንድ በጎ አድራጊዎች የሰበሰቧቸውን ሰጥተዋቸው ወደኢልጀሌ ተመለሱ። ከስደተኛው ጣቢያ ከምሽቱ በአራት ሰዓት ሲደረሱ ፤ ስደተኛው በሙሉ ሁኔታው አስገርሞት ምክንያቱን ለማወቅ ተቻኩለው ከየክፍሉ ወጥተው ሲጠይቋቸው እነርሱ የደረሰባቸውን በሙሉ በዝርዝር ሲነግሯቸው የእነርሱም የወደፊት ዕድል ያ እንደሚሆን አምነው ወደመኝታቸው ይሄዳሉ።

እንሄዳለን የሚለው ተስፋ በአእምሮቸው አለና ከእህቶች የተሰጣቸውን ልብሶች በየልካቸው በመስፋት ቁልፋቸውንም ከግራ ነቅለው በቀኝ በመትከል ከከተሜዎቹ ጋር ራሳቸውን ለማስተካከል፤ ጥረት በማድረግ ላይ ሳሉ፤ በክንፑ የነበሩት ስደተኞች በሙሉ ለዘለቄታው ከሚቆዩበት ሥፍራ ሲወሰዱ በቦታው አስራ አምስቱ ብቻ ቀሩ።

በወቅቱ እንደተነገረው አዲሱ የሠፈራ ጣቢያ የፍልስጤማዊያን ስደተኞች ይኖሩበት የነበረ ሥፍራ እንደነበር ተነገረ። አካባቢው ወባ እንደሚበዛበት ከዚያው ተጠቆመ።

አስራ አምስቱም ወጣቶች ሐመር እንዲገቡ ተፈቅዶ ኖሮ የፖሊስ ማክ መኪና መጥቶ በአራተኛው ቀን ወስዷቸው ለሹፌሩ በተነገረው መሠረት ከወስጥ ጸጥታ ጥበቃው ጽሕፈት ቤት ወስደ አወረዳቸው።

የኮሚሽኑ ነገረፈጅ ከጀኔቭ መጥቶ ስለነበር ከጸጥታው ጽሕፈት ቤት መጥቶ ዳግም ተገናኘን በማለት ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋውጠው፤ እርሱም ወደቢሮ ገብቶ ከአራት ሰዓት በላይ ስለነእርሱ ሲነጋገር ቆይተ በደስታ ከቢሮው ወጥቶ ሐመር እንዲገቡ እንደተፈቀደላቸው ነግሮአቸው፤ የሚከርሙበት ሆቴል



እንዲዘጋጅላቸው ለማድረግ ሲሄድ ከለኔሉም ከውጭ ከስብሰብ ሥር ከተቀመጡበት ቀዝቃዛ መጠጥና ፖኬት ሲጃራ እንዲታደለቸው አዘ ወዲያውኑ ብዙም ሳይቆይ የአማርኛና የሶማሊኛ ቋንቋ ራዲዮ ጣቢያ ዜና አጠናቃሪዎች ካሴታቸውን ይዘው ቃለ መጠየቅ ለማቅረብ ከጸጥታው ጽሕፈት ቤት መጡ። ከጥያቄዎቹም ጥቂቶቹ ይህን ይመስሉ ነበር፤

«የሶማሊያ መንግሥት ለትምህርት ወደከናዳ ሃገር ሲልከህ ምን ይሰማሃል?»

«የአዲስ አበባው ፋሽሽታዊው መንግሥት ልጆችህን ገሎብህ አንተን ከሃገርህ በማስወጣቱና የሶማሊያ መንግሥት ግን በእንክብካቤ በመያዙ ምን የምተሰጠው አስተያየት አለህ?» ሁሉም የተሰማውን ገለጸ። በሃገሪቱ ውስጥ የዜና እጥረት ስለነበር የሰጡትን ቃለ መጠየቅ ሃገሪቱን ለቀው እስከሚወጡበት ቀን ድረስ በየዕለቱ እየተደጋገመ ሲነገር ከረመ።

## ፸፩

በዋጋው ዝቅ ያለ ከከተማው ወጣ ያለ ቦታ ተመርጦ ሆቴል ተያዘላቸው። ከዚያም ርቀው ላለመሄድ የምግብ ኮንትራትም ከዚያው ሆነ። እነሱም ፍረሃት ስለነበረባቸው ብዙም ከአካባቢው ውጭ ርቀው መሄድን አልፈለጉትም።ዘበኛ መሣሪያ ይዞ አለመጠበቁ እንጂ ራሳቸውን በራሳቸው እንደእሰሩት ነበር። ቀደም ብሎ በአማርኛ ቋንቋ መነጋገሩ አደጋ እንደሚያመጣ ተነገር ስለነበር በመንገድ ላይ ሲሄዱ በተቻላቸው መጥን ደምፃቸውን ዝቅ አድርገው መናገር አለያም በሶማለኛው መጠቀም ነበር። ተሰስተው ሲናገሩ የሰማቸው ሃገሬ በጣም አድረጎ ይደነግጣል፤ በመንገድ ላይ ለሚያገኘው ሁሉ «አማሮችን ተመልከት» በማለት ሲጠቃቀሱባቸው ስለሚያዩ አዘውትረው ከተማ መውጣቱን አይፈልጉትም በተለይ ቋንቋውን በሚገባ የማይናገሩት ክፍሎች ያው እስር ቤት እንደነበሩ ነበር ማለት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ሁለት ሁለት በመሆን ከተማ በመውጣት ትልቁን ገበያቸውን እንደሃገር ቤቱ መርካቶ የሚደነቀውን ኢልጋብ እየተባለ የሚጠራውንም ለማየት ሲችሉ፤ በተለይ ከእስር ቤት የተዋወቋቸውን ሃገሬዎች ሲያገኟቸው፤ ይሰማቸው የነበረው ፍረሃት በመጥኑም ቢሆን እየተወገደ ሲመጣ፤ በከተማ ለነበሩት ሀበሾች የበርቀያ ልጆች በመሆናቸው በየጊዜው እንጀራው እየተጋገረ ደሮው እየተሠራ ይጠሩ ጀመር። እነሱም ለቀለብ ከሚሰጣቸው ሰለባ የሶማሌ ሽንልግ በማስተረፍ አንዳንድ ልብሶቻቸውን ለመቀየር ሲችሉ፤ሰውነታቸውንም በምግብ ለመጠገን ጥረት ያደርጉ ነበር። ዙሪት ያለ ገደብ ቢሆን ግን የኢትዮጵያ አየር ኃይል የሶማሊያን ጠረፍ ደበደበ የተባለ ዕለት እንድች ብሎ ከመኝታው ክፍል የሚወጣ አይኖርም። የኮሚሽኑም ጽሕፈት ቤት ይህንኑ ተገንዘቦ ከጸጥታው ጽሕፈት ቤት በቅርቡ

ወደካናዳ የሚሄዱ ስደተኞች ናቸው የሚል መታወቂያ እንዲይዙ ሲደረግ፤የኮሚሽኑም ነገረፈጅ የኢክስሬው ውጤት ከመጣ በቅርብ ወደካናዳ እንደሚሄዱ ሲነግራቸው ግን በአንዳንድ ጥብቅ በሆኑ አካባቢዎች በተለይ በወታደር ሠፈሮች ከመሄድ እንዲቆጠቡ በተደጋጋሚ ያስጠነቅቃል።

ይህ በዚህ እንዳለ ከአስራ አምስቱ ወስጥ አንደኛው መምህር ከነበሩበት ሆቴል በጸጥታ ጠባቂዎች ተይዘ ከሃገሪቱ የጸጥታ እስር ቤት ተወስዶ በቁጥጥር ሥር ዋለ። ሁኔታው የኮሚሽኑን ሠራተኞች ሆነ ወደ ካናዳ ለመሄድ በዝግጅት ላይ የሚገኙትን ስጋት ላይ ጣለ። ውሎ አድሮ ነገሩ ሲመረመር ግለሰቡ በሃገር ቤት የቀበሌ ተመራጭ በነበረበት ወቅት በሥልጣኑ በደል ፈጽሞብኛል ባይ ወጣት በስደት ከሐመር ከተማ ኖሮ «ደበኛዬን ከሃገር ያስወጣኝን አገኘሁት» በማለተ ለጸጥታው መሥሪያ ቤት አመልክቶ ኖሮ፤ መሥሪያ ቤቱም ጉዳዩን ለማጣራት ግለሰቡን ከሆቴል ከተኛበት ከፍል ተይዞ እንዲቀርብ ያደርጋል። ከዚያንም ነገሩ እንስከሚጣራ ተብሎ ከጸጥታው እስር ቤት ይጨመራል። ሌላ ያልጠበቁት ውዥንብር ይፈጠራል። ሁሉንም ሥራው ያውጣው ከማለት ሌላ ምን ይደረጋል? ቀደም ሲል ማንኛውም ሰው ሃገር ትቶ ከወጣ የነበረው መንግሥት ተቃዋሚና በግልም እንደተበደለ ይቆጠር ስለነበር ይህ አዲስና ያልጠበቁት ሁኔታ በመፈጠሩ እርስ በርስ መጠራጠር መጣ። የኮሚሽኑም ነገረፈጅ እውነተኛ ስደተኞች እስከሆኑ ድረስ መስጋት እንደሌለባችው ሲያስረዳ ግለሰቡንም ለማስፈታት ጥረት እንደሚያደርግ ቃል ገባ።

በዚያን ሁኔታ ተሸብረው ሳል የኤክስሬው ውጤት ከናይሮቢ ከኪኒያ ተልኮ ሲመጣ አንደኛው መምህር የሳንባ ነቀርሳ እንዳለበት የሚገልጽ መልክት አብሮ ተላከ። ሌላ ችግር ተፈጠረ። ሕክምና ካላለፋችሁ ካናዳ አትገቡም ተብሎ ቀደም ሲል ተነግሮ ስለነበር መምህሩም በመቅረቱ ወስዋ ራሱን በማስጨነቅ ወደ መጥፎ አዝማሚያ እያዘነበለ መምጣቱን የተመለከተው፤ የኮሚሽኑ ነገረፈጅ «የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ» በማለት ግለሰቡን ማጽናናት ሲያደርግለት ከዚያችም ሃገር በቅርብ እንደሚወጡ ሙሉ ተስፋ ሰጣቸው።

የእነሱን ጉዳይ ይከታተል የነበረውም ኮለኔል በየምሽቱ በመምጣት በመታሰራቸው በሕዝብ ቂም መያዝ እንደሌለባቸው በመደጋገም ሲያስገነዝባቸው፤ «ወጣቶችም ስለሆናችሁ ትምህርታችሁን ተምራችሁ ስትመለሱ ይህ አሁን በሁለቱ ጎርቤታማ ሃገሮች መካከል ያለውን ችግር በሁለቱም ውስጥ ኖራችሁ ያያችሁት ስለሆነ ብዙ መፍትሔዎችን ልታፈልቁ ትችላላችሁና ያለፈውን እርሱት አዲስ ዕቅድ በአዲስ ሃገር ጀምሩ» በማለት እያደጋገም ተመሰሳይ የሆነውን ምክሩን ሲለግሳቸው፤በእርግጥም ከሶማሊያ የሚወጡበት ቀን ቁርጡ ባይነገራቸውም፤ የልዩ ልዩ በሽታዎች ክትባት ሲደረግላቸው በእውነትም መውጣታቸው እየተቃረበ መሄዱ ለአስራ አራቱ ወጣቶች



ቢያስደስታቸውም የሁለቱ መምህራን ጉዳይ ገና ምን እንደሚሆን አልታወቀም ነበር።

## ፭፱

የኮሚሽኑም ነገረፈጅ በጠዋት ከሆቴላቸው መጥቶ «ደስ ይበላችሁ ከአራት ቀን በኋላ ከሶማሊያ ትወጣላችሁ» በማለት ደስታውን ያበስራቸዋል። እነሱም ደስታቸውን ለመግለጽ በያዙት ሆቴል ውስጥ እነስ ያለ የመሸኛ ደግስ አዘጋጅተው ከከተማም የነበሩት ወጣቶች ተጠርተው ፈንጠዝያ ሆነ። ወደ ካናዳ ከሶማሌ ለመሄድ የመጀመሪያዎቹ ስለሆኑ በዙም ስለኑሮው የሚያወራ አልነበረም። ግን ስለአሜሪካ ወሬው በሽበሽ ነበር። በዙዎቹ መኪና እንደገዙና የመኪናቸውን ፎቶ የላኩላቸው መሆኑን ሲገልጹ የሚኖሩበት እቤት ታጅመሃልን ይመስላል በማለት ሲያደንቁ ግን የሚሰራውን ሥራ ምን ዓይነት እንደሆነ ግልጸ የሃፈ ሳይኖር ቀርቶ ይሆን የደስታውን ሁኔታ ላለመበከል ታስቦ ምንም ችግር አይወራም ነበር። ወደ ካናዳም የስደተኛው መብት የተሰጣቸው ስለሃገሩ እንዲያውቁ ተብሎ የተላከላቸውን መጽሔቶች እየተመለከቱ የከተማዎቹን ውበት የመሬቱን ለምለምነት ከማድነቅ በስተቀር ስለውስጡ ጠለቅ ያለ በመጠኑም ቢሆን እንደአሜሪካኖቹ የሚያስጎመጅም ሆነ የሚያወናብድ ከካናዳ የፃፈም የለም።

ወደ ካናዳ የሚሄዱበት ቀን ነሐሴ ፰ቀን ፭፬ ዓምተ ምህረት መሆኑን ቀደም ብለው የሰሙት ጓደኞች በሃገሪቱ ውስጥ የተዋወቋቸው በሙሉ ከሆቴሉ አካባቢ መጥተው ተከለከሉ። ለአራት ወራት ጎረቤቶቻቸው የነበሩት በሙሉ ከቤታቸው ወጥተው፤ የሃገራቸውን መንግሥት ሲወቅሱ ወጣቶቹን ግን በቅርብ እንዳዩቸው ጥሩ ሰዎች መሆናቸውን በማድነቅ ምስጋናቸውን ሲገልጹ፤ ፍቅራቸውንም ትንሽ ረዘም የደረጉት ክፍሎች በሁለት ወር ውስጥ ታምነውና ተፈቅረው እንባው እንደ ውኃ ሲረጭላቸው፤በሳንባ በሽታ ተይዞ የነበረው መምህርም ወደ ካናዳ እንደሚሄድ ተነግሮት ግን ቀጥታ ከሆስፒታል እንዲተኛ እንደሚደረግ ተገለጸ። ትልቅ ችሮታ እውነተኛ እርዳታ ተደረገ!

ከሚሄዱበት ቀን ቀደም ብሎ በኬኒያው መሪ ላይ የመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ ተደርጎ ስለነበር የኬኒያው ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ዝግ ስለሆነ ነሐሴ ፰ ቀን የታቀደው ጉዞ ሳይሰረዝ አይቀርም የሚል ውዥንብር ከሆቴሉ ተነገረ። ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ሆነ። ለሁሉም የመሄጃው ሰዓት በመቃረቡ የጋራቸውን አንድ ሸንጣ ልብስ በኮሚሽኑ መኪና ላይ ጭነው አስራ አራቱ ወንዶችና አንዲቱ እህት ሆነው ከነበሩበት ሆቴል ለአስራ አምስት ደቃቂ ተጉዘው ከሶማሊያ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ደረሱ።

እኔም በመሄጃቸው ቀን በደስታ ፋንታ ተክዘ ለብቻው ተነጥሎ የቆመውን እውነቱን ተጠግቼው፤ ፤ ምን ይታይሃል? በማለት ጥያቄ በቀርብለት፤ ፊቱን ከችም አድርጎ «ምን ይታየኛል?» በማለት በቁጣ መንፈስ ሲመልስልኝ፤ እንደተናደደ ተረድቸው፤ ሳውቅ የፈለኩትን እንደ አወቀብኝ ገምቼ፤ ቃሉቴ ለመምረጥ ትንሽ ጊዜ ወስጄ፤ በአእምሮህ ውስጥ የተወለድክበትን ዕትብትህ የተቀበረበትን ትውልድ ከትውልድህ ዘመናት ከተቆጠረ ታሪክ ከተፃፈ ያንተ ከሆነችው ሃገርህ እየራክ መሄድህ አልታየህምን? ጊዜን ወደኋላ መልሰን ቀንና ሌሊት እንዳልተፈራረቁ ገምተን ደስታና ሐዘን እንዳልነበሩ ከደን በአንድነት በአንድ ዘመን የምትወዳቸው የሚወዱህ፤ የምታፈቅራቸው የሚያፈቅሩህ፤ በአንድነት ሆናችሁ በአገር ልጅነት ከርታችሁ በእንባችሁ ተሰባሰባችሁ አይታይህም? አብረሃቸው የዋልካቸው ፤ ቃልኪዳን የገባህላቸው፤ ቃልኪዳን የገቡልህ አይታዩህም? እነዚያ ወገኖችህ ውሉ ጠፍቶባቸው ሽቅብ ቁልቁል ሲባዝኑ ኑሮ አልጣፍ ብሎአቸው ዘዴ ነጋሪ አጥተው ሲተክዙ፤አይታዩህም? እውነት ተናጋሪዎቹ ቃልኪዳን ጠባቂዎቹ ወገን አኩሪዎቹ አይታዩህም? ታዲያ ምንድነው የሚታይህ? ያማረ ከተማ፤ የተዋበ ቪላ፤ ሽንጠ ረዥም መኪና ነውን? የሚታይህ? እርሱም ተከዝ ብሎ መጥቶ ያረፈውን ዲሲ ዘጠኝ የኬኒያውን አየር መንገድ አይሮፕላን ተመልክቶ፤ ለጊዜው ያ ነው ብሎ በጣቱ አመልክቶ «እውነቱ ይናገር» በማለት ንግግሩን ፈጥሞ ተለያየን።

ተ ፈ ጸ መ።

«......ታሪክን የታሪክ ሰዎች ሲመዘግቡት ለወደፊት ትውልድ ማስታወሻ ይሆናል። ሆኖም በውስጡ ያለፈ ሰው ሲዘግበው ከታሪክነትም አልፎ በብዙዎች ውስጥ የታመቀን ስሜት የሚያስተነፍስ የአዕምሮ ወጌሻ ነው።....ይህችን እውነት ለበስ ልብወለድ ያቀረበው ታደለ መኩሪያ ብዙዎች በተለይም ታሪክ ውለተኛው ናቸው።....የዳሸን ኮምፒውተረኞችም ያቀረቡት የአገራችን ፊደል የፅሁፍ ቴክኖሎጂ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስሜታቸውን በፅሁፍ እንዲለዋወጡ ማድረጉ ታሪክ የማይረሰው አስተዋፅዖ ነው.....»